አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ-ምረቃ መርሐ ግብር

# ጉዳያቸውን ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ያደረጉ የግዕዝ ቅኔያት ይዘታዊ ትንተና

በ

ላእከማርያም ብርሃኑ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ 2010

# ጉዳያቸውን ማኅበራዊ፤ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ያደረጉ የግዕዝ ቅኔያት ይዘታዊ ትንተና

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ-ምረቃ መርሐ ግብር

ለአማርኛ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ላእከማርያም ብርሃኑ

አማካሪ

ዘላለም መሠረት (ዶ/ር)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ 2010

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ-ምረቃ መርሐ ግብር

# ጉዳያቸውን ማኅበራዊ፣ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ያደረጉ የግዕዝ ቅኔያት ይዘታዊ ትንተና

በ

ላእከማርያም ብርሃኑ

የፈተና ቦርድ አባላት

| የአማካሪ ስም | ፊርማ |
|---|---|
| ____________________________ | ______________________ |

የፈታኞች ስም ፊርማ

| | |
|---|---|
| የውስጥ___________________________ | ______________________ |
| የውጪ___________________________ | ______________________ |

# ውዳሴ

“አቀድም አእኰቶቶ ለእግዚአብሔር” ከኹሉ አስቀድሜ ከማሕፀን ጀምሮ እስከዚች ሰዓት ድረስ የጠበቀኝን እና ለዚህ ስኬት ያበቃኝን ቸሩ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡ በማስከተልም በፊት በማስተማር፣ በኋላም ይህን ጥናት በማከናውንበት ወቅት ውድ ጊዜያቸውን መሥዋዕት አድርገው፣ ከልብ በመነጨ ቅንነት ሙያዊ ድጋፋቸውን በማበርከት፣ የጥናቱን ጽሑፍ በማስተካከል፣ ቅኔያቱን በማረም፣ መረጃዎችን በመጠቆም እና በማቀበል፣ ገንቢ አስተያየታቸውን በመስጠት፣ ይህ ጥናትና ምርምር ከፅንሰት እስከ ልደት፣ ከዚያም እስከ ጉርምስና እንዲደርስ ምሁራዊ እንክባካቤያቸው ሳይለየው ለዚህ ግብ እንዲበቃ ለረዱኝ አማካሪዬ ለዶክተር ዘላለም መሠረት ምስጋናዬ እጅግ በጣም የላቀ ነው፤ አክብሮቴም ከፍ ያለ ነው፡፡

በመቀጠልም፦ አይዞህ! በርታ! ተማር! በማለት ከመጀመሪያ ዲግሪ እስከ ኹለተኛ ዲግሪ እንዲዘልቅ በገንዘብ እና በሐሳብ ስለረዳሽኝ አክስቴ እማሆይ የሺ አማረ ዘለለው (እማዬ) ውለታሽ ብዙ ነውና፤ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡ እንዲሁም ለውድ ወንድሜ ለመምህር ጳውሎስ ዘማርያም ረቂቁን በማረም እና ሐሳብ በማፍለቅ ረገድ ረድተኸኛልና አምላክ ሊቃውንት ይጠብቅልኝ፡፡

በመጨረሻም እጅግ በጣም ለማከብራችሁ ለእናቴ እና ለአባቴ በእናንተ አማካይነት ወደዚች ምድር ተጠርቼ ከመጣሁ ጀምሮ የልጅ ናፍቆታችሁን ገድቤ የልጅነት ድርሻዬን ሳልወጣ በመቅረቴ ምንም ቅሬታ ሳይሰማችሁ በትምህርቴ እንዲበረታ ዐቅም ፈጥራችሁልኛልና እግዚአብሔር ረጅም ዕድሜ እና ጤና ይስጥልኝ፤ ወሮታችሁን አምላክ ይክፈላችሁ እላለሁ፡፡ እስቲ የአበውን ቅኔ ለአባቴ አበርክቼ ልጨርስ!

መርቆርዮስ አብ ይደልዎከ ፍሥሐ፤

ሃይማኖት ወልድከ አምጣነ ለፈረስ በጽሐ፡፡

# ማውጫ

ገጽ

ውዳሴ ........................................................................................................ i
ማውጫ ........................................................................................................ ii
አኅጽሮተ ቃላት ........................................................................................................ iv
አጠቃሎ ........................................................................................................ v
ምዕራፍ አንድ ........................................................................................................ 1
1. መግቢያ ........................................................................................................ 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ........................................................................................................ 2
1.2 የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት ........................................................................................................ 4
1.3 የጥናቱ ዐላማ ........................................................................................................ 5
1.4 የምርምር ጥያቄዎች ........................................................................................................ 6
1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት ........................................................................................................ 6
1.6 የጥናቱ ገደብ ........................................................................................................ 7
1.7 የጥናቱ ዘዴ ........................................................................................................ 7
1.7.1 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ........................................................................................................ 7
1.7.2 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ........................................................................................................ 8
1.7.3 የጥናቱ ንድፈ ሐሳባዊ ዘዴ ........................................................................................................ 9
ምዕራፍ ኹለት ........................................................................................................ 10
2. ክለሳ ድርሳን ........................................................................................................ 10
2.1 ፅንሰ ሐሳብ ........................................................................................................ 10
2.1.1 የግዕዝ ቅኔ ምንነት ........................................................................................................ 10
2.1.2 የግዕዝ ቅኔ አጀማመር ........................................................................................................ 11
2.1.3 የግዕዝ ቅኔና የታሪክ ግንኙነት ........................................................................................................ 13
2.1.4 የግዕዝ ቅኔ ዐይነቶች ........................................................................................................ 14
2.1.5 የግዕዝ ቅኔ መንገዶች ........................................................................................................ 18
2.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........................................................................................................ 21
2.3 ንድፈ ሐሳብ ........................................................................................................ 27
2.3.1 ነገረ ፍካሬ ........................................................................................................ 27

2.3.2 የነገረ ፍካሬ ንድፌ ሐሳብ እንደ ቅኔ መተንተኛ ........ 29
2.3.3 የትርጓሜ ባህል ........ 33
2.3.4 የእኔዎቹ ርእሰ ጉዳዮች / ማኅበረሰብ፣ ፖለቲካ እና ሃይማኖት / ........ 35
ምዕራፍ ሦስት ........ 38
3. የመረጃ ትንተና ........ 38
3.1 ማኅበራዊ ጉዳይ ........ 39
3·1·1 ምክር ........ 40
3.1.3 ፍቅር ........ 49
3.1.4 ሐዘን ........ 51
3.1.5 ፍላጎት ........ 53
3.1.6 ከሥራ የተለየ ስም ........ 57
3.1.7 ትዝብት አዘል ምኞት ........ 60
3.2 ፖለቲካዊ ጉዳይ ያላቸው ቅኔያት ........ 66
3.2.1 የምኒልክ ፖለቲካዊ አመራር ........ 67
3.2.2 የዘውዲቱና የኃይለሥላሴ ፖለቲካዊ ሽኩቻ /እሰጣ-አገባ/ ........ 71
3.2.3 የኃይለ ሥላሴ ንግሥና ........ 74
3.2.4 የኃይለ ሥላሴ አስተዳደራዊ በደል ........ 78
3.2.5 አብዮታዊ (ወታደራዊ) ሥርዓት ........ 83
3.3 ሃይማኖታዊ ጉዳይ ........ 86
3.3.1 ሃይማኖት እንደዐይን ........ 86
3.3.2 ቅብዐት ........ 88
3.3.3 ኩትልክና ........ 93
3.3.4 ሢመተ ጵጵስና ........ 100
ምዕራፍ አራት ........ 104
4.ማጠቃለያ ........ 104
ዋቢ ጽሑፎች
ዐባሪ
ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው

# አኅጽሮተ ቃላት

| | |
|---|---|
| ዘፍ. | ኦሪት ዘፍጥረት |
| ሳሙ. | መጽሐፈ ሳሙኤል (ቀዳማዊ እና ካልዕ) |
| ነገ. | መጽሐፈ ነገሥት (ቀዳማዊ እና ካልዕ) |
| ዜ.መዋ. | መጽሐፈ ዜና መዋዕል (ቀዳማዊ እና ካልዕ) |
| ኢዮ. | መጽሐፈ ኢዮብ |
| መዝ. | መዝሙረ ዳዊት |
| መሐልይ | መሐልየ መሐልይ ዘሰሎሞን |
| ኢሳ. | ትንቢተ ኢሳይያስ |
| ት.ወ. | ትርጓሜ ወንጌል |
| ማቴ. | የማቴዎስ ወንጌል |
| ማር. | የማርቆስ ወንጌል |
| ሉቃ. | የሉቃስ ወንጌል |
| ዮሐ. | የዮሐንስ ወንጌል |
| ሐዋ. | የሐዋርያት ሥራ |
| ጢሞ. | የጳውሎስ መልእክት ወደ ጢሞቴዎስ (1ኛና 2ኛ) |
| የሥ.ጥ.ቅ. | የሥነ-ጥበብ ቅርስ |
| መ.ሰ.ግ.መ.ቃ.ሐ. | መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ መዝገበ ቃላት ሐዲስ |
| ማ.ሌ.መ.ቃ. | ማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት |
| ዐ.ያ.መ.ቃ. | ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት |
| የኢ.ቤ.ክ.ታ. | የኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያን ታሪክ |
| የቤ.ክ.ታ.በ.መ. | የቤተ-ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ |

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት “ጉዳያቸውን ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሃይማኖታዊ ያደረጉ የግዕዝ ቅኔያት ይዘታዊ ትንተና” በሚል ርእስ ተመሥርቶ ተከናውኗል፡፡ የጥናቱ ዐቢይ ዐላማ በማኅበራዊ፣ በፖለቲካዊ እና በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ዙሪያ የቀረቡትን የግዕዝ ቅኔያት በፍካሬ ሥልት መሠረት መፈከር ነው፡፡ የሥነ-ትርጓሜን ንድፈ ሐሳብ የአጠናን ዘዴ በመጠቀም በማኅበራዊ ዐሥራ ስድስት፣ በፖለቲካዊ ዐሥራ ኹለት፣ በሃይማኖታዊ ዐሥር በጥቅሉ ሠላሳ ስምንት ቅኔያት ባላቸው የርእሰ ጉዳይ ሳቢነት ተመርጠው ተተንትነዋል፡፡ ይህን ጥናት ለማከናወን በቤተ-መጻሕፍት ውስጥ ቀዳማይ እና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን ተገልግያለሁ፡፡ በግዕዝ ቅኔያት ላይ የተካኼዱ ቀደምት ምርምራዊ ሥራዎች በሠምና ወርቅ ጓዞች፣ በታሪካዊ አጀማመር፣ በቅኔ ቤቶች ባህል ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ ይህ ጥናታዊ ምርምር የእነዚህን ቀደምት ጥናቶች ተገቢነት እና ክፍተቶች በተገቢ መንገድ መርምሯል፡፡ ቀደምት ምርምራዊ ጥናቶች ሦስቱን የነገረ ሰብእ ጉዳዮች ለይተው በንድፈ ሐሳብ ማኼጃነት አልተተነተኑም፡፡ ይህ ምርምራዊ ሥራ በእነሱ በዋናነት ያልተነሡትን ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሃይማኖታዊ ዕሳቤዎችን በማንሣት በፍካሬ ንድፈ ሐሳብ ሠረገላነት ተካኼዷል፡፡በትንተና ወቅት ቅኔያቱ በኹለት ጎራ ተዋግነው ቀርበዋል፡፡ በመጀመሪያው ጎራ በሰበካው ማኅበራዊ እና ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን የሚያነሡ ቅኔያት ተካተዋል፡፡ በኹለተኛ ጎራ ከዐፄ ምኒልክ እስከ ዘመነ ደርግ ድረስ ያሉት ፖለቲካዊ ቅኔያት ተቃኝተውበታል፡፡ በትንተናው ውስጥ በዋናነት ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሃይማኖታዊ ርእሰ ጉዳዮች ሒሶቻቸው፣ ዝንባሌያቸው፣ የሐሳብ ተዋረዳቸው በተለያየ አንጻር ተፈክረዋል፡፡ ለዚህም ማሳያነት ሦስት ዐበይት ነጥቦች ተነሥተዋል፡፡ ማኅበራዊ ጉዳዮቹ በአመክንዮ፣ በሰብኣዊ መሻት፣ በተመክሮ በሚያነሡት ርእሰ ጉዳዮች እርስ በርስ ተጣልፈዋል፡፡ፖለቲካዊ ጉዳዮቹ በሚያነሡት አሉታዊና አወንታዊ ዕሳቤዎች የመንግሥትን እና የሃይማኖትን አቋም አስተርጒመዋል፡፡ ሃይማኖታዊ ጉዳዮቹ የእርስ በርስ ሒሶችንና ፖለቲካዊ አንድምታዎችን በውስጣቸው ያዘሉ ኾነው ተገኝተዋል፡፡ በጥቅሉ የእነዚህ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሃይማኖታዊ ርእሰ ጉዳዮች እርስ በርሳቸው መሰናሰል፣ በእነርሱ ላይ የሚሰጠውን ሐቲት እና ፍካሬ ተመሳሳይ ቅርጽ እንዲይዝ አድርጎታል፡፡ ቅኔያቱ የየዘመናቱን ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን የሚያሳዩ እና በሀገሪቱ ውስጥ የተከሠቱትን ማኅበረ-ፖለቲካዊ እና ሃይማኖታዊ ዕሳቤዎች ለመንደፍ የሚያስችሉ ኾነው ተገኝተዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

ሀገራችን ኢትዮጵያ ለዐያሌ ዘመናት የቆዩ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን አስተሳስራ እያከናወነች ትገኛለች፡፡ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችም በሃይማኖታዊው መሪነት በአንድነት ሲጓዙ ቆይተዋል፡፡ አንዱ ለአንዱ ድጋፍ ሰጪ በመኾን፣ የማስፈጸሚያ ሥልት ኾኖ ሲያገለግል ይስተዋል ነበር፡፡ የማኅበራዊና የፖለቲካዊ ጉዳዮች ህልውና በሃይማኖቱ ላይ የተመሠረተ እንደነበር ታሪክ ያስረዳል[1]፡፡ ለእነዚህ የነገረ ሰብእ ጣጣዎች የሥነ-ጥበብ፣ የኪነ-ጥበብና የቅኔ ሊቃውንት ተቀኝተውላቸዋል፣ ዘምረውላቸዋል፤ ብዕራቸውን አስልተውላቸዋል (ፈቲነ ብርዕ አድርገውላቸዋል) ፡፡ ከጥበባቱም አንዱ የግዕዝ ቅኔ ነው፡፡ የግዕዝን ቅኔ በተመለከተ ኢትዮጵያን ልዩ ከሚያደርጓት በርካታ ነገሮች መካከል በዋናነት የራሷ የኾኑ ቁሳዊና መንፈሳዊ ባህል ያላት መኾኗ ነው፡፡ ይህም የዓለም መስሕብ ኾኖ እስከ አኹን ድረስ ስትደነቅ እንድትኖር አስችሏታል፡፡

ከመንፈሳዊ ባህሏ ውስጥ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ለአኹኑ ዘመናዊ ትምህርት መነሻ መሠረት የኾነው የአብነት ትምህርት ቤትና የሥርዓተ ትምህርቱ አሰጣጥ አንዱ ነው፡፡ በዚህ ትምህርት ቤት ተማሪው በየደረጃው የሚሸጋገርባቸው የተለያዩ ጉባኤ ቤቶች አሉ፡፡ እነሱም ንባብ ቤት፣ ዜማ ቤት፣ ቅኔ ቤትና መጽሐፍ ቤት ሲኾኑ ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የኾነው ቅኔ ቤት የሚለው ነው፡፡ በዚህ ጉባኤ ቤት ተፀንሶ የተወለደው ቅኔ የፍልስፍና ትምህርት በመባል ይታወቃል፡፡ ይህ የፍልስፍና ትምህርት ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡ የግዕዝ ቅኔ የአእምሮ የመራቀቅ ብቃት የሚታይበት፣ ውስጣዊ ትፍሥሕት የሚገለጽበት፣ የመጻሕፍት ምስጢራት ኹሉ የሚታወቅበት እንደኾነ በሙያው ሊቃውንት ዘንድ ይገለጻል፡፡ ሊቃውንቱ በዘመኑ የነበረውን ማኅበራዊ ትስስር፣ ፖለቲካዊ ፍንገጣና ሃይማኖታዊ ቅቡልነት አስመልክቶ ከሙያው ጋራ በማስማማት በቅኔያቸው ገልጸውታል፡፡

የኢትዮጵያ የግዕዝ ቅኔያት በሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ዘርፍ፣ በታሪክ ምርምር እና በነገረ ሰብእ ጥናት ከፍ ያለ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ የግዕዝ ቅኔ ብዙ ተነግሮለታል፡፡ ይህ ጥናት ግን የግዕዝን ቅኔያት ከማኅበራዊ፤ከፖለቲካዊ እና ከሃይማኖታዊ ሥሪት አንጻር

[1] ባሕሩ 2003፣87 ፣ ተክለጻድቅ 1961፣307: 308

የሚካኼድ በመኾኑ ለየት ያደርገዋል፡፡ በመኾኑም ይህ ጥናት በየምዕራፉ የሚያነሣቸው ርእሰ ጉዳዮች፣ ምዕራፍ አንድ መግቢያ፣ ምዕራፍ ኹለት፣ ክለሳ ድርሳን፣ ምዕራፍ ሦስት የመረጃ ትንተና እና ምዕራፍ አራት ማጠቃለያ ናቸው፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ቅኔ ምንድ ነው? ለሚለው ጥያቄ የሙያው ሊቃውንት የተለያየ ትርጕም ሰጥተውት እንመለከታለን፡፡ የተወሰኑትን ለመግለጽ ያህል ቅኔ የተራቀቀና ጠሊቅ የኾነ የፍልስፍና አስተሳሰብ መግለጫ መኾኑ ይነገራል[2]፡፡ ቅኔ በሀገራችን የቆየና የኖረ ጥበብ፣ ረጅም ዕድሜ ያስቆጠረ፤ በጣም የረቀቀና የጠለቀ ውበትና ኃይል ያለው ሙያ ሲኾን በየጊዜው እየበለጸገና እየሰፋ የመጣ አእምሯዊ ፍጡር ነው፡፡

ቅኔ የኢትዮጵያ ባህል ከፈጠራቸው እንዲሁም ካስገኛቸው ቅርሶች ኹሉ ልቡናን ለማስላት ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ ቅኔ በቋንቋ ላይ የተመሠረተ ጥበብ ሲኾን ልቡና ስሜትና አእምሮ ተዋሕደው በአንድነት የሚገለጹበት ፍልስፍና ነው፡፡ ቅኔ ስሜትንም ሐሳብንም መግለጫ ጥበብ እንጂ መሸሸጊያ ዋሻ አይደለም[3]፡፡

ቅኔ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሚሰጡ ትምህርቶች አንዱ ሲኾን፡፡ ቅኔ ከዜማ እና ተዛማጅ ከኾኑ ትምህርቶች የፈጠራን ችሎታ በማዳበር ይለያል፡፡ በቅኔያት ንጉሥ ሲከሰስ ሰማይ ሲታረስ ይታያል፡፡ በቅኔያት ወቅታዊ ክሥተቶች በማኅበራዊ፣ በፖለቲካዊ እና በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ጠገግነት በሠምና ወርቅ ሥልት ተዳሠዋል፡፡ ቅኔያቱ ማኅበራዊ ጉዳይን ማኼጃ አድርገው ማኅበረሰቡ የሚያከናውናቸውን የዕለት ከዕለት ተግባራት ያስቃኛሉ፡፡ በማኅበረሰቡ ዘንድ የሚስተዋሉት ሠናይና እኩይ፣ ሙገሳና ነቀፋ ተመሳጥረው እንዴት እንደሚቀርቡ ቅኔያቱ ራሳቸው ለራሳቸው ምስክር ኾነው ይታያሉ፡፡ ማኅበረሰቡ የሚነቅፏቸውንና የሚደግፏቸውን ነገሮች በማንሣት በቅኔያቱ ሲንጸባረቁ ይስተዋላል። ትምህርት የሌላቸው ሰዎች የተማረውን ሰው ተጽዕኖ ሲያደርጉበት ዐይተው የታዘቡትን ሲነቅፉ እንዲህ ይላሉ፤

**አስረጅ**፡-ከንቱ ውእቱ ትምህርቱ ለእስጢፋኖስ ካህን፤

እስመ በላዕሌሁ ነበሩ ዘኢተምህሩ አእባን።

---

[2] ብርሃኑ ድንቄ 1987፣6

[3] ዮሐንስ አድማሱ 1959፡1

**ትርጒም**፦ የካህን እስጢፋኖስ ትምህርት ከንቱ ነው፣

ያልተማሩ ድንጋዮች በበላዩ ተቀምጠዋልና ።

ማኅበረሰቡ የሚያወግዘውን ሥሥት ሲፈጽም የተገኘውን እንዲህ ይተቹታል፤ የሚደርስበትንም ጉዳት ያመለክቱታል።

**አስረጅ**፦ሐሜተ ክልዔቱ አኃው ዘኢፈርሀ ወልድ በልዐ በተከብቶ፣

ሥጋ ጥዑመ እንዘ የዐጹ ኖኅቶ፣

ወፍሉጠ ሞት ኮነ ባሕቲቶ ዘበልዐ እስመ ይመውት ባሕቲቶ።

**ትርጒም**፦ የኹለት ወንድማማችን ሐሜት ያልፈራ ሰው ወልድ

የጣፈጠን ሥጋ በሩን ዘግቶ በስውር በላ።

በሞትም የተለየ ኾነ (ብቻውን ሞተ) ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታልና።

ከፖለቲካ አኳያ ደግሞ የባለቅኔዎች አእምሮ ከወቅቱ የፖለቲካ ኹኔታ ጋራ ያለው ተራክቦ ምን እንደሚመስል በጥናቱ ይታያል፡፡ የወቅቱን የፍትሕ አሰጣጥና የፍትሕ መጥፋት፣ የተከሠቱትን ፖለቲካዊ ቀውሶች በማሳየት፣ በመደገፍና በመተቸት በቅኔያቱ ድርና ማግ አድርጎ የማቅረብ ጥበብ መኖሩን ቅኔያቱ ያሳያሉ፡፡ ሊቃውንቱ በፖለቲካው መሥገርትነት እንዳይሠገሩም ቅኔያቱን በማምለጫነት ይጠቀሙባቸዋል፡፡

**አስረጅ**፦ኵሉ ትውልድ በበመካኑ፣

ለኢትዮጵያ ድንግል ግብረ ዚኣሃ ይዜኑ፣

ድንግል ኢትዮጵያ

መንግሥተ ዘእንበለ ዘርዕ ወለደት አኮኑ።

**ትርጒም**፦ ትውልድ ኹሉ በየቦታው፣

የድንግል ኢትዮጵያን ሥራ ያወራል፣

ድንግል ኢትዮጵያ፣

መንግሥትን ያለዘር ወልዳለችና።

ከሃይማኖት አንጻር ቅኔያቱ የሃይማኖቱ አስተምህሮ /ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ/ በሚፈቅደው መሠረት የዕለቱን በዓል በታሪካዊ ጠገግነት በመጠቀም፣ የበዓሉን ባለቤት በማሞገስና በማወደስ በሠምና ወርቅ ተውበው ይነገራሉ፡፡

**አስረጅ**፡- ይቤ ዮሐንስ መምህረ ብዙኃን ውሉድ፣

አክብሮ ሰንበተ ሰይፍ በአንብሮተ እግር ወእድ።

**ትርጕም**፡-የብዙ ልጆች መምህር ዮሐንስ ሰይፍ ሰንበትን

ማክበር  እጅንና እግርን በማሳረፍነው አለ።

በቅኔ ሙያዊ ዕውቀት እና ፍልስፍና ዙሪያ የተደረጉ ምርምራዊ ሥራዎች እጅግ አናሳ ናቸው፡፡ እንዲህም በመኾኑ በቅኔ ሙያዊ ዙሪያ የሚደረግ ጥናት ገና ብዙ ምርምር የሚፈልግ ያልተነካ መስክ ነው፡፡ እንዲሁም ይኹን እንጂ በምርምራዊ ጥናት እና በመመረቂያ ጽሑፍ ዙሪያ እሰይ! አበጃችሁ የሚባሉ ጥቂት ሥራዎች አሉ፡፡ ጥናታዊ ምርምሮቹ በዋናነት በአጀማመሩ፣ በአገልግሎቱ፣ በባሕርዩ፣ በታሪካዊ አመጣጡ፣ በመዋቅራዊ ሥልቱ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ ለቅኔ ትምህርት የሰጡት ብያኔ ተግባራዊ፣ ሥርወ ቃላዊ፣ ታሪካዊ ዕሳቤን የተከተለ ነው፡፡ ከእነዚህ ጥናቶች በተለየ መንገድ ቅኔን በቋንቋ ላይ የተመሠረተ የስሜት፣ የአእምሮ እና የልቡና ውሑድ ፈጠራ መኾኑን በተለየ መንገድ የጠቀሰው ዮሐንስ አድማሱ ነው፡፡ ምርምራዊ ጥናቶቹ የቅኔን ትምህርታዊ ዕውቀት አጀማመሩን በአበው ይትበሀል ለያሬድ፣ የሰዋስው ሥልቱን ለዮሐንስ ገብላዊ፣ የቅኔን ጥበብ እና ፈጠራ ለተዋነይ ሰጥተው ያተቱ ምርምራዊ ሥራዎች ናቸው፡፡ እኔም እነዚህ ቀደምት ጥናቶች በርእሰ ጉዳይነት በዋናነት ያላነሡትን ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን በተለየ መንገድ የሚያሳዩትን ቅኔያት መርጬ፣ በፍካሬ መንገድ ተንትኛለሁ፡፡ በምርምራዊ ሥራ ውስጥ ቅኔያቱን በአንድም ኾነ በሌላ መልኩ ከሌሎች ጉዳዮች ይልቅ የዘመኑን መንፈስ የሚያሳዩ አንድበት ናቸው የሚል ማጠንጠኛ ሐሳብ ይዤ በሥነ ፍካሬ ንድፈ ሐሳብ እየታገዝኩ የቅኔያቱን ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሃይማኖታዊ አንድምታዎች አካኼጃለሁ፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት

በመጀመሪያ በአብነት ትምህርት ቤት በነበረኝ ቆይታ ስለ ዜማ፣ ቅኔ እና ትርጓሜ መጻሕፍት ተገቢ ትውውቅ ነበረኝ፡፡ በኋላ በድኅረ ምረቃ ፕሮግራም በቀሰምኩት የሥነ-

ጽሑፍ እና የባህል ዕውቀት ታግዤ የቅኔያትን ጥበባዊ ዋጋቸውን ይበልጥ መፈተሽ ተቻለኝ፡፡ በቀጣይነት በቅኔያት ላይ የተደረጉትን አጠቃላይ ጥናቶች ስመለከት በንድፈ ሐሳብ የተቃኙ ኾነው አላገኘኋቸውም፡፡ ቅኔያቱን በማሰባሰብ የዘመኑን አስተዳደር፣ ማኅበራዊ ችግር፣ የሚያወድሱበትን እና የሚያሔሱበትን ኹነት ለማጥናት ወሰንኩ፡፡ በቀደምት ምርምሮች ላይ ያየኹትን የንድፈ ሐሳብ ማሕቀፍ ጉድለት እና በርእሰ ጉዳይ ላይ ተመሥርቶ ቅኔ በጥልቀት አለመጠናቱን፣ እንደ አንድ ክፍተት በመውሰድ ጥናታዊ ምርምር ለማድረግ ተነሣሣሁ፡፡

በመቀጠልም በዐማርኛ ቋንቋ ሥነ- ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት በነበረኝ ቆይታ ለረዥም ጊዜያት ልምድ ባለኝ መስክ ላይ ጥናታዊ ሥራ ባቀርብ ውጤታማ ሥራ ስለሚኾን ይበልጥ መነቃቃት ፈጠረልኝ፡፡ በመጨረሻም በቅኔ ዙሪያ የተሠሩትን ጥናታዊ ሥራዎች በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኬኔዲ እና በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ቤተ መጻሕፍት ባደረኩት ፍተሻ የግዕዝ ቅኔያት በሌሎች ርእሰ ጉዳዮች ላይ እንጂ ከማኅበራዊ፣ ከፖለቲካዊና ከሃይማኖታዊ ጉዳይ ጋራ በተያያዘ መልኩ በተዘረፉ የግዕዝ ቅኔያት የተጠና ጥናታዊ ሥራ አለመኖሩ ይህን ጥናታዊ ሥራ ለመሥራት እንዲወስን አግዞኛል፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዐላማ

ይህ ጥናት አንድ ዐቢይ ዐላማ እና አራት ንኡሳን ዐላማዎች አሉት፡፡ ዐቢይ ዐላማው በማኅበራዊ፣ በፖለቲካዊ እና በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ዙሪያ የቀረቡትን የግዕዝ ቅኔያት በፍካሬ ኀዳና መፈከር ነው፡፡ ከዐቢይ ዐላማው ጋራ የተሰናኙ አራቱ ንኡሳን ዐላማዎች ለምርምራዊ ሥራ ምልዐት ተመርጠዋል፡፡

- በማኅበራዊ፣ በፖለቲካዊ እና በሃይማኖታዊ ቅኔያት ውስጥ ተደጋግመው የሚነሡትን መባያ ጉዳዮች መተንተን
- በቅኔያቱ ውስጥ ተደጋግመው የሚነሡትን የተጠየቅ ዐይነቶች እና የገቡበትን ኺደት መፈከር
- በቅኔያቱ ውስጥ የሚነሡት ዕሳቤዎች ለቅኔ ቴክኒካዊ ብልኀት ያላቸውን አስተዋፅኦ መግለጽ እና
- የነገረ ፍካሬ ንድፈ ሐሳብ ሦስቱን የነገረ ሰብእ ጉዳዮች ለመተንተን ያለው ጠቀሜታ እስከ ምን መኾኑን መፈተሽ የሚሉ ናቸው፡፡

## 1.4 የምርምር ጥያቄዎች

ይህ በቅኔያት ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ የሚደረግ ምርምራዊ ጥናት አራት መሠረታዊ ጥያቄዎችን በምርምር ሥራው ውስጥ ይመልሳል፡፡

- ቅኔያቱ የሚያቀነቅኑት ርእዮተ ዓለማዊ ዕሳቤዎች እንዴት ተገለጹ?
- በቅኔያቱ ውስጥ የተነሡት የሐሳብ ተዋረዶች እና የዕሳቤ ቅጦች ምንድ ናቸው?
- ስለማኅበረ-ባህላዊው  ዓለም ቅኔያቱ በምን መልክ ይናገራሉ?
- በቅኔያቱ ውስጥ የተነሡት ሒሶች ተጠየቃዊ ዘላቂነታቸው ምን ያህል ነው?

## 1.5  የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናታዊ ሥራ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

ሀ. የግዕዝን ቅኔያት ለሚያጠኑ  ተማሪዎች ቅኔያቱ በትንተና መልኩ ስለተገለጹ ጥናቱን በማየት የቅኔያቱን ትርጕምና የትንተና ሥልት ለማወቅ ይረዳቸዋል

ለ.ጥናታዊ ሥራው በማኅበራዊ፣ በፖለቲካዊ እና በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ ጥናት ለሚያደርጉ ባለሙያዎች የዘመኑን ወቅታዊ፣ ሀገራዊ፣ትንሣኤና ውድቀት በቅኔያት ስለሚዳሠሥ ታሪክን በመጠቆም ግብአት ይኾናል፤ ያሳውቃል፡፡

ሐ. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ያለው የፍልስፍና ሀብት የጥናትና ምርምር መሥመር ኾኖ እንደሚያገለግል ሊጠቁም ይችላል፡፡

መ.ይህ ጥናታዊ ሥራ በተመረጡ ቅኔያት ላይ ከቋንቋ እና ከሥነ-ጽሑፍ ሕግ አንጻር ትንተና ስለሚሰጥ ለዐማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት በመረጃነት ያገለግላል ፡፡

ሠ. በግዕዝ ቋንቋ እና ሥነ-ጽሑፍ መስክ ጥናትና ምርምር ለሚያደርጉ ተመራማሪዎች ቅኔያቱን ቴክኒካዊ ብልኀት መሠረት አድርጎ ስለሚያይ የቅኔያቱን ኀቡእ ምስጢር ለመረዳት ያስችላል፡፡

ረ. ከባህል ጥናት አንጻር ቅኔያቱ የተሠሩበትን ሠማዊ ቅብዐቸውን በመመርመር የአንድን አካባቢ ባህል ለማወቅ ይጠቅማል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ገደብ

ይህ ጥናት ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሃይማኖታዊ ነገሮችን ጉዳያቸው አድርገው የቀረቡትን የግዕዝን ቅኔያት መሠረት በማድረግ ምስጢራዊ ፅንሰ ሐሳቡን ይፈክራል፡፡ ቴክኒካዊ ብልኀቱን ይዳሥሣል እንጂ ስለ ቅኔ መንገዶች፣ ስለቅኔ ይትበሀል፣ ስለ ቅኔ ቈጠራ፣ ነገራና ዘረፋ፣ ስለዜማ ልክ እና ስለ ቅኔ መቀኘት፣ ስለ ቅኔ ቤት፣ ስለ ቅኔ አቀራረብ አይናገርም፤ እንዲሁም የሠምና ወርቅን ፅንሰ ሐሳብና የቅኔን ቅርጽ አያነሣም፤ ምክንያቱም እነዚህ በቀደምት አጥኚ ሥራዎች የተዳሠሡ በመኾናቸው አይዳሠሡም፡፡ይህ ጥናት ማኅበራዊ፣ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ይዘት ባላቸው ስምንት የግዕዝ ቅኔ ዐይነቶች /ጉባኤ ቃና፣ ዘአምላኪየ፣ ሚበዝኁ፣ ዋዜማ፣ ሥላሴ፣ መወድስ፣ ሣህልከ እና አሠረ ንጉሥ/ ላይ ትንተና በመስጠትና ቴክኒኩን በመፈተሽ ትኩረት አድርጓል፡፡

## 1.7 የጥናቱ ዘዴ

### 1.7.1 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ይህ ጥናት ቀዳማይ እና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም ተካኼዷል፡፡ ጥናቱ ሰነድ ፍተሻን የሚጠቀም ስለኾነ እንደ አስፈላጊነቱ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አብያተ መጻሕፍት እና ቤተ መዛግብት ውስጥ የሚገኙ ምርምራዊ ሥራዎች ተፈትሸዋል፡፡

በዚኹ መሠረት በቀዳማይ ምንጭነት ሰባት መጻሕፍት ተመርጠዋል፡፡እነዚህም መጻሕፍት በሀብተማርያም ወርቅነህ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት፣ በኀሩይ ወልደሥላሴ መጽሐፈ ቅኔ፣ በአድማሱ ጀንበሬ መጽሐፈ ቅኔ ዝክረ ሊቃውንት፣ በይኄይስ ወርቄ ንባብ ወትርጓሜ ዘቅኔያት፣ በዓለማየሁ ሞገስ የግዕዝ ቅኔ ዜማ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ የግዕዝ ቅኔያት የሥነ- ጥበብ ቅርስ እና በእነኤልያስ ነቢየ ልዑል ትርጓሜ ቅኔ ፈለገ ሕይወት የተዘጋጁ ናቸው፡፡መጻሕፍቱ በቀዳማይ ምንጭነት ጥንታዊ የቅኔ ስብስብ በመያዛቸው እና ሊቃውንቱ ለትምህርቱ መስክ ባላቸው ቅርበት ተመርጠዋል፡፡ ከዚኽም በተጨማሪ በቀዳማይ መረጃነት ያገለገሉ መጻሕፍት አብዛኛዎቹ በ1960ዎቹ ውስጥ የታተሙ እና የወቅቱን ፖለቲካዊ ኹኔታ የሚገልጹ ቅኔያት የተካተቱባቸው ኾነው ተገኝተዋል፡፡

በኹለተኛ ደረጃ ምንጭነት ያገለገሉ የተለያዩ የቅኔ መጻሕፍት፣ የታሪክ መጻሕፍት፣ ጥናታዊ የምርምር ሥራዎች፣ የሥነ ፍካሬን እና አርእስተ ጉዳዮችን የሚያበለጽጉ ሥራዎች ተመርጠው፤ ለሒሳዊ ንባብ ማኼጃነት አገልግለዋል፡፡ የቅኔያቱ ምርጫ በኹለት ጎራ

ተመድቧል፡፡ በመጀመሪያው ጎራ ማኅበራዊ እና ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን የሚያነሡ ቅኔያት በርእሰ ጉዳይ ሳቢነት ተለይተው ተመርጠዋል፡፡ ይኸም ምርጫ በቅኔያቱ ዐይነት ሳይኾን በሚያነሡት አርእስተ ጉዳይ ላይ ይመሠረታል፡፡ በኹለተኛ ጎራ ዘመናዊ የኢትዮጵያን ታሪክ የሚቃኙ ፖለቲካዊ የርእዮተ ዓለምነት ያላቸው ቅኔያት በዘመን ተለይተው ተካተዋል፡፡ እነዚህም ቅኔያት በሦስት ሥርዓተ መንግሥት ከዐፄ ምኒልክ እስከ ደርግ የነበረውን ማኅበረ-ፖለቲካዊ ጉዳዮች የሚያነሡ ናቸው፡፡ በቅኔያቱ ውስጥ የሚታየው ርእዮተ ዓለማዊ አተያይ ሃይማኖታዊ ይዘት ያለው ፖለቲካዊ አተያይ ነው፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ሠላሳ ስምንት ቅኔያት ሦስቱን አርእስተ ጉዳዮች ለማሳየት ገላጭ ኾነው በመገኘታቸው ተመርጠዋል፡፡ በትንተና ውስጥ ያልተካተቱ ቅኔያት ተመሳሳይ ሐሳብ የሚያነሡ እና ሐቲቱን ለማኼድ ሚዛን የሚደፉ ኾነው ባለመገኘታቸው አልተካተቱም፡፡ በሦስቱ አርእስተ ጉዳይ ሥር የተካተቱ ንኡሳን ጉዳዮች በቀረቡበት ማሕቀፍ ሰፊውን የባህል ርእዮተ ዓለም በሚያስተረጉሙበት መልኩ ተደራጅተዋል፡፡

### 1.7.2 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

በዚህ ጥናት ለምርምር ተግባር ከሚውለው መረጃ ዐይነትና መረጃዎቹ ከሚተነተኑበት መንገድ አንጻር ዐይነታዊ የምርምርን ሥልት ተከትሏል፡፡ በዚህ ሥልት ከትርጉም ነገሮችን ከመረዳት ከስሜታዊነት ጋራ የሚዛመዱ እውነታዎች ይመረመራሉ፡፡ የጉዳዩን ምንነት ባሕርይ አወቃቀር ለማሳየት ይሞከራል ይህንን የምርምር ሥልት ጥናታዊ ሥራዬን ለማካሄድ ስመርጥ ሥነ-ሰብአዊ አመለካከት ስለሚታይበትና በግኝት ላይ ስለሚያነጣጥር ተመራጭነት አግኝቷል፡፡ በእውነታ ላይ ተመሥርቼ ግላዊ አስተሳሰብና አጠቃላይ ተለዋዋጭ ጉዳዮችን በመግለጽ እና በማብራራት አቅርቤአለሁ፡፡ የሚገኘው መረጃ የሚተነተነው ዐይነታዊ የአተናተን ዘዴን በመጠቀም ነው፡፡ ዐይነታዊ ዘዴ ማለት በቁጥር ሊገለጹ የማይችሉ እንደ ልብ ወለድ፤ ሥነ ግጥምና የግዕዝ ቅኔያት ያሉ ሥራዎች የሚተነተንበት ዘዴ ነው፡፡ ለዚህ ጥናትም ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን መሠረት አድርገው የተነገሩ ቅኔያትን ቴክኒክ ለማስረዳት ያገለግላሉ ተብለው የተመረጡ ቅኔያትም በዚሁ የአተናተን ዘዴ ተተንትነዋል፡፡

### 1.7.3 የጥናቱ ንድፈ ሐሳባዊ ዘዴ

የዚህ ጥናት ዐቢይ ዘዴ በማኅበራዊ፣ በፖለቲካዊና በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ የተነገሩትን የግዕዝ ቅኔያት በፍካሬ ሥልት መተንተን ነው። ሥነ ዘዴው በኹሉም መስክ ውስጥ የሚሠርጽ ለኹሉም የትምህርት መስኮች ፍካሬ በማኼጃነት የሚያገለግል ነው፡፡

በነገረ ፍካሬ ሊቃውንት ከተሰጠው ገለጻ የሚከተለውን ዐቢይ ሐሳብ በዋናነት እናገኛለን። የትኛቸውም ሰብኣዊ ኾነ መለኮታዊ ድርሳናት በየትኛውም ቋንቋ በየትኛውም ዘዴ ቢጻፉ ሐሳባቸው ግልጽ አይኾንም፤ ሊኾንም አይችልም። ስለዚህ ይህ ሥነ-ዘዴ እውነታን በተለያዩ አንጻሮች በመፈከር አማራጭ መንገድ ይፈጥራል። ጸናን የኾኑትን ሐሳቦች በትርጓሜ በማቅናት ግልጽነት እንዲኖራቸው ያደርጋል[4]።

እኔም የማጠናቸው ቅኔያት ፈርጀ ብዙ የኾኑ የነገረ ሰብእ ጉዳዮችን የያዙ በመኾናቸው በተለያየ አንጻር ትርጓሜ የሚሹ ስለኾኑ ለጥናታዊ ምርምሩ ፅንሰ ሐሳባዊ ማኼጃነት የትርጓሜ ፈለግ የተሻለ ኾኖ አግኝቸዋለሁ፤ የታሪክን፣ የፖለቲካን የባህልን የማኅበረሰብእን እና የነገረ መለኮትን ጣጣ በትርጓሜ ፈለግ አውጥቶ ማሳየት ላይ ትኩረቴን አድርጌአለሁ፡፡

በሙያው ሊቃውንት ጠቃሚ ለውጦችን ለማምጣት በዋናነት የሰብኣዊ ዕውቀትን ግዛት በማስፋት የተነገሩትን የግዕዝ ቅኔያት በመሰብሰብ ትንተና መስጠት ነው፡፡ የዘመኑን የአስተዳደር ኹኔታ፣ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን ከታሪክ ጋራ እያዛመዱ መተንተን፤ ቅኔያቱ የነገረ ሰብእን ጣጣ ማኼጃ አድርገው እንዴት እንደተከየኑ ተተንትነዋል፡፡

[4] Gayle and Alan 1981፡1

# ምዕራፍ ኹለት

# 2. ክለሳ ድርሳን

## 2.1 ፅንሰ ሐሳብ

### 2.1.1 የግዕዝ ቅኔ ምንነት

ስለ ግዕዝ ቅኔ ምንነት በሙያው ያለፉ ምሁራን ልዩ ልዩ ብያኔ ሰጥተዋል[5]፡፡ "ቅኔ ቀነየ=ገዛ ካለ ግሥ የተገኘ ጥሬ ዘር ነው፤ ፍቺውም መገዛት ማለት ነው" የሚል ብያኔ አቅርበዋል[6] ፡፡የቅኔን ትርጒም በሚመለከት በሚከተለው መልኩ ገልጸዋል፡፡ "ቅኔ ማለት ቀነየ ገዛ፣ ተቀነየ ተገዛ፣ ከሚለው አንቀጽ ብዙ ኃይለ ቃልን የሚያሰባስብ ዘር ሲኾን ትርጓሜው የገዥንና የተገዥን ምልክት የሚያሳይ ሰዋስው ነው፡፡" በተጨማሪም[7] "የጥንት ሕዝቦች [8] በተለይ ነቢዩ ዳዊት የራሱን ግጥም ገጥሞ ፈጣሪውን ከማመስገኑም በላይ ሌላው ሰው ቅኔ እንዲቀኝ፣ ምስጋና እንዲያቀርብ ሲያዝ ‹ተቀነዩ ለእግዚአብሔር በፍርሃት› ሲል ዘምሯል" በማለት ብያኔያቸውን ሰጥተዋል፡፡ እንግዲህ ከላይ የተጠቀሱት ጸሐፍት የቅኔን ምንነት ሲገልጹ ለሃይማኖት ምስጋና ብቻ እንደሚውል አድርገው ነው፡፡

ሌላው ስለግዕዝ ቅኔ ከተናገሩት ሊቃውንት መካከል ዕንባቆም የግዕዝን ቅኔ በተመለከተ የቤተ-ክርስቲያን የፍልስፍና ትምህርት መኾኑን አንሥተው፣ የትምህርቱም ቅደም ተከተል ከንባብና ከጸዋትወ ዜማ ቀጥሎ፣ ከትርጓሜ መጻሕፍት አስቀድሞ በጒርምስና ወራት መኾኑን ገልጸዋል፡፡ ምክንያቱንም ሲያብራሩ የቅኔ ትምህርት የረቀቀና የጠለቀ መንፈሳዊ ጥበብ በመኾኑ ከሀገር ወጥቶ፣ ከዘመድ ርቆ፣ ፈተናውን ታግሦ የሚማሩት በመኾኑ የመንፈስና የሥነ-ልቡና ዝግጅት ስለሚያስፈልገው ነው ይላሉ[9]፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ሊቃውንት የተለየ ብያኔ ያቀረቡት ይኄይስ ደግሞ የቅኔን ምንነት በሚከተለው መልኩ ገልጸዋል፡፡"ቅኔ የተባለውም ድርሰት የታሪክና የስሜት መግለጫ እንደመኾኑ መጠን ማናቸውም ሰው የጓደኛውን ሕይወት ታሪክ ለምስጋናም ኾነ ለነቀፌታ በአሽሙር ጠቅሶ በተናገረ ጊዜ እገሌ በእገሌ ተቀኘበት" ይባላል[10]፡፡

---

[5] አድማሱ (1963፡9)
[6] ኤልያስና ከፍያለው (1992፡16)
[7] ሀብተ ማርያም (1963፡172)
[8] ዕብራውያን ግጥም እየገጠሙ ማለትም ቅኔ እየተቀኙ አምላካቸውን አመስግነዋል፡፡
[9] ዕንባቆም 1966፣117
[10] ይኄይስ 1960፡8

ከዚህ ላይ እንደተገለጸው ቅኔ ለመንፈሳዊ ተግባር ብቻ ሳይኾን ለዓለማዊ ጉዳዮችም መግለጫ እንደሚኾን ምሁሩ ይናገራሉ፡፡ ቅኔ ታሪክን ለመግለጽ ከፍተኛ ሚና ያለው መኾኑን ይገልጻሉ፡፡ በማኅበራዊ ግንኙነት ዙሪያ ፍቅርም፣ ጥላቻም ሲከሠት የስሜት ማስተላለፊያ ኾኖ እንደሚያገለግል ከጥቅሱ መረዳት ይቻላል፡፡በተጨማሪም ዜና ማርቆስ የሚቀጥለውን ሐሳብ አቅርበዋል፡፡"ቅኔ መሳፍንቱ፣ የሴት ወይዘሮው፣ ነገሥታቱና ጳጳሳቱ ሕዝቡን በበጎ አስተዳደር ሲመሩ የሚሞገሱበትና የሚወደሱበት፣ ሕዝቡን በአስተዳደር ሲበድሉ ደግሞ የሚወቀሡበት፣ የሚዘለፉበትና የሚመከሩበት ድርሰት ነበር"[11]፡፡

ይህ እንግዲህ የኹለቱ ምሁራን ብሂል እንደሚገልጸው ቅኔ ለተለያየ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች አገልግሎት እንደሚሰጥ ነው፡፡ መልካሙን ኺደት ለማሞገስ፣ መጥፎውን አካኼድ ለማስተካከል በመልእክት ማስተላለፊያነት እንደሚያገለግል የሊቃውንቱ ብያኔ ይጠቁማል፡፡

### 2.1.2 የግዕዝ ቅኔ አጀማመር

የግዕዝ ቅኔ ጀማሪ ማነው? ጉዞውስ ከየት ወዴት ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሣት አንድ ዐይነት መልስ ማግኘትም ኾነ መስጠት አስቸጋሪ ቢኾንም ስለ ቅኔ ጀማሪና ታሪካዊ ጉዞ የጸሓፊዎችንና የተመራማሪዎችን ሐሳብ በቅደም ተከተል ለማሳየት ይሞከራል፡፡ በመጀመሪያ ከቅዱሳት መጻሕፍት መገኘቱን የሚገልጹ አሉ[12]፡፡ የቅኔ መገኛው ቅዱስ መጽሐፍ እንደኾነ የተጠቀሱትን መረጃዎች መሠረት አድርገው ይናገራሉ[13]፡፡

የተወሰኑት ደግሞ በስድስተኛው ምእት ዓመት በዐፄ ገ/መስቀል ዘመነ መንግሥት የተነሣው ቅዱስ ያሬድ የቅኔ ጀማሪ ለመኾኑ በራሱ የድርሰት ሥራዎች ውስጥ ያሰፈራቸውን ግጥሞችና ሥንኞች በመጥቀስ ቅዱስ ያሬድ የቅኔ ፈጣሪ መኾኑን ይናገራሉ[14]፤

በመኾኑም የቅኔ ፈጣሪ ቅዱስ ያሬድ ይኹን እንጂ እንደአኹኑ ቤት የመታ አልነበረም ይላሉ፤ ለዚህም የአንዱን ሊቅ ቅኔ ማስረጃ አድርገው ይጠቅሳሉ [15]፡፡

---

[11] ዜና ማርቆስ 1994፡4

[12] ለዚህም በማስረጃነት የሚጠቀሙት በመጽሐፈ መሳፍንት 9፡7-11 ያለውን በዜና መዋዕል 25፡17 የተገለጸውንና በማቴዎስ 13፡1-18 የተጠቀሰውን ምሳሌ፣ መዝሙረ ዳዊትን መሐልየ መሐልይን በማንሳት

[13] አድማሱ 1963፡ 19፤ ፍቅረ ድንግል 1963፡3)

[14] ዕንባቆም 1958፤ አድማሱ 1963 ፡10፤ ሀብተማርያም 1963፡172፤አፈ-ወርቅ ዘውዴ 1980፡16

[15] ተትሕተ ያሬድ ዘኢተትሕተ፤ለቅኔያቲሁ ደቂቅ እስመ ኢሐነጸ ቤተ፡፡

ትርጉም፡- ያልተዋረደው ያሬድ ተዋረደ፣ ለልጆቹ ቅኔዎች ቤት አልሠራምና፡፡

ማርዬ ይህንኑ ሐሳብ በመደገፍ “ቅኔን ቅዱስ ያሬድ ከፈጠረው በኋላ በየዘመናቱ የተነሡ ሊቃውንት ዜማ ልኩን እየመጠኑ፣ ምስጢሩን እያራቀቁ አስፋፍተው ዛሬ ካለበት ደረጃ አድርሰውታል” በማለት አብራርቷል[16]፡፡ ስለዚህ አሻሻሉት ማለት ፈጠሩት ማለት ስላልኾነ የቅኔ ፈጣሪ ቅዱስ ያሬድ እንደኾነ ሊቃውንቱ በብዛት ይስማማሉ፡፡

በሌላ በኩል ዋድሎች የቅኔ ደራሲ ዮሐንስ ገብላዊ ነው ማለታቸውን ምሁራኑ ያስረዳሉ፡፡ ዮሐንስ ገብላዊ የቅዱስ ያሬድን ቅኔዎች መርምሮ፣ የቅዱስ ያሬድን ፈለግ ተከትሎ ቅኔን በሠምና ወርቅ ለማጉላት፣ ምስጢሩን ለማርቀቅ፣ መንገዱን ለማስፋፋት፣ ቤቱን ለመሙላት በቅቷል ሲሉ ያስረዳሉ[17]፡፡ አኹንም ይህንን ብያኔ ስንመረምረው የቅኔ ፈጣሪው ቅዱስ ያሬድ ነው ወደሚለው ይወስደናል፡፡

ጎንጆች በበኩላቸው የቅኔ ፈጣሪ ተዋነይ ነው እንደሚሉ የሙያው ሊቃውንት ሐሳብ አቅርበዋል[18]፡፡ እንደገለጹት ተዋነይ በ14ኛው ክ/ዘመን የነበረ ነው፡፡ ከልጅነቱ የድርሰትና የፍልስፍና ተውህቦ የተሰጠው ነበር፡፡ከየሊቃውንቱ ተምሮ አገባብን ካጠናቀቀ በኋላ ደቀ እስጢፋኖስ (ጣና ደሴት) ገብቶ፣ ብዙ መጻሕፍትን አንብቧል፡፡ ከዚያም የቅኔን መንገድ እና ዐይነት አስማምቶ፣ ሳያስረዝም አገባቡን አሳጥሮ፣ ለኹሉም መርሕ የሚኾን አብነት ጽፎ በጎንጅ ሲያስተምር ሞቷል የሚል ሐሳብ የሰጡበት ኹኔታ ይታያል፡፡

ዮሐንስ ደግሞ እስከ አኹን ከተነሡት ሐሳቦች ስለ ቅኔ አጀማመር የተለየ ሐሳብ ሲሰጥ ይስተዋላል፡፡ የቅኔ ጀማሪ ዘሱቱኤል (እንዲሪም) የሚባል የአገው ሰው ነው ካለ በኋላ በማስረጃነት የዘሱቱኤል ቅኔ ተብሎ የሚጠቀሰውን ያነሣል[19]፡፡ ምስጢሩንም ሲያስረዳ ለአንድ አገው ዘጠኝ ልብ ካለው በዘጠኝ ልቡ ቢሠራ ከእግዚአብሔር አያንስም፤ እግዚአብሔርን ሳያህል አይቀርም ነበር ማለት ነው ሲል በቅኔ አመጣጥ ላይ ለየት ያለ ታሪካዊ መረጃ ይሰጣል፡፡

በአጠቃላይ የቅኔ ፈጣሪ ማን እንደኾነ በእርግጠኝነት ለምን እስከ አኹን አልታወቀም ለሚለው ጥያቄ ዮሐንስ  መልስ ይሰጣል፡፡ “ሠምና ወርቅ” ብሎ በሰየመው ዲማጽ ላይ መምህራኑም ኾኑ ደቀመዛሙርቱ በቅኔው ቅርጽና መልክ፣ በጥበቡ ረቂቅነት፣ በውበቱ ኃይል ከመጠን በላይ ይደነቃሉ፡፡ ከዚህም የተነሣ እውነተኛውንና ቀጥተኛውን ታሪክ፣ መርምሮ፣ ተንትኖ ለማወቅ ጊዜ ያላቸው አይመስልም፤ የጥበቡ ረቂቅነትና የውበቱ

[16] ማርዬ (2006፡59)
[17] ፍቅረ ድንግል 1963፡1፤ አፈ-ወርቅ 1980፡17
[18] ዓለማየሁ (1950፤117) እና እነኤልያስ (1992፣17)
[19] ዮሐንስ 1959 ፡ 5 መኑ ጠቢብ ወመለብው፣ ከመ እግዚአብሔር አገው ፡፡

ማራኪነት ልብን ገዝቶ ይይዛል፡፡ ከተገኘው የቅኔ ውጤት እንጂ ከአስገኚው ጋራ ብዙም ግንኙነት የላቸውም፡፡ ማነው? የሚለውን ቃል ጥያቄ ትተው ምንድነው? የሚለውን ቃል ጥያቄ ይከታተላሉ ሲል ገልጿል[20]፡፡

### 2.1.3 የግዕዝ ቅኔና የታሪክ ግንኙነት

የግዕዝ ቅኔ ሲታሰብ ታሪክ አይቀሬ ጉዳይ ነው፡፡ ያለ ታሪክ ቅኔ መቍጠርም ኾነ መቀኘት ፈጽሞ አይታሰብም፡፡ በመጀመሪያ ታሪክ ማወቅ ግዴታ ነው፡፡ ታሪክ ለግዕዝ ቅኔ መሠረት ነው፡፡ የግዕዝን ቅኔ ከታሪክ፣ ታሪክን ከግዕዝ ቅኔ ለይቶ መመልከት አይቻልም፡፡ ለታሪኩ መፈጠር ምክንያት የሚኾኑትም ዕለቱን እና ወቅቱን ጠብቀው የሚነገሩ የበዓላት፣ የአጽዋማት እና የክረምት ትረካዎች ሲኾኑ ለእነዚህም በመነሻነት የሚያገለግሉት የብሉያት፣ የሐዲሳት፣ የሊቃውንት እና የአዋልድ መጻሕፍት ናቸው፡፡ ከባለ ታሪኮቹ መካከልም ሥላሴ ፣ መላእክት፣ ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ ጻድቃን፣ ሰማዕታት፣ ነገሥታት፣ መኳንንት እና የተፈጥሮ ክሥተቶች ማለትም የዕፀዋት መለምለም፣ መድረቅ እና የሰብል መብቀል በባለታሪክነት ለቅኔ አገልግሎት ይውላሉ፡፡ የታሪክን ምንጭ፣ ባለታሪኮችን እና ታሪክ ከቅኔ ጋራ ያለውን ቁርኝት በተመለከተ ታደለ ገድሌ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡ “የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ እና የአንድምታ ትርጓሜም የመላእክትን፣ የጻድቃንንና የሰማዕታትን ተራዳኢነትና ተጋድሎ በተመለከተ በየዕለቱ የቅኔ መምህሩ ሲተርክና ሲተነትን በአንክሮ ያዳምጣል፡፡ የቅኔ ኅዳና ምስጢሩ ሲገባው ደግሞ ድርጊቱን በሠምና ወርቅ እያስጌጠ ቆጥሮ ይቀኛል”[21]፡፡ከታሪክ በኋላ ባለቅኔው በተለያዩ የቅኔ መንገዶች ቀምሞ ቅኔውን ሲያቀርበው ይበል ያሰኛል፡፡ ስለዚህ ታሪክ ለግዕዝ ቅኔ የጀርባ አጥንት ነው ቢባል ነገሩ እሙን ነው፡፡

ሌላው ደግሞ የግዕዝ ቅኔ ከማኅበራዊ፣ ከፖለቲካዊና ከሃይማኖታዊ ጉዳዮች ጋራ ያለው ትስስር እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ለዚህም መረጃ የሚኾነው ሊቃውንቱ በቅኔያቸው የወቅቱን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ እና ማኅበራዊ ጉዳይ ሲያቀርቡ ይታያል፡፡ ይህንም ለማ በቅኔያቸው ገልውታጸል[22]፡፡

---

[20] ሠምና ወርቅ 1959፡3

[21] ታደለ 1997፡6

[22] ምኒልክ ግበር ላዕለ ሮምያ መጠነ እዴከ ትክል፡አምጣነ ለዐጺድ በጽሐ ማእረራ ወመዋዕሊሃ ለሀጉል፡፡

ትርጕም፦ምኒልክ! በሮምያ ላይ እጅህ እንደቻለ መጠን አድርግ፣ መከሯ ለመታጨድ፣ ቀኗም ለጥፋት ቀርቧልና (መጽ.ትዝታ፡200)፡፡

ከዚህ ላይ የሊቁ ቅኔ እንደሚያመለክተው የግዕዝ ቅኔ በማንኛውም ጉዳይ ዙሪያ መቅረብ የሚችል ጥበባዊ ፈጠራ መኾኑን ያስረዳል፡፡

### 2.1.4 የግዕዝ ቅኔ ዐይነቶች

ስለ ግዕዝ ቅኔ ዐይነቶችና ትርጕም የተለያዩ ሊቃውንት በዝርዝር ጽፈዋል፡፡ የቅኔ ዐይነቶች በአብዛኛው የሚለያዩት በቅኔዎቹ መጠንና በሚያተኩሩበት ርእሰ ጉዳይ ነው፡፡ የቅኔ መጠን የሚለካው በስንኞቹ ብዛትና ርዝመት ነው፡፡ ርእሰ ጉዳያቸው ደግሞ ቅኔያቱ የሚያነሡት ጭብጥ ነው፡፡ በመጠንና በትኩረት ያላቸውን ልዩነት በመመልከት ቅኔያቱ ሲከፋፈሉ በዋናነት ዐሥራ ሰባት የቅኔ ዐይነቶች አሉ[23]፡፡ የቅኔያቱን ትርጕምና የሚቀርቡበትን ጊዜያትም ሊቃውንቱ በስፋት ገልጸዋል፡፡

1. ጉባኤ ቃና

ይህ ቅኔ ኹለት ቤት ያለው ነው፡፡ ይህም የመለኮትና የትስብእት ምሳሌ ነው፡፡ ጉባኤ ቃና ከዋና ዋና የቅኔ ዐይነቶች አንዱ ነው፡፡ ከሚዜምበት የዜማ ሥልት አንጻር ደግሞ ግዕዝና ዕዝል ጉባኤ ቃና ተብለው ስለሚከፈሉ ኹለት ዐይነት ጉባኤ ቃና ቅኔዎች አሉ ማለት ይቻላል፡፡ ትርጕሙም የቅኔ ትምህርት ተሳካ፣ ተዋጣ፣ ተዋጣለት፣ ጉባኤው ተቃና ተጀመረ ማለት እንደኾነ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ በሌላም በኩል የቅኔው ኹሉ መግቢያ መቃኛ ማለት እንደኾነ ይገልጻሉ፡፡ ይህም የቅኔ ዐይነት በቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ውስጥ የሚቀርበው መወድስ በሚደረስበት ጊዜ "አምላኪየ አምላኪየ እገይሥ ኀቤከ" ተብሎ ከሌሎች ቅኔዎች በፊት ነው[24]፡፡

---

[23]
1. ግዕዝና ዕዝል ጉባኤ ቃና ቅኔ
2. ዘአምላኪየ ቅኔ
3. ሚ በዝኁ ቅኔ
4. ዋዜማ ቅኔ
5. ዐጭር ዋዜማ ቅኔ
6. ሥላሴ ቅኔ
7. ዘይእዜ ቅኔ
8. ሣህልከ ቅኔ
9. መወድስ (ፍታሕ ሊተ) ቅኔ
10. መወድስ (ኵልክሙ) ቅኔ
11. ዐጭር ኵልክሙ ቅኔ
12. ሕንጼሃ ቅኔ
13. ግዕዝ ክብር ይእቲ ቅኔ
14. ግዕዝ ዕጣነ ሞገር ቅኔ
15. ዕዝል ክብር ይእቲ ቅኔ
16. ዕዝል ዕጣነ ሞገር ቅኔ
17. ግዕዝና ዕዝል አሠረ ንጉሥ ቅኔ

[24] ሀብተማርያም 1963፡176፣ በላይነህ 1999፡42፣ ማርዬ 2006፡39

## 2. ዘ አምላኪየ

ዘ አምላኪየ የተባለው ቅኔ ሦስት ቤት ያለው ነው፡፡ ይኸውም በሥላሴ ይመሰላል፡፡ መካከለኛው ቤት መንደርደሪያ ይባላል፡፡ ዜማው ኹልጊዜ ዕዝል ብቻ ነው፡፡ በቤ ተክርስቲያን የሚቀርበው በዐቢይ ጾም መወድስ ሲቆምና በስብሐተ ነግህ አደራረስ ጊዜ በተለይም ሰኞ፣ ማክሰኞና ሐሙስ በኾነ ጊዜ ነው፡፡ ስሙም ዘአምላኪየ የተባለበት ምክንያት የቅኔው መጀመሪያ "አምላኪየ አምላኪየ እገይሥ ኀቤከ" የሚለው የዳዊት መዝሙር እየተዘመረ ስለሚቀርብ ነው[25]፡፡

## 3. ሚ በዝኁ

ሚ በዝኁ ቅኔ እንደ ዘአምላኪየ ቅኔ ሦስት ቤት አለው፡፡ ሦስትነቱ የሥላሴ ምሳሌ ነው፡፡ የመሀሉ ቤት መንደርደሪያ ይባላል፡፡ ዜማውም ኹል ጊዜ ግዕዝ ነው፡፡ ሚ በዝኁ የተባለበትም ምክንያት "እግዚኦ ሚ በዝኁ እለ ይሣቅዩኒ" ከተባለው የዳዊት መዝሙር የሚነሣ ስለኾነ ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያን የሚቀርበው እሑድ ኹል ጊዜ በዐቢይ ጾምና መወድስ በሚደረስበት ጊዜ ነው[26]፡፡

## 4.ዋዜማ ቅኔ

ዋዜማ ባለ ዐምስት እና ባለ ኹለት ቤት ሲኾን ዜማውም አራራይ ነው፡፡ ምሳሌነቱም ረጅም ዋዜማ ዐምስት ቤት መኾኑ የዐምስቱ አዕማደ ምስጢራት ምሳሌ ሲኾን ዐጭር ዋዜማ ደግሞ የትስብእትና የመለኮት ምሳሌ ነው፡፡ ዋዜማ ማለት ብዙ ጊዜ በየበዓላቱ ዋዜማ የሚደርስ ቅኔ ስለኾነ በዚያው ስም ዋዜማ ተብሎ ተጠርቷል፡፡ ረጅም ዋዜማ በበዓላት ዋዜማ (ከበዓላቱ አንድ ቀን ቀድሞ) ሦስት የዋዜማ ቅኔዎች ይቀርባሉ፡፡ ዐጭር ዋዜማ ግን በቅኔው መንገድ ቦታውን ስለያዘ ብቻ ዋዜማ ተባለ እንጂ የሚቀርበው በመወድስ አደራረስ ጊዜ ነው፡፡ ከእርሱም በፊት የሚዘመረው የዳዊት መዝሙር "ለእግዚአብሔር ምድር በምልዓ፤ እግዚአብሔር ነግሠ" የሚል ነው[27]፡፡

## 5.ሥላሴ ቅኔ

ሥላሴ ቅኔ ቤቱ ስድስት ሲኾን ምሳሌነቱም የስድስቱ ቃላተ ወንጌል ነው፡፡ ዜማው ኹል ጊዜ ዕዝል ነው፡፡ ቅኔውም የአበው (የሽማግሌዎች) ቅኔ ተብሎ ስለሚታሰብ ብዙ ጊዜ የሚሰጠው ለዐዋቂዎችና ለታላላቅ ሰዎች ነው፡፡ የሥላሴ ቅኔ የሚቀርበው በዋዜማ ክሥተትና አርያም አደራረስ "በጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅና በይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ

---

[25] ሀብተ ማርያም 1963፡176፣ በላይነህ 1999፡44
[26] ኅሩይ 1918፡6፤ማርዬ 2006፡41
[27] ሀብተ ማርያም 1963፡177

አበዊነ" ጊዜ ሰብሕዎ በሚለው መዝሙር ነው፡፡ ሥላሴ የተባለበት ምክንያት "ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ" በሚለው በጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅ ድርሰት እየገባ የሚነገር ስለኾነ አምላከ አብርሃም፣ አምላከ ይሥሐቅ አምላከ ያዕቆብ እያሉ ሦስትነትን የሚገልጸውን እየዘመሩ ስለሚጀምሩት ሥላሴ የሚለው ስያሜ ተሰጥቶታል[28]፡፡

**6.ዘ ይእዜ ቅኔ**

ቅኔው ዘ ይእዜ የተባለው ከዳዊት መዝሙር "ይእዜ ትሥዕሮ ለገብርከ" በማለት ስለሚጀምር ነው፡፡ ዘይእዜ ቅኔ ዐጭርና ረጅም ተብሎ በኹለት ይከፈላል፡፡ ረጅሙ ባለ ዐምስት ቤት ሲኾን የዐምስቱ አዕማደ ምስጢራት ምሳሌ ነው፡፡ ዜማው ግዕዝ ነው፡፡ ዐጭሩ ደግሞ ሦስት ቤት ያለው ሲኾን ስሙም ሣህልከ ተብሎ የሚጠራበት ምክንያት "ተሣሃለኒ እግዚኦ በከመ ዕበየ ሣህልከ" የሚለውን መዝሙር እየዘመሩ ስለሚዘምሩት ነው፡፡ሣህልከ ቅኔ ብዙ ጊዜ የሚያተኩረው ከሃይማኖታዊ ቀኖና ውጭ ለኾነ ተግባር ማለትም ስለሀገር፣ ስለመንግሥት እና ስለማኅበራዊ ጉዳይ ነው፡፡ የሚቀኘውም ሰው በዕውቀቱም፣ በዕድሜውም ከፍ ያለ ምስጢር ያደላደለ፣ ታሪክን በደንብ ያወቀ መኾን አለበት፡፡ ረጅሙ ዘ ይእዜ የሚቀርበው በታላላቅ በዓላት ዋዜማ በሚቆምበት ጊዜና በስብሐተ ነግህ አደራረስ ጊዜ ነው፡፡ ሣህልከ የሚባለው ዐጭሩ ዘ ይእዜ ግን መወድስ በሚደርስበት ጊዜ ብቻ ነው የሚቀርበው[29]፡፡

**7.መወድስ ቅኔ**

መወድስ የሚለው ቃል ወደሰ አመሰገነ ከሚለው ግሥ የተገኘ ስለኾነ መወድስ የሚለው ስያሜም ከምስጋና ጋራ የተገናኘ በመኾኑ የቅኔው መጠሪያ ኾኗል፡፡ መወድስ የተባለው ቅኔ ኹለት ዐይነት ነው፡፡ አንደኛው "ፍታሕ ሊተ" የሚባለው በስምንት ቤት ይከፈላል፡፡የስምንቱ ብሔረ ኦሪት ምሳሌ እንደኾነ ይነገራል፡፡ ዜማውም አራራይ ነው፡፡ ኹለተኛው ደግሞ ኵልክሙ ዘጠኝ ቤት አለው፡፡ የዘጠኙ ሐጹረ መስቀል ምሳሌ ነው፡፡ ሌላው ዐጭር ኵልክሙ የተባለው ባለ ኹለት ቤት ነው፡፡ የመወድስ ቅኔ የሚቀርበው በመወድስ አቀራረብ ጊዜ "ፍታሕ ሊተ እግዚኦ ወተበቀል በቀልየ" በሚለው መዝሙር ነው፡፡ መንደርደሪያው ሦስተኛው ቤት ሲኾን ዐምስተኛው ቤት ለዓለም ይባላል፡፡ "ፍታሕ ሊተ" የተባለው የዳዊት መዝሙር በሚጀመርበት ቃል ስለተጠራ እንደኾነና "ኵልክሙ" የተባለው ደግሞ "ኵልክሙ አሕዛብ ጥፍሑ እደዊክሙ" የተባለው መዝሙር እየተዘመረ

[28] በላይነህ 1999፡52፣ ማርዬ 2006፡42

[29] ሀብተ ማርያም 1963፡178፣ ጎሩይ 1918፣6

ስለሚጀመር መኾኑ ተገልጿል፡፡ ኵልክሙ የተባለው ቅኔ አብዛኛውን ጊዜ ለታላላቅ ሰዎች፣ ለደብር አስተዳዳሪዎች፣ ለሊቃውንት የሚሰጥ የቅኔ ዐይነት ነው[30]፡፡

**8.ሕንጼሃ ቅኔ**

ሕንጼሃ ቅኔ ኹለት ቤት ነው፡፡ ይኸውም ክሥተት አርያም አደራረስ "ይባርክዎ ኵሉ ግብረ እግዚእ ለእግዚአብሔር" በሚለው ጸሎት መጨረሻ የሚቀኙት ቅኔ ነው[31]፡፡

**9.ክብር ይእቲ ቅኔ**

ክብር ይእቲ ቅኔ ግዕዙም፣ ዕዝሉም አራት ቤት አለው፡፡ ምሳሌነቱም የአራቱ ወንጌላውያን ነው፡፡ ክብር ይእቲ ኹል ጊዜ ነገረ መስቀልን የያዘ ስለኾነ እንደ መርዶ ይቈጠራል፡፡ ሲቀኙትም በጣም በለሆሳስ መኾኑ ስለዚህ ነው ይባላል፡፡ ይኸውም በቅዳሴ ጊዜ ድርገት ከመወረዱ አስቀድሞ የሚቀኙት ቅኔ ነው፡፡ ክብር ይእቲ የተባለበት ምክንያትም ባለ ቅኔው ይህን ቅኔ ተናግሮ ሲጨርስ መዘምራኑ ተቀብለው አንድ ጊዜ ከዘለቁት በኋላ ባለቅኔው "ክብር ይእቲ ዛቲ ለኵሉ ጻድቃኑ" ብሎ የሚሰግድ ስለኾነ ነው[32]፡፡

**10.ግዕዝና ዕዝል ዕጣነ ሞገር**

ግዕዝ ዕጣነ ሞገር ሰባት ቤት ነው፡፡ ከዚሁም ሦስቱ ቤት አሠረ ንጉሥ ይባላል፡፡ ዕዝል ዕጣነ ሞገር ዐሥራ አንድ ቤት ነው፡፡ ከዚህም ዐምስቱ ቤት አሠረ ንጉሥ ይባላል፡፡ ዕጣነ ሞገር የተባለበት ምክንያት በቅዳሴ መጨረሻ የሚቀኙት ስለኾነ ምዕራገ ጸሎት፣ ምዕራገ ዕጣን ማለት ነው ይባላል፡፡ አንዳንዶች ሊቃውንት  ወገረ ከሚለው አንቀጽ የወጣ ቃል ነውና ወገረ=ጣለ ማለት ስለኾነ ቅዳሴው ተፈጸመ ሐመደ ዕጣን የማፍሰሻ ጊዜ ማለት ነው ይላሉ፡፡

**11. አሠረ ንጉሥ**

አሠረ ንጉሥ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው በግዕዝና በዕዝል ዕጣነ ሞገር ከመንደርደሪያው ቀጥሎ የሚገባ ቅኔ ነው አሠረ ንጉሥ የተባለበት ምክንያት ለነገሥታት ምስጋና ብቻ እንጂ የበዓል ቅኔ ባለመኾኑ ነው፡፡ በቀድሞ ዘመን ለነገሥታት ምስጋና ብቻ ይቀርብ ነበር፤ በኋላ ግን ለነገሥታት ዘሮችና አገልጋዮች፣ ለመሳፍንትና ለመኳንንት፣ ለማንኛውም የበላይ ሹመት ላለው ጌታና አለቃ ኹሉ ምስጋና እያደረጉ ማቅረብ የተለመደ ኾነ ይላሉ[33]፡፡

---

[30] ሀብተማርያም 1963፡178፤ ጎሩይ 1918፡7፤ በላይነህ 1999፡58

[31] ጎሩይ 1918፡7

[32] ጎሩይ 1918፡7፤ ሀብተማርያም 1963፡179

[33] ጎሩይ 1918፡8፤ ሀብተ ማርያም 1963፤179

### 2.1.5 የግዕዝ ቅኔ መንገዶች

የቅኔን መንገዶች በተመለከተ እንደባለሙያዎች አገላለጽ ኹለት ዐይነት አመለካከት አለ፡፡ የተወሰኑት የቅኔን መንገዶች በሦስት ዐበይት ክፍሎች ይከፍሏቸዋል፡፡ እነሱም ፩. ሠምና ወርቅ ፪. ብሂል ብሂል ፫. ኅዳና ብለው ይመድቧቸዋል፡፡ ሌሎቹ ደግሞ የቅኔ መንገዶች ብዙና ልዩ ልዩ ናቸው በማለት መቶ ዐሥራ ሰባት የሚኾኑ የቅኔን መንገዶች ከአስረጅ ቅኔዎች ጋራ ያስቀመጡበት ኹኔታ ይታያል፡፡ ይኹን እንጂ አንዱ ከአንዱ ጋራ የሚመሳሰልበት ኹኔታ ይስተዋላል፡፡ በዚህም ጥናት ሰፊ ልዩነት ያላቸውን ዐሥራ አራት የቅኔ መንገዶች በመለየት ማብራሪያቸውን ከነምሳሌያቸው ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ የቅኔ መንገዶቹ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. **ተራ ምሳሌ (ሠምና ወርቅ)**

በቅኔ ውስጥ ሠምና ወርቅ ኾነው የሚነገሩበት ቃላት በተራ ወይም በተርታ ጎን ለጎን ተሰልፈው ሲታዩ አሰካኩ ተራ ምሳሌ ይባላል[34]፡፡

2. **ኅብር መንገድ**

በቅኔ ውስጥ ሠምና ወርቅ ኾነው የሚመሰሉት ስሞች በኹለት ቃላት በመነገር ፈንታ በአንድ ቃል አማካይነት ኹለቱም ተጠቅልለው በተነገሩ ጊዜ አካሄዱ "ኅብር" ይባላል፡፡ ኅብር ቅኔን ለመቀኘት ከሚረዱ ነገሮች አንዱ ኅብርነት ያላቸውን ኹለት ትርጒም ይዘው የሚገኙትን ቃላት ማጥናትና መልመድ ነው፡፡

3. **ውስጠ ወይራ፡-**

ይህም መንገድ የሚጠቀመው ወርቁ ዘርፍ ያለው እንደኾን ነው፡፡ ውስጠ ወይራ የተባለበት ምክንያት "መሶበ አይሁድ" የሚለው ተናባቢ በውስጡ መስቀል የሚለውን ቃል ይዞ በመገኘቱ ነው፡፡ ክርስቶስ ኅብስት ተሠርዐ በመሶበ አይሁድ ወይም ኅብስት ተሠርዐ በመሶበ አይሁድ፡፡ ውስጠ ወይራ ጥቅሙ ከተናባቢው ውስጥ የወርቁን ቃል ማስገኘት መኾኑ ከላይ ተጠቅሷል፡፡ ነገር ግን ይህ አካሄድ አልፎ አልፎ ችግር ይፈጥራል፡፡ ለምሳሌ "መሶበ አይሁድ" ከሚለው ተናባቢ ውስጥ መስቀል የሚለውን የወርቅ ቃል አውጥተናል፡፡ ይህንን የምንለው የአካባቢውን ማስረጃ በማየት በግምት ነው፡፡ ነገር ግን የቃሉ አለመነገር ሙሉ በሙሉ እርግጠኞች ኾነን ትክክለኛውን ቃል ከማወቅ ያግዳናል፡፡ "መሶበ አይሁድ" ከሚለው ተናባቢ ውስጥ ባለቅኔው ሊያወጣ የፈለገው "መቃብር" የሚለውን ቃል ሊኾን ይችላል፤ ምክንያቱም ይህም ቃል ለአንባቢያን ተስማሚ ነውና፡፡ እንግዲህ በውስጠ ወይራ

---

34 ኪዳነ ወልድ 1948፡160፤ፍቅረ ድንግል 1963፡20

ቅኔ የወርቁ ቃል ባለመነገሩ ምክንያት የአድማጩ የትምህርት ደረጃ ከፍተኛ ካልኾነ በስተቀር አንዳንድ ጊዜ ምስጢር በከንቱ ባክኖ ሊቀር ይችላል፡፡

### 4. ዝምድ መንገድ

እንደ ኅብር እና እንደ ውስጠ ወይራ የቃላት ቁጠባ ባይኖረውም ዝምድ ከውስጠ ወይራ ይልቅ ግልጽ በመኾኑ ተወዳጅ መንገድ ነው፡፡ ምሳሌ፡- "ክርስቶስ ኀብስት ተሠርዐ በመስቀል መሶበ አይሁድ" ይህ አካሄድ ዝምድ የተባለበት ምክንያት ወርቁ ከራሱ ይልቅ ለሠሙ አድልቶ የራሱን ዘርፍ ስለ ሰጠው ኹለቱ ነገሮች የተፈቃቀሩና የተዛመዱ መኾናቸውን ለመግለጽ ነው፡፡

### 5. ዐይነ ውሀ (ልብሰ ወርቅ)

ይህ ስያሜ የተወሰደው መልክን ወይም ጥላን በውሀ ውስጥ ከማየት ጋራ በማመሳሰል ነው፡፡ ለምሳሌ ውሀን  በአንድ ሰፊ ዕቃ አድርገን ከወለሉ ላይ አስቀምጠን ከውስጡ ብንመለከት የቤቱን ጣራ እንመለከታለን፡፡ ሌላም ብዙ ነገር እናያለን፡፡ ነገር ግን እጃችንን ከውሀው ውስጥ ብንከተው ምንም የምንጨብጠው ነገር የለም፡፡ እንዲኹም በዚህ ዐይነት ቅኔ ውስጥ በተነገሩት ጥቂት ቃላት አማካይነት ያልተነገሩትና ሊኖሩ የሚያስፈልጉት ቃላት ኹሉ ወለል ብለው ስለሚታዩ አካሄዱ ዐይነ ውሀ ተብሎ ተሰይሟል፡፡ የመንገዱን ጠቃሚነት በሚከተለው ምሳሌ እንይ፤ "እግዚአብሔር ይሬዕየኒ" ይህ በዐይነ ውሀ መንገድ የተነገረ ነው፡፡ የዐይነ ውሀ ጠቃሚነት በጥቂት ቃላት ሙሉ ዐሳብ  መግለጽ መቻሉ ነው፡፡ ቃላትን ለመቆጠብ ከሌሎች መንገዶች ኹሉ በይበልጥ የተሻለ ነው[35]፡፡

### 6. ሠም ለበስ

በልብስ ተሸፍኖ የተቀመጠ ወይም የተኛ ሰው በትክክል ማንነቱ ባይታወቅም ሰው መኾኑና ሕፃን ወይም ትልቅ መኾኑ እንደሚታወቅ ኹሉ እንዲሁም በዚህ ዐይነቱ የቅኔ መንገድ ምንም ሠሙ ወርቁን ቢሸፍነው ወርቁ ከውስጡ መኖሩ ይታወቃል፤ ነገር ግን በትክክል ይህ ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡

### 7. ጽድቅ መንገድ

ጽድቅ መንገድ ማለት ሙያዊ ቴክኒክ የጎደለው ማለት ነው፡፡ ይኸውም ሠምና ወርቅ ኅብር የሌለው እውነቱን (ታሪኩን) ብቻ በቅኔ መልኩ የሚያቀርብ ነው፡፡

---

[35] ሀብተ ማርያም 1963፡200

**8. ጉራማይሌ (ፍርንዱስ)**

ይህ የቅኔ መንገድ ግዕዝ እና ዐማርኛ እኩል በእኩል በቅኔው ውስጥ እየተቀላቀሉ የሚቀርቡበት አካኼድ ነው፡፡

**9. ሠም ገፊ፡**

ይህ የቅኔ መንገድ የሽማግሌ ጭውውት ወይም የብልኅ ሰው ምክር ይመስላል፡፡ የተጣላን የሚያስታርቅና ጥፋተኛን የሚገሥጽ ሰው ንግግሩን በምሳሌ እንደሚጀምር ኹሉ በዚህም ቅኔ ውስጥ ባለቅኔው ቅኔውን በምሳሌ ይጀምራል፡፡ በዚህ አካሄድ ውስጥ ማስተዋል የሚገባው በምሳሌ መጀመርንና ከምሳሌውም በርከት አድርጎ መለገሱን ነው፡፡ ሠም ገፊ የተባለበትም ምክንያት የሠሙን ታሪክ በቅድሚያ በመተረኩ ነው፡፡

**10. ወርቅ ገፊ**

በዚህ ዐይነት ቅኔ ውስጥ ባለቅኔው በቅኔው መጀመሪያ ላይ አንድ ዐሳብ ይሠነዝራል፡፡ ከዚህ በኋላ እስከ ቅኔው መጨረሻ ድረስ የዐሳቡን ልክነት ለማስረዳት ልዩ ልዩ ማስረጃዎችን እያስገባ ቅኔውን ይጨርሳል፡፡

**11.ፍላጻ (የቀስት ጦር)**

ይህ መንገድ ከቃላቱ የአቀማመጥ ለውጥ በስተቀር በንግግር ጣዕም ረገድ ፍላጻና ዝምድ የሚሰጡት አገልግሎት ተመሳሳይ ነው፡፡ ብያኔውም የሠም ባለቤት ከወርቅ ዘርፍ ተናቦ እየቀደመ የወርቅ ባለቤት ሲከተል ፍላጻ ይባላል፡፡ አሰካኩም "ክርስቶስ ኅብስት ተሠርዐ በመሶበ አይሁድ መስቀል" "መስቀል" የሚለው ቃል በዝምድና አካሄድ ይዞት የነበረውን ስፍራ ለቆ፣ ተስፈንጥሮ፣ በመጨረሻ ላይ ሄዶ እንደቆመ ማስተዋል ይገባል፡፡ ፍላጻ ያሰኘውም ይኸው ግብሩ ነው፡፡ የፍላጻ ጥቅም አንድ ቅኔ በዝምድ መንገድ ቤት ለመምታት፣ ዜማ ለማስተካከል ሲያስቸግር ለመለወጫ ኾኖ ማገልገል ነው[36]፡፡

**12.ሠረዝ መንገድ**

በጀመሩበት ከሚጨርሱት የቅኔ መንገዶች አንዱ ሠረዝ የተባለው ነው፡፡ በዚህ ዐይነት የቅኔ መንገድ ውስጥ ባለቅኔው በቅኔው መጀመሪያ ላይ ስለኹለት ወይም ስለ ሦስት ነገሮች የሚናገር መኾኑን ይገልጣል፡፡ ከዚያ በኋላ ስለ እያንዳንዱ በየተራ ያትታል[37]፡፡

---

[36] ዓለማየሁ 1950፡126
[37] ኪዳነ ወልድ 1948፡167

**13.ውስጠ ዘ መንገድ**

ውስጠ ዘ ማለት በውስጡ ዘ ያለበት ቃል ማለት ነው፡፡ ዘ የተባለው የግዕዝ አገባብም ሲፈታ "የ" ማለት ይኾናል፡፡ ውስጠ ዘ ከአንድ ግሥ ከሚወጡ የቃል ዘሮች (ዘመድ ዘር፣ ባዕድ ዘር ወዘተ) ውስጥ አንዱ ነው፡፡

**14.አንጻር መንገድ**

ይህ የቅኔ መንገድ ከሠም ገፈ ጋራ ተመሳሳይ ነው፡፡ ኾኖም በሠም ገፈ ውስጥ ለወርቁ ተመሳሳይ ወይም አፍራሽ ኾኖ የሚገባው ሠም ተረትና ምሳሌን የመሰለ ወይም ሕይወት የሌለው ነገር ሲኾን፣ በአንጻር መንገድ ግን ብዙውን ጊዜ ሠም ኾኖ የሚገባው እውነተኛ ታሪክ ነው፡፡አንጻር ቅኔዎች ለመቀኘት በቅዱሳት መጻሕፍትና በታሪክ እንዲሁም በሕገ ፍጥረትና በሥነ-ፍጥረት ሰፊ ዕውቀት ያስፈልጋል[38]፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ዐቢይ ርእስ ስለ ቅኔ ምንነት በሙያው ሊቃውንት የተሰጠው ብያኔ ተመርምሯል፤ ከዚያም በቅኔ አጀማመር ዙሪያ የተለያዩ ትረካዊ ሐሳቦች ተዳሰዋል፤ በማስከተልም የቅኔና የታሪክ ግንኙነት በሚለው ንኡስ ርእስ ታሪክ ለቅኔ የጀርባ አጥንት መኾኑና እንዲሁም የታሪክ መገኛ ምንጮቹ በስፋት ታይተዋል፡፡ በመቀጠልም ከጉባኤ ቃና እስከ አሠረ ንጉሥ ያሉት ዐሥራ ሰባቱ የቅኔ ዐይነቶች ተብራርተዋል፡፡በመጨረሻም ከብዙዎቹ የቅኔ መንገዶች የተወሰኑትን ከነሙሉ ማብራሪያቸው ለማየት ተሞክሯል[39]፡፡

## 2.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ይህ ጥናት በግዕዝ ቅኔ ላይ በመኾኑ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኬኔዲ ቤተ መጻሕፍት እና በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም በቅኔ ዙሪያ የተሠሩ (ዲማጸች) የመጀመሪያ፣ኹለተኛና ሦስተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ከዚህ ጥናታዊ ሥራ ጋራ ያላቸው ተመሳሳይነት እና ልዩነት ተብራርተው እንደጥናት ዕድሜያቸው በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

መጀመሪያ ዮሐንስ አድማሱ "ሠምና ወርቅ" (1959) ብሎ ያቀረበው ጥናታዊ ሥራ በቅኔ መንገድ በሠምና ወርቅ ዙሪያ ትኩረት ያደርጋል፡፡ በጥናቱ የቅኔ መንገድ በጥልቀት ተመርምሯል፡፡ ዮሐንስ በሠምና ወርቅ ሥልት ላይ ትኩረት ሰጥቶ፤ ቅኔን ራሱን አስችሎ በማጥናት የሠምና ወርቅን ፅንሰ ሐሳብና ዐዋጆቹን ማብራራት ችሏል፡፡ ይህ ጥናታዊ ሥራ ከዚህ ጥናት ጋራ ተመሳሳይነትና ልዩነት ይታይበታል፡፡የሚመሳሰልበት ነገር ጥናቱ የቅኔን

---

[38] ኪዳነ ወልድ 1948፡170

[39] የዐሥራ አራቱን የቅኔ መንገዶች ምሳሌያቸውን በዐባሪ ላይ ማየት ይቻላል፡፡

አመጣጥና አጀማመር በመቃኘቱ እና የምሰላን ጉዳይ በማየቱ በመጠኑም ቢኾን ግንኙነት አለው፡፡ የሚለይበት ጉዳይ ደግሞ ጥናታዊ ሥራው ትኩረቱ በቅኔ መንገድ በሠምና ወርቅ ላይ መኾኑ ነው፡፡ ሌላው የዓላማ ልዩነት ነው፡፡ ዮሐንስ በጥናታዊ ሥራው ዐላማ ያደረገው የሠምና ወርቅን ፅንሰ ሐሳብ እና አዋጆቹን መተንተን ነው፡፡ የዚህ ጥናታዊ ሥራ ዐቢይ አቅጣጫ ግን በግዕዝ ቅኔያት ውስጥ የነገረ ሰብእን ጉዳይ መመርመር ነው፡፡ ዓላማውም በቅኔያቱ አማካይነት የትርጓሜ (ፍካሬ) ሥልትን መሠረት በማድረግ በማኅበራዊ ጉዳይ ላይ የተነገሩ የግዕዝን ቅኔያት ፅንሰ ሐሳብ መፈከር ነው፡፡ ስለኾነም ይህ ጥናት ከተጠቀሰው ጥናታዊ ሥራ በአቀራረብም ኾነ በዐላማ ይለያል፡፡

ኹለተኛ ፍቅረ ድንግል "ቅኔ መቀኘትና መቍጠር (በግዕዝ)"(1963) ባቀረበው ጥናት የቅኔ ይትበሀል ተዳሷዋል፡፡ በጥናታዊ ሥራው የቅኔ መንገዶች በስፋት ታይተዋል፡፡ ፍቅረ ድንግል ጥናታዊ ሥራውን ሲያቀርብ በቅኔ ይትበሀል እና ስለመቀኘት መቁጠር ላይ ያተኩራል፡፡ አጥኚው የቅኔ ምስጢር ከሥርዓተ ግጥም አንጻር ለዘመኑ ተመራማሪ እንዲመች አድርጎ ማቅረቡን እንደ ዐላማ ይዞ ተነሥቷል፡፡ ፍቅረ ድንግል ከግጥም አንጻር ቅኔን በማጥናቱ ለተመራማሪዎች ሰፊ ዕድል እንደፈጠረ በግቡ አሳይቷል፡፡ ይህ ጥናታዊ ሥራ ከዚህ ጥናት ጋራ አንድነትና ልዩነት አለው፡፤ አንድነቱ ስለቅኔ ታሪካዊ አመጣጥ እና የቅኔን መንገዶች በመዳሰሱ ተመሳሳይነት አለው፡፡ ልዩነቱ ደግሞ የትኩረት አቅጣጫው በቅኔ ይትብሀል ላይ መኾኑ ነው፡፡ እንዲሁም በዐላማ ልዩነት ይታያል፡፡ ፍቅረ ድንግል ለጥናታዊ ሥራው ዐላማ አድርጎ የተነሣው የቅኔ ምስጢር ከሥርዓተ ግጥም አንጻር ለዘመኑ ተመራማሪ ማቅረብ ነው፡፡ የዚህ ጥናታዊ ሥራ ዐቢይ ትኩረት ግን ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸውን ቅኔያት በመሰብሰብ ትንተና መስጠት ነው፡፡ ዐላማውም ፖለቲካዊ ሥልትን አስመልክቶ የቀረቡ ቅኔያትን መተንተን ነው፡፡

ሦስተኛ ጽጌ አባተ "ቅኔያዊ ውርስ" (1972) በሚል ርእስ ያቀረበው ጥናታዊ ሥራ በቅኔ ትርጓሜ እና ከየት መጣ ሳይንሳዊ ትንተና ላይ ያተኩራል፡፡ ጽጌ በጥናቱ ውስጥ የቅኔን ምንነት፣ የቅኔን አጀማመር እንዲሁም የቅኔን ትምህርት ቤቶች፣ የቅኔን ዐይነቶች አካቷል፡፡ የጥናቱ ዐላማም የግዕዝ ቅኔን ለአንባቢያን ማስተዋወቅ ነው፡፡ ይህ ጥናታዊ ሥራ ከዚህ ጥናት ጋራ የሚገናኝበትና የሚለይበት ጉዳይ አለው፡፡ የጽጌ ጥናታዊ ሥራ በትኩረት አቅጣጫው ተመሳሳይነት አለው፡፡ የግዕዝ ቅኔ ምንነትና የግዕዝ ቅኔ አጀማመር በሚሉት ነጥቦች አንድነት ይኖረዋል፡፡ ልዩነት ደግሞ ጽጌ ስለቅኔ ትምህርት ቤት እና ስለቅኔ

ዐይነቶች ብሎ ባነሳቸው ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ ይለያል፡፡ እንዲሁም የዐላማ ልዩነት ይስተዋላል፡፡ ጽጌ ዋና ዐላማው አድርጎ የተነሣው የግዕዝ ቅኔን ትርጓሜ እና ከየት መጣ የሚለውን ለአንባቢያን ማቅረብ ነው፡፡ ይህ ጥናት ግን የትኩረት አቅጣጫው የግዕዝን ቅኔ ከሃይማኖታዊ አገልግሎቱ አንጻር የቅኔያቱን ውስጣዊ ምስጢር ተንትኖ ማሳየት ነው፡፡

አራተኛ ይኄይስ ኃይለ ሚካኤል"የግዕዝ መወድስ ቅኔ" (1975) ብሎ ባቀረበው ጥናታዊ ሥራው የግዕዙን ቅኔ ቅርጽ እና ይዘት ከሥነ-ግጥም አንጻር ምን ዐይነት ተመሳሳይነት እንዳለው በማሳየት ላይ ትኩረት ይሰጣል፡፡ ይኄይስ የቅኔን ቤት ጠቀሜታ፣ የቅኔን ዐይነቶች በጥናቱ ውስጥ አካቷል፡፡ በተለይ ከቅኔያት መካከል "መወድስን" በመውሰድ ያለውን ቅርጽ እና ይዘት በጥናታዊ ሥራው አሳይቷል፡፡ ጥናታዊ ሥራው ከዚህ ጥናታዊ ሥራ ጋራ የሚገናኝበትና የሚለያይበት የአቅጣጫ ትኩረት አለው፡፡ ይኄይስ የዚህ ጥናት አንድ አካል የኾነውን የግዕዝ መወድስ ቅኔን በማንሳቱ እና የቅኔውን ትርጒም በማቅረቡ ከዚህ ጥናት ጋራ ተመሳስሎ ይታይበታል፡፡ ልዩነቱ ግን በይኄይስ ጥናት ቅኔያቱ ሃይማኖታዊ ይዘት ብቻ ያላቸው መኾኑና በትንተና መልኩ ተብራርቶ ባለመቅረቡ ከዚህ ጥናት ይለያል፡፡ ይኄይስ ለጥናታዊ ሥራው ዐላማ አድርጎ የተነሣው የግዕዝን መወድስ ቅኔ ለአንባብያን ማስተዋወቅ ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዐላማ ግን ከሃይማኖታዊው ጭብጥ በተጨማሪ በግለሰቦች ሙገሳና ነቀፋ እንዲሁም የወቅቱን ፖለቲካዊ ኹኔታ ጠገግ አድርገው የቀረቡ ቅኔያትን አራቆ በትርጓሜ ሥልት መሠረት መመርመር ስለኾነ ልዩ ያደርገዋል፡፡

ዐምስተኛ አበበ ከበደ "የመልአከ መልአክ ተስፋ የዋሸራ ውስጠ ዘ የግዕዝ ቅኔና ቅኔው ከሌሎች ቅኔዎች የሚለይባቸው ባሕርያት"(1993) በሚል ርእስ ባቀረበው ጥናት ከቅኔ መንገዶች በአንዱ የቅኔ መንገድ "ውስጠ ዘ ቅኔ" ላይ ትኩረት ሰጥቶ አጥንቷል፡፡ ጥናታዊ ሥራውን ለመሥራት ዐቢይ ዐላማ ያደረገው የውስጠ ዘ ቅኔን ምንነት፣ ትርጒምና ምስጢር ለአንባብያን ማሳወቅ ነው፡፡ አበበ በአንድ የቅኔ ሥልት ላይ ትኩረት በማድረግ፣ ጥናታዊ ሥራውን አቅርቧል፡፡ እንዲሁም የውስጠ ዘ ቅኔን ባሕርይና አጀማመር በጎጃም መኾኑን ገልጿል፡፡

አበበ ምንም እንኳን የቅኔያቱን ትርጒምና ምስጢር በማቅረቡ ከዚህ ጥናታዊ ሥራ ጋራ ተቀራራቢነት ቢኖረውም በይዘቱ፣ በአቀራረቡና በዐላማው ግን የመለያየት ኹኔታ ይታያል፡፡ አበበ በውስጠ ዘ መንገድ ላይ ተመሥርቶ ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸውን ቅኔያት

ተመልክቷል፡፡ ዐላማውም የውስጠ ዘ ቅኔን ልዩ ባሕርያት ባብዛኛው አንባቢ ዘንድ ከሚታወቀው ከሠምና ወርቅ ቅኔ ጋራ በማነጻጸር  ማመልከት ነው፡፡ በዚህ ጥናታዊ ሥራ የሚቀርቡት ቅኔያት ግን የይዘት አቅጣጫቸው ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ ያደረጉ ናቸው፡፡ የዚህ ጥናት ዐቢይ ዐላማም ጉዳያቸው ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ የኾኑ የግዕዝን ቅኔያት ሰብስቦ በመተንተን ሦስቱ የነገረ ሰብእ ጉዳዮች እንዴት እንደተሳሰሩ የቅኔያቱን ቴክኒካዊ ብልኀት  መዳሰስ ነው፡፡

ስድስተኛ ይኩኖ አምላክ መዝገቡ "በግዕዝ ቅኔ ሠም ውስጥ የሴት ገጸ ባሕርያት ገለጻ" (1997) ዙሪያ ጥናታዊ ሥራውን በግዕዝ ቅኔ ላይ አካኺዷል፡፡የጥናቱ መነሻ ምክንያትም የግዕዝ ቋንቋ እንደማንኛውም ሥነ-ጽሑፍ ሰዋዊ ጉዳዮች እንደሚቀርቡበት ለማመልከት ነው፡፡[40] በጥናቱ ሴቶች በሠናይና በኢሠናይ ገጸ ባሕርያት የተሳሉባቸውን የግዕዝ ቅኔያት በመለየት ሰፊ ትንተና ሰጥቷል፡፡ የጥናቱ ዋና ዐላማ የግዕዝ ቅኔያትን ከያሉበት መድበላት ለጥናቱ ተስማሚ የኾኑትን መርጦ ይዘታቸውን ማጥናትና ማብራራት ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዐቢይ ዐላማ ግን በነገረ ማኅበረሰብ፣ በነገረ ፖለቲካና በነገረ ሃይማኖት ዙሪያ የቀረቡ ቅኔያትን መመርመር ነው፡፡ የይኩኖ ጥናት በትኩረት አቅጣጫው በግዕዝ ቅኔ ሠም አማካይነት የማኅበረሰብ አካል ስለኾኑት ሴቶች ሰፊ ትኩረት አድረጓል፡፡ የእኔ የትኩረት አቅጣጫ ደግሞ አጠቃላይ ኹሉንም ማኅበረሰብ ለማየት የተሞከረ ሲኾን በሠሙ ብቻ ሳይኾን እንደ ቅኔያቱ ሥሪት ወርቁንም እንደመባያ ጉዳይ አድርጌ ተጠቅሚያለኹ፡፡ ይኩኖ በጥናቱ የግዕዝ ቅኔን ሠማዊ ባሕርይውን በማየቱና በሴቷ ገጸ ባሕርይ  ማኅበራዊን ጉዳይ በማንሣቱ ከዚህ ጥናት ጋራ ተመሳሳይነት አለው፡፡ የሚለይበት ደግሞ የሴቶችን ገጸ ባሕርይ ብቻ ለይቶ በማየቱና ሌሎች የነገረ ማኅበረሰብን ጉዳዮች ባለማንሣቱ ከእኔ ጥናታዊ ሥራ ይለያል፡፡ የእኔ ጥናት ግን የግዕዝ ቅኔያትን ከማኅበራዊ፣ ከፖለቲካዊና ከሃይማኖታዊ ጉዳዮች አንጻር በማየቱ ይለያል፡፡ ሌላው ይኩኖ አምላክ ከሌሎቹ አጥኚዎች በተለየ ኹኔታ የቅኔያቱን ሠማዊውን ባሕርይ ብቻ በመመርመር ማኅበራዊ ፋይዳዎችን አይቷል፡፡ ሌሎቹ ጥናቶች ሃይማኖታዊና ሰዋስዋዊውን ባሕርይ  ተመልክተዋል፡፡

---

[40] የግዕዝ ቋንቋ የሃይማኖት ቋንቋ በመኾኑ የመለኮትን ኀይል፣ የመላእክትን ሥነ-ፍጥረትና የቅዱሳንን ገድል ብቻ ያትታል ሰዋዊነት ይጎድለዋል የሚለውን ሐሳብ በመንቀፍ ነው፡፡ ቋንቋው ከሥነ-ጽሑፍ የሚጠበቀውን የሰውን ልጅ ፍልስፍና፣አኗኗር፣ ፍቅር፣ ጥላቻ፣ሀዘን፣ ደስታ፣ ፍርሀትና ድፍረት ባማረ መልኩ የሚገልጽ ነው ይላል፡፡

ሰባተኛ በላይነህ ደሴ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ “የቅኔ ቄጠራ፣ ነገራና ዘረፋ በተመረጡ የጎጃም ጉባኤዎች ውስጥ”(1999) በሚል ርእስ ባቀረበው ጥናት የጥናቱ ዐቢይ ዐላማ አድርጎ የተነሣው በግዕዝ ቅኔ ጉባኤዎች ውስጥ በትምህርትነት የሚቀርቡና በተለምዶ የሚከናወኑ ተግባራትን በጽሑፍና በምስል ቀርጸ ለዘመናዊውና ለተተኪው ትውልድ ማስተማርና ማስተላለፍ ነው፡፡ በዚህ መነሻነት ትኩረቱ በጎጃም የቅኔ ጉባኤዎች ላይ ኾኖ በይዘቱም ስለጎጃም የግዕዝ ቅኔ ቄጠራ፣ ነገራ፣ ዘረፋና ሌሎች የግዕዝ ቅኔ ትምህርት ቤት ሥርዓቶችን ተመልክቷል፡፡በላይነህ በጥናቱ የግዕዝን ቅኔ አስመልክቶ በቃላዊነቱ ዕውቅና ያለውን የግዕዝን ቅኔ ለኹሉም ተደራሽ እንዲኾን ጥበባዊ ቅርሱን ሰንዶ ለትውልድ ለማቆየት ያደረገው አስተዋፅኦ በመጠኑም ቢኾን ከዚህ ጥናት ጋራ ያዋግነዋል፡፡ ነገር ግን ይህን ጥናት ልዩ የሚያደርገው በሊቃውንቱ የተፈጠሩትን የግዕዝ ቅኔያት ከማኅበራዊ፣ ከፖለቲካዊና ከሃይማኖታዊ ዐውዳቸው አንጻር መፈተሹ ነው፡፡በላይነህ ቅኔያቱ ገና ሲፀነሱ ያለውን ኺደት የተመለከተ ሲኾን ይህ ጥናት ግን ከውልደት በኋላ ያለውን ጣጣ ተመልክቷል፤ በተፈጠሩበት ነገረ ጉዳይ ላይ ትኩረት በማድረግ ፅንሰ ሐሳባቸውን መመርመር ይኾናል፡፡ቅኔያቱ ከአንድ ማሕፀን ተወልደው የተለያዩ ነገረ ጉዳዮችን ይዘው ይገኛሉ፡፡ከዚያም እንደ ጉዳያቸው በያዙት ሐሳብ መሠረት በመመደብ ነገረ ማኅበረሰብ፣ ነገረ ፖለቲካና ነገረ ሃይማኖት ብሎ መፈከር በመኾኑ ይህን ጥናት ከተጠቀሰው ጥናት ልዩ ያደርገዋል፡፡

በመጨረሻም በስርግው ገላው “Historical Development of Geez Qene in Different periods” (2009) በሚል ርእስ ለዶክትሬት ማዕረግ ማሟያ በቅኔ ላይ የተካኼደ አንድ ጥናታዊ ምርምር ተገኝቷል፡፡ይህ ጥናታዊ ምርምር በውጭ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት የቀረበ ነው፡፡ ጥናታዊ ምርምሩ ሰፊ ርእሰ ጉዳዮችን የዳሰሰ ኾኖ አግኝቸዋለሁ፡፡ይኹን እንጂ በዋናነት የሚያተኩረው በቅኔ ይዘት እና ቅርጽ ታሪካዊ እድገት ላይ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ቅኔ የሥነ ግጥም ባሕርይ እንዳለው፣ቃላዊ ሥነ-ጽሑፍን እንደሚመለከት ተጠቁሟል፡፡ ጥናታዊ ምርምሩ በዋናነት ከእኔ ጋራ የሚመሳሰለው ማኅበራዊ፣ባህላዊ፣ሃይማኖታዊ እና ፖለቲካዊ ክሥተቶችን ከመግለጽ አንጻር ቅኔ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ማቅረቡ ነው፡፡ ይኹን እንጂ ከላይ እንደጠቀስኩት ዋና አትኩሮቱ ታሪካዊ እድገቱ ላይ በመመሥረቱ ከእኔ ጥናት ጋራ ልዩነት አለው፡፡ ቅኔ የኢትዮጵያውያን ዕሳቤ፣ስሜት፣ሐሳብ እንደሚያሳይ ስርግው በጥናታቸው አንሥተዋል፡፡ የእኔ ጥናት ከዚህ

ሐሳብ ጋራ የተጎዳኘ ነው፡፡ በዚህ ጥናት የቅኔ ታሪካዊ እድገት ሲጠና በየዘመናቱ ተከፋፍሎ ቀርቧል፡፡ ሰፊ የታሪክ ጊዜያት ተዳሰዋል፡፡ የእኔ ጥናት ከማኅበራዊ፣ከፖለቲካዊ እና ከሃይማኖት አንጻር  የተሰበሰቡ ቅኔያትን ያጠናል፡፡ የታሪክ ዘመኑም ከዐፄ ምኒልክ እስከ ዘመነ ደርግ ባሉ ውሱን ቅኔያት ላይ የመሠረተ ነው፡፡ ኹለቱ ጥናቶች ከሚያጠኑት የዘመን መጠን እና ስፋት አኳያ ልዩነት አላቸው፡

ስርግው የቅኔያትን አገልግሎት ከሃይማኖት አንጻር ከዜማ ጋራ በማስተሳሰር፣ዓለማዊ ጠቀሜታውንም ከሠምና ወርቅ ፅንሰ ሐሳብ ከምጣኔ ጋራ እንደሚገናኝ ገልጸዋል፡፡ በቀጣይነትም ስርግው በጥናታቸው ልዩ ትኩረት የሰጡት ለድጓ ት/ቤት እና ለድጓ ቅኔዎች ነው፡፡ በጥናታቸው ውስጥ የድጓ ቅኔዎች ምን ዐይነት መኾናቸውን በመግለጽ፣   በድጓ እና በቅኔ መሀል ያለውን ጥብቅ ግንኙነት እማሳየት ላይ አተኩረዋል፡፡ ስርግው ቅኔ ከመካከለኛ ዘመን እስከ ዘመናዊ የቅኔ ዘመን ድረስ ከቅኔያቱ በመነሣት ያመጣው የቅርጽ እና የይዘት ለውጥ የየዘመናቱን ቅኔ በመመደብ አጥንተዋል፡፡ የእኔ ጥናት ግን የቅኔ ታሪካዊ እድገትን ስለማይመለከት በቅኔ እና በድጓ መሀል ያለውን ትስስር እና የእድገት ሽግግር አይዳስስም፡፡ በኹለቱ ጥናቶች መሀል ያለው ግንኙነት  ከዘመናዊ ቅኔያት ይጀምራል፡፡ ይኹን እንጂ በዘመናዊ ቅኔያትም ኹለቱ ጥናቶች የዐላማ እና የአንጻር ልዩነት አላቸው፡፡ በእኔ እና በስርግው ጥናት መሀል ከጥናቱ አመክንዮ፣ ከዐላማ፣ከወሰነ ጥናት እና ከሥነ ዘዴ አንጻር ልዩነት አለ፡፡ ለስርግው የጥናቱ አመክንዮ የቅኔ ታሪካዊ እድገት በቅጡ አለመታወቁ እና ከሃይማኖት አንጻር ብቻ ያለው አገልግሎቱ መወሳቱ ነው፡፡ ለእኔ ጥናት መነሻ ቅኔያት የዘመኑን መንፈስ ከማኅበራዊ እስከ ፖለቲካዊ ማሳየታቸውን መፈተሽ ላይ ነው፡፡ ሌላው ልዩነት በወሰነ ጥናት ነው፡፡ ስርግው በቅኔ ይዘት እና በቅርጽ ላይ በዋናነት መመሥረታቸውን በመግለጽ የጥናቱን ወሰን አመላክተዋል፡፡ የእኔ ጥናት ግን ቅኔያት ከማኅበራዊ እስከ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ድረስ የጊዜውን መንፈስ በማሳየታቸው ላይ በማተኮሩ የተገደበ ነው፡፡ ስርግው ጥናታዊ ምርምሩን በመስክ እና በቤተ መጻሕፍት በማድረጋቸው እኔ ግን በቤተ መጻሕፍት ሥራዎች ላይ ብቻ በማተኰሬ ከሥነ ዘዴ አንጻር  ተመሳስሎ እና ልዩነት አለ፡፡

ስርግው በሥነ ዘዴ ውስጥ ንጽጽራዊ ዘዴን፣ ሀገር በቀል መንገድን፣ፍካሬን እና የታሪክ ዐውድን ተጠቅመዋል፡፡ የእኔም ጥናት ከዚህ ጥናታዊ ምርምር ጋራ በሚከተለው ዘዴ በፍካሬ፣በትረካ ዐውድ፣በሀገር በቀል መንገድ ተመሳሳይነት አለው፡፡ ነገር ግን ስርግው

ንጽጽራዊ ዘዴ ሲጠቀሙ እኔ በነገረ ፍካሬ ላይ በማተኰሬ በኹለቱ ጥናታዊ ምርምሮች መሀል የሥነ ዘዴ ልዩነት አለ፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ የጥናት ሥራዎች ጉዳያቸውን በግዕዝ ቅኔያት ላይ ትኩረት አድርገው በመሠራታቸው ከእኔ ጥናታዊ ምርምር ጋር ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ ነገር ግን የቅኔ ታሪካዊ እድገት፣ስለሴት ገጸ ባሕርያት፣ የቅኔ መንገዶችን፣ የቅኔን ቅርጽና ቈጠራ፣ ነገራና ዘረፋና መቀኘት የሚሉትን በዋናነት በማንሳታቸው እንዲሁም ቅኔን ከሃይማኖታዊ አገልግሎቱ አንጻር ብቻ መመልከታቸው ከዚህ ጥናት ይለያሉ፡፡ ይህ ጥናት ከተገለጹት ጥናታዊ ሥራዎች የሚለየው በተወሰነ የዘመን ዐውድ ላይ ተመሥርቶ፤ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ይዘት ባላቸው ቅኔያት ላይ ማተኮሩ ነው፡፡

# 2.3 ንድፈ ሐሳብ

## 2.3.1 ነገረ ፍካሬ

ይህ ጥናታዊ ምርምር በግዕዝ ቅኔያት ላይ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሃይማኖታዊ ትንተና ለመስጠት በነገረ ፍካሬ ንድፈ ሐሳብ ይገለገላል፡፡ የነገረ ፍካሬ ንድፈ ሐሳብ የቅኔያትን የአርቅቆት ዕሳቤዎች ለመተንተንና ለመፈከር ወሳኝ እና ተመራጭ ንድፈ ሐሳብ ነው፡፡ የቅኔያት ምስጢር በአተረጓጐማቸው በብዙ ኅዳና የሚጓዙ በአንድነት ነጠላ ትርጒም የማይጠቃለሉ ናቸው፡፡

የባለቅኔው አእምሮ በገባበት ስፍራ እና ኩነት ውስጥ ንቡር የኾነውን እና የተለመደውን ዕሳቤ በእንግዳ ዕሳቤ እያጣለፈ የሚያመጣው ነውና፡፡ ስለዚህ የባለ ቅኔው ጥበብ የተለመዱ ጉዳዮችን በቅኔያዊ ዕሳቤው በዐዲስ ቀለማት አስጊጦ በነገሮች ላይ ለነበረን ግንዛቤ እና ዕውቀት ዐዲስ የአተያይን፣ የአተረጓጐምን ኅዳና ይጠርግልናል፡፡

ባለ ቅኔው ትናንት የተጠቀመው መባያ ጉዳይ /የቅኔውን ማሳያ/ ሠማዊ አስተማስሎ እየደገመ የሚኖር አይደለም፡፡ትናንት ለሌላ ፅንሰ ሐሳብ ሠረገላ አድርጎ የተጠቀመው ሠማዊ መባያ ሌላ የተለየ ፅንሰ ሐሳብ ለመግለጥ ይጠቀምበታል፡፡ "የምንኖርባት ዓለም እንደ መጽሐፍ ተገልጦ የማያልቅ ገጸ ትርጓሜዎች ስላሏት"[41]፡፡ መቼም መች አእምሮው ከቅኔ አርቅቆት አይፋታም፤ ትናንት ባረቀቀው ውብ ቅኔ ረክቶ መንፈሱ አያርፍም፡፡ ትናንት ያረቀቀውን፣ በአደባባይ የዘረፈውን፣ በቅኔ ማሕሌት የተቀኘውን ቅኔ በሌላ ስፍራ

[41] Cavalaro, 49

ለተመሳሳይ ግብር አይጠቀምበትም፡፡ ይህ ዕሳቤ “የቅኔ ቋንጣ የለውም” በሚለው ብሂለ አበው ዘወትር ይወሣል፡፡ የተደረገን ቅኔ መልሶ ማድረግ በቅኔ ባህል እና ልማድ እጅግ ነውር ነው፡፡ በስርቆት የመምህሩን ቅኔ በቅኔ ማሕሌት ሲያደርግ ተሰምቶ “ቅኔያቸውን ሰምተናል፤ የኔታ ደኅና ናቸው?” የሚሉ የግብሩን ጸያፍነት የሚተርኩ ትርክቶች በየቅኔ ቤት ይነገራሉ፡፡ይህ ብሂል በሰው ጌጥ አያጌጡ እንደማለትና የሙያ ስርቆት ልማድ ማክሰሚያ ተግሣጽ ነው፡፡ ይህን መሰሉ ዕሳቤ ከዚህ በተጨማሪ ቅኔ የትርጓሜ ጠባይ ስላለው ኹሌም እራሱን በዐዲስ መልክ እየተረጐመ መኖሩን ማሳያ ነው፡፡

በሌላ መልኩ የቅኔ ባህል ለመጻሕፍት ትርጓሜ የመሠረት ድንጋይ ነው፡፡ በመጻሕፍት ቤት ትርጓሜ ተምሮ በመምህርነት ለመመረቅ ዋንኛው መስፈርት በቅኔ ዕውቀት መብሰል እና መላቅ ነው፤ የሰዋስው ሥርዓት በአግባቡ ያለየ የመጽሐፍ መምህር የእቃ ቤት መጽሐፍ አስነባቢ ነው እንጂ የተለየ ስፍራ እና ክብር አይሰጠውም፡፡

በመጻሕፍት ትርጓሜ ከጥሬ ንባብ እስከ ተለያዩ የአንድምታ ሥልቶች ለመረዳት የቅኔ ትምህርት ቁልፍ ነው፡፡የመጽሐፍ ትርጓሜ የሚጠቀምባቸው የአንድምታ ሥልቶች ከቅኔ ዕውቀት ተዘርፈው በመጻሕፍት ቤት የተለመዱ ናቸው፡፡ በዚህ እና በመሰል ባሕርያቱ ቅኔን በነገረ ፍካሬ ንድፈ ሐሳብ መሠረትነት ማጥናት ተገቢ ነው፡፡ ምስጢር በብዙ አቅጣጫ፣ በብዙ ኅዳና ለመረዳት ያስችላል፡፡ የባለቅኔው አእምሮ የሚፈልገውን መልእክት ለማሥረጽ በዙሪያው የሚገኙ፣ በውስጡ የሚመላለሱ፣ መንፈሱን ያስደሰቱ እና የተጫኑት ዕሳቤዎች ኹሌም በዐዲስ የመተርጐሚያ አማራጭ ያቀርባል፡፡

ይህም ኺደት በውክልና፣ በፍልስፍናዊ አርቅቆት፣ታሪክን በዐዲስ መንገድ በመተርጐም፣ የተፈጥሮ እና የማኅበረሰብ ጉዳዮች ባልታየ ገጽታ በማቅረብ ቅኔያቱን ያስውባቸዋል፡፡ አእምሮውን በተገላጩ እና በገላጩ ላይ ሲያተኩር ተገላጩ (ወርቅ) የማይለወጥ ዕሳቤ ኾኖ ሲቀርብ ማሳያው /ሠማዊ አስተማስሎ/ ግን ኹሌም ይለዋወጣል፡፡ባለቅኔው የተቀኘበት ዐውድ ምንም እንኳን ቢታወቅም የቅኔ ሠማዊ ትርጕም /የሐሳብ አቅጣጫ/አንድ ነው ብሎ ማሰብ ተገቢ አይመስልም፡፡ በገላጩና በተገላጩ መሀል ተፈጥሯዊ ግንኙነት የሌለውን ያህል ተወካይ እና ውኩሉ አንድ ለአንድ በኾነ ገለጻ የተወከሉ አይደሉምና፡፡

ስለዚህ ባለቅኔው የተቀኘበት ሠማዊ ዐውድ እንዳለ ኾኖ ሠማዊ ወካዩ እንደ አንባቢ /ተርጓሚ/ አእምሮ ተወላላጅ ትርጕሞች ያመነጫል፡፡ አንድን ሠማዊ ማሳያ በቅኔው ዐውድ ውስጥ ብንከተው አማራጭ ትርጕም እንዲያስከትል በደረቅ ቀኖና ልንገድበው አይቻለንም፡፡ የአንድ ቅኔ ተመራማሪ አእምሮ በተባለውና በተነገረው የቅኔ ሠማዊ

ትርጒም ረክቶ መንፈሱ ማረፍ የለበትም፡፡ይህም ቅኔን የመፈከር ኅዳና እንደ ነገረ ሃይማኖት ዕሳቤ ቀኖናም አይደለም፡፡ከአንድ ሠማዊ ትርጒም ሌላ ተጨማሪ ትርጒም በዐውዱ ላይ ማከል የሃይማኖት ሐሳብ እንደ ማፍለስ ሊቈጠር አይገባም፡፡ በቅኔ ትምህርት ቤቶች ባህል ምንም እንኳን የተነገረውን ትርጒም ተቀብሎ መሔድ የተለመደ ቢኾንም ከሠማዊ ተወካይ ተለዋዋጭ ባሕርይ በመነሣት ተጨማሪ ትርጒም መኖሩን እንረዳለን፡፡

ነገሩን አርቀን ከተመለከትነው እስከ ዓለም ፍጻሜ ብንኖር እንኳን አንድን ነገር ገልጸን ወደ መረዳት ደረጃ አንደርስም፡፡ ይህ ጥልቅ የትርጓሜ ባህል በቅኔያት ውስጥ በጉልሕ ይታያል፡፡ ሊቃውንቱ እጅግ በመራቀቅ የገለጡት ያንኑ ጉዳይ ቅኔ ጀማሪውም በዐዲስ መንገድ ለመውሰድ የራሱን የዕሳቤ ብርሃን ይረጭበታል፡፡

በገለጻውም መንገድ ጀማሪው ባለቅኔ ከሊቁ የተሻለ ሠማዊ ማሳያ ሊያመጣ ይችላል፡፡ በጀማሪው ዘንድ የሚታየው የአሣሣል፣ የሰዋስው ዕውቀት፣ ከሙያ ጋራ ገና የመተዋወቅ ዕድሉ ዐዲስ ከመኾኑ በስተቀር፣ የዕሳቤ ኅዳናው ተመሳሳይ ነው፡፡ በዚህ መሠረተ ሐሳብ ቅኔያትን በነገረ ፍካሬ ንድፈ ሐሳብ መተንተኛነት ማቅረቡ የተሻለ እንደኾነ አስባለሁ፡፡

## 2.3.2 የነገረ ፍካሬ ንድፈ ሐሳብ እንደ ቅኔ መተንተኛ

በነገረ ፍካሬ ሊቃውንት ዕሳቤ መሠረት፣ "እንደተረዳናቸው የምንቈጥራቸው ርእሰ ጉዳዮች፣ ቆየት ብለን ስናስባቸው፣ አልያም ጥያቄ ተጠይቀን ለመመለስ ስንቃጣ ጉዳዩን አለመረዳታችን ይታወቀናል"[42]፡፡ ይኸን እንጂ ተርጒመን ለማስረዳት እንሞክራለን፡፡ በቅኔ የትምህርት ጥበብ ውስጥ ይህን ኹኔታ በአግባቡ ባንረዳውም ነባር ባህል ነው፡፡

ባለቅኔው አንድን ፅንሰ ሐሳብ /ሃይማኖታዊ ጉዳይ/ አንድ ጊዜ ገልጦት በቃኝ ብሎ አያርፍም፡፡ የራሱን የፈጠራ ዐቅም እየተጠቀመ ባገኘው አጋጣሚ ትናንት ከተቀኘው ቅኔ የተሻለ ቅኔ ቈጥሮ ለማምጣት ከአእምሮው ጋራ ኹሌም ይሟገታል፡፡ ባለቅኔው እንደገለጠው እየታሰበው፣ በደስታ ቢሞላም፣ ሰሚዎቹ ይበል! ይበል! ቢሉት፣. ጉዳዩ መቼም ቢኾን አይገለጥም፡፡ ይህ አለመግለጥ /የትርጓሜ መቋጫ አለመኖር/ በቅኔ ጥበቡ እንዲገፋ ያደርገዋል፡፡ እያደር በቅኔ ጥበቡ እየገፋ በኼደ ቁጥር የተፈጥሮ፣ የማኅበረሰብን እና የሃይማኖት ተርጓሚ ሊቅ መኾኑ ውስጥ ውስጡን ለራሱ ይታወቀዋል፡፡ስለዚህ በነገረ ፍካሬ የአስተሳሰብ አቅጣጫ "የትኛውም መጽሐፍ በእግዚአብሔር ይኹን፣ ከኹሉ በላቀ ሊቅ

[42] Gayle L.Ormiston and Alan D.Schrift, 1

ቢጻፍ፣ ግልጽና ቀላል አይኾንም"[43]፡፡ ይህ ኺደት ለመተርጐማኑ ዐዲስ ትርጓሜ እንዲጽፉ /ዐዲስ ቅኔ እንዲቀኙ/ ምክንያት ይኾናል፡፡ከዚህ በመነሣት ትርጓሜ ከሰው ሕይወት ጋራ የተቆራኘ በመኾኑ ሕይወት ከምድር ፈጽማ እስካልጠፋች ድረስ ትርጓሜ አይቀርም፡፡ ትናንት ግልጽ የኾነልን ሐሳብ ቆይተን ስንመለከተው ሕጸጽ ስለሚኖረው በዐዲስ መንገድ ለመተርጐም እንነሣለን፡፡ "አንድን ርእሰ ጉዳይ ወስደን መቶ ማብራሪያ መጻሕፍት ብንሠራለት ከዚያም በቃው ለማለት ድፍረቱ የለንም" [44] ፡፡ ቢኖረንም አመኔታው ዘለቄታ የለውም፡፡ በትርጓሜ ኀዳና አማራጭ ርዕሰ ጉዳዮችን ማቅረብ፣ አንድን ርእሰ ጉዳይ በተለያየ መንገድ ከመተርጐም ልማድ ያጠጠ ነው፡፡

ስለዚህ ባለቅኔ በተወሰኑ ወርቃዊ መባያዎች ዕድሜ ልኩን ቅኔ  ሲቈጥር እና ሲዘርፍ ይኖራል፡፡በዚህ ኺደት የባለቅኔው አእምሮ ከቅኔ ፈጠራ ዓለም ጋራ የተሰናኘ ነውና፤ በዚህ ዓለም ውስጥ በጉልሕ መባያዎች በመመሥረት ዕሳቤዎች፣ ያሔሳል፤ ያደንቃል፡፡ ዛሬ በቅኔ አርቅቆቱ ፈጠራ እና መላምት መነሻ የኾነው ለነገ ዕሳቤ ሥንቅ እየኾነው ለቀጣዩ እያለ በቅኔ ፈጠራው መንገድ ዘልቆ ይጓዛል፡፡ለዚህ ኹሉ መነሻው የሰው ልጅ በተፈጥሮ ዕውቀት የመሻት ፍላጎት ስላለው በቀደሙት ዕሳቤዎች ላይ ይራቀቃል፡፡ በዚሁ መንገድ ባለቅኔውም ዐዲስ መንገድን እና ዐዲስ ቀመርን በመጠቀም የቅኔ አርቅቆት ለመፍጠር ይጣጣራል።

በዚህም በአጽናፈ ዓለሙ ውስጥ የሚገኙትን ነገሮች በሚመራመርበት ኺደት የተለያዩ ዕሳቤዎችን አጣምሮ እና አዋሕዶ ይመረምራል፡፡ መተርጐምነቱ በአንድ ርእሰ ጉዳይ ውስጥ አይወሰንም፡፡ ስለዚህ ባለቅኔው ታስቦ የማያውቅን ጉዳይ ሳይኾን በዕሳቤ ውስጥ የነበሩትን ጉዳዮች በዐዲስ አተያይ በማቅረብ አማራጭ ትርጓሜ ይሰጣቸዋል፡፡

በዚህ የቅኔ አርቅቆት ኀዳና ፈርጀ ብዙ ትይዩ  የዕሳቤ ኀዳናዎች በመኖራቸው "አንድ በቅጡ የሚታወቅን ጉዳይ የቅኔ ፈጣሪውን /ሠማዊ መባያውን/ በመጠቀም በቅጡ ያልታወቀን /ወርቃዊ መባያን/ ለመግለጽ ይሞከራል" [45]፡፡ ሠምና ወርቁ ስምሙ በኾኑ ቁጥር ዐዲስ የትርጓሜ አማራጭ ይገኛል፡፡ ይህ ኺደት በጥልቀት ሲጠና "ወደ ዐውድ ትርጓሜ ክበብ እና ወደ ሐቲት ተሰናስሎ ዕሳቤ ይወስደናል" [46]፡፡ በቅኔ ፈጠራ ውስጥ የትርጓሜ ክበብ የየዘመናቱ ሊቃውንት የተውትን አሻራ፣ ቅኔያቱ የሚፈጠሩበት ሳምንታዊ፣ ወርኃዊ፣ ወቅታዊ እና ዓመታዊ ዑደተ ዕሳቤን የሚጠራ በመኾኑ ክበባዊነት አለው፡፡

---

[43] Gayle L.Ormiston and Alan D.Schrift,1
[44] Gayle L.Ormiston and Alan D.Schrift,1
[45] Gayle L.Ormiston and Alan D.Schrift,3
[46] Gayle L.Ormiston and Alan D.Schrift,3

በዚህ ኺደት ውስጥ ቃላዊ ተስተላልፎ ተከትሎ ቃላዊ ኅትመት /የኅትመት ያህል መሠራጨት እና አለመለወጥ እንደአንድ ክሥተት ይከሠታል፡፡ አንዱ ቅኔያዊ ሐቲት ከሌላው ጋራ በተሰናሰለ ቁጥር የርእሰ ጉዳዩን ስፋት እና ጥልቀት የባለቅኔዎቹን የአተያይ ምጥቀት እንረዳበታለን፡፡ ምንም እንኳ የቅኔ ፈጠራ ዕውቀት ከሃይማኖታዊ አገልግሎት ጋራ ቢተሳሰርም፣ የቅኔ ባለሙያዎች በተወሰኑ ቅኔያት አለመገልገላቸውን ስናጤን፤ ፍጹማዊ በኾነ መልኩ ነገሮችን ለመግለጽ የመፈለግን ምኞት አርግዞ እናገኘዋለን፡፡

በመተርጐም ኀዳና ነገሮችን ለመግለጽ ብንፈልግም፤ መቼም ቢኾን የተገለጡ አይኾኑም፡፡ ባለቅኔው ዕሳቤዎቹን ለመግለጽ የሚጠቀመው በቋንቋ አማካይነት ነው፡፡ ይኹን እንጂ ቋንቋ የምልክት ሥርዓት ነው፡፡ በዚህ ኺደት በቋንቋ ጸናን ኾነው የሚቀሩ ዕሳቤዎች መኖራቸው ታሳቢ መኾን አለበት፡፡ በቋንቋ ማሥገሪያ በቀላሉ የማይሠገሩ፤በቋንቋ ምልክታዊ ሥርዓት የማይዳኙ አእላፍ ክፍተቶች አሉ፡፡ ይህ የተሟላ አለመኾን የትርጓሜ ተሰናስሎ እንዲፈጠር መንገድ ይፈጥራል፡፡

በዚህ ኺደት ውስጥ ፍጹማዊ  የመፈከሪያ መንገድ አይኖርም፡፡ ኹሉም የመፈለግ ኺደት አለ፡፡ ይኹን እንጂ ከባዶ መነሻ ማንም አይነሣም፡፡ የአንዱ የዕሳቤ አቅጣጫ ከሌላው ጋራ እየተጠለፈ ፍጹም የኾነ ዕውቀት ወደ መሻት ኀዳና ያመራል፡፡ በዚህ ኺደት ውስጥ ኹለት ቁልፍ ቃላት ይህን ኺደት በቅጡ እንድንረዳ ያግዙናል፡፡ እነርሱም ማስተሳሰር እና ቋንቋዊ ጨዋታ ናቸው፡፡ማስተሳሰር ቋንቋን፣ ዕሳቤን እና ፍካሬን በቅኔ የፈጠራ ጥበብ ውስጥ  በማራቀቅ ነው፡፡ይህ ኺደት በዕሳቤ በመጠበብ፣ ከፍካሬ መበልጸግ የሚወለዱ ነገሮችን የማስተሳሰር ኀዳና ነው፡፡

"የቋንቋ ጨዋታ"[47] ደግሞ የፍካሬ /የቅኔ ዕሳቤ ጥበብ የቋንቋ ጨዋታ መኾኑን በአጽንዖት መመርመርን ይመለከታል፡፡በዚህ ተውኔታዊ በኾነ ሥልት ቃላት ወትሮውን ከሚያስተላልፉት ትርጒም ውጭ ዐዲስ ዕሳቤ ይገለጥባቸዋል፡፡ ኹሌም በቋንቋ ጓዝ በመጫወት ጥበባዊ ዕውቀቱ ይሠርጻል (Wittgensteinian:5)፡፡

በዚህ ኺደት ውስጥ ሕግ፣ ቀዳማዊ መርሖ፣ የመጨረሻ ሐሳብ ብሎ ነገር አይሠራም፡፡ጥበባዊ ሥራው ለእነዚህ ሕገጋት አይገዛም፡፡ የቅኔ ኀያላን በመጡ ቁጥር ነባር ግዛቶች ይሰፋሉ፤ ዕሳቤዎቹ  ይታደሳሉ፡፡ በሕግና በሥርዓት ጽኑ ድንጋጌ የማይዳኙ ዕሳቤዎች መመንጨታቸው አይቀሬ ጉዳይ ነው፡፡ አንድ የቅኔ ፍካሬ ከታሪክ፣ ከባህል፣ ከተለየ ዐውድ ጋራ ይገናኛል፡፡ ይህ ማለት ግን የትርጒም ወሰኑ የተገደበ መኾኑን

[47] Gayle L.Ormiston and Alan D.Schrift, 5

አያመለክትም፡፡ ከታዋቂ ምንጭ መቀዳቱ ሌላ አማራጭ ዕሳቤን እንዳንመለከት አያደርግም፡፡ ጉዳዩን በጥልቀት ስናጤነው የሚገለጽበት ሌላ ጎዳና ይታየናል፡፡

Gayle L.Ormiston and Alan D.Schrift ሚሼል ፉኮን ጠቅሰው እንዳሉት "ትርጓሜ እራሱን እየተረጎመ ይኖራል"[48]፡፡ እንደሚለው ብሂል የቅኔ ዕሳቤ ከዚህ ዕድል አያመልጥም፡፡የቅኔ ጎዳናዎች የሚመለከቱት የትርጓሜን ዓለም ውስብስብነት ነው፡፡በዚህ ኺደት ውስጥ "ተመክሮ እና ራስን ማረም" [49]፡፡ በሥነ ፍካሬ ሊቃውንት የተነሡ ነጥቦች ናቸው ፡፡

በቅኔ ፈጠራ ጥበብ ውስጥ ተመክሮ ትልቅ ሚና አለው፡፡ አንድ ደቀ መዝሙር ከአንድ ቅኔ ቤት የቀሰመውን ዕውቀት ይዞ ጉባኤ አይዘረጋም፡፡ አቻ ከኾኑ የቅኔ ጉባኤዎች ገብቶ ከመነሻ እስከ መምህርነት የሚያዘልቁትን ዕውቀቶችና ይትበሀሎች ያደላድላል፡፡ይህ ኺደት ተመክሮ በትርጓሜ ጎዳና ወሳኝ መኾኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በዚህ ጥበባዊ የፈጠራ ሥልት ውስጥ ከተመክሮ በተጨማሪ ኹሌም ቢኾን እራስን ማረም ወሳኝ ነገር ነው፡፡ ስለዚህም እነዚህ ኹለቱ አቅጣጫዎች ባለቅኔውን በቅኔ ጥበብ እንዲያድግ ይረዱታል፡፡

በዚህ ኺደት የትርጓሜ ባህል ይፈጠራል፤ይዘምናል፡፡ሌላኛው ከነገረ ትርጓሜ በተቃራኒ የሚነሣ ዕሳቤ ነገሮችን ለመረዳት የምንኼድበት ጎዳና ከነገሩ ይነጥለናል የሚል ነው፡፡ይህ ዕሳቤ ነገሮች መገለጽ ካለባቸው በቀጥታ መገለጥ አለባቸው ከሚል ዕሳቤ ጋራ የሚገናኝ ነው፡፡ በቅኔ የፈጠራ ሥልት ርእሰ ጉዳዮችን ለመረዳት በሚደረግ ኺደት፤ ከምንኖርበት ዓለም ጋራ ግንኙነት እንፈጥራለን፡፡ አካባቢያችን፣ መሻታችን፣ ደስታችንን፣ ሐዘናችንን፣ መጠነ ርእያችንን በማነጻጸር አቅርበን የበለጠ የማወቅ ዕድል እንፈጥራለን፤በርእሰ ጉዳዩ ላይ ትርጓሜው ብዥታ አይፈጥርብንም፡፡

ስለዚህ ባለቅኔ ድንበር አሥማሪ፣ ተርጓሚ፣ የሚኖርበትን ዓለም በዐዲስ መንገድ አዋቅሮ ለመረዳት የሚጥር መተርጕም ነው፡፡ ስለዚህም በትርጓሜ ባህል ተመሥርተን ኹሉንም ዕሳቤዎች በትውፊቱ ሕግና መርሕ ማንጸሪያነት ለማየት እንገደዳለን፡፡

---

[48] Gayle L.Ormiston and Alan D.Schrift,7
[49] Gayle L.Ormiston and Alan D.Schrift,7

## 2.3.3 የትርጓሜ ባህል[50]

በቅኔ ትምህርት ቤት እራሳቸውን የቻሉ ፈለጎች ይፈጠራሉ፡፡ ዋድላ፣ ጎንጅ፣ ዋሸራ የቤተ ቅኔ ፈለጎች መፈጠሪያ ስፍራ ናቸው፡፡ እነዚህ በአገባብ ዕውቀት ማስፋፋት፣ በቅኔ ሰዋስዋዊ ሙያ አርቅቆት፣ በሠምና ወርቅ ፈጠራ የተመሠረቱ ቅኔ ቤቶች የየራሳቸው የኾነ የይትበህል ትውፊት አላቸው፡፡ የሚመሳሰሉበት እና የሚለያዩበት ባህል አንዱ መገለጫቸው ነው፡፡ የቅኔ ባለሙያው በዕውቀት ከገፋ በኋላ ይትበህሉን ለማደላደል በየቅኔ ቤቱ እየገባ ይማራል፡፡

በትርጓሜ ባህል ውስጥ በዋናነት ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች አሉ፡፡እነዚህም የቅኔያቱን የፍልስፍና ጨመቅ በአግባቡ ተረድቶ ማራቀቅ፣ የሰዋስው ሥርዓቱን በአግባብ መጠንቀቅ፣ በፍጻሜም ቅኔያቱ የሚሠሩበትን ተናጠላዊ እና ኹለንተናዊ ሕግ መረዳት፣ በአንድ የቅኔ ፈጠራ ኺደት ጥበብ ውስጥ ያለውን ውስጣዊ ውቅረት መረዳት፣ ትኩረት የሚሰጣቸው ተጠቃሽ ነጥቦች ናቸው፡፡በዚህ ኺደት ውስጥ የአንድን ቅኔ ውስጣዊ እድገት ከሌላ የቅኔ ይትበህል ጋራ በማነጻጸር የመመርመር ተግባር ይካኼዳል፡፡

AST የሚባለው የሥነ ትርጓሜ ባለሙያ በፍካሬ ወቅት የሚከናወኑ ሦስት ደገኛ ነጥቦች ያነሣል፡፡እነዚህም ገጸ ንባባዊ፣ የሥነ ፍቺ እና የመንፈስ ተገንዝቦት ናቸው [51]፡፡እነዚህ ነጥቦች ከቅኔ ፈጠራ ጥበብ ጋራ የሚሰናኙ ናቸው፡፡በቅኔ ዐውዳዊ ጥናት የሚገለገሉበትን ኺደት ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡

ገጸ ንባባዊ ትርጕም በቅኔ ቤት በቅኔ ዘረፋ ወቅት ቅኔ ተቀባዩ ተማሪ ተማሪዎች ገጸ ንባቡን በቃል ከዘለቁ በኋላ ቆሞ ያስፈታል፡፡ይህ ኺደት በቅኔ ትርጓሜ ውስጥ ዐቢይ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ኺደት የተለየ ቃልን፣ የርእሰ ጉዳይ መረዳትን፣ በጥቅሉ የሰዋስውን ግንዛቤ እና የጥንታዊ ጽሑፎችን ግንዛቤ የሚጠይቅ ነው፡፡

የሥነ ፍቺ ግንዛቤ በቅኔ አርቅቆት ወቅት የሠምና ወርቅ ኺደት የተፈጠረበትን አጠቃላይ ነጥብ መረዳትን የሚያጠቃልል ነው፡፡ አንድ ትርጕም በመፈለግ የቅኔውን ታሪክ እና የቅኔ ፈጣሪውን ሕይወት ተመክሮዎች ከመረዳት ጋራ ይገናኛል፡፡ባለቅኔው የቅኔያት ታሪክ ይነድፋል፡፡ ይህንም ሲያደርግ የራሱ የሕይወት ጉዳዮች በቅኔ ፈጠራ ውስጥ ይፋተላሉ፡፡

የመንፈስ ተገንዝቦት በቅኔያት ውስጥ ያሉት መሪ ሐሳቦች፣ የቋንቋ መርሖዎች፣ የባለቅኔያቱን አእምሮ፣ የሕይወት መስተጋብር ተረድቶ በዐዲስ መንገድ የማዋቀር ኺደት

[50] Gayle L.Ormiston and Alan D.Schrift,11
[51] Gayle L.Ormiston and Alan D.Schrift,12

ነው፡፡ብዙ ዘመናት ባስቈጠሩ ቅኔያት እና በተፈጠሩበት ኺደት መሀል ያለው የማይታየውን ሥረ መሠረት በቋንቋ መጠቆሚያ፣ መሪ ሐሳቦች በመሻት ቅኔያቱን ማዋቀር በዚህ ግንዛቤ ደረጃ ይከናወናል [52]፡፡በቅኔ የፍካሬ ጎዳና "ዋና" የሚባለውን ነጥብ የመፈለግ ኺደት አለ፡፡ ስለዚህ ቅኔ አስተርጓሚው ፍዝ ተሳታፊ መኾን አይገባውምና፡፡ ከባለ ቅኔ የተሻለ የትርጒም አማራጭ በማምጣት በቅኔ ፈጠራ ብቻ ሳይኾን በቅኔ አተረጓጎም መላቅ አለበት፡፡በዚህ ኺደት ደቀመዝሙር የማየት፣ የማግኘት፣ የማሰላሰል ሚናው ከፍ ያለ ነው፡፡ ትርጓሜ ምን ጊዜም ቢኾን፣ የዕይታ፣ የማሰላሰል፣ የማግኘት ተግባር ነው ፡፡ ሊሰፉ እና ሊገልጠው የሚችለው በዚህ መንገድ ነው፡፡ በዚህም ኺደት ትኩረት ያልሠጠነውን ዐብሮን የኖረ እና ያለንን ነገር ወደ ማየት ደረጃ እንደርሳለን፡፡ በመተርጐም ገንዘብ እናደርገዋለን፡፡ ይህም ኺደት የተለያዩ ርእዮተ ዓለማዊ አተያዮችን እንድንፈትሽ መንገድ ይከፍትልናል፡፡

Betti የሚባለው የሥነ ፍካሬ ተመራማሪ በትርጓሜ ኺደት ውስጥ መኖር ያለባቸውን አራት መሠረታዊ ነጥቦች ይጠቅሳል፡፡እነርሱም የርእሰ ጉዳይ የበላይነት /የትርጓሜ ቀኖና/ ፣የተጣጣመ የትርጓሜ ቀኖና፣ የርእሰ ጉዳዩ እርግጠኝነት እና የሥነ ፍቺ ቀኖና ናቸው [53]፡፡ የርእሰ ጉዳይ የበላይነት በየትኛው የትርጓሜ ኺደት ርእሰ ጉዳይ ገዥ ነው፡፡ እንደ ባህለ ማኅበረሰቡ ዕሳቤ መሠረት የዋናነት ስፍራ አለው፡፡ ይህ መሥፈርት በቅኔ ፈጠራ ተግባር ውስጥ ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ ባለቅኔው ርእሰ ጉዳይ ተሰጥቶት /በቅኔ ቈጠራ ባህል እና ወግ መሠረት በተመረጠ ታሪክ/ ቅኔያት ይቈጥራል፤ ይዘርፋል እንጂ ያለ ርእሰ ጉዳይ ቅኔያቱን አያቀርብም ፡፡

የተጣጣመ የትርጓሜ ቀኖና (ሥርዓት) መኖር ወሳኝ መርሕ ነው፡፡ በዚህ መሠረት በዋናነት በቅኔ ትርጓሜ ኺደት ውስጥ የሰዋስው፣ የታሪክ፣ የምስጢር፣ የአርቅቆት፣ የተጣጣመ ፍቺ እንዲኖር ይጠበቃል፡፡ ይህ መሥፈርት ባልተሟላበት ኺደት ቅኔው ቅቡል አይኾንም፡፡

የርእሰ ጉዳዩ እርግጠኝነት በቅኔ ፈጠራ በማሳያው መንገድ ካልኾነ በሚገለጸው ርእሰ ጉዳይ የሚሰጠን ሒስ አናሳ ነው፡፡ይህ በቅኔ ፍካሬ ኺደት ትኩረት የሚሰጥበት እርግጠኝነትን የመፈተሽ ኺደት በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ የሚደረጉ ሒሳዊ ትንታኔዎች እምብዛም

[52] Gayle L.Ormiston and Alan D.Schrift,13

[53] Gayle L.Ormiston and Alan D.Schrift :19-23

አይታይም፡፡ አልፎ አልፎ ግን ነባር እና ቅቡል የኾኑ ርእሰ ጉዳዮች የሚያሔሱ ቅኔያት ስላሉ ርእሰ ጉዳዩን የመፈተሸ የትርጓሜ ኺደት በቅኔያት ውስጥ ይገለጣል፡፡

የሥነ ፍቺ ቀኖና የመተርጐም፣ የማመስጠር፣ የማራቀቅ ኺደት በመኾኑ በቅኔ ጉባኤያት መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም ኺደት "የጋራ አእምሮን" እና "የትርጐም ቅጦችን" በማዛመድ፣ በማነጻጸር፣ በመቃረን እና በማጣመር የትርጓሜ ኅዳና የማስፋት ተግባር ይኖራል፡፡በዚህም ኺደት የውክልናን ተግባር እና ገለፃ በመጠቀም ነገሮችን ወደ መረዳት ብርሃን የማውጣት ተግባር የባለ ቅኔው የትርጓሜ ተግባር ነው [54]፡፡

በዚህ የፈጠራ ቴክኒክ መሠረት ታሪክ ማዋቀር፣ ለሥነ ውበት ስፍራ መስጠት፣ የሰውን ህልውና አትኩሮ ውስጥ በማስገባት መተንተን ተግባራዊ ይኾናል፡፡ ስለዚህ ቅኔ ከፈጠራ ኺደቱ፣ ከአተረጓጐም ሥልቱ፣ ከአርቅቆት መንገዱ ጋራ ተያይዞ የትርጓሜን መንገድ የሚከተል ነው፡፡ስለዚህ የሥነ ፍካሬ ኅዳና ቅኔን ለመተንተን ተመራጭነት አለው፡፡በርእሰ ጉዳይነት የተመረጡት ማኅበረሰብ፣ ፖለቲካና ሃይማኖት ሰፊ የኾነ የትርጓሜን ዕሳቤ የሚፈልጉ ናቸው፡፡እነዚህም ርእሰ ጉዳዮች በራሳቸው የትርጓሜን መንገድ የሚፈጥሩ ናቸው፡፡

## 2.3.4 የእኔዎቹ ርእሰ ጉዳዮች / ማኅበረሰብ፣ ፖለቲካ እና ሃይማኖት /

በባለቅኔዎቹ ዕሳቤ ውስጥ በሠማዊ ይኹን በወርቅ የቅኔ አስተማስሎ እነዚህን ጉዳዮች እንዴት እንደ ተረጐሟቸው እንደ አሔዷቸው ለማሳየት እሻለሁ፡፡ርእሰ ጉዳዮቹ በራሳቸው በጣም ሰፊ የኾኑ ዕሳቤዎች የያዙ ናቸው፡፡ መሠረታዊ የኾነ ባሕርያቸው እንደ ርእሰ ጉዳዩ ሰፊ ጥናት እና ምርምር የሚካኼድባቸው ናቸው፡፡ እኔ የቅኔን ፍልፍስናዊ ሐሳብ ከነገረ ፍካሬ ጋራ በማጣመር የመለኮታዊ አካላት /ሥላሴ/ ያህል፤በሰብኣዊ ዓለም ውስጥ ገዥ የኾኑ እነዚህን ርእሰ ጉዳዮች እዳስሳለሁ፡፡ በነዚህ ርእሰ ጉዳዮች ላይ የማቀርበው ሐተታ ከቅኔያት ጋራ የሚያያዝ እና የባለ ቅኔዎቹ ሒሳዊ ዕሳቤ መገለጫ የኾኑበትን መንገድ በማሳየት ላይ ይመሠረታል፡፡

Michaels:-እንደሚለው "ታሪክ፣ ትእምርት፣.ሥነ ምግባራዊ፣ ማኅበራዊ ዕሴቶች በነገረ ሃይማኖት ጥናት የሚተኮርባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ በዚህ ዕሳቤ መሠረት ስለ ሃይማኖት ስንናገር አንድ ሐረግ እንደምንስብ ብቻ ሊታሰብ ቢችልም ዱሩን እያሰብን ነው፡፡ ከሃይማኖታዊ ጉዳዮች ጋራ የማይተሳሰሩ ማኅበራዊ እና ሥነ ምግባራዊ ጉዳዮች የሉም፡፡"

[54] Gayle L.Ormiston and Alan D.Schrift,19

በእነዚህ ላይ የሚሰጠው ሒስ በማኅበረሰቡ ባህል እና ዕሴት፣ ህላዌ ላይ የሚሰጥ ሒስ ነው[55]፡፡

Kant በነገረ ሃይማኖት እና በአመክንዮ ላይ ባቀረበው ምርምራዊ ሥራው "እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰቡን/የእግዚአብሔር መንጋ/ ናት፡፡ በጋራ በኾነ ሥነ ምግባራዊ ደንቦች አንድ የኾኑ እነዚህ ሕዝቦች ተከፋፍለዋል፤ ተበታትነዋል፡፡ ክርስቶስ እነዚህን አንድ ለማድረግ ነው የሞተው፡፡ የአብያተ ክርስቲያናት ኹኔታ ግን ከዚህ የአንድነት ሐሳብ በተቃራኒ ነው" [56]፡፡በዚህ ኢማኑኤል ካንት ገለጻ መሠረት በሃይማኖት ዓለም ውስጥ የሚነሡ ጉዳዮች የማኅበረሰቡን አጠቃላይ ሕይወት ሊያበለጽጉ ወይም ሊጎዱ፣ ሊያከስሙ እንደሚችሉ ማሳያ ናቸው፡፡ በነገረ ሃይማኖት ዙሪያ የሚነሡ ነጥቦች ውለው ዐድረው የማኅበረሰቡ ዐቢይ ችግር ኾነው ይገኛሉ፡፡ ለዚህም የቤተ ሃይማኖቱ ቀኖናዎች የየራሳቸውን አስተዋፅኦ ያደርጋሉ፡፡ "ክርስቶስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወደ ምድር ይዞ መጣ ይህን በማድረጉ ተሳስቷል፡፡ በዚህ ፋንታ የካህናት መንግሥት በመሀላችን ተቋቋመ" [57]፡፡ ከዚህ ሐሳብ ጋራ ሙሉ በሙሉ ባንስማማም ችላ የማንለው ቁም ነገር አለው ፡፡ሃይማኖት የመንግሥት ሥርዓት ያህል ተፈሪነት አለው፡፡ አልያም ኹለቱ ያላቸው ውሕደት እስከ ወዲያኛው የማይነጠል ይኾናል፡፡ ነጋሽ አንጋሽ በመኾን የጋራ ሚና አላቸው፡፡ባለቅኔዎቹ የታዘቧቸውን ጉዳዮች በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ አቅርበዋል፡፡ ሒሳዊ ቅኔያት በውስጣቸው ከጥቃቅን ጉዳዮች እስከ ዐበይት ሐሳቦች አካተዋል፡፡

ዱራንት Deweyን ጠቅሶ ስለ ማኅበረሰብ እና ስለ ፖለቲካ በሚናገርበት ወቅት ምንም ፍጹም የኾነ፣ የበሰለ ነገር የለም፡፡በማኅበረሰብ እና በፖለቲካ ዓለም የምርምር ዓለም ውስጥ መልካም እና መጥፎ በምንለው ሰው መሀል ያለው ልዩነት እና ወሰን በቅጡ አይታወቅም፡፡ በማኅበረሰብ፣ በባህል እና ፖለቲካ ዕሳቤ ውስጥ ነገሮች እያደር እየበሰሉ የሚኼዱ እንጂ ፍጹም እንከን አልባ የኾኑና የተዋጣላቸው አይደሉም"[58] ስለዚህ በማኅበረ-ፖለቲካ ዓለም ውስጥ "በመልካም" እና "በመጥፎ" ሰው መሀል ያስቀመጥነው ልዩነት፣ በየሥርዓቱ መሀል ያቀነቀነው ሐሳብ ዘላቂነት አይኖረውም፡፡ በዚህም ሳቢያ የባለቅኔዎቹ አእምሮ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ርእሶች ይፀንሳል፡፡በዚህ መሠረት ላይ ኹነው የማኅበረሰቡን ውስጣዊ ዓለማት በሚገልጹት በማኅበረሰብ፣ ፖለቲካዊእና በሃይማኖት

[55] Michaels :196
[56] Durant,212
[57] Durant,212
[58] Durant,393

አተያይ ላይ ተመሥርተው፤ አቋመ ማኅበረሰቡን ያሔሳሉ፡፡እኔ በዚህ ምርምራዊ ጥናት ውስጥ እነዚህን ርእሰ ጉዳዮች፣ እንደ አዕማድ በመውሰድ፣ በጣምራ የማኅበረሰቡን አጠቃላይ ገጽታ እንዴት እንደሚያሳዩ፤ በትንተናው ክፍል ውስጥ በሰፊው አሳያለሁ፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. የመረጃ ትንተና

"ጉዳያቸውን ማኅበራዊ ፣ ፖለቲካዊ እና ሃይማኖታዊ ያደረጉ የግዕዝ ቅኔያት የይዘት ትንተና" በሚል ርእስ የቀረበው ይህ ጥናት ግቡን ለማሳካት የተሰበሰቡ መረጃዎችን በቅኔያቱ አስረጅነት በመተንተን ፍካሬውን ያኼዳል፡፡ የግዕዝ ቅኔያት የተለያዩ ሠም ጠቀስ አርእስተ ጉዳዮችን ለመግለጽ በመሣሪያነት እንደሚያገለግሉ በምዕራፍ ኹለት ተገልጿል፡፡ በዚሁ መሠረት የተመረጡት ሠላሳ ስምንት ቅኔያት ስምንት የግዕዝ ቅኔ ዐይነቶች ናቸው ፡፡ እነዚህም ጉባኤ ቃና፣ ዘአምላኪየ፣ ሚበዝኁ፣ ዋዜማ፣ ሥላሴ፣ መወድስ፣ ሣህልከ እና አሠረ ንጉሥ ቅኔያት ሲኾኑ ከእነዚህም መሀል ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ለመግለጽ የሚያስችለው መወድስ ቅኔ አብላጫ ቁጥር ወስዷል፡፡ ሌሎች የቅኔ ዐይነቶች አርእስተ ጉዳዮቹን በሚያነሡበት አግባብ መሠረት ተመርጠዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ በመጀመሪያ የማኅበራዊ ጉዳይ ሥሪት ሠረገላ የኾኑ ቅኔያት ዕሳቤዎች ታይተዋል፤ ቀጥሎም ፖለቲካዊ ነክ ዕሳቤ ያላቸው ቅኔያት ተመርምረዋል፤ በመጨረሻም ለሃይማኖታዊ ፍልስፍና እና ማጠየቂያነት ያገለገሉ ቅኔያት ተፈክረዋል፡፡

በዚህ ጥናትና ምርምር ውስጥ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች የነገረ ሰብእን ጉዳዮች ለመመርመር የሚያስችሉ ዐበይት መሣሪያዎች ናቸው፡፡ በእነዚህ መሣሪያነት ፈርጀ ብዙ ገጽታ ያለውን የነገረ ሰብእ ጉዳይ ማጥናት ተመራጭ ሥልት ነው፡፡ ይህን ፈለግ በመከተል የቅኔ ጥበብ ሊቃውንት የማኅበረሰቡን የወቅቱን ፖለቲካዊ ጉዳይ፣ የቤተ ሃይማኖቱን አጠቃላይ ገጽታ ውስጥ የታዘቡትን፣ የሰሙትን፣ያዩትንና ያስተዋሉትን ነገር ሠምና ወርቅን በተላበሰ መንገድ እና ከፍ ባለ ዘይቤ ገልጸውታል፡፡ በዚህ ግብራቸው የማኅበረሰቡን ዐይን÷ ዐይን አድርገው ያያሉ፤ይመለከታሉ፡፡ የማኅበረሰቡን እዝነ ልቡና ገንዘብ አድርገው ያስተውላሉ፤ ይታዘባሉ፤ ያሔሳሉ፤ የማኅበረሰቡን አንደበት አንደበት አድርገው ይናገራሉ፤ ይወስናሉ፤ ይፈርዳሉ፡፡ይህ ኹሉ ግብር የሚከናወነው በቅኔ አርቅቆት ውስጥ ነው፡፡ እኔ በዚሁ መሠረተ ሐሳብነት በማኅበራዊ ርእሰ ጉዳይ ሥር ዐሥራ ስድስት፣ በፖለቲካዊ ርእሰ ጉዳይ ሥር ዐሥራ ኹለት፣ በሃይማኖታዊ ርእሰ ጉዳይ ሥር ዐሥር ቅኔያት መርጬ የጋራ ሐሳባቸውን እና ተዛምዷቸውን በማመሳከር የነገረ ሰብእ ሐሳብ በትርጓሜቸው በሚኼዱበት ሥልት ለፍካሬ ጎዳና ተገልግዬባቸዋለሁ፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ እነዚህ የነገረ ሰብእ ፍልስፍናዊ ዕሳቤዎች

በማኅበራዊ መባያዎች ሥግው ኾነው በቅኔያቱ ፍካሬ ተገልጠዋል፡፡ ባለቅኔያቱ ለሦስቱ ዐበይት የነገረ ሰብእ ጉዳዮች ማሳያነት የተቀኟቸው ቅኔያት የተጠየቅ ሕግ የሐሳብ ተዋረድ የዕሳቤ ቅጦች፣ ተጠየቃዊ ዘላቂነት፣ ከሊቃውንቱ ርእዮተ ዓለም ጋራ ተሳስሮ በፍካሬ ኅዳና እንዲሠርፁ ተደርጓል፤ በትንተናም ታይቷል፡፡ በዚህ ፈለግ ባለቅኔዎቹ ዕሳቤዎቹን ለመግለጽ የተጠቀሙባቸው ትእምርቶች እና ዕሳቤዎቹ በራሳቸው ለቅኔ ቴክኒክ ያበረከቱት አስተዋፅኦ በፍካሬው ጨመቅ ውስጥ ተገልጧል፡፡

## 3.1 ማኅበራዊ ጉዳይ

ማኅበር የሚለው ቃል ማኅበር፡- በቁሙ፣ አንድነት፣ ጉባኤ፣ ሸንጎ፣ ብዙ ሰው፣ ቤተ ክርስቲያን፣ ሥርዓተ ማኅበር የሚል ትርጒም አለው [59]፡፡ ስለ ቃሉ ትርጒም ይህን ካልኩ የማኅበራዊ ጉዳይን እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡ ማኅበራዊ ጉዳይ ሲባል ኅብረተሰቡ የእኔ ብሎ በዕለት ከዕለት ሕይወቱ ውስጥ የሚያከናውነው የሕይወት ቅምምስ ነው፡፡ በኅበረተሰቡ ሚዛን ተመዝኖ የሚጸድቅና ይኹንታ የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡በዚህም ምክንያት ሕይወቱና ሞቱ በአስገኚው ቡድን ይወሰናል[60] ፡፡ ከቡድኑ ሥርዓት የማፈንገጥ ሥልጣኑ የተገደበ ነው፡፡ ማኅበራዊ ጉዳይ እጅግ ውስብስብ የኾነ ሀገር ሙሉ ሐሳብ ነው፡፡ይህ ሐሳብ ኹልጊዜ እንደ ምርምር አቅጣጫ በማኅበረሰብ ተመራማሪዎች ዘንድ ይጠናል፡፡ጥናታዊ ምርምሩ ማኅበረሰብ የሚባለው ሰብአዊ ቡድን እስካለ ድረስ የሚቀጥል ነው፡፡የዚህ ጥናት አትኩሮት በመስክ ጥናት በሚሰበሰቡ ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ አይደለም ፤እንደዐቢይ ሐሳብ ሥነ-ጽሑፍ የወቅቱን ማኅበራዊ ጉዳይ የሚያሳይ እና የሚነድፍ መኾኑን መሠረት አድርጓል፡፡ በዚህ ማኅበራዊ ፅንሰ ሐሳብ ማኼጃነት ግዘፍ ይነሣሉ የተባሉትን "ንኡሳን"እና "ዐቢያን" የዕሳቤ ቅጦች በየዘመናቱ ከተነገሩት ቅኔያት መካከል ነቅሶ በማውጣት ይፈክራል፡፡ ለዚህ የትርጓሜ ኺደት ለማሳየት የሚያገለግሉ ዐሥራ ስድስት ቅኔያት በትንተና ሥልት ቀርበዋል፡፡

---

59 ኪ.ወ.ክ፣ 1948፡ 471

60 ማ.ሌ.መ.ቃ፡1978፡200

### 3·1·1 ምክር

**ቅኔ፩ ጉባኤ ቃና**

አርምሚ ባሕር በስመ ሠለስቱ ሥላሴ፤

እስመ ኢተውኅጠ ለኪ ነገረ ዚአኪ ሙሴ[61]፡፡

**ትርጒም፡-** አንቺ ባሕር በሦስቱ ሥላሴ ስም ዝም በይ፤

ያንቺ ነገር ሙሴ አልተዋጠልሽምና ::

**ትንተና**

የቅኔው ወርቃዊ ጉዳይ ሥላሴ ሰውን የሚረዱ ከክፉ የሚያድኑ ናቸው፡፡ ስማችውም የኀይል ምንጭ የኾነውን ያህል የነገር መቆሚያ የሐሳብ መቁረጫ ነው፤ በሥላሴ ስም ከተባለ ማንም አይንቀሳቀስም፡፡ ሌላው ሙሴ በመልአኩ መሪነት የኤርትራ ባሕር እንደየብስ ኾናለት ከዕሥራኤል ሕዝብ ጋራ በሰላም ባሕሩን መሻገሩን የሚያሳይ ነው [62]፡፡ ወደ ሠሙ ትርጉም ስንመለስ ደግሞ አንዳንድ ነገር የማይወጣለት ሰው አለ፡፡ንግግሩ ከዝምታ የማይሻል፣ ጉንጭ- አልፋ ነው። እንዲህ ዐይነቱ ሰው ዝምብሎ ነገሬ ያምርልኛል በማለት ይደሰኩራል፡፡ አድማጩ ግን ይሉኝታ ይዞት ዝም ሊል ይችላል። ኹሉም በውስጡ አይጨርስም እንዴ? የሚሰማው እንደሌለ አይገባውም እንዴ?እያለ የጎንዮሽ ሌላ ወሬ ይይዛሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ የግላቸውን ዓለም ፈጥረው የሚያነበው ሲያነብ የሚጽፈው ሲጽፍ ዝም ብሎ ጊዜው ይነጉዳል። ከታዳሚም ኾነ ከአስተባባሪ ዝም በይ! በከንቱ ነው የምትደክሚው፤ ነገርሽ ምንም ተቀባይነት አላገኘም፤ ዝም ብትይ ይሻልሻል በማለት ይመክራታል።“መካሪ አታሳጣኝ አይደል ነገሩ! ”፡፡

የሰው ልጅ ንግግር ተቀባይነት እንዳይኖረው ከሚያደርጉ ነገሮች መካከል የዝግጅት ማነስ ከብዙኃኑ ማፈንገጥ ወይም ያፈነገጠ ሐሳብ ማመንጨት ንግግሩ ከሰማዕያኑ ጋራ የሰቀቀ ሲኾን፤ሲቀል ወይም ሲከብድ በተናጋሪና በሰማዕያን መካከል ልዩ ጥላቻ ካለ እነዚህ ነገሮች በንግግር ወቅት ነገሩ ከተናጋሪ ወደ ሰሚ እንዳይተላለፍና ተቀባይነት እንዳይኖረዉ ማነቆ ይኾናሉ፡፡ እንዲሁም አንዳንድ ተናጋሪ በታዳሚ ዘንድ ተቀባይነት ሲነጥፍበት በውስጡ እርር ድብን ሊል ይችላል ፡፡ ከዚህ ላይ ከመበሳጨት ይልቅ ቀደም ብሎ ራስን መፈተሽ

---

[61] አድማሱ 1963፡480

[62] ዘጸ.14፡16-29

ግድ ይላል፤ ተቀባይነት ያጣሁበት ምክንያቱ ምንድነው? ብሎ ራስን መጠየቅም ያስፈልጋል፡፡ወደ ሕዝባዊ እምነት ስናመራ ደግሞ በተናጋሪዋ ላይ የፈጣሪ ቁጣ እንዳለባት ኀጢአተኛ እንደኾነች ተደርጎ ይታሰባል፡፡ እንደ አስረጅ የሚጠቅሱት "እግዚአብሔር ሲጣላ ብትር አቆርጥም፤ ያደርጋል እንጂ ነገር እንዳይጥም " በማለት የሕዝቡን አባባል በመውሰድ ያቺ ሴት "እግዜር የተጣላት" መኾኗን ለማስረገጥ ይናገሩታል፡፡ እንግዲህ ያም ተባለ ይህ የነገርን ተቀባይነት ይታደሉታል እንጂ አይታገሉትም፡፡ አንድም እራስን ዐውቆ ነገሩን ማቆም ወይም ዝም ማለት ተገቢ ነዉ፡፡በሥላሴ ስም ዝም በይ እስከምንባል መጠበቅ ተገቢ አይደለም፡፡ የሥላሴ ስም አስፈሪ በኾነ መንገድ የቀረበ ነው፡፡በሥላሴ መባል የነገሩን ክቡድነት ያመለክታል፡፡አንድም ዝም በይ የሚለው አካል ከቅንአት፣ ዕውቅና እንዳያገኝ ከመፈለግ፣ ራስን ብቻ ተናጋሪ ነገር አዋቂ አድርጎ ከመቊጠር አኳያ ሊኾን ይችላል፡፡አንዳንድ ሰዎች የእነሱ ዕውቅና እየጎለበተ እንዲኼድ፣የሌሎቹ እየቀጨጨ እንዲመጣ ከማሰብ፤ ሌሎች በዝምታ ተውጠው እንዲቀሩ ይጥራሉ።ለመናገር ብትሞክር እንኳን ነገርሽ አይጥምም፤ ይበቃል፤ ሰዓት የለም፤ ሰሚ ይሰለቻል እያሉ በሰበብ-አስባቡ ንግግሯን ማናጠብ ይቀናቸዋል። በዚህ ጊዜ የተናጋሪ ልበ ሰፊነት ግድ ይላል፤ የመጣውን ነገር እንደ አመጣጡ ተቀብሎ ማስተናገድ፣ ሰምቶ እንዳልሰሙ፣ አይቶ እንዳላዩ ታጋሽ መኾን ያሻል።

**ቅኔ ፪ ጉባኤ ቃና**

ኢትጻባእ ቶማስ ዘምስለ ቶማስ ጎርከ፣

እመ ሀለወከ አድግ አምጣነ መሥነቅት አልብከ[63]፡፡

**ትርጕም፦**ቶማስ ከጎረቤትህ ከቶማስ ጋራ አትጣላ፤

አህያ ቢኖርህ አቁማዳ የለህምና ፡፡

**ትንተና**

የቅኔው ወርቃዊ ጉዳይ በቅኔ ቤት የቅኔ መቊጠሪያ ታሪክ መሠረት ሰማዕቱ ቶማስ በየወሩ በዘጠኝ የሚውለው ነው፡፡ ሐዋርያው ቶማስ ደግሞ በኻያ ስድስት ይውላል፡፡ የኹለቱ ታሪክ ሰማዕታት በመኾናቸው ይመሳሰላል፡፡ሰማዕትነት በተቀበሉበት ኺደት ግን ይለያያሉ፡፡ በሌላ አገላለጽ በቅኔ ቤት ባለአህያው ቶማስ ከተባለ የመርአሱ መኾኑ ከታሪኩ

[63] ሥ.ጥ.ቅ.1995፡190

የተነሣ ይታወቃል፡፡ ባለአቁማዳው ከተባለም የሕንደኬው ወይም ሐዋርያው ቶማስ መኾኑን ኹሉም የቅኔ ተማሪ ያውቀዋል፡፡ቅኔው የኹለቱን የተጋድሎ ታሪክ በማነጻጸር ቀርቧል፡፡ የመርአሱ ቶማስ እጁንና እግሩን በሰማዕትነት ስለተቆረጠ በቅርጫት ውስጥ ኾኖ፣ አህያ ላይ ተጭኖ እየኼደ ሰብኳል፡፡የሕንደኬው ቶማስም ሰወነቱ ተገፎ ቁርበቱ አቁማዳ ተደርጎ ሥቃይ ተቀብሏል፡፡፤ ኹለቱ ቶማሶች አንደኛው አህያ አለው፣ ማለት በአህያ ተጭኖ ያስተምር ነበር ማለት ነው፡፡በስም ሞክሼ የኾነውን ቶማስን አሕዛብ ሰውነቱን ገፈው አቁማዳ አውጥተውት ስለነበር አቁማዳውን ተሸክሞ ያስተምር እንደነበረ ከሃማኖታዊው ታሪክ እንረዳለን፡፡

ወደ ሠማዊ ባሕርዩ ስናመራ በሠሙ የተነገረው የማኅበረሰቡ ጉዳይ ነው፡፡ በማኅበረሰቡ ኑሮ ውስጥ ሕይወትን ለመምራት የሚያስፈልጉ ጉዳዮች አሉ፡፡እነዚህን ነገሮች ኹሉም ሰው ኹሉንም ሊያሟላ አይችልም፤አንዱን ሲያሟላ ሌላው ይጎድልበታል፤ በመኾኑም የሌለውን ካለው ተውሶ እያሟላ ኑሮውን ይቀጥላል፡፡ ስለዚህ የጎደለን ዕቃ ከሌላ ለመጠየቅ ጠባይን ማሳመር ግድ ይላል፡፡ለዚህም ነው፣ ከጎረቤቱ ለመጣላት ያሰበውን ሰው አትጣላ፤ ነገ ከነገ ወዲያ አቁማዳ መለመንህ አይቀርም፣ ስለዚህ አትጣላ፤ ለአንተ አህያ ቢኖርህ አቁማዳ ስለሌለህ ከጎረቤት መጣላት ይቅርብህ አለው፡፡ መካሪውም የቤቱን ምስጢር የሚያውቅ ነው፤ በቤት ውስጥ ያለውንና የሌለውን ነገር ያውቃል ማለት ነው፡፡

ጎረቤት በሐዘኑም በደስታውም ፈጥኖ ደራሽ ነው፡፡ "ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጎረቤት" የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡ከጎረቤት ጋራ መጣላት ተገቢ አይደለም፡፡እንደባህሉ ጉርብትና ከፍተኛ ደረጃ የሚሰጠው ማኅበራዊ ትስስር ነው፡፡በጉርብትና የመረዳዳት መንፈስ ስለሚኖር የግንኙነት መሥመሩ የጠበቀ ነው፡፡ማኅበራዊ መስተጋብሩ፣ ከሰው ልጅ መፈጠር ጋራ ተያይዞ የመጣ፣ ረጅም ዕድሜ ያለው፣ የቡድኖች ስብስብ ነው፡፡በዚህም መካከል ያለው ግንኙነት መሰናክል እንዳይገጥመው ከፍተኛ ጥንቃቄ ይደረጋል፡፡በኾነ አጋጣሚ ግጭት ቢፈጠር እንኳን ሳይውል ሳያድር በሽምግልና ችግሩ ይፈታል፡፡ ስለዚህ ጉርብትና በባህሉ የክብር ቦታ የሚሰጠው ስለኾነ ማኅበረሰቡ ከጎረቤትህ ጋራ አትጣላ የሚለውን ምክር ሲጠቀም እንመለከታለን፡፡

## ቅኔ ፫ ጉባኤ ቃና

ገሪማ ኢትሑር ዘእንበለ ሰብእ ፍናከ፣

ቀተልተ እስጢፋ አእባን እስመ ተለዉ ድኅሬከ[64]፡፡

**ትርጉም፦**ገሪማ ያለሰው መንገድህን አትኺድ፤

የእስጢፋኖስ ገዳዮች/ድንጋዮች በኋላ ተከትለውሃልና ፡፡

**ትንተና**

የቅኔው ወርቃዊ ተስተላልፎ አባ ገሪማ ከጓድኞቹ ጋራ ሲኼድ ምግብ ሳይበላ፣ ግን የበላ መስሎ ይጓዝ ነበር፡፡ በኋላ ቅዳሴ ሲገባ ወንድሞቹ ሲያሙት አለመብላቱን ድንጋዮቹ መሰከሩ፡፡ሰማዕቱ እስጢፋኖስም ወንጌል ሲያስተምር በድንጊያ መወገሩን ለመግለጽ ነው፡፡ከማኅበራዊ ጉዳይ አንጻር ሲታይ በአንድ አካባቢ ለብቻ የማይኼድበት አካባቢ ይኖራል፤በቡድን ካልኾነ በቀር በተናጠል ሊታለፍ የማይቻል ጫካ ይኖራል፡፡አንዳንድ ሰው ቦታውን ካለማወቅም ኾነ እያወቁ ማነው የሚነካኝ? ብሎ ከማሰብ ብቻውን ለመኼድ ሲሞክር የአካባቢ ሰዎች ወይም ቤተሰቦቹ ብቻህን አትኺድ ከሰው ጋራ መኼድ አለብህ፤ ጠብቀህ ሰዎች ሲሰባሰቡ፤አብረህ ኺድ፤አለበለዚያ ሽፍቶች ብቸኝነትህን ዐይተው ይከተሉሃል፤ ተከትለውም ይገድሉሃልና ብቻህን አትኺድ ብለው ይመክሩታል፡፡ ምክሩን መስማትና መጠቀም የራሱ ጉዳይ ነው፡፡ አልሰማም ብሎ ብቻውን የሚጓዝ ከኾነ፣ በሌሎች ጉዳት ይደርስበታል ብቸኝነቱን ዐይተው አካሉን ያጎድሉታል፤ ገንዘቡን ይዘርፉታል፣ ተመክሮ ለማይሰማ ሰው ዕጣ ፈንታው፣ ዕድል-ተርታው ይህ ነው /ጽዋ-ተርታው ይህ ነው/

“ምከረው ምከረው እንቢ ካለ መከራ ይምከረው” አይደል ብሂሉ! አትኺድ የሚለው አካል፣ ከልምድ ወይም ለሰውዬው ከማዘን አንጻር ሊኾን ይችላል፡፡አንድም፡- ሰው በዚህ ዓለም ፍና ሲኖር ከማኅበረሰቡ ተለይቶ መኖር አይችልም፤ ወደደም-ጠላም ከሰው ጋራ መጓዝ ግዴታው ነው፣ በሐዘን በደስታው፣ በዕድር በማኅበር፣ ከሰው ጋራ ካልኼደ፤ ማኅበረሰቡ ራሱ ሽፍታ ይኾንበታል፣ያገለዋል፤ እንደ ዕብድ ይፈርጀዋል፡፡እሱ የተነካ ነው ተብሎ ከኢጥዑያን ይመድቡታልና ያለ ሰው አትኺድ አለ፡፡

---

[64] ሥ.ጥ.ቅ.1995፡189 (ባለቅኔው መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ)

**ቅኔ ፬ መወድስ**

አፉሁ ለሰብእ ቀታሊ ርእሱ

እስመ በዘአርመመ አፍ ኢይበውእ ዕፄ ገዳም

ዝኒ ሐሰት ከመ ኢይትበሀል ዮም

መካሕ ወልደጌራ፣ ለእመ ሜረዮ በፅርፈት ደም

ለዳዊት ልብሰ ሕማም

ላዕለ ሰሎሞን በቈለ አሜከላ ዳዊት ቂም፡፡

ተቀትለሂ ግብረ ሳዖል በፍትሐ ዳዊት ሥዩም

ገዘምኩ እመ ይቤ እንዘ ኪያሁ ኢይገዝም

አመኒ አፉሁ ነበበ ሃይማኖተ ኬፋ በሮም

ለፋሲለደስ ረሲዓን ሰሐብዎ በልጓም[65]፡፡

**ትርጉም**፡- የሰው አፉ ራሱን ገዳይ ነው፤

ዝም ባለ አፍ የዱር ዝንብ አይገባበትምና

ይህንም አኹን ሐሰት ነው እንዳንል ተመኪ የጌራ ልጅ

የሕማም ልብስ ዳዊትን በስድብ ቀለም ቢነክረው

የዳዊት ቂም ደንደሮ የሚባል እሾህ በሰሎሞን ላይ በቀለ፡፡

የሳዖል አገልጋይም እርሱን /ሳዖልን/ ሳይቆርጥ

ቆረጥኩ ቢል በሹም ዳዊት ፍርድ ተገደለ፤

የጴጥሮስን ሃይማኖትም በሮም በተናገረ ጊዜ

ዝንጉዎች ፋሲለደስን በልጓም ሳቡት::

## ትንተና

ወርቁ የጌራ ልጅ ሳሚ የሳዖል ባርያ ነው፡፡ ዳዊት በስደት ላይ እያለ አፈር በእጁ እየረጨበት የጭንጋፍ ልጅ እያለ ተሳደበ፡፡ የዳዊት አገልጋዮች ሊገሉት ቢፈልጉ ዳዊት

[65] ኅሩይ፣ 1918፡56

ከእግዚአብሔር የተፈረደብኝ ፍርድ ነው ተውት አትንኩት አለ፡፡ የዳዊት የስደት ዘመን ሲያበቃ ሳሚ ተይዞ በግዞት በአንድ አካባቢ ብቻ እንዲኖር ከዚያ ውጭ ሲኼድ ከተገኘ እንዲገደል ተወሰነበት፡፡ በቀጣይም ይህንኑ በደል ለልጁ ሰሎሞን በመንገር ቅጣቱ እንዲቀጥል ተደረገ፡፡ ከተወሰነበት ውሳኔ ውጭ ሲንቀሳቀስ ተገኝቶ ተገደለ፡፡ የዳዊት ቂም በሰሎሞን ተወርሶ ሰሎሞን ሳሚን ተበቀለው፡፡ የሳዖል አሽከር የነበረው አማሌቃዊው ሰው ሳዖልን በሰይፍ ሳይገድለው ገደልኩት ብሎ ለዳዊት ስለነገረው በዳዊት ፍርድ በገዛ አፉ መጥፋቱን ይገልጻል፡፡ ባለቅኔው በዚህ አላበቃም ፋሲለደስ የተባለው ሰማዕት ወንጌል በመስበኩ እንደ እንስሳት በአፉ ልጓም እንደተደረገበት ያስረዳል[66]፡፡

በማኅበረሰቡ ዘንድ ዝምታ አንድ የመልካምነት መገለጫ በመኾን ሲያገለግል ኖሯል፡፡ “ዝምታ ወርቅ ነው” እየተባለ ሲነገር መኖሩ የታወቀ ነው፡፡ የወርቅነት ማዕረግ አግኝቶ የክብር ስፍራ ተሰጥቶት ሲሞካሽ የተመለከቱት ባለቅኔ ለሰው አፉ ገዳዩ ነው፡፡ ዝም ባለ አፍ ዝምብ አይገባበትም፤ በለፈለፉ ባፍ ይጠፉ ነውና አፍ እና ዝንብ ምን አገናኛቸው? ከመናገር ጋራ ተያይዘው የሚመጡት ዝንቦች ጤነኞች አይደሉም፤ ሰውነትን የሚጐዱ ለኅልፈት የሚዳርጉ ናቸው፡፡ ዝንብ የተባሉት መናገርን መሠረት አድርገው በሰው ላይ ጫና የሚፈጥሩ ጠላቶች ናቸው፡፡ የመናገር ነጻነትን የሚያቀጭጩ የሰውን አፍ ጠብቀው እገሌ ምን አለ? እገሌ ምን ተናገረ? እያሉ ወሬ በመልቀም የገቢ ምንጫቸውን የሚያጎለብቱ አሉ፡፡

ለዚህም ነው በማኅበረሰቡ መናገር ተነቅፎ በተቃራኒው ዝምታ የተወደሰው፤ “በለፈለፉ ባፍ ይጠፉ” የተባለውም ለዚህ ነው፡፡ አበውም ተናግረው ነገራቸው ተቀባይነት ሲያጣ ወይም በመናገራቸው ዛቻ፣ነቀፋ ስድብ ሲደርስባቸው “እምተናግሮ ይኄይስ አርምሞ ከመናገር ዝምታ ይሻላል” ይላሉ፤ በመናገራቸው ሲጸጸቱም ይስተዋላል፡፡ ይህ ነገር ሐሰት ነው እንዳይባልም በመናገራቸው ምክንያት ልዩ ልዩ ስድብ፣ የመታሰርና የመገደል ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ አንድ ሰው ካልተናገረ ማንነቱ አይታወቅም፡፡ የዕውቀትም ኾነ የአስተሳሰብ አድማሱ ከዕውቅና በታች ነው፡፡ ማንም ሊያውቀው አይችልም፡፡ ሰዎች ዝምታ የሚያበዙባቸው ምክንያቶች ኹለት ናቸው፡፡ እነሱም መጻኢና ኀላፊ ሲኾኑ፤ ኀላፊ ማለት ከዚህ በፊት በመናገራቸው ምክንያት የማይረሳ ጠባሳ ይደርስባቸውና የዚያን ዓመታት በመዝከር ይፈራሉ፡፡ መጻኢው ገና በይኾናል ድንጋጤ የናላ፣ ፍርሃት የልቡና

[66] 2ሳሙ.1፡1-16

ያድርባቸዋልና በዝምታ ዋሻ ውስጥ ተጠልለው ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ፡፡ በውስጣቸው ሲሸሙ ሲሽሩ ያለ ቃለ-ጉባኤ ሲሰበሰቡ ዘመናት ያልፋሉ፡፡ በእነዚህ በኹለቱ ምክንያቶች የሰው ልጅ "ለምባዳ" ኢነባቢ ኾኖ ይኖራል፡፡ ሐሳቡን በትክክል ሳይገልጽ ዙሪያ እንደዞረ ያልፍበታል ወይም ያልፍለታል፡፡

## 3.1.2 ትዳር

**ቅኔ ፩ ሚበዝኁ**

ለገብረ ሕይወት ልሂቅ

መነነቶ ጥቀ፣ ልብሰ ብዑላን መርዓት ፡፡

ለገብረ ሕይወት ልሂቅ እስመ ኵለንታሁ ሢበት።

ወግብረ ዚአሁ መልአክ፤ ምስለ መባልዕት አዝማድ

አምጣነ አልቦ ጽዕለት[67]፡፡

**ትርጒም**፡-ገብረ ሕይወት ሽማግሌን፣ የባለጸጎች ልብስ ሙሽራ ናቀችው፤

የገብረ ሕይወት ሽማግሌ ኹለንተናው ሺበት ነውና፤

ሥራው ግን መልአክ ነው፤ ከዘመዶቹ ምግቦች ጋራ ጠብ የለውምና፡፡

### ትንተና

የቅኔው ወርቃዊው አመስጥሮ ገብረ ሕይወት የገዛ ጠጉሩ ልብስ ኾኖት፣ሌላ ልብስ አለመልበሱን እና እንደ መላእክት ምግብ ሳይፈልግ መኖሩን ይገልጻል። በማኅበረሰቡ አንድት ሴት ከዕድሜዋ ጋራ ተመጣጣኝ ያልኾነ ባል ታገባና ከእሱ ጋራ መኖርን አትፈልግም፡፡ ምክንያቱም ሽበት በሽት ስለኾነ፤ የሚገርመው ግን ጠባዩ በጣም ምቹ፤ሥራው እንደመልአክ ነው፡፡ የጠባይ ጌታ መኾኑ የተመሰከረለት ነው፤ ይኹን እንጂ ጠባዩ ሊገዛት አልቻለም፤ እሷ የምታየው ሽበቱን ነው፡፡እሷ የምትመለከተው ሽማግሌ አግብታ የሽማግሌ ሚስት ኾና ሽማግሌ እየጠረች ናት የሚለውን ሐሜት ነው፡፡

---

[67] ይኄይስ 1960፡36

አንድም ሽበት የዐዋቂነት፣ የትልቅነት ክብር ነው፡፡ ኾኖም ከተገኘ በማኅበረሰቡ ዘንድ ከፍ ያለ ቦታ ይሰጠዋል፤ የክብር ስፍራ ይቸረዋል፤ በነገሮች ኹሉ ጣልቃ እየገባ እንዲዳኝ የዳኝነት ሥልጣን ይሰጠዋል፡፡ኾኖ ካልተገኘ ግን በተቃራኒው ይሰደብበታል፡፡ ለዚህም ነው ባለቅኔው "ወበሢበቱ ለሰብእ ኢናከብሮ ቀዲሙ" ሲል ትልቅ ኾኖ፣ ነገር ግን በግብሩ የወረደውን ሰው ነው በዚህ መልኩ የሚተቸው፡፡ የሙሽራዋን ኹኔታ ስንመለከት የላዩን እንጂ ሥነ-ምግባሩን አልተመለከተችም፡፡ምግባሩ መልካም ከኾነ በሥራው መጽናናት ነበረባት፤ ነገር ግን ከላይ የሚታየውን ብቻ መስፈርት አድርጋ ናቀችው ፡፡ወጣትም ኾኖ ብልሹ ምግባር ካለው የበለጠ ሊያበሳጫት ይችላል፡፡ይህን አላሰበችም፡፡ ሽበት ከላይ ነው፤ ምግባር ግን ከውስጥ ነው፡፡ ከዚህ ላይ ውስጣዊ ውበት ትኩረት ሲነፈገው ይስተዋላል፡፡ሰው እንደምርጫው ነው፡፡ይህቺ ሙሽራ ትኩር ብላ የተመለከተችው ግን የላዩን የውበት መጓደል ነው፡፡"መልከ ጥፉ በስም ይደግፉ" ዐይነት ኾነባትና ልትቀበለው አልቻለችም፡፡አንድም የናቀችበት ምክንያት ሽበቱ ሽፋን ይኹን እንጂ በፍቅር ላይጣጣሙ ቢችሉስ ማን ያውቃል? ይህ እውነት እንግዲህ ለሙሽሪት ብቻ ነው ግልጽ የሚኾነው፡፡ ችግሩን ገልጾ ለመናገር ከባህል አንጻር ችግር አለ፡፡ባህሉ በፍቅር አለመግባባትን ክሡት ለማድረግ አይፈቅድም፤ ከዚህ አትለፍ ብሎ ያስቀመጠው የራሱ ድንበር አለው፤ ያን አልፎ ቢገኝ ይወገዛል፤ ይጋዛል፤ ይወገራል፡፡ ለባህሉ ክብር ሲባል የተለያዩ ምክንያቶችን እየፈጠሩ የመለያየት ነገር ይከሠታል፤ የባህሉን ድንበር መተላለፍ ቢቻል ግን ልዩነትን መታደግ ይቻል ነበር፡፡ከምክንያታዊ ሐሰተኛነት የማምለጫም ዘዴ ነበር፡፡

### ቅኔ ፪ መወድስ

ብእሲት ባሕር ምልዕተ ዐመፃ

ለብእሲሃ ምልክዓም እፎኑመ ታቀልሎ?

እመ እገሪሁ ያቀርብ ተኀፅበኒ ብሂሎ፤

እገሪከ ኢየኀፅበከ አኮኑ ትቤሎ፡፡

ወአምጽአት ምክንያተ፣ እንዘ ትብል ማይ ውስተ ቤትየ ኢሀሎ፡፡

ለፈርያንሰ እመ ሠምረቶ እንበለ ንስቲት ተሀጕሎ፣

ሐዊራ ውስተ ፍኖቱ ፈረሰ ትትቄበሎ፤

ወበተዋንዮ ብዙኀ እንዘ ታስተሜኒ ኵሎ፤

ምዕረ ትጼዐኖ ወምዕረ ትሰቀሎ[68]፡፡

**ትርጕም፡-**በደልን የተመላች ባሕር ሴት ሙሴ ባልዋን ምንኛ ታቀለዋለች?

ታጥበኛለች ብሎ እግሩን ቢያቀርብ፣ እግርህን አላጥብህም ብላዋለችና፤

ምክንያትም አመጣች፣ በቤቴ ውስጥ ውሀ የለም ስትል፡፡

ያለትንሽ ጥፋት ፈርያንን ግን ብትወደው፣ከመንገዱ ኺዳ ፈረስን ትቀበለዋለች፤

በብዙም ጨዋታ ኹሉን እያስመኘች፣ አንድ ጊዜ ትጫነዋለች አንድ ጊዜም

ትሰቀለዋለች /ትቀመጥበታለች/ ፡፡

**ትንተና**

በሃይማኖቱ ዕሳቤ በዕሥራኤል ታሪክ ውስጥ ሙሴ የኤርትራን ባሕር ተሻግሮ ከጠላት አምልጧል፡፡ ፈርያንና ሠራዊቱ ግን ለመሻገር ሲሞክሩ መስጠማቸውን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ወደ ማኅበራዊ ሐቲት ስንመጣ ደግሞ በደለኛ ሴት ባልዋን አታከብርም፤ ታቃልላለች፤ ከሥራ ውሎ መጥቶ እግሬን ዕጠቢኝ ሲላት፣ አላጥብም፤ ውሀ የለኝም ትላለች፡፡ ባህሉ የትዳር አጋሯ እግር አጣቢ አድርጎ ያስባታል፡፡ባልና ሚስት ተከባብረው፣ ተመካክረው፣ በፍቅር እንዲኖሩ እንጂ በየጊዜው እንዲጨቃጨቁ፣ እንዲናናቁ አልነበረም፤ በእነዚህ ባለትዳሮች ግን ይህ ተቃራኒ ኾኖ ይገኛል፤ መከባበር የሚባል ነገር በመካከላቸው ፈጽሞ የለም፡፡ ለዚህም መገለጫው አለመታዘዝ ነው፡፡ምን አልባት፣ ያቀረበችው ምክንያት እውነት ከኾነ ሊያስኼድ ይችላል፤ ነገር ግን ይህ ምክንያት ለጊዜው ማምለጫ ነው የሚመስለው፤ ምክንያቱም ቆይቶ የሚያመጣው ነገር የቀረበውን ምክንያት ያፈርሰዋል፡፡ሌላ በኹለታቸው መካከል ጣልቃ የገባ ሰው አለ፡፡ የቤቱ ባለቤት ያልኾነው መጣ ሲባል ከሩቅ ዐይታ፣ በደስታ ትቀበለዋለች፣ ከባሏ ጋራ የሌለ ጨዋታ ከእሱ ጋራ ትጫወታለች፤ ምክንያቱም ባል ሥራዬን፣ ቤቴን እያለ ደፋ ቀና ሲል፣ እሱ ግን ለጊዜው፣ ስለሚያስደስታት፣ ከላዩ ላይ እየተሰቀለች /ሥጋዊ ፍላጎቷን ስለሚወጣላት/ በልዩ አቀባበል ትቀበለዋለች፡፡ አንዳንድ ሴቶች ባላቸው ደክሞ ሠርቶ ሲያንቀባርራቸው እሱ በሚያመጣው ገንዘብ ከሌላ ጋራ ሲጨፍሩ ይስተዋላሉ፤ ለባላቸው ምንም ቦታ ሳይሰጡ ለውጭ ሰው

[68] አድማሱ 1963፡197 (የቅኔው ባለቤት መሪጌታ መንግሥቱ በጌምድር)፡፡

መልካም መስለው ይታያሉ፡፡ "የውስጥ ቀጋ የውጭ አልጋ" የኾኑ ሴቶች አሉ፡፡ ደግነት ግን ከቤት መጀመር ነበረበት፡፡

የሚገርመው ነገር የውጩ ሰው ከሩቅ ሲመጣ ከመንገድ ተቀበለችው፤ ባሏን ግን ከመንገድ መቀበል ይቅርና ከቤት መጥቶ በራሱ ቤት ማዘዝ አልቻለም፤ እግሬን ዕጠቢኝ ብሎ ቢለምናትም ምክንያት እየደረደረች አላጥብህም አለችው፡፡ "በማን ላይ ቆመሽ እግዜርን ታሚያለሽ" አይደል ብሂሉ፣! ወይም ቀድመው ቢወያዩ እኮ ይኽ ኹሉ አይፈጠርም ነበር፤ ከግልጽነት ማነስ የተነሣ፣ እሱም በሚስቱ ዘንድ ክብር አጣ፡፡ እሷም የውጭ ሰው ለመደች፡፡ "ሳይቃጠል በቅጠል" ይሏል ይህ ነው፡፡ መፈራረት የሚያስከትለውን ጥፋት የሃይማኖት ሰዎችና የሀገር ሽማግሌዎች ሊፈቱት አይችሉም፤ ምን አልባት ራሱ ነገረ ጉዳዩ ያስከተለው ችግር በአስተማሪነት ከመለሰው ነው እንጂ፡፡ ከዚያ በኋላ የሚኖረው ተነሳሒነት በባል ዘንድ ተቀባይነት ላይኖረው ይችላል፣ በመሀል ቤት፣ ተስፋ መቁረጥና ራስን ማጥፋት ይከሠታል፡፡ ወደቀቢጸ ተስፋ በማሽቆልቆል ነገሩ የከፋ ይኾናል፡፡ ሰሚም ከማዘን ይልቅ ይበላት፤ ሲያንሳት ነው እያለ በፍርድ ላይ ፍርድ ያጸናባታል፡፡ "ብልኀ የዓመቱን፣ ሞኝ የዕለቱን" የሚለው ብሂል በእሷ ይፈጸማል፡፡

### 3.1.3 ፍቅር

**ቅኔ ፩ ጉባኤ ቃና**

ኒቆዲሞስ ፈትሐ ወለተ ዳዊት ዘሠምሮ፣

ሠናይተ ላሕይ ወንጌለ በበዓለ ጥምቀት ነጺሮ [69]፡፡

**ትርጉም፦**ኒቆዲሞስ በጣም ይወዳት የነበረ የዳዊትን ሴት ልጅ ኦሪትን ፈታ፣

በጥምቀት በዓል ላይ ደም ግባቷ ያማረ ቆንጆ ወንጌልን ዐይቷልና፡፡

#### ትንተና

ታሪኩ ኒቆዲሞስ የኦሪት መምህር ሲኾን በወንጌል ማመኑን፣ ወደወንጌል መምጣቱን የሚያሳይ ነው [70]፡፡ ከዚህ ላይ ጉዳያችን የሠሙ ጣጣ ስለኾነ ትኩረቱ ሠሙ ላይ ነው። አንዳንድ ሰው፣ ቀደም ብሎ የሚወዳት ፍቅረኛ ትኖረውና፣ ከዚያች ጋራ ብዙ ዐብሮ ካሳለፈ በኋላ፣ ደም ግባቷ ያማረ ከመጀመሪያዋ የተሻለች፣ ሲያገኝ ያቺን የመጀመሪያዋን

[69] ማርዬ 2006፡142

[70] ዮሐ.3፡1-12

ይተዋታል፡፡ ይህ እንግዲህ በሰዎች ዘንድ የሚከሠት፣ ጉዳይ ነው፡፡የዐይን ዐዋጅ የኾነበት ሰው ያየውን ኹሉ ይከተላል፤ በአንድ አይጸናም፡፡ የተወሰነ ጊዜ ከአንዱ ጋራ፣ ሌላ ጊዜ ከአንዱ ጋራ እያለ፣ ፍትወታዊ ፍላጎቱን ማርካት ይፈልጋል፡፡

የጥምቀት በዓል ብዙ ጊዜ ታይተው የማይታወቁ ቆንጆዎች የሚታዩበት ነው፡፡ "ለጥምቀት ያልኾነ ቀሚስ" እየተባለ ያለ የሌለውን ለብሶ፣ ተኩሎ ተቀብቶ ሲመጣ ጎረምሳው ኹሉ ይሳባል፡፡ በዚህ አጋጣሚ በለስ የሚቀናቸውም አይጠፉም በጥምቀት ጎረምሶችና ኮረዶች ነፃነት ያገኛሉ፡፡ ዓመቱን ሙሉ በቁጥጥር የከረሙት በዚህ ቀን ነጻ ይኾናሉ፤ የፍቅር ጨዋታን በነጻነት ይጫወታሉ፡፡ በዚህ ግርግር መካከል ጓደኛ ያለው የተሻለ ሲያገኝ ይቀይራል፤ ጓደኛ የሌለው አጋጣሚውን ተጠቅሞ ፍቅር ይመሠርታል፡፡ ስለዚህ የጥምቀት በዓል የመተጫጨት ተግባርም እንደሚከናወንበት ይጠቁማል፡፡ ባለቅኔው በጥበቡ እንደገለጸው የጥምቀትን በዓል ባህላዊ ዕሴት አስመልክቶ በዐጭሩ የገለጸበት አጋጣሚ አለ፡፡ ሌላው በጥምቀት በዓል ላይ ያለ የሌለ ቆንጆ እንደሚታይ ያመለክታል፡፡

### ቅኔ ፬ ዋዜማ

ስምዖን ለመርዓቱ፣ እምነ ኵሉ አክበራ ወእምነ ኵሉ አልዐላ፣

ኢትፃኢ አፍአ አኮኑ ይቤላ፣

ኪያሃ ኢይርአይ ጸዳለ ፀሐይ ወዕብላ፡፡

ወይቤ በፍጽም ወበከዋላ፣

ይትልዉኪ ሰብአ ምድር ኵላ [71]፡፡

**ትርጕም፡-**ስምዖን ሚስቱን

ከኹሉ አብልጦ አከበራት፤ከኹሉም አብልጦ ከፍ አደረጋት፤

የፀሐይና የጨረቃ ብርሃን እንዳያያት ወደ ውጭ አትውጭ ይላታልና፡፡

በፊትና በኋላም የምድር ሰዎች ኹላ ይከተሉሽ ብሏታልና ፡፡

---

[71] አድማሱ1963፡113 (ባለቅኔው መሪጌታስመኝ ዘጠለዛሞ)

### ትንተና

ወርቁ ስምየን በላኤ ሰብእ መጀመሪያ ሚስቱን በመጨረሻም ሌሎችን ሰዎች መብላቱንና ሚስቱም ከፀሐይና ከጨረቃ ዓለም መለየቷን ይጠቁማል። ለሚስቱ እንኳን የማይራራ ጨካኝ መኾኑን አመልካች ነው፡፡ ሠሙ "ፀሐይ አይንካሽ"፣ "ደጅ አትውጪ"፣ ሰዎች ይከተሉሽ" የሚሉት ፍቅር ቀመስ ቃላት ናቸው፡፡ በማኅበረሰቡ አንዳንድ ሰው ሚስቱን ከኹሉም አብልጦ ይወዳታል፤ያከብራታል፤ ከኹሉም አስበልጦ ከፍ ያደርጋታል፡፡ ስለዚህ የፀሐይና የጨረቃ ብርሃን እንዳያገኛት ወደውጭ አትውጭ ይላታል፡፡ ብትወጣም እንኳን በአጃቢ ነው ብቻዋን አትወጣም ወንድ ልጅ ሚስቱን ከወደዳት፣ ኹሉንም ነገር እሱ መሸከም ይፈልጋል ሚስት እንድትሠራ ፀሐይ እንዳቃጥላት አይፈልግም አኹንም በዚህ ቅኔ የሚስተዋለው ይህ ነገረ ጉዳይ ነው፡፡ በባልና ሚስት መካከል ትልቁ ጉዳይ ፍቅር መተሳሰብ ነው፣ ፍቅር ካለ ኹሉም አለ፡፡ እንደውዝም ብሎ ጊዜ ለማሳለፍ ወይም ለልጆቹ ብዬ ነው እንጂ የእሷ ነገር የእሱ ነገር እየተባባሉ መኖር አያድርስ ነው፡፡ ካለ መኖር የማይሻል መኖር ሕይወትን ለማጣጣም ማነቆ ይኾናል፡፡ የሚወዳት ከኾነ ግን፣ እሱ ጠቁሮ በፀሐይና በብርድ እየተሰቃየ ያመጣውን እየተጠቀመች ንግሥት ኾና እንድትኖር ያደርጋታል፡፡

### 3.1.4 ሐዘን

**ቅኔ ፩ ዋዜማ**

በምንት ነዐድዎ

ለሐዘነ ልብ ባሕር እንተ ያሰጥም አእጋረ?

ሐመር ሀብተ ካህናት አኮኑ ተሰብረ፤

ወበምንት ንሬኢ ገጸ መጻሕፍት ምስጢረ?

መጽሔተ አእምሮ ጎንደር እስመ ተመዝበረ፤

ወመሰለ ግብጻዌ ብሔረ[72]፡፡

**ትርጕም፡-** በምን እንሻገረዋለን? እግሮችን የሚያሰጥም የልብ ሐዘን ባሕርን በምን እንሻገረዋለን፡፡ የካህናት ሀብት መርከብ ተሰብሯልና፡፡ የመጻሕፍት ገጽ

---

[72] ጎሩይ 1918፡99

ምስጢርንም በምን እናያለን? የአእምሮ መስታወት ጎንደር ተዘርፏልና /ተቃጥሏልና/፡፡ ግብጻዊ ሀገርንም መሰለ::

**ትንተና**

ወርቁ ቅኔው በጎንደር ምዝባሬ ጊዜ የተነገረ ሲሆን በቃል ሲተላለፍ ቆይቶ በኋላ የኅትመት ብርሃን አግኝቷል፡፡ ከኃይለ ሐሳቡ የተነሣ ግን ሳይረሳ ዘመናትን ተሻግሯል፡፡ለዚህም ታሪክ በ1879 ዓ.ም ማህዲስቶች የጎንደርን ከተማ ማውደማቸውን ይናገራል[73]፡፡ ይህ ክሥተት በሕዝቡ ዘንድ ጠባሳ ኾኖ የወቅቱን ኹኔታ ያሳያል፡፡ ይህ ሀገርን ማውደም እና ሕዝብን የማጥፋት ተግባር በማኅበራዊ ልማድ በሐዘን ማሳያነት ቀርቧል፡፡አንዳንድ ማኅበራዊ ጉዳይ ካለው ክደት የተነሣ ጥያቄ ኾኖ የሚኖርበት ኹኔታ ይፈጠራል፡፡ መልስ ቢሰጠውም ጥያቄነቱ ይበልጥ ሚዛን ያነሣል፡፡ ከእነዚህ ጉዳዮች መሀል አንዱ ሐዘን ነው፡፡ ሐዘን አይፈለግም መከሰቱ አይቀርም፡፡ መጠኑ ሲጨምር ግን ታላቅ ባሕር የሚኾንበት አጋጣሚ ይፈጠራል፡፡ ችግሩ ግን የሐዘኑ መከሰት ሳይኾን መሻገሪያ መንገድ የማጣት ነው፡፡ ችግሩ ግላዊ ሲኾን የሚያስተዛዝን አይጠፋም፡፡ የጋራ ሐዘን ከኾነ የችግሩን ክብደት ያሳያል፡፡ ትላልቅ ሥልጣኔ የተጠነሰሰባቸው የሕዝብ ባህል እና ዕውቀት የተከማቸባቸው ከተማዎች በሚጠፉበት አጋጣሚ የሐዘን ድባብ ይፈጠራል፡፡ የካህናቱ ሥጋዊ እና መንፈሳዊ ሀብት በመርከብ ተመስሎ እንደ ኖኅ መርከብ የመዳን መርከብ ሳይኾን "የጥፋቱን ውሀ" አስገብቶ በዚህም ተሰባብሯል፡፡

የባህልና የዕውቀት፣ ሃይማኖታዊ አስተምህሮ ማዕከል የኾነችው ጎንደር ከመስታወት ጋራ ተመስላ የውበትና የሕይወት ምስል እንዳላሳየች ኹሉ ዛሬ እንዳልነበር ኾናለች፡፡ ከዚህም ጋራ ተያይዞ የሊቃውንቱ "ገጽ/ፊት" የመጻሕፍት ምስጢር በተመሰለበት ኺደት ከእይታ ተሰውሯል፡፡ የውበትእና የመንፈስ ተልዕሎ አይታይበትም፡፡ በዚህ ቅኔ ውስጥ የ "ሀገር" መስታወትነት "የመንፈሳዊ ሀብት" መርከብነት "የሐዘን" ማየ ኖኅነት የምንመለከትበት ማኅበራዊ ብስባሴ እና ቀውስን ከፖለቲካዊ ምስቅልቅል ጋራ የሚቀርብበት ነው፡፡

በፍጻሜ ባለቅኔው የራሱን ሀገር አኹን ያለችበት ኹኔታ ዋዕይና ሐሩር ከሚጸናባት ከግብፅ ምድረ በዳ በማነጻጸር የደረሰው ጉዳት መጠን ምን ያህል ከፍ ያለ መኾኑን ይገልጻል፡፡ እንዲሁም የልብ ሐዘንን እንዴት እንቋቋመዋለን? አንዱ አንዱን እንዳያጽናናው ሐዘን

[73] ባሕሩ 2003፡65

በየደጁ ኾኗልና፡፡ የቤተ መቅደስ ንዋያት ተመዝብረዋልና የመጻሕፍትን ምስጢር መመርመር አይቻልም፡፡ ምክንያቱም የትርጓሜ ትምህርት የሚሰጥባት ጎንደር እንደ ግብጽ ሀገር በድርቡሽ፣ ፈርሳለችና /ተቃጥላለችና/፡፡

### 3.1.5 ፍላጎት

**ቅኔ ፩ ሥላሴ**

ውሉደ ዘረከቡ

በኀጢአ ብእሲት ይቴክዙ

ወዘረከቡ ብእሲተ በኀጢአ ውሉድ ይላሑ

እስመ ባዕድ ፍና ብእሲት ወለወልድ ፍናሁ

እምትካዘ እሉሰ ለምጽ ኅሊናተ ሎጥ ይንጽሑ

አዋልድ ለሎጥ ተራድኦሁ

አምጣነ አዋልድ በለፌ አዋልዲሁ

ወበለፌ አንስተ ኮናሁ [74]፡፡

**ትርጒም፡-** ልጆችን ያገኙ ሚስትን በማጣት ያዝናሉ

ሚስትን ያገኙ ደግሞ ልጅን በማጣት ያለቅሳሉ

የሚስት መንገድና የልጅ መንገድ ልዩ ናቸውና ፡፡

ግን የሎጥ አሳቦች ከነዚህ ትካዜ ለምጽ ይንጹ

ሴቶች ልጆቹ ሎጥን ተራዱት

ሴቶች ልጆች በዚህ በኩል ልጆቹ ናቸውና

በዚያ በኩል ደግሞ ሚስቶቹ ኾነውታልና ፡፡

**ትንተና**

የቅኔው ሃይማኖታዊ ታሪክ ሎጥ በወይን መጠጥ ሠክሮ ከኹለቱ ሴቶች ልጆቹ ጋራ ሩካቤ ሥጋ መፈጸሙን የሚያሳይ ነው[75]:: ማኅበራዊው ጉዳይ ኹሉን አሟልቶ አይሰጥ፤ ለአንዱ

[74] አድማሱ 1963፡41 (የቅኔው ባለቤት መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ)
[75] ዘፍ.19፡30-38

የሚሰጠው ለሌላው ይርቅበታል፤ ለአንዱ ርካሽ የኾነው ለሌላው ይሰቅበታል፡፡ የሰው ልጅም አንዱን ነገር ሲያገኝ ባለው ነገር ከመጽናናት ይልቅ በሌለው ነገር ሲብከነከን ይስተዋላል፡፡ ልጅ ያገኙ በሚስት ዕጦት ያዝናሉ ሚስት ያገኙ በልጅ ዕጦት ያለቅሳሉ፡፡ "ይቴክዙና ይላሑ" የሚሉት ቃላት እንደርእሰ ጉዳዩ ክብደት የተላለፉ ናቸው፡፡ የሚስት ዕጦት ለትካዜ እንድሚያጋልጥና የተሰጠውም ደረጃ ሐዘን እንደኾነ ይገልጻል፡፡ ምክንያቱም ከጥሩም ይኹን ከመጥፎ በመደበኛም ይኹን በኢመደበኛ ዞሮ ዞሮ ልጁ ስለተገኘ ጉዳቱ ብዙም አይደለም የኹለተኛው ልጅ ማጣት ግን የሚያስለቅስ ጉዳይ ኾኖ ቀርቧል፡፡ የሰው ልጅ በዚህ ምድር ሲኖር ዐይኑን በዐይኑ ማየት ይፈልጋል፡፡ ራሱን መተካት ካልቻለ የመኖር ትርጕሙ ከንቱ ይኾንበታል፤ ወደቀቢጸ ተስፋ ይሸቆለቆላል፡፡ እንደየእምነቱ ለታቦታት ይሳላል፤ ለጠንቋይ ይገብራል፤ በየሐኪም ቤቱ እየተመላለሰ ባለሙያዎችን ያማክራል፡፡ ኹሉም እንደየልምዳቸው የራሳቸውን የተስፋ ቃል እየለገሱ የገቢ መጠናቸውን ያሳድጉበታል፡፡ ኹልጊዜ ወደእነሱ እንዲመላለስ የዘወትር ባለጉዳያቸው እንዲኾን ይፈልጋሉ፡፡ በመጨረሻ ግን ይህን ኹሉ ሞክሮ መፍትሔ ሲያጣ ያለቅሳል፡፡ ይኽ የመጨረሻው ደረጃ ነው፤ እስከ አኹን የደከመባቸው ሙያተኞች አንዱ እንኳን አለመሻሉን በትዝብት ተመልክቶ፤ በዕድሉ ያለቅሳል፡፡ በማልቀሱ የሚመለስ የተፈለገው ነገር የሚገኝ ኾኖ ሳይኾን የነገሩን ኃያልነት የልብ ስብራት የደረሰበት መኾኑን ለመግለጽ ነው፡፡ የኹለቱ መንገድ ለየቅል ነውና የልጅና የሚስት መገኛቸው የተለያየ በመኾኑ በአንድ ጊዜ /በአንድ ላይ/ ሊገኙ አልቻሉም፡፡ መልካም ሚስት ተገኝታ ልጅ ላይገኝ ይችላል ልጅ ተገኝቶ መልካም ሚስት ላትገኝ ትችላለች የልጅ አለመውለድ ጉዳይ ከራስ ኀጢአተኛነትና በደለኛነት ጋራ ተያይዞ ስለሚታይ ለቅሶው የፀናበት ለዚህ ነው፡፡

ከማኅበራዊ ጉዳዮችም የመገለል ኹኔታን ስለሚያስከትል በውስጥ የመብሰክሰክ ነገር ይኖራል፤ በዚህ ጊዜ የልብ ስብራትን በእንባ የመደለል ኹኔታ ይከሰታል፤ እንደጊዜያዊ መፍትሔ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ መፍትሔው ግን ያን የታጣውን ነገር ያስገኛል ወይ? ሲባል መልሱ የባለጉዳዩ ይኾናል፡፡ ነገር ግን ከባህሉ አንጻር እንባ ውስጣዊ የልብ ሐዘንን መግለጫ መሣሪያ ተደርጎ ስለሚወሰድ የነገሩን አስከፊነት በእንባ ገለጸው እንባ የሚወዱት ሲሞት የፈለጉት የተመኙት ሲጠፉ፤ ተስፋ ያደረጉት ሲከዳ፤ ሊከሰት ይችላል፡፡ እንባ በዓለም የሐዘን መግለጫ መሣሪያ ኾኖ ያገለግላል፡፡ የእንባን መሣሪያነትም በመጽሐፍ ቅዱስ ሳይቀር ስግዉ ኾኖ እናገኘዋለን፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር በሚያስተምርበት

ወቅት የሀገሪቱን ጥፋት የሰዎችን ሞት ሲመለከት ያለቅስ እንደነበር ተጽፏል "ወርኢያ ለሀገር በከየ ላዕሌሃ ወርእዮ ለዘያገብኦ በከየ ላዕሌሁ ወአንብዐ እግዚእ ኢየሱስ"[76]፡፡ ከዚያም ባለቅኔው ተስፋ አስቆርጦ /ከቀቢጸ ተስፋ አድርሶ/ አልተወዉም ኹለቱም በአንድ ላይ ሊገኙ እንደሚችሉ ያመለክታል ከመጽሐፍ ቅዱስ ምንጭ ጠቅሶ ሎጥ ልጆቹ ሚስትም ኾነውታል ይላል አንዳንድ ጊዜ ተስተካክለዉ የተገኙለት ሰው ይኖራል ፡፡

**ቅኔ ፪ ሥላሴ**

አእዱግ ዘአጥረዩ

በኀሚሠ መሥነቅት ይጻምዉ

ወዘአጥረዩ  መሥነቅተ ለአጥርዮተ አድግ ተግሁ፤

እስመ ባዕድ እምረባሐ አድግ ለመሥነቅት ረባሑ፤

በቍዔቱሰ ለቶማስ በቋዒ ለእመ አኮ ከማሁ፤

እለ አጥረይዎ ይትፌሥሑ፤

እስመ መሥነቅተ ጽድቅ ይከውን ማዕሰ ሥጋሁ፤

ወመሥነቅቶ ይጼዐን ለሊሁ [77]፡፡

**ትርጕም፡-**አህዮችን የገዙ

አቁማዳን በመፈለግ ይደክማሉ፤

አቁማዳን የገዙ ሰዎች ደግሞ አህያን ለመግዛት ተጉ፤

የአቁማዳ ጥቅም  ከአህያ ጥቅም የተለየ ነውና፡፡

የጠቃሚ ቶማስ ጥቅም ግን እንደርሱ ሳይኾን የገዙት ይደሰታሉ፡፡

የሥጋው ቆዳ የእውነት አቁማዳ ይኾናልና፤

አቁማዳቸውንም እሱ ራሱ ይጫናልና /ይሸከማልና/፡፡

---

[76] ዮሐ፡11፡35

[77] አድማሱ 1963፡42 (ባለቅኔው መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ)

## ትንተና

የቅኔው ሃይማኖታዊ ጭብጡ ሐዋርያው ቶማስ ወንጌልን ሲሰብክ ክርስቶስን ያልተቀበሉት የእምነት ተቃራኒዎቹ ቆዳውን ገፈው አቁማዳ አውጥተው አሸዋ ሞልተው በራሱ ላይ አሸክመውታል፡፡ የአህዮቹንና የአቁማዳን አገልግሎት ፈፀመ ማለት ነው፡፡ ይህንም ባለቅኔው ሲያመሰጥረው ቶማስን አህያና አቁማዳ አድርገው ቢጠቀሙበትም ተጠቃሚዎች አይደሉም፡፡ኹለቱን በአንድ ይዞ በመገኘቱ ተጠቃሚው ቶማስ ነው ይላል፡፡ ወደማኅበራዊው ሐቲት እንመለስ "አህያ ያላችው አቁማዳን በመፈለግ ይደክማሉ፤አቁማዳን የገዙ ሰዎች ደግሞ አህያን ለመግዛት ተጉ፡፡" አህያ ለመግዛት ትጋት ሲያስፈልገው አቁማዳ ለመፈለግ ግን ድካም ያስከትላል፡፡ምክንያቱም አህያው ቢኖር የሚፈለገው ነገር (ቁሱ) በአቁማዳ ካልታሰረ በአህያው ላይ መጫን አይቻልም፡፡አቁማዳ ካለ ግን ከታሰረ በኋላ አህያ መፈለግ ይቻላል፡፡ስለዚህ የአህያ አለመኖር ለመግዛት ተነሣሽነትን ሲፈጥር፤ የአቁማዳ አለመኖር ግን ድካምን አስከትሏል፡፡ኹለቱን አሟልቶ መገኘት አልተቻለም፡፡አንዱ ሲገኝ ሌላው ይታጣል፤ የዓለም ነገር ዘወትር አይሞላም፡፡ከዚህ ላይ እንደባለቅኔው ገለጻ አህያ ከሌላቸው ይልቅ አቁማዳ የሌላቸው የበለጠ ይደክማሉ፡፡አቁማዳ ያላቸው ነገር ግን አህያ የሌላቸው አህያ ለማግኘት መትጋት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከባለአቁማዳዎቹ ትጋት ይፈለጋል፡፡ ባለአህዮቹ ግን መድከም ይገባቸዋል፡፡ምክንያቱም አቁማዳ ያላቸው ባለቤት የሌለው ተባራሪ አህያም ሊያገኙ ይችላሉ፤ከከፋም ራሳቸው ይሸከማሉ፡፡አቁማዳ የሌላቸው ግን እህሉን በምን ያስሩታል፡፡አህያ ቢኖር ሳይታሰር አይጫንም ያለው አማራጭ አቁማዳ ለማግኘት በየቦታው መፈለግ ነው፡፡የኹለቱ አገልግሎታቸው ለየቅል ስለኾነ ኹለቱንም አሟልቶ መገኘት ግድ ይላል፡፡አኹን ግን አንዱ ሲኖር ሌላው እየጎደለ ለሚያስቸግራቸው ኹለቱንም የሚያሟላ ነገር ተገኘላቸው "በአንድ ድንጋይ ኹለት ወፍ" ይሏል ይህ ነው፡፡ይህም በድካም ለተሰቃዩ ሰዎች ልዩ ብሥራት ነው፡፡ኹለቱን በአንድ የሚይዘውን ለማግኘት ግን ቀድሞ መግዛት ግድ ይላል፡፡ ይህም የተለየ ተአምር ነው፤ አቁማዳም አህያም የሚኾን መገኘቱ ለሰሚ ገራሚ ለርእይ ማራኪ ጉዳይ ነው፡፡በዓለማችን ዐዲስ ነገር ሲመጣ ሰው ለመግዛት ይሽቀዳደማል፤ ነገር ግን ቀድሞ የተሰለፈ ይገዛል፡፡

### 3.1.6 ከሥራ የተለየ ስም

**ቅኔ ፭ ዋዜማ**

ለመልአክ ኢናከብሮ

ለእመ አሥረጸ ክንፈ በመጠነ ነዊኀ ቆሙ፤

ለዖፍ ወለትንንያ እስመ ክንፍ ቦሙ፡፡

ወበሢበቱ ለሰብእ ኢናከብሮ ቀዲሙ፤

ጸዐዳ ሢበት እስመ ሀለዎሙ፤

ለዕፀው ወአእባን ኵሎሙ[78] ፡፡

**ትርጕም፡-** በረዥም ቁመቱ ልክ

ክንፍን ቢያበቅል መልአክን አናከብረውም፤

ለዎፍና ለትንኝ ክንፍ አላቸውና፡፡

በመጀመሪያም ሰውን በሽበቱ አናከብረወም፤

ለድንጋዮችና ለዕንጨቶች ኹሉ

ነጭ ሽበት አላቸውና፡፡

**ትንተና**

ታሪክ፡- ክፍለ ዮሐንስ ማሕሌት ቆመው እያሉ ካህናት በምቀኝነት ንጉሡ ዐፄ ዳዊት በሚመጡበት ጊዜ እንዳያዩት ብለው ድርብ ጃኖቸውን እንደ ክንፍ ዘርግተው ጋርደውት ትከሻ ለትከሻ ገጥመው ጥምጥማቸውን ግንብ አስመስለው እሱን ወደ ኋላ ይገፉት ነበር፡፡ ክፍለ ዮሐንስ የት ኼዶ ነው? ተብለው ሲጠየቁ አላየነውም አሉ፡፡ንጉሡ ቅሬታውን ዐውቀው ከካህናት ጋራ ተከባብረህ ኑር፤ ካህናት እኮ እንደመላእክት ናቸው አሉት፡፡ በዚህ ጊዜ ምስጢር ተገልጾለት ይህን ቅኔ ተቀኝቷል[79]፡፡

"ክንፍ" እና "ሽበት" የተመረጡበት ምክንያት፣ የትልቅነት መገለጫዎች ስለኾኑ ነው፡፡ ወደ ማኅበራዊው አተያይ ስንመጣ አንድ ሰው ሽማግሌ ኾኖ፣ ነገር ግን ከእሱ የማይጠበቁ ተግባራትን ሲያከናውን ሲገኝ የዕንጨት ሽበት ይባላል፡፡ "ኢናከብሮ" የተባለበትን

[78] አድማሱ 1963፣236 (የቅኔው ባለቤት ሊቁ ክፍለ ዮሐንስ)፡፡
[79] እነኤልያስ፡1992፣125፡፡

ምክንያት ቀጥሎ የሚያመጣው ነውና እንዲህ አለ፡፡ ከዚህ ላይ የተነጻጸሩት  መልአክ እና ሽማግሌ ናቸው፡፡ እነዚህ ኹለቱ ፍጡራን በሰዎች ዘንድ ልዩ ክብር አላቸው፡፡ ክብራቸውም በባህልና በእምነት የሚታይ ነው፡፡ ባህል እና እምነት የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ኹለት ገጽታ ናቸው፡፡

ዕድሜውና ሥራው አይጣጣም ሲል ነው የዕንጨት ሽበት የተባለው፡፡ በእምነትና በባህል ከፍ ያለ ስፍራ የተሰጣቸው ናቸው፡፡ ከእምነትና ከባህል አንጻር የማስታረቅ፣ የማማለድ ተግባር አላቸው ተብሎ በኅብረተሰቡ ዘንድ ይታመንባቸዋል፡፡ ነገር ግን መልአኩም፣ አረጋዊውም በኅብረተሰቡ ዘንድ የተጣለባቸውን ኀላፊነት እንዳልተወጡ ይጠቁማል፡፡ በዚህ ጊዜ ክንፉም ከዎፍና ከትንኝ ያልተሻለ ይኾናል፡፡ የመልአክነቱን ሥራ የማይወጣ ከኾነ ተገቢውን ክብር አንሰጠውም፡፡ መልአክን በክንፉ አናከብረውም፡፡ በክንፍ ከኾነማ ለዎፍና ለትንኝም ክንፍ አላቸው፡፡ሰውንም በሽበቱ አናከብረውም፡፡ ከአንድ ሽማግሌ የሚጠበቀውን አገልግሎት ለኅብረተሰቡ መስጠት ይገባዋል፡፡ ሳይኾን ቀርቶ ቢልከሰከስ ግን ይሰደብበታል፡፡ በሽበት ከኾነማ ለዕንጨቶችና ለድንጋዮችም ሽበት አላቸው፡፡ በማኅበረሰቡ ክንፍና ሽበት የሚያስከብሩ ጉዳዮች ናቸው፡፡

በሃይማኖቱ  ዕሳቤ የብቃት ደረጃን ሲጠቁም፣ በባህላዊው አመለካከት ሽበት ዐዋቂነትን ብዙ የሕይወት ቅምምስ መኖሩን ያመለክታል፡፡ በማኅበረሰቡ ሕይወት ውስጥ ጣልቃ እየገባ እርስ በርስ መከባበር እንዲኖር የሚያዋግን ነው፡፡ ነገሮችን የማስተካከል ኀላፊነት አለበት፡፡ እንግዲህ ይኽን ኹሉ ሥልጣን አሻፈረኝ በማለት የማይሠራ ከኾነ ሽምግልናውን ይሰደብበታል፤ ማለትም ከግዑዛኑ ከዕንጨቶችና ከድንጋዮች ጋራ ተነጻጽሮ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ ቅኔው ሰው የሚከበረው በሥራው በሕይወቱ እንጂ በሽበቱ አለመኾኑን ያመለክታል፡፡ በማኅበረሰቡ ዘንድ የክብር ቦታ ለማግኘት ኹኖ መገኘት አስፈላጊ ነው፡፡ ክንፍም እንዲሁ መብረሪያነቱ ቀርቶ መነቀፊያ ይኾናል፡፡ አንድም አንዳንድ ሰው ከላይ አምሮ ውስጡ ግን መጥፎ መሠርይ የኾነ አለ፤ ስሙም መልአክ ሊኾን ይችላል፡፡ ነገር ግን ኹኖ ባለመገኘቱ በዚያ ስም ይተችበታል፡፡

## ቅኔ ፩ መወድስ

ምንትኑ ለስም በቀኍዔተ ዚአሁ

እመ ተሰምየ ብርሃነ ጽልመተ ሌሊት ገብር

ወዓዲ ጥዑመ እመ ይሰመይ መሪር?

ተሰምዮተ ወይን ወብርሃን

ኢበቍዐ አኮኑ ለአውናን ወኤር፡፡

ወበቅድመ ኢዮአብ ፍሬ ሣዕር፣

ሐመልማለ ሣዕር ኮነ አበኔር ወልደ ኔር፡፡

ብርሃንሰ እመ ተሰምየ ወልደ ባሕርየ አብ ኄር፣

ኮኖ መራሔ ፍና ለዕውር ወለዕውር

ለእመ ተሰምየ ወይነ ጥዑመ ነገር፣

ኮኖ ሰማዕተ ጽድቅ ወይነ ቤተ ቃና ዘመደ ፍቅር [80]፡፡

**ትርጒም፡**-የስም ጥቅሙ ምንድነው?

የሌሊት ጨለማ/ አገልጋይ ብርሃን ቢባል፣መራራም ጣፋጭ ቢባል፣

ወይንንና ብርሃንን መባል፣ ለአውናንና ለኤር አልጠቀመምና፡፡

በኢዮአብ /የሣር ፍሬ ፊትም፣ የኔር ልጅ አበኔር የሣር ቅጠል ኾኗልና፡፡

ቸር የአብ የባሕርይ ልጅ ግን ብርሃን ቢባል፣ለእውር ልጅ እውር መንገድ መሪ ኾነው፣

የነገር ጣፋጭ ወይንም ቢባል፣ የፍቅር ዘመድ የቃና ቤት ወይን

የእውነትም ምስክር ኾነው ፡፡

### ትንተና

የስም ጥቅሙ ምንድነው? የሌሊት ጨለማ /አገልጋይ/ ብርሃን ቢባል መራራም ጣፋጭ ቢባል፣ "መልከ ጥፉ በስም ይደግፉ" እንደሚባለው ስሙና ግብሩ ያልተስተካከለ ሰው ሲገጥመው ወይም ስሙን ሰጥተው ሹመቱን ሲነሱት የሚናገረው ነገር ነው፡፡ አንድም

[80] አድማሱ፣1963፡407 (የቅኔው ባለቤት መምህር አካለ ወልድ)፡፡

ስሙን ይይዝና በሥራ ላይ ዜሮ የሚኾን ከኾነ፣ ስም ብቻ እየተባለ ይተቻል፡፡ ሌላው ደግሞ፣ ስሙ መላክ ኾኖ ሥራው ግን ሰይጣን የኾነ ሰው አለ፡፡ በስም የከበረ ይኾንና በአመለካከትና በአስተሳሰብ የወረደ ይኾናል፣ ስለዚህ የስም ጥቅሙ ምንድንነው? በስምና በተሰያሚ መካከል አንድነት ከሌለ፣ ስምን መላክ ያወጣዋል መኾኑ ቀርቶ፣ ሳጥናኤል ይኾናል ማለት ነው፡፡ ጨለማ ብርሃን፣ መራራ ጣፋጭ የሚባል ከኾነ የስም ጥቅሙ ምንድነው? ከዚህ ላይ ስሙ ሳይኾን ያበሳጨው፣ የተሰየመው አካል፣ እንደስሙ ኾኖ አለመገኘቱ ላይ ነው፡፡

ስም የማንነት መገለጫ ነው፣ በስም አንዱን ከሌላው እንለይበታልን፣ዕድሜውን፣ ደረጃውን ጾታውን፣ አካባቢውን፣ የምንለይበት ዋነኛ መሣሪያ ነው፤ ስም በሰዎች ዘንድ ሰው ከሚለው ግዙፍ አካል ቀጥሎ የሚሰጥ ነው፣ የሰው ልጅ ያለስም አይኖርም፡፡ አጋጣሚ ቢጠፋበት እንኳን ቶሎ የመሰየም ጉዳይ አለ፡፡ያለ ስም መኖር አይቻልም የስም አገልግሎቱ ሰፊ ነው (የትየ ለሌ ነው)፤ ነገር ግን ጥቅሙ ምንድነው? ሲባል እናያለን፣ ይህ ነቀፌታ የደረሰበት እንግዲህ በአግባቡ አልተጠቀመበትም ማለት ነው፡፡ ትክክለኛ ስም ያልተሰጣቸውን ለመጠቆም ነው፣ ያለስማቸው ስም የተሰጣቸው አሉ፤ ስም ዋጋ አጣ፤ ጨለማው ብርሃን፣ መራራው ጣፋጭ ይባላል፤ ስለዚህ የስምን ዋጋ እያሳጣነው ነው፡፡ ወልደ አብ ብርሃን ሊባል ይገባዋል፤ እውር አብርቷልና፡፡ የቃና ወይን ጣፋጭ ሊባል ይገባል፡፡

### 3.1.7 ትዝብት አዘል ምኞት

**ቅኔ ፩ ጉባኤ ቃና**

ከንቱ ውእቱ ትምህርቱ ለእስጢፋኖስ ካህን፤

እስመ በላዕሌሁ ነበሩ ዘኢተምህሩ አእባን [81] ፡፡

**ትርጉም፡-**የካህን እስጢፋኖስ ትምህርት ከንቱ ነው፤

ያልተማሩ ድንጋዮች በላዩ ተቀምጠዋልና፡፡

ወርቁ የእስጢፋኖስ ትምህርት በአይሁድ ዘንድ ከንቱ ነው፡፡ ለትምህርቱ ዐጸፋ በላዩ ላይ ድንጋይ አስቀመጡበት ማለት፣ በድንጋይ ወገሩት፣ እስጢፋኖስ ሲያስተምር ከሚያውቁት ወደማያውቁት ነው፡፡ ስለአብርሃም ሲነግራቸው ሰምተውት ነበር፡፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ሲደርስ ግን ተበሳጩ፡፡ "የሰማይ ደጅ የእግዚአብሔር ልጅ የለውም" ከየት አምጥቶ ነው

[81] ዕንባቆም፡1966፡131 (የቅኔው ባለቤት መሪጌታ ደለለ)፡፡

በሚል ተቃውሞ የድንጋይ በረዶ አዘነቡበት [82]፡፡ የእስጢፋኖስ ሰማዕትነትና የምሁራኑ የሕይወት ውጣ ውረድና ድካም ዐብሮ የሚናበብ ነው፡፡ ድንጋዮች ያልተማሩ ሰዎችን የሚጠቁሙ ናቸው፡፡በምስጢር የተለያየ ቢኾንም በመጽሐፍ ሰዎች በድንጋይ ተወክለው የቀረቡበት አጋጣሚ አለ፡፡ "እግዚአብሔር ከነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣለት ይችላል" [83]፡፡

ሠሙ ባለቅኔው በተማረውና ባልተማረው መካከል ያለውን ሰፊ ልዩነት አስተውሏል፡፡ የተማረውን በከንቱነት ሲፈርጀው፣ ያልተማረው በበላይነት የክብር ስፍራ ተሰጥቶት ይታያል፡፡ በማኅበረሰቡ አንድ ሰው፣ በመንፈሳዊውም ኾነ በዘመናዊ ትምህርት በቂ ዕውቀት ይኖረዋል፤ "የቀለም ቀንድ" ኾኖ እያለ የክብር ቦታ ይነፈገዋል፤ የበታች ኾኖ ሲረገጥ ይኖራል፡፡ ያልተማረው በአፈ ቀላጤነት እያምታታ የክብር ቦታ ተሰጥቶት እናያለን፡፡ ይህ ጉዳይ ለምን ተከሠተ? ሲባል፣ ያልተማረው ለሚኖርበት ዓለም ተስማሚ ኾኖ ተገኝቷል፡፡ እሱ በዓለሙ ዘንድ ዓለምም በእሱ ዘንድ ስምሙ ናቸው፡፡ ከዓለም ጋራ ወዳጅነት መሥርቷል ማለት ነው፡፡ "ዓለምሰ ያፈቅር እሊአሁ " ዓለም የራስዋ የኾኑትን ትወዳለች፡፡አይደል! ነገሩ "ዓለም" ሲባል ሰው የሚኖርበትን አጽናፈ ዓለም ሳይኾን ሐቅን መሠረት ያላደረገውን ኑሮ እና ፌስታ ማለታችን ነው፡፡ በምሁሩ ላይ ያልተማሩት የሚቀመጡበት ከኾነ ዓለም አሠልጥናቸዋለች ማለት ነው፡፡ የዓለም መስፈርት "ንጉሥ የወደደውን፣ ዘመን የወለደውን" ተከትሎ መንጎድ ነው፡፡

የተማረ ሰው ለኅሊናው ሲቆም፣ ያልተማረው ግን ከኅሊና ይልቅ፣ ጊዜያዊ ጥቅም መሠረት አድርጎ ስለሚጓዝ፣ ነገር በማመላለስ፣ በማጭበርበር፣ አልያም ከፍሎ ሥልጣኑን ይይዝና በተማረው ላይ ተጽዕኖ ሲያሳድር ይስተዋላል፡፡ ይህን ያየ ተመልካች ዝም ብሎ አያልፍም፤ ትዝብቱን ይናገራል፡፡ "አይ መማር ከንቱ! " መማር እንደዚህ ከኾነ ቢቀር ይሻላል፤ ካለመማር የማይሻል መማር ነው፡፡ መማሩ ከበታችነት፣ ነጻ የማያደርገው ከኾነ ካልተማሩት በምን ይሻላል? እያሉ ትዝብታቸውን ይናገራሉ፡፡ "በመማር አለቃህን ቀንስ" የሚለው ብሂል በዚህ ሰው ዘንድ አይሠራም፡፡ የተማረው ሰው ለወቅቱ "ነፋስ" ተስማሚ ላይኾን ይችላል፡፡ ያልተማሩት ሰዎች ግን ከጊዜው ጋራ ዐብረው የሚከንፉ፣ በደመቀበት የሚያጨበጭቡ ስለኾኑ የበላይነት የማያገኙበት ምክንያት የለም፡፡ በወቅቱ የሚባለውን

---

[82] የሐ 7፥55-58

[83] ማቴ.3፥9

ነገር መልካምነቱንና መጥፎነቱን ሳይመረምሩ፣ ተሸካሚ ከኾኑ ሥርዓቱ የሐሳብ ሰረገላ ስለሚያደርጋቸው፣ በሥልጣን ስም "በቀቀናዊ" ዙፋን ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ሥልጣናቸውን ተጠቅመው የተማረውን አካል ማሳደድ ይጀምራሉ፡፡ ከላዩ ላይ ኾነው አድራጊ ፈጣሪ ይኾኑበታል፡፡ "ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል" አይደል! ብሂሉ፡፡

የተገፍዖ መጠኑ ይለያይ እንጂ ከቤት እስከ አደባባይ ከአደባባይ እስከ ቤተ መቅደስ ድረስ ይዘልቃል፡፡ በቤተ መንግሥት ውስጥ ያለው ግፍ ቤተ መቅደስም ካባ ለብሶ አለ፡፡ ቤተ መንግሥት ያለው ዱላ በቤተ መቅደስ በመቋሚያ ተለውጦ ይገኛል፡፡ መደገፊያ ብቻ ሳይኾን መምቻም ጭምር ነው፡፡ በላዩ ላይ የተቀመጡት ድንጋይ የኾኑ ሰዎች ናቸው፡፡ድንጋይ በባሕርዩ ግዑዝ ፍዝ ይቡስ ነው፡፡ ሰዎቹም ሰብአዊነት የሌላቸው ይቡሳን አእምሮ ናቸው፡፡ ከድንጋይ ምን ይጠበቃል? በምሁሩ ላይ በደል ቢያደርሱ አይገርምም፡፡ የመማር ጥቅሙ ያልገባቸው፣ ለዕውቀት ቦታ የነፈጉ ናቸው፡፡ የተሻሉ ሰዎች ቢቀመጡበት እኮ አይቆጭም፡፡ ተቀማጮቹ ግን ድንጋዮች ናቸው፡፡ አንድም ያልተማሩት የተማረው ይንቀናል ብለው ከማሰብ፣ ከሥጋት በመነጨ ፍርሀት በተማረው ላይ የተለየ ጫና ሲፈጥሩ ይስተዋላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ምሁሩ ይፈልሳል፤ አማራጭ ከሌለው ከሥር ኾኖ ሲረገጥ ይኖራል፡፡ በአንድም በሌላ መንገድ የተማረ ሰው ይገፋል፡፡ በእግዚአብሔር ስም ይገፋል፤ በመንግሥት ስም ይገፋል፤ የተማረ ሰው ስፍራ ማጣት በየትኛውም ዘመን ውስጥ የሚነሣ ነው፡፡ ዓለማችን ባብዛኛው ከተማረው ይልቅ ባልተማረው ኃይል የመጐተት ባሕርይ አላት፡፡

### ቅኔ ፪ መወድስ

ጸላእኩ ሰብአ እምነ ርእስየ

ዘትርጓሜሁ በቀል ወዘንባቡ ሐሰት፣

እስመ እምልሳኑ ለሰብእ ዘይበልዖ መሬት

ለፌ ትሕትና ወለፌ ትዕቢት

ይወፅኡ ለስብከት ፣

እንዘ በላዕሌሁ ይሂሉ እንተ ኢይትርፍ ሞት፡፡

ልብየሂ ለእመ ጌሠ መንገለ ሐተታ ገነት

ባቲ ዘተጋብኣ ጥበባተ ሰሎሞን ጽጌያት፣

ዕሩያነ ኮኑ በሳምናዊ ሰዓት

ሰብእ በዐመፃ ወእግዚአብሔር በምሕረት [84]፡፡

**ትርጕም፡-**ትርጓሜው በቀል ንባቡም ሐሰት የኾነን ሰው ከራሴ ጀምሮ ጠላሁ፣

መሬት ከሚበላው ሰው እንደበት

በወዲያ ትሕትና በወዲህ ትዕቢት

ለስብከት ይወጣሉና

የማይቀር ሞት በላዩ ላይ እያለ፡፡

ልቤም የሰሎሞን ጥበቦች አበቦች

ወደ ተሰበሰቡባት ገነት ምርምር ቢገሠግሥ፣

በስምንተኛው ሺህ አንድ ሆኑ

ሰው በበደል እግዚአብሔርም በምሕረት፡፡

## ትንተና

ሰውን መጥላት ምክንያቱ በቀል፣ ሐሰትና ትዕቢት ሰው አንዳንድ ጊዜ መፈጠሩን ይጠላል፣ ሰው የሚባለውንም ፍጡር ከራሱ ጀምሮ ማየት አይፈልግም፡፡ የሚያደርጋቸው ድርጊቶች፣ ሰው የሚባለውን ፍጡር የሚያስጠሉ ናቸው፡፡ ምክንያቱም በቀል፣ በውስጡ አርግዞ የሚጓዝ ፍጡር ነው፣ በአፍ ግን በሐሰት ይሸነግላል፡፡ በአፉ የሚናገረው፣ ከሆዱ ያለውን አይደለም በውስጡ ያለው የበቀል የማጥፋት ሐሳብ ኾኖ እያለ በአንደበቱ ግን የሕይወት የመልካምነት ቃልን ይናገራል፡፡ በየጊዜው ይለዋወጣል፤ አንድ ጊዜ ትሑት ይኾናል፤ ሌላ ጊዜ ትዕቢተኛ ይኾናል፡፡ ወጥ የኾነ አቋም አይኖረውም ባለቅኔው ይህን ተሐዝቦቱን ከራሴ ጀምሮ ሰው የተባለውን ፍጡር ጠላሁት ይላል፡፡ ብዙ ጊዜ በዓለሙ በቀለኛ ሰው አለ፣ ነገር ግን ያ በቀሉ ምንም የማይታወቅበት፣ በንግግሩ መልካም መስሎ ስለሚታይ አይነቃበትም፣ በዚህም መሰርይነቱ ብዙ ሰዎችን ይጎዳል፡፡ አሳቻ ሲያገኝ ገፍቶ ለመጣል፣ ወደኋላ አይልም፡፡

---

[84] ጎሩይ 1918፡187

በቀል፣ ሐሰትና ትዕቢት በማኅበረሰቡ ዘንድ የተነቀፉ ናቸው፡፡ በቀለኛ ሰው፣ ከሰዎች ጋራ ተግባብቶ መኖር አይችልም የተበደለውን በደል የማይረሳ ከኾነ ያንን ሲያንሰላስል በልቡ ቂም ቋጥሮ፣ ስለሚኖር በቀላሉ ለመግባባት አይችልም ቻል አድርጎት ቢግባባ እንኳን፣ የኾነ ሰዓት ላይ ሞቅ ሲለው ፀብ ሊያነሳ ይችላል ስለዚህ በማኅበረሰቡ ዘንድ የተጠላ ይኾናል፡፡ ሲበዛም ውፁእ ሊኾን ይችላል፡፡ ሐሰት የሰይጣን ፍሬ (ልጅ) እንደኾነ በቅዱስ መጽሐፍ ተጠቅሶ እናገኘዋለን [85]፡፡ ስለዚህ ሐሰት የሚናገር የሰይጣን የልጅ ልጅ መኾኑ የማይቀር ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ የዚህ ዐይነቱ ሰው ድምሩ /ቁጥሩ/ ከሰው ወገን ባለመኾኑ፣ በሰዎች ዘንድ የተጠላ፤ ለእምነት የማይበቃ፣ ንግግሩ ተቀባይነት የሌለው፤ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በዚህም በማኅበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም፤ በእድር በማኅበር ግሉል ይኾናል፡፡ ትዕቢትም ከእነዚህ ከኹለቱ ተነጥሎ አይታይም፡፡ ያው ቤተሰብ ናቸው ብሎ መውሰድ ይቻላል፣ በትዕቢት የተወጠረውን ሰው ሰዎች ይንቁታል፤ያቃልሉታል፡፡

ሌላው እነዚህ ነገሮች ለምን ተከሰቱ ሲባል፣ በማኅበረሰቡ ዘንድ የሚሰጠው መልስ የስምንተኛው ሺህ ውጤት እንደኾኑ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ "በስምተኛው ሺህ ሰው በበደል እግዚአብሔር በምሕረት አንድ ኾኑ" ይላል፡፡ የሰው ልጅ የሚበድልባቸው ነገሮች በቀል፣ ሐሰትና ትዕቢት ናቸውና፡፡ ከዚያም ትዝብታቸውን ሲገልጹ ሞት እንዳለባቸው አይረዱም እንዴ? ሞት በላዩ ላይ እየጨፈረበት እንዴት እንደዚህ ሐሰት ይናገራል? እሞታለሁን አያስብ እንዴ? በማለት ይናገራል፡፡ እሞታለሁን ባለማሰብ ሰው በሰው ላይ በደል ይፈጽማል፡፡ በዚህ ምክንያት ከራሴ ጀምሮ ሰው የሚባለውን ፍጡር ጠላሁት ይላል፡፡

**ቅኔ፫ መወድስ**

ኵሉ ይትኀባእ እመ ኀሠሥዎ

እመ ኢፈቀድከ አይ ዘይትወሀበነ ግብር

እምነ ፍተ ቃሕም ኅብስት እስከነ ነጥበ ማይ ቈሪር፡፡

ዝሰ ይጽንሐነ  ህልው አግዓዚ በሰማይ ወምድር

እንበለ ምክርከ ሠርዌ ምክር

አድምዖ መቃብር ኢንክል ወረኪበ ሞት ወሰነ ጻዕር ፡፡

---

[85] ዮሐ.8፡44

እስመ ኀጥአ ዘይቀትሎ አመ ተባጽሕዎ ፀር፡፡

ሳዖል ዘተውህቦ ሀብተ አክሊለ ወርቅ ወመንበር፡፡

ወአመ ተመከረ ኢዮብ በዕጸበ ደዌ መሪር ፡

ተመነየ መቃብረ ወኢረከቦ ለመቃብር [86]፡፡

**ትርጒም፦** ኹሉ ቢፈልጉት ይታጣል፡፡

ካልፈቀድህ ግን ከግብረ ጉንዳን ቍራሽ እንጀራ ዝምሮ

እስከ ቀዝቃዛ ውሀ ጠብታ ድረስ ግድ የሚሰጠን ምንድር ነው?

በሰማይና በምድር ያለህ ጌታ  ይህስ ይቈየንና፤

ያለ ምክር አለቃ ምክርህ መቃብርን ማግኘትን አንችልም፤

የጭንቅ (ፍጻሜ) ዳርቻ ሞትንም ማግኘት አንችልም፤

የወርቅ ዘውድና የዙፋን ሀብት የተሰጠው ሳኦል ጠላቶች

በተገናኙት ጊዜ ራሱን የሚገድለው ሰውን አጥቶአልና ፡፡

ኢዮብም በመረረ ደዌ ጭንቅ በተፈተነ ጊዜ መቃብርን ተመኝቶ አላገኘምና፡፡

**ትንተና**

ወርቁ ንጉሡ ሳኦል ጠላቶቹ ሲይዙት ለመሞት ፈልጎ አላገኘም [87]፡፡ ኢዮብም በደዌ ዳኛ ባልጋ ቁራኛ ተይዞ ሲጨነቅ መቃብርን ተመኝቶ አላገኘም [88]፡፡

ኹሉ ነገር ሲፈለግ ይታጣል፤ ለአንድ ነገር ሰፍ ሲባልለት እልም ይላል፡፡ ሳይፈለግ ደግሞ በራሱ ጊዜ ይመጣል፤ ሲፈለግ ግን ይሰቃል፡፡ ሲፈለግ መቃብር አይገኝም፤ ሞትም እንደዚያዉ አድሬሱ ይጠፋል፡፡ እነዚህ ኹለት ነገሮች በማኅበረሰቡ ዘንድ ፈላጊ የሌላቸው ተፈላጊነታው እጅግ የወረደ ነው፡፡ እነሱ ግን ፍጥረቱን ኹሉ አሳደው ሲይዙ ይስተዋላሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ቢፈለጉም እንኳን ሰላማዊ ፍለጋ አይደለም፡፡ ከቀቢጸ ተስፋ ወይም ከሞትና ከመቃብር የሚልቁ ክፍተቶች ሲፈጠሩ ብቻ ነው፡፡ በሰላማዊ ሰዓት ግን ማንም አይፈልጋቸውም፡፡ ይኹን እንጂ ሰዎች ከሚችሉት በላይ ወይም ሊሸከሙት የማይችሉት

[86] ኅሩይ 1918፡115 (ባለቅኔው ሊቁ ክፍለ ዮሐንስ ናቸው)፡፡
[87] 1ሳሙ.31፡4፤ 1ዜ.መዋ.10፡4
[88] ኢዮ.2፡22

የሕይወት ፈተና ሲደርስባቸው መጠለያ ዋሻ፣ መሰወሪያና መደበቂያ ዱር፣ ወይም ጫካ አድርገው ይገለገሉበታል፡፡ ነገር ግን በዚህ ቅኔ የተነገረን ተፈልገው መጥፋታቸውን ነው፡፡ ሞትና መቃብር በአድማ የተባበሩበት ኹኔታ ወይም አጋጣሚ ይስተዋላል፡፡ ነገሩን ተጨባጭ ለማድረግም ከመጽሐፍ ቅዱስ በሞትና በመቃብር እጦት የተሰቃዩ ኹለት ሰዎችን ለምስክርነት ያቆማል፡፡ ሳኦልንና ኢዮብን ሳኦል የወርቅ ዘውድ የዙፋን ሀብት የተሰጠው ነው፡፡ ነገር ግን በጠላቶቹ ሲከበብ በጠላት ተገድዬ ታሪኬ ከሚበላሽ ግደለኝ እያለ ቢጮኽ ገዳይ ያጣበት፤ ሞት የሸሸበት አጋጣሚ አለ፡፡

ኢዮብም በመረረ ደዌ በተፈተነ ጊዜ መቃብርን ተመኝቶ አላገኘውም፤ ኢዮብም በጽኑ ደዌ በቁስለ ሥጋ ሲሰቃይ እግዚአብሔርን አላማረረም፡፡ ነገር ግን መከራ ሲበዛበት መቃብርን ተመኘ፤ በምኞት ሊያገኝ አልቻለም፡፡ እንግዲህ እነዚህ ነባር ሰዎች የተጠቀሱት ሞትና መቃብር ሲፈለጉ እንደማይገኙ ወደላይ እንደሚሰቁ ለአስረጂነት ነው፡፡ ከሞትና ከመቃብር የከፋ ነገር የለም፤ እነዚህ እንኳን ይታጣሉ፤ በመፈለግ ብቻ የሚኾን ነገር የለም፡፡ ኹሉም ነገር ራሱ ፈልጎ ሲመጣ አቀባበሉን ማሳመር እንጂ ሲፈለግ ለምን አልተገኘም? ብሎ ቢፎከር የጨለማ ገልማጭ መኾን ነው፡፡

## 3.2 ፖለቲካዊ ጉዳይ ያላቸው ቅኔያት

በማርክሳዊ እና በሌኒናዊ መዝገበ ቃላት ፖለቲካ የሚለው ፅንሰ ሐሳብ ከታሪካዊ አመጣጡ፣ ከይዘቱ፣ ከተወሰኑ መደቦች ግንዛቤ አንጻር ብያኔ ተሰጥቶታል፡፡ ቃሉ "ፖሊቲ" ከሚባል የግሪክ ቃል የተገኘ የትናንሽ መንግሥታት መንግሥታዊ ተቋማት መጠሪያ ነበር፡፡ በዘመናዊ ፅንሰ ሐሳቡ የኅብረተሰብን አደረጃጀት፣ የመንግሥትን ይዘት፣ ዐይነት፣ ቅርጽ፣ ተግባር፣ መደቦችን እና የኅብረተሰብን ክፍሎች ምንነት የሚያጠና ነው፡፡የሕዝብን ትግልና ግንኙነት መሠረት በማድረግ ህልውናውን ያስቀጥላል፡፡ እንዲህ ይኹን እንጂ የተወሰነ መደብ ግንዛቤ፣ ተግባር፣ እንቅስቃሴም በዚህ ፅንሰ ሐሳብ ይካተታል፡፡የሥልጣኑ ዐቢይ መሠረት ኢኮኖሚ ነው፡፡ በአስተሳሰብ ደረጃ ዋና ሚና የሚይዙት ላዕላይ መዋቅር ላይ የሚገኙ ናቸው [89]፡፡ እኔ በቅኔያቱ ውስጥ የምመረምረው ከፖለቲካዊ አስተዳደር ጋራ የተገናኙ ሒሳዊ አስተያየቶችን ነው፡፡የቤተ ክህነቱ ልሂቃን የዚህ ፖለቲካ ሥርዓት አንድ አካል፣ አልያም የፖለቲካዊ ሥርዓት የሚያርቁ ናቸው፡፡ ከፖለቲካ እውነታም የተነጣ

[89] 1978፥508

ኹለቱ ተቋማት እርስ በርስ የሚመጋገቡ ነበሩ፡፡ እኔ ከዚህ ፅንሰ ሐሳብ ውስጥ የተወሰነ ወገን ያለውን ግንዛቤ እና አስተሳሰብ ተግባር ምን መኾኑን ከቤተ መንግሥት እና ከቤተ ክህነት አንጻር ለመፈተሸ እሞክራለሁ፡፡ ሊቃውንቱ ነገረ መለኮታዊ ዕሳቤዎች በሠማዊ ዐውዳቸው በመጠቀም ለሥርዓተ መንግሥቱ ያላቸውን ድጋፍ የሚገልጹበት አንድ ዐይነት ዕሳቤ በቅኔ ውስጥ እንመለከታለን፡፡ ቤተ ክህነት የሰማይን መንግሥት ብቻ ለመስበክ አለመቆሟን የምንረዳበት ነው፡፡ የምድሩን ሥርዓት የሚመሠርቱ እና የሚሰብኩ መልካምነቱን የሚያውጁ ዐዋጅ ነጋሪዎች ናቸው፡፡ ኹለቱ ኀያላን ተቋማት በጋራ የሚሠሩዋቸውን ፖለቲካዊ ተግባራት በቅኔ ውስጥ መታዘብ እንችላለን፡፡ በዚህም የተነሣ ሊቃውንቱ በቅኔያቱ የነገሥታቱን ፖለቲካዊ አሠራራዊ እና አስተዳደራዊ በደል በሙገሳ፣ በነቀፋና በማስጠንቀቂያ የዘመኑ መንፈስ ምን እንደሚመስል በቅኔያቱ አመስጥረዋል፡፡

## 3.2.1 የምኒልክ ፖለቲካዊ አመራር

**ቅኔ ፩ ሣህልክ**

ምኒልክ በጽዮን አመ ተከሥተ፣

ነሢኦ እምድር ሰይፈ ቊጥዓ መሬተ፣

ለአዳም ጸብእ ድኅረ ለሐኮ

ነፍሐ በመልዕልተ ገጹ መንፈሰ ትዕግሥተ [90]፡፡

**ትርጒም፡-** ምኒልክ በጽዮን በተገለጠ ጊዜ ከምድር የቁጣ ሰይፍ አፈርን ይዞ፤

አዳም ጥልን ከአበጀው በኋላ በፊቱ ላይ ትዕግሥት እስትንፋስን እፍ አለበት ፡፡

**ትንተና**

ታሪኩ፦ ከአዳም አፈጣጠር ጋራ የተያያዘ ነው፡፡ "ወገብሮ እግዚአብሔር ለሰብእ እመሬተ ምድር ወነፍሐ ውስተ ገጹ መንፈሰ ሕይወት ወኮነ እጓለ እመ ሕያው" [91]፡፡ እግዚአብሔር አምላክ በዕለተ ዐርብ አዳምን ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ ከሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ ከፈጠረው በኋላ የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበትና ሕያው ፍጥረት ኾነ ይላል[92]፡፡ ባለቅኔው ይህን ሐሳብ ከሥነ-ፍጥረት በመውሰድ ለወርቁ ማምጠቂያነት ተጠቅሞበታል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ

---

[90] ኅሩይ 1918፡164 (የቅኔው ባለቤት ብላታ ኅሩይ)፡፡

[91] ዘፍ.2፡7

[92] ሞገስ፣ 1957፡67

የተገለጠውን የሰውን አፈጣጠር በንጉሥ ምኒልክ ዘመን  የተከሠተውን ፖለቲካዊ ኹኔታ ለማሳየት ተገልግሎበታል፡፡ እንደሚታወቀው ቅኝ ገዥ አካላት አፍሪካን ለመቀራመት በነደፉት የፖለቲካ አቅጣጫ ውስጥ ኢትዮጵያን መቈጣጠር ወሳኝ የኾነ ስፍራ ነበረው፡፡ በወቅቱ የነበሩት የሀገሪቱ መሪ ዳግማዊ ምኒልክ ያጋጠማቸውን ፖለቲካዊ ቀውስ መፍትሔ ለማበጀት የሚጠቀሙበት ፖለቲካዊ ሥልት በባለቅኔው አእምሮ የተለየ ዋጋ ተሰጥቶታል፡፡

ስለዚህም ይህ ፖለቲካዊ ክሥተት ከቤተ ሃይማኖት ከቀሰመው ዕውቀት ጋራ በማነጻጸር በቅኔ ጥበብ ይቀኝበታል፡፡ በቅኔው ውስጥ የሰው ልጅ የተፈጠረው  ኹሉን በሚችለው ፈጣሪ የፈጣሪነት ሥልጣን ሲኾን ፈጣሪ የሰውን ልጅ ከመሬት አፈር ወስዶ እንዳበጀው፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ መረዳት ይቻላል፡፡ ምንም እንኳን ፈጣሪ የሰውን ልጅ ከመሬት አፈር ያብጀው እንጂ ከመሬት መፈጠሩ ብቻ ሰው ለመኾኑ በቂ ባለመኾኑ የሕይወት እስትንፋስ እፍ ብሎበት ሕያው ሰው እንደኾነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪክ ይናገራል፡፡ በቅኔው ውስጥ አዳም በጦርነት ተመስሎ ሲቀርብ ኹሉን ቻይ ፈጣሪ በንጉሥ ምኒልክ ተመስሏል፡፡ አዳም የተፈጠረበት መሬት ከመቆጣት ሰይፍ ጋራ ተመስሏል፡፡ ከመሬት የተፈጠረው ኹሉ ለዘለዓለም ቋሚ ባለመኾኑ ጦርነቱም ቋሚ አለመኾኑ የመቆጣት ሰይፍ አፈር ብቻ አዳምን ሕያው ሰው እንደማያደርገው ሰይፍ መታጠቅ ብቻም ፖለቲካዊ ድል ኣያጎናጽፍምና፡፡ አዳም ሕያው ነፍስ ለመኾን የፈጣሪ እስትንፋስ እንደሚያስፈልገው በጦርነት ወቅትም ንጉሡን ድል ለመጎናጸፍ ያበቃው ልዩ ኃይል "ትግሥት" መኾኑን አሳይቷል፡፡ በጦርነት ጀብደኝነት ብቻ ሳይኾን፣ ድል የሚያመጣው ትግሥት የተሞላ ፖለቲካዊ ችሎታ ነው በማለት አመስጥሯል፡፡

## ቅኔ ፪ . አሠረ ንጉሥ

ምኒልክ ኢብልዐ ኀፍረተ ቀትል፣ እምነ ይሁዳ ዘተርፈ፡፡
ወበበትረ እድ ዘኮነት ለከንቱ፣ ዘባነ ፀሩ ቀሠፈ
እስመ ፀር ስመ ዘተሳተፈ፡፡
ትምክሕተ ሰናክሬም ቈጽለ ጊዜ ነግሀ ተዐጽፈ
ወበሠርከ ፍሬሁ ተነግፈ[93]፡፡

[93] ኀሩይ 1918፡331 (ባለቅኔው መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ)፡፡

**ትርጒም፡-** ምኒልክ ከይሁዳ የተረፈ በጦር መሸነፍ ምግብን አልበላም፡፡ ለከንቱ በኾነች በእጁ ብትርም የጠላቱን ጀርባ ገረፈ፡፡ በስም የተሳተፉ ጠላት የሰናክሬም ትምክሕት ቅጠልን በጠዋት ጊዜ ለብሷልና፡፡ በማታ ግን ፍሬው ረገፈ፡፡

**ትንተና**

ከዚህ ላይ ባለ ቅኔው እንደጠቆመው በባህላዊው ዕይታ ትራፊ መብላት የበታችነት ደረጃን፣ ድህነትን፣ ችግረኛነትን ያሳያል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትረካ ይሁዳ ጌታውን በመሸጥ በሕይወቱ መጥፎ ታሪክ ያስመዘገበ ሰው ነው፡፡ ትራፊ የተባለው በጦርነት መሸነፍ ነው፡፡ ትራፊና ኀፍረት በምሳሌነት ቀርበዋል፡፡ ንጉሥ ምኒልክ የይሁዳን ትራፊ አልበላም ማለት ይሁዳ የሸጠው እግዚአብሔር ከእሱ ጋራ ስለነበር በጦርነቱ አልተሸነፈም ማለት ነው፡፡ ይህም የምኒልክን የጦር ጥበባዊ ብልኀት ያመለክታል፡፡ ሌላው ሰናክሬም በኃይል በጉልበት በሚታዩ ነገሮች ላይ ተመክቶ ወደ ሕዝቅያስ ዘመተ፡፡ ሰናክሬም የተመለከተው በእሱና በሠራዊቱ መካከል ያለውን ኃይልና ብዛት ነበር፡፡ ሕዝቅያስ ግን ወደ አምላኩ ጸለየ፡፡ "ኃይልና ማዳን የአንተ ነው፡፡ ጠላትን በአንተ ማሸነፍ እችላለሁ" አለ [94]፡፡ እንደ ቅጠል የበዛው የሰናክሬም ሠራዊት ፍሬ አልባ ኾነ፡፡ ፍሬ የአንድ ዛፍ ወይም ተክል ውጤት ነው፡፡ ለሌላው የሚያበረክተው የማንነቱ መገለጫ ነው፡፡ ካላፈራ ግን የመቆረጥ ዕድሉ የሰፋ ይኾናል፡፡ ይህ ሠሙ ነው፡፡

ወርቁ ግን የሮማ ሠራዊት በትምክህት በኃይል ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለመያዝ ሞከሩ፡፡ በጠዋት ለምልሞ በዝቶ የታየው ሠራዊት በጠዋት ምድሪቱን አልብሷት ነበር፡፡ ምኒልክ ወደ ፈጣሪው በመጸለዩ እግዚአብሔር ኃይል ኾነው፡፡ የሮማ ሠራዊት በቅጠል ብቻ ቀረ፣ የድል ፍሬ አልተገኘበትም፤ ምክንያቱም በምኒልክ ጦር በኋላ ፍሬው ረግፏልና፡፡ የሮማውያን ክብርና ዝና በኢትዮጵያውያን ተተካ፡፡

**ቅኔ ፲. መወድስ**

በሕፅነ ምኒልክ ይርፍቅ ሰማዕተ ልዕልና
ወበሕፅነ ሰማዕት ይትሐወስ አሠረ ምኒልክ ላእክ
እስመ እምሮምያ ፈተት አድባረ ድንጋይ ወሀውክ
ምኒልክ ንጉሠ አድኅኖ ዘኢዮር መልአክ፡፡

[94] 2ኛ ነገ 19፤14፥35

ወእግረ ምኒልክ ኢይትሀወክ

እስመ በቅድሜሁ የሐውር ጸያሔ ፍኖት ወልደ አምላክ

ቡርክትሂ ገነተ ጽጌ እስመ ውእቱ ቡሩክ፡፡

ዓለመ ምኒልክ ቀዳማዊ ዘይመጽእ ምኒልክ

ወሎቱ ሶርያ ትሰግድ ወታስተበርክ፡፡

በጽባሕ እስመ ቀርበ ሙስና ሮምያ መሥዋዕተ ሠርክ [95]፡፡

**ትርጕም፡-** ከፍ ከፍ ማለት ሰማዕት በምኒልክ አጠገብ ይቀመጥ፡፡ በሰማዕት አጠገብም የአገልጋይ ምኒልክ ዱካ ይንቀሳቀስ፡፡ የኢዮር መልአክ የማዳን ንጉሥ ምኒልክ የድንጋጤና የሁከት ተራራን ከሮም ቀርቧልና የምኒልክ እግርም አይታወክም፡፡ የአምላክ ልጅ መንገድ ጠራጊ በፊቱ ይኼዳልና፡፡ ገነተ ጽጌም የተባረከች ናት፤ እንደ ቀዳማዊው ምኒልክ ዓለም የሚመጣው ምኒልክ ቡሩክ ነውና ሶርያም ፈጽማ ትሰግድለታለች፡፡ በጠዋት የሮም ጥፋት የሰርክ መሥዋዕት ቀርቧልና ትሰግድለታለች፡፡

**ትንተና**

ባለ ቅኔው ቅዱስ ጊዮርጊስን ከምኒልክ፣ ምኒልክን ከቅዱስ ጊዮርጊስ ነጥሎ ማየት እንደማይቻል ይጠቁማል፡፡ በአጠገብ የሚቀመጥ የመጨረሻ ታማኝ ቀራቢ የኾነ ነው፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ ከንጉሡ አጠገብ በመኾኑ ንጉሡም በአጠገቡ ይንቀሳቀሳል፡፡ ምኒልክ ወደ ዐድዋ ዘመቻ በሚኼዱበት ጊዜ ቅዱስ ጊዮርጊስን ይዘው ነበር፡፡ ለሮማውያን መደምሰስ ታላቁ ምስጢር ይህ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ንጉሥ ምኒልክ ለኢትዮጵያውያን የማዳን መልአክ ኾኖው ተመስለዋል፡፡ በሮማውያን ላይ ሽብርና ጥቃት ደረሰባቸው፡፡

ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ መንገድ ጠራጊ ወልደ አምላክ በፊቱ ስለሚኼድ ነው፡፡ መንገድ ጠራጊ የተባለው መጥምቁ ዮሐንስ ነው፡፡ የጌታ መንገድ ጠራጊ ኾኖ የኦሪትን ማለፍ የወንጌልን መቅረብ አስቀድሞ ተናግሯል፡፡ መንገድ ጠራጊ ቀጥሎ ላለ ተልእኮ መንገዱን ምቹ የሚያደርግ ፋና ወጊ ማለት ነው፡፡ ዮሐንስ ከክርስቶስ በፊት ተራራው ይቅና፤ ሰንከልካላውም ይስተካከል፤ ጎድጓዳው ይሙላ እያለ አስተምሯል፡፡ ይህ ለክርስቶስ ትምህርት ምቹ አድርጎታል፡፡ ንጉሥ ምኒልክም ጠላቶቹን ለማሸነፍ የቻለው እግዚአብሔር በፊቱ ስለሚኼድ ነው፡፡

[95] ጎሩይ 1918፡255 (የቅኔው ባለቤት መምህር ጽጌ)፡፡

ኢትዮጵያ ሀገረ እግዚአብሔር ስለኾነች እግዚአብሔር ለወራሪ አሳልፎ አይሰጣትም፡፡ እግዚአብሔር ከፊቷ ስለሚቀድም አሸናፊ ትኾናለች ይላል፡፡ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን የሚቀርበውን መሥዋዕት ያነሣል፡፡ መሥዋዕት ለኀጢአት ሥርየት፣ ለሀገር ሰላም፣ ለበረከት ለአምላክ የሚቀርብ ነው፡፡ መሥዋዕት የጸሎት ማሳረጊያ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ዕረፍት ይደረጋል፡፡ ምንም ሥራ አይሠራም ይህ መሥዋዕት የሠርክ ኾኖ ሳለ በጠዋት ቀረበ ይለናል የሰዓት መፋለስ ይታያል፤ ከሮማ ጥፋት ጋራም ተነጻጽሯል፡፡ የሮማ ጥፋት አንድ ቀን እንኳን ሳይውል በጠዋት ተከናወነ፡፡ ከዚያም ኢትዮጵያውያን ዕረፍት አገኙ፡፡ ይህም የምኒልክን ፖለቲካዊ ብቃት ያሳያል፡፡ ለዚህም ታሪክ መረጃ ነው፡፡ ምኒልክ የክተት ዐዋጅ ሲያውጁ በቆራጥነትና በፍጹማዊ የሀገር ፍቅር ነበር [96]፡፡

### 3.2.2 የዘውዲቱና የኃይለሥላሴ ፖለቲካዊ ሽኩቻ /እሰጣ-አገባ/

ቅኔ ፩. መወድስ

መልአከ ብሥራት ማቴዎስ ለንግሥተ ክብር

ዜነዋ ብሥራተ እንዘ ወርቀ ግፍዕ ትፈትል፡፡

ከመ እምኔሃ ይትወለድ ኃይለሥላሴ ልዑል፡፡

ዘይሥዕር መርገማ ለሔዋን በቀል፡፡

አመ ዲበ መንበር ይሰቀል፡፡

እስከነ ሚካኤል አርመመ ወተደመ ገብርኤል፡፡

ጠብለለቶሂ በልብሰ ወርቅ አስካለ ማርያም ድንግል

ለዘእንበለ ርኵስ ወለደቶ ኃይለ ሥላሴ አማኑኤል፡፡

አስከበቶ ዳግመ ውስተ ቤተ መንግሥት ጎል፡፡

እንዘ ይሰግዱ በቅድሜሁ መኳንንተ ዕበይ ኪሩቤል [97]፡፡

**ትርጒም፡-** የብሥራት መልአክ ማቴዎስ ለክብር ንግሥት ለዘውዲቱ የመገፋትን ወርቅ ስትፈትል ብሥራት ነገራት፡፡ ኃይለ ሥላሴ ልዑል ኢየሱስ ክርስቶስ ከእሷ እንደሚወለድ ነገራት፡፡ የሔዋንን መርገም በቀል ይሽር ዘንድ፡፡ በዙፋንም ላይ በተሰቀለ ጊዜ ሚካኤል ዝም እስከሚል፣ ገብርኤልም እስከሚደነቅ ድረስ አስካለ

---

[96] ባሕሩ፣ 2003፡85፣87

[97] ጎሩይ 1918፡36

ማርያም ድንግልም ንግሥት ዘውዲቱ ማርያም በወርቅ ልብስ ጠቀለለችው፤ ያለርኩሰት የወለደችው ኃይለ ሥላሴ አማኑኤልን ጠቀለለችው፡፡ ዳግመኛም በቤተ መንግሥት በረት ውስጥ አስተኛችው፡፡ ታላላቅ መኳንንት ኪሩቤል በፊቱ እየሰገዱ በቤተ መንግሥት በረት አስተኛችው፡፡

## ትንተና

በዚህ ቅኔ የኢየሱስ ክርስቶስ ከብሥራት እስከ ስቅለት ያለው ታሪካዊ ኺደት በሠምነት ተጠቅሷል፡፡ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ድንግል ማርያምን ሐርና ወርቅ ስትፈትል ኢየሱስ ክርስቶስ ከእሷ እንደሚወለድ ነግሯታል፡፡ እንዲሁም አማኑኤልን ያለመለወጥ መውለዷን፣ በጨርቅ ጠቅላላ በበረት ባስተኛችው ጊዜ መላእክት ሰግደውለታል፡፡ ተወልዶም የሔዋንን በደል ለመደምሰስ ሲሰቀል ሚካኤል ዝም ሲል ገብርኤል መደነቁ በማምጠቂያነት ቀርቧል፡፡

ወርቁ ደግሞ ንግሥት ዘውዲቱ ግፍ ደርሶባቸዋል፡፡ "ተገፍዖ እንዘ ትፈትል" ማለት ዘውዲቱን በወቅቱ የደረሰባቸውን የፖለቲካ ተጽዕኖ ያሳያል፡፡ ንግሥናው ለእሳቸው ሲገባ ለልጅ ልጁ ለኢያሱ ተሰጠባቸው፡፡ የትዳር ሕይወታቸውም ሲታይ እቴጌ ጣይቱ ለሥልጣን ሽሚያ ሲሉ ሥልጣኑ ከዘራቸው እንዳይወጣ በማሰብ በወንድሟ ልጅ ራስ ጉግሳና በዘውዲቱ መካከል ጋብቻ እንዲፈጸም አደረጉ፡፡ ይህም የዘውዲቱ ምርጫ አይመስልም፡፡ በአባታቸው እና በእንጀራ እናታቸው በደል ደርሶባቸዋል፡፡ አባታቸው ሥልጣኑን ለኢያሱ ተናዘዙ፡፡ ባለቅኔው ይህን መገፋትሽን ለማስወገድ ኃይለ ሥላሴ ይነግሣል፤ ንጹሕ ዘር የሰሎምን ዘር ኃይለ ሥላሴ በቤተ መንግሥት በዙፋን ይቀመጣል ይላል፡፡ የወርቅ ልብስ የተባለው ሥልጣን ነው፡፡ የሥልጣኑን መሸጋገር ያጠይቃል፡፡ በሥራው ወይም በአስተዳደሩ መኳንንቱ ይደነቃሉ ይላል፡፡ ለሥልጣኑ አክብሮት ይሰጣሉ ለማለት ነው፤ ምክንያቱም ሳይወዱ በግድ ለኃይለ ሥላሴ ካልተገዙ ቅጣት ይደርስባቸው ነበር፡፡ አንገዛም የሚሉትንም ዋጋቸውን ይሰጣቸዋል፡፡የዘውዲቱን በቀል ሽሯል ማለት ይህ ነው [98]፡፡

### ቅኔ ፬. መወድስ

አስካለ ማርያም ምክረ ኢያስሕቱኪ፣

ጠበብተ ሮምያ ወጽርዕ አምሳለ ብልጣሶር መዘክር፣

[98] ባሕሩ፥ 2003፥127

በከመ አስሐታ ለሔዋን አርዌ አርማጌዶን ደብር

ይትሀየድ መንግሥትኪ

በከመ መንግሥቱ ለብልጣሶር ገብር፡፡

ከመ መንግሥተ ሮብዓም ለሳምር፡፡

ለምድረ አግዓዚ ርስትኪ እስመ ተካፈልዋ ፀር፡፡

አንተሰ ኃይለ ሥላሴ ተረፈ ኢዮስያስ በዡር፡፡

ንቃሕ እምንዋም ከመ ኅዳገ ወይን ላእከ ጌዶር፡፡

ወአመ ተማከሩ ብከ ሕዝበ አኪጦፌል በትር፡፡

ከመ ጸበለ ምድር ዘነፋስ ምክሮሙ ይዘርዝር [99]፡፡

**ትርጕም፡-**አስካለ ማርያም (ንግሥት ዘውዲቱ) በምክር እንዳያስቱሽ በብልጣሶር መታሰቢያ አምሳል የሮምና የግሪክ ፈላስፋዎች እንዳያስቱሽ የፍርድ ቀን አውሬ ተራራ ሔዋንን እንዳሳታት፡፡ መንግሥትሽ ይቀማ ዘንድ እንደብልጣሶር አገልጋይ መንግሥት እንደ ሳምር ንጉሥ እንደ ሮብዓም መንግሥት፡፡ የነፃነት ምድር ርስትሽን ጠላት ተከፋፍለዋታልና፡፡ ከአለቃ ኢዮስያስ የተረፍክ አንተ ኃይለ ሥላሴም ከእንቅልፍ ንቃ፡፡ የአኪጦፌል ሕዝብ በትር በተማከሩብህ ጊዜ በነፋስ ላይ እንዳለ የምድር አቧራ ምክራቸው ይበተን፡፡

## ትንተና

በዚህ ቅኔ በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪካዊ መነሻነት ከብሉይ ኪዳን ሦስት ነገሥታት ተጠቅሰዋል፡፡ነገሥታቱ በመጥፎም ይኹን በመልካም ያስመዘገቡት ታሪክ ነው፡፡ ብልጣሶር የማይገባውን የቤተ መቅደስ ንብረት የራሱ በማድረጉ በከለዳውያን ተገደለ፡፡ ሮብዓምም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሠራ፡፡ ጣዖትን በማምለክ የአባቶቹን ኀጢአት ደገመው [100]፡፡ በዚህም በሞት ተቀጥቷል፡፡ በነዚህ ነገሥታት ተመሳሳይ ቅጣት ይታያል፡፡ ኢዮስያስን ደግሞ በተቃራኒው በእግዚአብሔር ፊት ቅን ነገር አደረገ [101]፡፡ ኢዮስያስ ወደ ቀኝ ወደግራ ሳይል በመልካም አካኼድ ተጓዘ፡፡ የተበላሹ ነገሮችን አስተካከለ፡፡ ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን አነጻ፡፡ በዚህ የተነሣ ንጉሡ ተሐድሶ ይባላል፤ ይህ የምናብ ማምጠቂያው ነው፡፡ምስጢሩ ደግሞ በቅኔው ውስጥ የፖለቲካ ልዩነት መፈጠሩን ኹለት ቡድኖች

[99] ኅሩይ 1918፡364 (ባለቅኔው መምህር ወልደ ሚካኤል)፡፡
[100] 2ኛዜ.መዋ.12፥2
[101] 2ኛዜ.መዋ 34፥7

መኖራቸውን እንታዘባለን፡፡ ባለቅኔ ተዛማጅ የፖለቲካ ሥልት ይከተላሉ የሚባሉትን የዐፄ ኃይለ ሥላሴን ወገን የሚደግፍ ነው፡፡ ሐሳቡ ግን አንዱን አሞግሶ ሌላውን መስደብ እና መንቀፍ ሳይኾን አንድ ዐይነት አስተሳሰብ በኹለቱ ቡድኖች መሀል መኖር እንዳለበት የሚጠቁም ነው፡፡

ለዚህ ማሳያነት ሔዋን /የአሳች ምክርን መቀበል/፣ ብልጣሶር /የመንግሥትን መነጠቅ/፣ ሮብዓም /የመንግሥትን መከፈል/፣ አኪጠፌል /የመፈንቅለ መንግሥትን ምክር/ በሚገልጡ መንገድ በንግሥት ዘውዲቱ እና በአጋሮቻቸው ላይ ያለውን አጠቃላይ ሥጋት የሚገልጥ ነው፡፡ በሌላ መልኩ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ /በኢዮስያስ/ ኹሉን የሚያድስ ንጉሥ አምሳያ ስለሚቀረጽ በዚያ ወገን የሚያነሣው ምንም ዐይነት ሒስ የለም፡፡

ንግሥት ዘውዲቱ የሮማ ፈላስፎች እንዳያስቱሽ፤ በሔዋን የታየው የመሳሳት ታሪክ በአንቺም እንዳይደገም፤ በብልጣሶርና በሮብዓም መንግሥት የደረሰው የሥልጣን መነጠቅ በአንቺም እንዳይከሠት፤ ምክራቸውን አትስሚ፡፡ በፍርድ ቀን ማለት ሥልጣንን የሚነጥቁ ሀገርን የሚወሩ በሚመጡ ጊዜ እንደ ሔዋን እንዳያስቱሽ በአሠራርሽ መበርታት አለብሽ ማለት ነው፡፡ መንግሥትሽን ኃይለ ሥላሴ ይወስድብሻል፤ የሚል ሥጋት ነበር፡፡ ኃይለ ሥላሴም በኢዮስያስ መንገድ መኼድ አለብህ፤ ለጠላቶችህ አትተኛላቸው ተነሥ፤ መነሣትም ብቻ አይደለም፤ አትዘናጋ፡፡ እነሱ በአንተ ላይ ቢመክሩም ምክራቸው እንደምድር ትቢያ ይኾናል፡፡ የሚመክሩት ምክር ዋጋ የለውም፤ በምክራቸው አትጎዳም ይለዋል፡፡ ባለቅኔው ለንግሥት ዘውዲቱ የማስጠንቀቂያ ደውል ካሰማ በኋላ ኃይለ ሥላሴን ንጉሠ ተሐድሶ በማለት ከፍ ሲያደርግ ይታያል፡፡ ባለቅኔዎቹ ይህን ያህል ወደ ሀገሪቱ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ገብተው ሐሳብ ይሠነዝራሉ መልካም መስሎ ለታያቸው ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡

### 3.2.3 የኃይለ ሥላሴ ንግሥና

**ቅኔ ፩. መወድስ**

ኃይለ ሥላሴ ኢታንክር እመ እቤለከ፣

ርኢኩከ አንሰ ታሕተ ዕፀ ሐረር ዐባይ፡፡

እስመ ሀለወከ ትዕርግ መንበረ ምኒልክ ሰማይ፡

ወብከ ዘተሐቱ፣ በዘዕንቍ መንበረ አቡከ ምኒልክ ባሕርይ

መካነ ሥላሴ ትሴሰይ፣ ዘትረ ገብረ መድኅን መዓር

ስውጠ አንክሮ ሥርናይ፡፡

ሊተሰ ያሰጥመኒ ዕመቀ ፍሥሓ ቀላይ፡፡

እንዘ ፍትሐ ዚአከ እሰምዕ በዐውደ ምኒልክ ደብረ ምስካይ፡

እስመ ከመ የዋህ በግዕ ወከመ ተኩላ ዕቡይ

ኅቡረ ይትርአዩ ባዕል ወነዳይ [102]፡፡

**ትርጕም፡-** ኃይለ ሥላሴ! እኔ ከሐረር ዕንጨት በታች ዐየውህ ብዬ ብልህ አታድንቅ! ወደ ምኒልክ ዙፋን ሰማይ ትወጣ ዘንድ አለህና አታድንቅ፤ ባሕርይ በሚባል ዕንቍ ምሳሌ ባጌጠ በተሸለመ በምኒልክ በአባትህ ዙፋን ላይ እንደ ዕንቁ የምታበራበት ጊዜ አለና፡፡ ከዕፀ በለስ በታች ዐየሁህ ብልህ አታድንቅ፡ መካነ ሥላሴ ግን ስንዴ አድናቆት የተቀላቀለው የመዓር ግብረ መድኅንን ወለላ ትመገባለች ማለት ከገብረ መድኅን አንደበት እንደማር ወለላ ኾኖ የሚፈሰውን የወንጌል ትምህርት ትቀበላለች፡፡ እኔን ግን ጥልቅ የኾነ የደስታ ባሕር ያስጥመኛል፡፡ የተገፉ ሰዎች መጠጊያ የሚኾን በምኒልክ አደባባይ የአንተን ፍርድ ስሰማ ደስታ እንደ ባሕር ኾኖ ያስጥመኛል፣ደስ ይለኛል፡፡ የዋህ በግ እና እንደነጣቂ ተኩላ ባለጠጋና ደሀ አንድነት ይሰማራሉና፤ ያንተን ፍትሕ ስሰማ ደስ ይለኛል፡፡

**ትንተና**

የዚህ ቅኔ መሠረታዊ መነሻ በሐዲስ ኪዳን ዮሐ.1፤46 ጀምሮ ያለው ታሪክ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ናትናኤልን ክፋትና ተንኮል የሌለበት እውነተኛ ዕሥራኤላዊ እነኾ! አለ፡፡ ናትናኤልም ከወዴት ታውቀኛለህ? ሲለው፣ፊልጶስ ሳይጠራህ በበለስ ሥር አይቼሃለሁ፡፡ ዐየኹህ ስላልኩህ አታድንቅ፤ ገና ብዙ ተአምር ታያለህ ብሎታል፡፡ ይህን ያለው ሦስት ዓመት ከሦስት ወር የሚያደርገውን ተአምር ሲጠቁመው ነበር፡፡ ወደ ምስጢሩ ሲገባ ደግሞ ባለቅኔው የዐፄ ኃይለ ሥላሴን ለንጉሠ ነገሥትነት መታጨት ኢየሱስ ናትናኤልን ሳይጠራው አስቀድሞ በበለሱ ዛፍ በታች አይቼሃለኹ ያለውን ታሪክ በመውሰድ አስቀድሞ ገና በሐረርጌ መራሔ ሀገር ሳሉ ለዚህ ሹመት ተገቢ መኾናቸውን ያመለክታል፡፡

---

[102] ኅሩይ 1918፡283 (የቅኔው ባለቤት አርአያ ሥላሴ ወረታ)፡፡

ቅኔው የቀረበው ኃይለ ሥላሴ የአባታቸው የልዑል ራስ መኮንን ስም እንዳይጠፋ ብለው በሐረር ጋራ ሙለታ ደጃዝማች ተፈሪ ተብለው በተሾሙ ጊዜ ነው፡፡ ልጅ ኢያሱ በደጃዝማች ተፈሪ መኮንን ላይ የነበራቸው አመለካከት በጎ አልነበረም፡፡ ልጅ ኢያሱ ተፈሪን ለማጥፋት ጉድጓድ ይምሱ ነበር፡፡ ባገኙት አጋጣሚ ኹሉ የግድያ ሙከራ ለማድረግ ወደ ኋላ አይሉም ነበር፡፡ ይኹን እንጂ አልተሳካላቸውም፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ "በዚያን ጊዜ በግና ተኩላ በአንድነት ይሰማራሉ" የሚል አለ[103]፡፡ በእርሱ መሾም ዙፋኑ እንዲያበራ፤ በሚሰጠው ፍርድ የተነሣ ተኩላ እና በግ ዐብረው የሚሰማሩ አድርጎ የሚያቀርብ ቅኔ ነው፡፡ አንድም ልጅ ኢያሱን እንደ ተኩላ፣ ደጃዝማች ተፈሪን እንደ የዋህ በግ፣ እንደ ድሀ ልጅ መስለው የተቀኙት የልጅ ኢያሱን በተፈሪ ላይ ተደጋጋሚ ዛቻ በማየት ነው፡፡ ተባርዮ የማያስቀር እግዚአብሔር ግን ታሪክን ለወጠ፡፡ ደጃዝማች ተፈሪ ሥልጣን ሲያገኙ፣ ልጅ ኢያሱ ግን ታሰሩ፡፡ ከዚያ ደጃዝማች ተፈሪ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተብለው ነገሡ፡፡ ይህ እንግዲህ የእግዚአብሔር ሥራ ታላቅ በመኾኑ ነው፡፡ ሌላው ኃይለ ሥላሴና ናትናኤል በአስተማስሎ ቀርበዋል፡፡ናትናኤል ተንኮል የሌለበት እውነተኛ ዕሥራኤላዊ እንደተባለ ኹሉ ኃይለ ሥላሴም በአመራሩ ፊት ዐይቶ አያዳላም፤ በእውነት ይፈርዳል፡፡ ፍርዱ ቀጥተኛ ናት፡፡ በእሱ ዘንድ ደሀና ሀብታም አይለያዩም በማለት ባለቅኔው በቅኔው አመስጥሮ ፖለቲካዊ አመለካከቱን ይገልጻል፡፡ ዐቢይ አትኩሮቱ ለመራሔ መንግሥቱ ቤተ ክህነታዊ ድጋፍን መስጠት፣ የእርሱ መልካም ነገሮች፣ ይመጣሉ ተብለው የሚታሰቡትን ተስፋዎች በመጠቃቀስ ማወደስ እና መስበክ ነው፡፡

**ቅኔ ፪. መወድስ**

ተፈሪ አባ ጠቅል ዮሐንስ ጸያሔ ፍኖት፡፡

ሰመዩከ ሕዝብ ነቢየ መንግሥት ልዑል፡፡

ለእመ ትብሎሙ አንተ ለሰብአ አውሮጳ በኃይል፡፡

ነስሑ ወእመኑ

እስመ ቀርበት ለሰብአ አውሮጳ ኢትዮጵያ ወንጌል፡፡

ወሙሴ አባ ጠቅል

[103] ኢሳ 11፥6

ይዕድው ሕዝብ ባሕረ ኤርትራ ዘትከፍል፥፤

ኤልያስሂ ጠቅል ተፈሪ ዘትኤዝዞ በቃል፡፡

ለአክዓብ ምክረ ልቡና ነቢያተ ሐሰት ከመይቅትል፡፡

ድኅረ መሥዋዕተ ፍቅር አቅረብከ ለነገሥተ ብዕል፡፡

በሠረገላ ነድ እስመ አዕረገ ሰማየ አውሮጳ መካነ ሣህል [104]፡፡

**ትርጒም፡-**የጠቅል አባት ተፈሪ መንገድ ጠራጊ ዮሐንስ! ሕዝቡ የመንግሥት ነቢይ ልዑል አለሁ፤ አንተ የአውሮጳን ሰዎች በኃይል ንስሓ ግቡ እመኑ ቀርባለችና፡፡ የጠቅል አባት ሙሴም ሕዝቡ ይሻገሩ ዘንድ የኤርትራን ባሕር የምትከፍል፡፡ በቃል የምታዘው ጠቅል ተፈሪ ኤልያስም የሐሰት ነቢያትን ይገድል ዘንድ የልቡና ምክር አክዓብን በቃል የምታዘው ጠቅል ተፈሪ ኤልያስም ለባለጸጋ ነገሥታት የፍቅር መሥዕዋትን ካቀረብክ በኋላ በእሳት ሠረገላ ወደ አውሮጳ ሰማይ የይቅርታ ቦታ አርገሃልና፡፡

**ትንተና**

ይህ ቅኔ በጉራማይሌ መንገድ የቀረበ ነው፤ጉራማይሌ የተለያዩ ቋንቋዎችን በመቀየጥ ቅኔ የሚቀርብበት ሥልት ነው፡፡ በአንድ ቅኔ ውስጥ የግዕዝና የዐማርኛ፣ የግዕዝና የእንግሊዝኛ፣ የግዕዝና የትግርኛ፣ የግዕዝና የኦሮምኛ እንዲኹም የግዕዝና የዐረብኛ፣ የግዕዝና የዕብራይስጥ ቃላት ሊቀየጡ ይችላሉ፡፡ ለምን ይደረጋል ሲባል እዝነ ሰማዕያንን ለመሳብ፣ የባለቅውን ስፍሐ አእምሮ ለመጠቆም እንደኾነ ይታሰባል፡፡ ጉራማይሌነትም ለቅኔያቱ ውበት ስለሚሰጣቸው ተወዳጅ ይኾናሉ፡፡

መጥምቁ ዮሐንስ የኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ ጠራጊ ኾኖ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ እያለ ወንጌልን ማስተማሩ የቅኔው ላዕላይ ፋይዳ ኾኖ ተነግሯል፡፡ ካህናትና ሌዋውያን ነቢይ ነህ? ክርስቶስ ነህ? ይሉት ነበር [105]፡፡ ሌላው ሙሴ የኤርትራን ባሕር ከፍሎ ሕዝበ ዕሥራኤልን ማሻገሩ ነው፡፡ እንዲሁም ነቢዩ ኤልያስ በመሥዋዕቱ ፍርድ ሰጭነት ነቢያተ ሐሰትን እንዲገድል አክዓብን አዞ፣ በእሳት ሰረገላ ወደ ሰማይ አርጓል፡፡ ይህ እንግዲህ በማጠየቂያነት የቀረበው ነው፡፡ በወርቁ አባ ጠቅል ተፈሪ በብሉይ ኪዳን ሦስት ነቢያት ተመስለዋል፡፡ ነቢያቱ ኀላፊነታቸው ሕዝብን መምራትና ማስተማር ነበር፡፡

---

[104] ኀሩይ 1918፡346 (ባለቅኔው ሰሎሞን የኔነህ)

[105] ዮሐ1፤19-23

አባ ጠቅል ተፈሪም ሕዝብን በማገልገል ለሕዝቡ በማሰብ ኢትዮጵያ ዓለም አቀፋዊ ዕውቅና እንድታገኝ አስችሏልና፡፡

የኤርትራ ባሕር የተባለው የመከራው ዘመን ነው፡፡ በሕዝበ ዕሥራኤል አንጻር ኢትዮጵያውያን ባሕሩን መሻገራቸው መከራው ማለፉን ይጠቁማል፡፡ የሐሰት ነቢያት የተባሉትም ጠላቶቹ ናቸው፡፡ ኃይለ ሥላሴ ከተረጋጉ በኋላ የውጭ ግንኙነት መጀመራቸውን ነው፡፡ ከዚህ ላይ ኢትዮጵያ በወንጌል ተመስላለች፡፡ ወንጌል ብሥራት ዐዲስ ሕግ ናት፡፡ ኢትዮጵያም ከዐምስት ዓመቱ መከራ በኋላ ወደ ዐዲስ ምዕራፍ መሸጋገሯን ቅኔው ያመለክታል፡፡ አባ ጠቅል ተፈሪ ወደ ውጭ አገር ኼደው ስለ ሀገራቸው ስለመንግሥታቸው ሲነግሯቸው ኢትዮጵያን ከፍ ከፍ አደረጓት፣ ኢትዮጵያም ተቀባይነትን አገኘች፡፡ ምክንያቱም የኢትዮጵያን ነጻነት ለአውሮጳውያን ነግረዋቸዋልና፡፡ “መሥዋዕተ ፍቅር” ዓለም አቀፋዊ ግንኙነትን ይጠቁማል፡፡ አባ ጠቅል ተፈሪ በፍቅር ስለቀረቧቸው ከአውሮጳውያን ጋራ መልካም ግንኙነት ፈጠሩ፡፡ “ሠረገላ ነድ” የተባለው በአውሮፕላን (በጄት) መብረራቸውን የሚያጠይቅ ነው፡፡ በታሪክ እንደተገለጸው ኃይለ ሥላሴ ኢትዮጵያን በዓለም ፊት የዘመናዊነት ካባ ለማሰጠት ይጥሩ ነበር [106]፡፡

## 3.2.4 የኃይለ ሥላሴ አስተዳደራዊ በደል

ቅኔ ፩. መወድስ

*ኦ ሊቅነ ንጉሠ ነገሥት፣*

*ለመስቀልከ ንሰግድ ወለትንሣኤከ ቅድስት፣*

*ንሴብሕ ደርገ ለአንክሮ መድኅን ስቅለት*

*ይቤሉ እኂዞሙ*

*መስቀለ ዘቦቱ ተረክበ ድኅነት፣*

*ቀሳውስተ ሕግ መኳንንት፣*

*አምጣነ መስቀል ተገብረ ለአድኅኖ ዓለም መንግሥት፡፡*

*ተዋለጡሂ ወተባረዩ እምቅድመ ኵሉ ፍጥረት፣*

*በዕለት ዐርብ መንግሥትከ ብርሃነ መዓልት ወሌሊት፣*

[106] ባሕሩ 2003፡216

*ወአመ እምሉዓሌ ተነግፉ ከዋክብተ ክብር መከርት፣*

*ታሪክከ ወርኀ ውላጤ በደመ ኃያላን ተሜረየት* [107]፡፡

**ትርጒም፡-***የነገሥታት ንጉሥ አለቃችን ሆይ! ለመስቀልህ እንሰግዳለን፡፡ ልዩ ለኾነችው ትንሣኤህም የመዳን አድናቆት ስቅለትን ፈጽሞ እናመሰግናለን፡፡ የሕግ ቀሳውስት መኳንንት በእሱ ድኅነት የተገኘበት መስቀልን ይዘው ይላሉ፡፡ መንግሥት ዓለምን ለማዳን መስቀል ተደርጓልና፡፡ በዕለተ ዐርብ የቀንና የሌሊት ብርሃን መንግሥትህም ከፍጥረቱ ሁሉ ፊቱ ተለዋወጡ፤ ተፈራረቁም፡፡ የክብር ከዋክብት አማካሪዎችም ከከፍታቸው ረገፉ፡፡ የመለወጥ ጨረቃ ታሪክህ በኃያላን ደም ተነከረች፡፡*

**ትንተና**

በዚህ ቅኔ በማምጠቂያነት የቀረቡት የነገሥታት ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ እና በስቅለቱ የተፈጸሙት ታምራት ናቸው፡፡ ቀሳውስት በስቅለት ቀን እንደ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መስቀሉን ይዘው በዜማ ለመስቀልህ እንሰግዳለን፣ ለትንሣኤህም ምስጋና እናቀርባለን ይላሉ፤ በመስቀልህ ድኅነት ተደርጓልና፡፡ በዕለተ ዐርብ ጌታ ሲሰቀል ፀሐይ ጨልማለች፤ ከዋክብት ረግፈዋል፤ ጨረቃ ደም ኾናለች [108]፡፡

ምስጢሩ ግን የቤተ ክህነቱ ወገኖች ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በሚወስዷቸው እርምጃዎች ሙሉ በሙሉ ይስማማሉ ባንልም፡፡ ለቤተ መንግሥቱ ቀረብ ያሉት ምሁራን ግን ለንጉሣዊ ሥርዓቱ የራሳቸው ድጋፍ ነበራቸው፡፡ መስቀል አዳኝ፣ ስግደት የሚገባው ዓለምን የተቤዠ ነው የሚለውን አስተምህሮ ቀጥታ በመውሰድ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በሥልጣናቸው ላይ አመፅ እንደፈጸሙ ታስበው በሞት ፍርድ ያስገደሏቸውን ሰዎች ቅጣት ተገቢነት የሚደግፍ ነው፡፡ በደጃች በላይ የተወሰደው የመስቀል ቅጣት ዓለም ከዳነበት የክርስቶስ ሞት ጋራ በማነጻጸር ለዓለም ድኅነት የክርስቶስ ሞት ተገቢ የኾነውን ያህል ለሥርዓተ መንግሥቱ መጽናት የበላይ ሞት ተገቢ ነው የሚል ነው፡፡ በዕለተ ዐርብ በክርስቶስ ስቅለት የተደረጉ ተአምራት የከዋክብት መርገፍ ከመፈንቅለ መንግሥት መካሪዎች መውደቅ አንጻር በማቅረብ ለሥርዓተ መንግሥቱ መሪ ውዳሴን ያቀርባል፡፡ ከዚህ ጋራ በተያያዘ የጨረቃ ደም መኾን ከንጉሡ ታሪክ ጋራ በአስተማስሎ ቀርቧልና በኀያላን ደም ስለተነከረች ነው በማለት

---

[107] ዓለማየሁ 1967፡102

[108] ማቴ. 27፥45

የንጉሡን በሥልጣን ለመቆየት የተደረጉ ትግሎች ከመለኮታዊ ተአምር ጋራ በማጣቀስ አንክሮ ውዳሴን በማቅረብ ለሥርዓቱ ያለውን ድጋፍ ይገልጣል፡፡

ሲጠቃለል መኳንንቱ መስቀል ይዘው ለመስቀልህ እንሰግዳለን ይላሉ ማለት መኳንንቱ ተሰቅለዋል ኃይለ ሥላሴ መኳንንትን አሰቅለዋል፡፡ የእሳቸውን ሥልጣን ለማራዘም ተቃራኒ (የተለየ) አመለካከት የነበራቸውን ሀገር ወዳድ ጀግኖች በስቅላት ቀጥተዋቸዋል፡፡ በሕዝብ ፊት ይህን ያየህ ተቀጣ ዐይነት ሰቀሏቸው፡፡ አማካሪዎች ኹሉ በሞት ረገፉ፡፡ በዚህ ጊዜ የኃይለ ሥላሴ ታሪክ በመኳንንቱ ደም ተበላሸ ማለት በሕዝብ ዘንድ ጥላቻን አስከተለ ይላል፡፡ ይህ ጥበብ ረቂቅ የኾነውን የንጉሡን በደል በውበቱ ልሂቅነት ጆሮ ያለው ይስማ ዐይነት መልእክት ሲያስተላልፍ ይስተዋላል፡፡ የቅኔ ውበቱ አንዱ በጥበቡ እያዋዙ ባለ ጉዳዩን መሸንቆጡ ነው፡፡ ኃይለ ሥላሴ በኢየሱስ ክርስቶስ ሲመሰሉ መኳንንቱ ደግሞ በቀሳውስት ተመስለዋል፡፡ መስቀል ኅብር ነው፡፡ በቅኔው ላይ የታየው የአመሳሰል ሥልት ፍልስፍናውን ይበል ያሰኘዋል፡፡ ታሪክ እንደሚያስረዳው ኃይለ ሥላሴ በላይ ዘለቀንና መንግሥቱ ንዋይን በአደባባይ እንዲሰቀሉ አድርገዋል [109]፡፡

### ቅኔ ፪. መወድስ

አንቀጸ አባግዕ ፍትሕ ለእመ ጠፍአኒ፣

በመንፈቀ ሌሊት ተንሣእኩ ወለፍትሐ ነገሥት ኃሠሥክዎ፣

በማኅደሩ ለሰብእ ወኢረከብክዎ፣

እስመ በነቢያት ከመተነግረ፣

በጊዜነ እምፍቅረ ንዋይ ይመውት ሀለዎ፣

ወበመቅበርተ ጽድቅ ኅልያን

ልዑላን ሰብእ ይቀብርዎ ሕያዎ፡፡

ነዳያንሂ ሰብአ ኑባሬ እለ አብዝኑ ለብዎ፡፡

ለምውት ፍትሐ ብሔር በክላህ ኢላህውዎ፣

ወጊዜ ዐመፃ መቅበርት ከመ ይደልዎ፣

[109] ባሕሩ 2003፡221፣224

አምጣነ ሥዩማን መኳንንት ቀተልዎ ወቀበርዎ [110]፡፡

**ትርጒም፡-** የበጎች በር ፍትሕ (ፍርድ) በጠፋኝ ጊዜ በመንፈቀ ሌሊት ተነሣሁ፡፡ ፍትሐ ነገሥትንም ፈለኩት፡፡ በሰዎች መኖሪያም አላገኘሁትም፡፡ በነቢያት እንደተነገረ በጊዜያችን በገንዘብ መውደድ ይሞት ዘንድ አለውና፡፡ በእውነት ቀባሪዎች ከፍ ከፍ ያሉ (ባለሥልጣናት/ ሰዎችም በሕይወት እያለ ይቀብሩታል፡፡ ማስተዋልን ያበዙ የመቀመጥ ሰዎች ነዳያንም ለሚች ፍትሐ ብሔር በጨኸት አላላቀሱለትም፡፡ በበደል ጊዜም /እውነት በሌለበት ዘመን) ቀባሪ ይገባው ዘንድ አላለቀሱለትም፡፡ሹማምንት መኳንንት ገድለውታልና ቀብረውታልም፡፡

## ትንተና

በዓለማችን ሀብት ዝና ሥልጣን አለን የሚሉ ሰዎች ለተለያየ ጥቅም በመታለል አንዱን ሲገድሉ ሌላውን ሲያድኑ ይስተዋላሉ፡፡ ሰውን በሕይወት እያለ ከጨዋታ ውጭ እያደረጉ በቁሙ ሲቀብሩት ይታያሉ፡፡ ይህን የተመለከቱ ነዳያን በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚኖሩት ደግሞ በግፍ የተሰቃየው ሰው ሲሞት አያለቅሱም፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰው በዚህ ምድር ሥቃይ ሲበዛበት እንኳን ሞቶ ተገላገለው ይባላል፡፡ በሕይወት እያለ ያላገኘውን ዕረፍት በሞቱ እንዳገኘ ተቆጥሮ ይወራለታል፡፡ ይህ እንግዲህ የሠሙ ኅዝ መኾኑ ነው፡፡

የወርቁ አመስጥሮ ደግሞ እውነተኛ ፍርድ ጠፋ፤ በፍትሐ ነገሥት የተጻፈውን አይጠቀሙበትም የትንቢት ፍጻሜ ስለኾነ እውነት በገንዘብ ተሸጠ፤ ሙሰኞች ሕያውን ቀበሩት፤ አይጠቀሙበትም፡፡ የተጻፈው ሕግ ለስም ብቻ ኾነ፡፡ ማኅበረሰቡም ለሚች ሕገ መንግሥት አላለቀሱለትም ሲል እያወቁ ዝም አሉ፤ መናገር አልቻሉም በስምንተኛው ሺህ ምን እውነት አለ? እያሉ ከማጕረምረም ውጪ አልተናገሩም፡፡ የባለሥልጣኑን ሥራ እያወቁ በእውነት እንደማይፈርዱ እውነትን በመቅበር የተካኑ መኾናቸውን ተረዱ፡፡ ከመናገር ዝም ይሻላል፤ ብለው በሐሜት ብቻ ቀሩ፡፡ ከዚህ ላይ ባለ ቅኔው የወቅቱን ፖለቲካዊ ኹኔታ ይናገራል፡፡ በባለሥልጣናቱ ዘንድ ፍርድ እንደጠፋ ያሳያል፡፡ እነሱንም በጥበባዊ ብልሃቱ ተው ተመለሱ ያለፈው ይብቃ ይላቸዋል፡፡ የዘመኑን ብልሹ አስተዳደር በቅኔው አዋዝቶ ይጠቁማል፡፡

[110] ዓለማየሁ 1967፡109

**ቅኔ ፫. ሣህልከ**

አልብየ ምት ብሂሎትኪ፡፡

ኢትዮጵያ እሙን ወኢይትሔሰው ቃልኪ

ለመርዓዌ ሕግ እስከ ምጽአቱ፣ ምተኪ አምጣነ ኢኮነ ዘሀሎ ምስሌኪ[111]፡፡

**ትርጕም፡-** ኢትዮጵያ! ባል የለኝም ማለትሽ እውነት ነው፡፡ ቃልሽም አይታበልም የሕግ ሙሽራ እስከሚመጣበት ድረስ ካንቺ ጋር ያለው ባልሽ አይደለምና ባል የለኝም ማለትሽ እውነት ነው ቃልሽም አይታበልም፡፡

**ትንተና**

ይህ ቅኔ ታሪክ ጠቀስ ነው፡፡ኢየሱስ ክርስቶስ ከሳምራዊቷ ሴት ጋራ ያደረገው ንግግር ቃል በቃል ተጠቅሶበታል፡፡ በዋናነት ሐሳቡ ፈትነት እና ሙሽራነት ከሀገር ጉዳይ ጋራ አያይዞ ለመግለጽ እንደማሳያ ኾኖ አገልግሏል፡፡ኢየሱስ ክርስቶስ ውሀ ልትቀዳ የመጣችውን የሰማርያ ሴት አግኝቷት ሐሳብ ከተለዋወጡ በኋላ አምላክነቱን ለማስረዳት ኺደሽ ባልሽን ጠርተሽ ነይ አላት፡፡ ከዚያ አስቀድሞ ስድስት ባሎች ሞተውባታል፡፡ አኹን በቤት ያለውን የሸሸገች መስሏት የለኝም አለች፡፡ ክርስቶስ ግን የለኝም በማለትሽ እውነት ተናገርሽ፡፡ አኹን ካንቺ ጋራ ያለው ባልሽ አይደለም አላት፡፡ ብትኼድ ሞቶ አግኝታዋለች፡፡ ይህንኑ ለሰማርያ ሕዝብ ነግራ እንዲህ ያለ ነቢይ ውሀ ስቀዳ አግኝቼው እንዲህ ብሎኝ ተፈጸመብኝ አለቻቸው ዮሐ 4፡15-19፡፡ ለአንዲት ሴት መክበሪያዋ ባሏ ነው፡፡ ባል ከሌላት አትከብርም፡፡

በዚህ ቅኔ ውስጥ ሀገር እንደ ድንግል ሙሽራ፣ መራሔ መንግሥት እንደ ባል ቀርቧል፡፡ እንደልማዱ ሴት ልጅ በፈትነት ቢኾን የከንፈር ወዳጅ አታጣምና አብሯት ሲወጣእና ሲገባ ትከበራለች፡፡ የሙሽሪት ልብ ግን ሙሽራዋ /መራሔ መንግሥት/ እስካልመጣ ድረስ ባጣቆየ አብሯት የሚቆየው ኹሉ አካሏን እንጂ ልቧን አይገዛውም፡፡ ባል የለኝም ማለት በውስጧ የምትቀበለውን ያህል በአንደበቷ ትናገረዋለች፡፡

የሴት ገላ ከሀገር ጋራ መራሔ መንግሥት በባል በማቅረብ ቅኔው ኹሉም የአንድ ሀገር የፖለቲካ ሥርዓት ገላጭ የኾነ ማሳያን ተጠቅሟል፡፡ “አንጻር” በአንዳች አጋጣሚ መራሔ መንግሥት የኾነ ኹሉ የድንግል ኢትዮጵያ የልጅነት ውበት፣ ልምላሜእና ሙቀት

[111] እነኤልያስ 1992፡404 (ባለቅኔው ድማኅ ገነት ወርቅነህ የደብረ ኤልያስ አለቃ)፡፡

ቢፈልገውም በምንዝርእና በአለቃ ስሜት መንፈሱ ስለተያዘ አብሯት አይዘልቅም፡፡ ያው ለጊዜው ማስፈራሪያ ሀገር የሚባል የሴትነት ወጓን ያሟላላት ይኾናል፡፡ ሙሽራዋን በንጽሕና /በእምነት/ የማትችል ሙሽሪት ልቡና ቢኾን ጤናማ ነው ብሎ ለማሰብ ይከብዳል፡፡ የሙሽራው መምጫ ጊዜ አይታወቅም ዐይን ቢንከራተትም በጊዜ የተገደበ አይደለምእና ከንቱ ምኞት ይመስላል፡፡ ኢትዮጵያ በሳምራዊቷ ሴት ተመስላለች፡፡ ለሀገር ባሏ ክብሯ ንጉሥ ነውና፡፡ ንጉሡ ነገሥቷን በማጣቷ ዐዲሱ ሙሽራ እስኪመጣ ድረስ ከአንቺ ጋራ ያለው ባልሽ አይደለም ማለት ኃይለ ሥላሴ በድል አድራጊነት እስኪመለሱ ድረስ ለጊዜው የነበረው የኢጣልያ መንግሥት ለኢትዮጵያ ክብር ባል ንጉሥ አለመኾኑን ያጠይቃል፡፡ ባለቅኔው የኢጣልያ መንግሥት ከኢትዮጵያ እንደሚወጣ፤ ኃይለ ሥላሴ ወደመንበረ መንግሥታቸው እንደሚመለሱ ያመሰጥራል፡፡ በሌላ አባባል ቅኔው ሀገሪቱ በ1933 የተቀዳጀችውን ድል በትንቢት መልክ ይገልጸዋል፡፡

### 3.2.5 አብዮታዊ (ወታደራዊ) ሥርዓት

**ቅኔ ፩. መወድስ**

ለአዳም ወሔዋን ጥበባቲሁ፣

አበ ኀደርት ሀፍ ይብሎሙ ብዙኀ ወተባዝኁ፡፡

ወለኀደርት ሀፍ ዳግመ ሥቃያቲሁ ዘበዝኁ፣

ይቤሎ ማርክሲዝም፤

ብላዕ በሀፈ ገጽከ ወዕፁብ ዜናሁ፡፡

ለሙሴ ኃይለ ሥላሴ፤

ነቢየ ሐዊር ድኅሪት እስመ ጠፍአ መቃብሪሁ፡፡

ነዳያንሂ ኀደርት ሀፍ እለ ይትፌሥሑ፡፡

ለዝናም አብዮትነ እስመ ደምፀ እገሪሁ፡፡

ወበማርክሲዝም ተነግፈ ለዕፀ አድኅሮት ፍሬሁ፡፡

ለበለስ ፊውዳሊዝም አምጣነ አኮ መዋዕሊሁ፡፡

**ትርጒም፡-**የወዛደሮች አባት የኾነው ማርክስ እግዚአብሔር፣ አዳም እና ሔዋን ፍልስፍናዎችን ብዙ ተባዙ አላቸው፡፡ ዳግመኛም አዳም ወዛደርን ማርክሲዝም

እግዚአብሔር በፊት ወዝ ማለት/ወጥተህ ወርደህ ጥረህ ግረህ/ ብላ አለው፡፡ ወደ ኋላ የመሄድ የነቢይ ኃይለ ሥላሴ ሙሴ ዜናም በጣም የሚያስደንቅ ነው፡፡ ምክንያቱም መቃብሩ ጠፍቷልና፡፡ ድሆች ወዛደሮችም አብዮታችን ዝናብ በብዛት ዘንቧልና የሚደሰቱ ናቸው፡፡ የአድኀሮት ዕፅ ፍሬም በማርክሲዝም በረዶ ረገፉ፡፡ ምክንያቱም የበለስ ፊውዳሊዝም ጊዜ አኹን አይደለምና ፍሬው ረገፈ፡፡

## ትንተና

ቅኔው በመጀመሪያ ደረጃ ሠሙ ሲታይ እግዚአብሔር አምላክ አዳምንና ሔዋንን ከፈጠረ በኋላ ብዙ ተባዙ ምድርን ሙሏት የሚል ትዕዛዝ ነገራቸው፡፡ ከዚያም በሠሩት በደል ምክንያት ወጥተህ ወርደህ በፊትህ ወዝ ብላ በማለት መርገማዊ መርዶውን አሰምቶታል፡፡ ይላል፡፡ ቀጥሎም እስከ አኹን ድረስ የሙሴ መቃብር አለመታወቁን ይገልጻል በመጨረሻም ጌታ የረገማትን በለስ በማንሳት የልምላሜ ጊዜዋ አለመኾኑን ይጠቅሳል፡፡ ይህ ኹሉ ማምጠቂያው መኾኑ ነው፡፡

ወርቁ ግን ባለቅኔዎች እንደሥርዓቱ የማሰብ፣ የማሰላሰል፣ ሐሳብን የመለወጥእና አብሮ ከዐዲሱ ሥርዓት ጋራ የመጓዝ ባህል አላቸው፡፡ የዚህ ስሜት የራስ ጥቅም መሠረት ያደረገ ብቻ ነው የሚል መደምደሚያ ላይ አያደርሰንም፡፡ ይልቁንም ለየዘመናቱ አስተሳሰብ እራስን ክፍት በማድረግ የዘመኑን ርዕዮተ አብዮታዊ ዕሳቤ በፍጥነት መቀበላቸውን አመላካች ነው፡፡ “በላብህ ድካም ብላ” ያለው ፊጣሪንእና ማርክስታዊ ርዕዮተ ዓለማዊ ዕሳቤን ያነጻጽራል፡፡ የሙሴ ነቢይነትእና አድኀራዊ ሥርዓት በማነጻጸር ያን ያህል ታዋቂ እንዳልኾነ ኹሉ የሙሴ መቃብር እንዳልታወቀ ኹሉ የአንድ'ነሪያን ሥርዓት ግብአተ መሬቱ መፈጸሙእና ፈጽሞ መጥፋቱን ያነሣል፡፡ አብዮታዊ ለውጥ ከክረምት ወቅት መግባት ጋራ በማነጻጸር በዚህም በሚገኘው ፍሬ የደሀዎች ደስታ መኾኑን ያበስራል፡፡ በክረምት ወቅት ልምላሜ የማይታይባቸው ቅጠላቸው ከሚረግፉ እይታዎች መሀል በለስን ከፊውዳሊዝም ጋራ በማነጻጸር በአብዮቱ ማግሥት የሥርዓቱን ውድመትና ውድቀት ይናገራል፡፡

የማርክስ አመለካከት ኹሉም የሥራውን ማግኘት አለበት፡፡ አንዱ በደከመበት ሌላው መጠቀም የለበትም የሚል ነው፡፡ ወዛደሮች የድካማቸውን ዋጋ ማግኘት አለባቸው ይላል፡፡ የኃይለ ሥላሴ መንግሥት እያበቀላት ነው፡፡ አብዮቱ ተተካ በዚህም የተጨቆኑ ላብ አደሮች ይደሰታሉ ምክንያቱም የፊውዳል ሥርዓት አልቆለታል፡፡ ጊዜው አይደለምና

ከአብዮቱ በፊት መሬት የመሬት ከበርቴዎች በተባሉ ጥቂት ሰዎች ተይዞ የጥቂቶች መጠቀሚያ ስትኾን፤ አብዛኞቹ ግን ጭሰኞች ኾነው መሬት አልባ አርሶ አደሮች ነበሩ፡፡ በኋላ ይህ ኹሉ ተለውጦ በተቃራኒው ሲኾን ይታያል፡፡ እንግዲህ የዚህን ቅኔ ጭብጣዊ ፋይዳ ስንመለከተው በወቅቱ የነበረውን ፖለቲካዊ አመለካከት የነጉሡን ከሥልጣን መወገድና የሥርዓቱን መደምሰስ በምትኩም እንዲመጣ የተፈለገው አብዮት መከሰቱን፤ በጭቆና የነበሩት ወዛደሮች እኩል ተጠቃሚ መኾናቸውን ያጠይቃል፡፡ ለዚህም ታሪክ ምስክር ነው [112]፡፡

**ቅኔ ፪. ማህልክ**

ኵሉ ትውልድ በበመካኑ፣

ለኢትዮጵያ ድንግል ግብረ ዚአሃ ይዜኑ፣

ድንግል ኢትዮጵያ፣

መንግሥተ ዘእንበለ ዘርዕ ወለደት አኮኑ፡፡

**ትርጕም፡-** ትውልድ ኹሉ በየቦታው የድንግል ኢትዮጵያን ሥራ

ያወራል ድንግል ኢትዮጵያ መንግሥትን ያለዘር ወልዳለችና፡፡

**ትንተና**

ለሠሙ ማምጠቂያው ቅድስት ድንግል ማርያም በትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ 7፤14 እንደተገለጸው ያለወንድ ዘር ኢየሱስ ክርስቶስን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ወልዳለች፡፡ ለወርቁ ኢትዮጵያ በድንግል ማርያም ተመስላለች፡፡ ድንግል ማርያም የሰማይና የምድር ንጉሥ አስገኝ እንደኾነች ኢትዮጵያም የምድራውያን ነገሥታት መገኛ ናትና፡፡ ኢትዮጵያ ያለ ዘር መንግሥትን ወለደች ማለት ለዐያሌ ዘመናት የሰሎሞን ሥርወ መንግሥት እየተባለ በዘር ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የኃይለሥላሴ መንግሥት በ1967 ዓ.ም ፈረሰ፡፡ በአንድ በኩል ስንመለከተው ታላቅ ድል ነው፤ ነገሥታቱ “የሰሎሞን ዘር ነን” በማለት ሥልጣን ከዘራቸው እንዳይፍልስ ዘብ አድርገው ተጠቅመውበታል፡፡የሰሎሞን ዘር ለመኾናቸው ትውልድ ይቆጠርላቸዋል ወይ? ለሚለው ጥያቄ መልሱ የራሳቸው የነገሥታቱ ነው፡፡ የዘውዳዊው ሥርዓት መገርሰስ ከድንግል ማርያም በድንግልና የመውለድ ተአምር ጋራ እንደማይተናነስ በንጽጽር ቀርቧል፡፡ሊቃውንቱ በወቅቱ የታዘቡትን አስገራሚ ጉዳይ በኪናዊ ብልኀት አመስጥረውታል፡፡ ቅኔው ኢትዮጵያ ንጉሣዊ ዘር በሌለው በደርግ

[112] ባሕሩ 2003፡ 254

መንግሥት መመራቷን ያጠይቃል፡፡ አይነኬ የነበረው ንጉሣዊ አገዛዝ አቅሙን አጣ፡፡ የደርግ መንግሥት ተተካ [113]፡፡

በጥቅሉ ቅኔያቱ ከዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት፣ እስከ ንግሥት ዘውዲቱ እና ተፈሪ መኮንን ሥልጣን ዘመን፣ የዐፄ ኃይለ ሥላሴ የሥልጣን ዘመን፣ የዐዲሱ አብዮታዊ እንቅስቃሴ የፖለቲካ ኺደት ምን መኾኑን የሚቃኙ ናቸው፡፡ በዚህም ኺደት ባለቅኔዎቹ ከመራሕያነ መንግሥት ጎን የሚቆሙ፣ እንደ እየወቅቱ ሐሳባቸውን የሚለዋውጡ እና የወቅቱን የፖለቲካ ሥርዓት የሚደግፉና የሚያሔሱ ናቸው፡፡

## 3.3 ሃይማኖታዊ ጉዳይ

ሃይማኖት የሚለውን ቃል ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ሲተረጒሙ "ሃይማኖት በቁሙ፣ ማመን፣ መታመን፣ እምነት፣ ጽኑ ተስፋ፣ የአምልኮት ባህል፣ በልብ በረቂቅ ሐሳብ የሚሳል" በማለት ገልጸውታል [114]:: ሃይማኖት የመንፈሳዊ እና ሥጋዊ ባህል የጋራ ግዛት ነው፡፡ በባሕርይው ግን ወደ መንፈሳዊ ሰብአዊ ሀብት የሚያደላ ነው፡፡ ከሰው ልጅ ተፈጥሮ ባሕርያት ጋራ ተያይዞ የሚከሠት ከፍ ያለ፣ ለዕሳቤ የጸነኑ ሐሳቦች የሚታሰቡበት ባህል ነው፡፡ በቅኔ ውስጥ አትኩሮ ተሰጥቶት በእምነት ሕይወት አስፈላጊነት፣ በሃይማኖት ዕውቀት ተቃርኖ፣ ለቤተ ሃይማኖት በሚደረጉ ውሳኔዎች የተለያዩ ቅኔዎች ተደርገዋል፡፡ የግዕዝ ቅኔ ከሚቀርብባቸው ጉዳዮች አንዱ ሃይማኖት ነው፡፡ለዚህም የሃይማኖቱ ዕውቀት አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ በተለያዩ ጊዜያት ሃይማኖቱን የሚቃረኑ ጉዳዮች ሲነሡ በቅኔያቱ ለመሞገት ጥልቅ የኾነ የሃይማኖት ዕውቀት ወሳኝ ነው፡፡መሠረታዊ የሃይማኖት ትምህርት ማወቅ ተቃራኒውን ክፍል በቅኔ መልስ ለመስጠት እውነቱን ከሐሰት ለመለየት ያስችለዋል፡፡

### 3.3.1 ሃይማኖት እንደዐይን

ቅኔ ፩ ዋዜማ

ለአብ ኢነጸርዎ

ምሉዓነ ዐይን ኪሩቤል እንዘ ቅሩባን እሙንቱ፣

አካሎሙ እስመ ይከድኑ በአክናፍ ስድስቱ፡፡

---

113 ባሕሩ 2003፡226፣227

114 መ.ሰ.ወ.መ.ቃ.ሐ. 1948፡369

እስጢፋኖስሰ ርኁቅ በጽርየተ አሚን መጽሔቱ፣

ነጸረ አበ ምስለ ክልዔቱ፣

እስመ ዐይኑ ሃይማኖት ውእቱ [115]፡፡

**ትርጕም፡-** ዐይንን የተሞሉ ኪሩቤል ቅርቦች ሲኾኑ አብን አላዩም፣

አካላቸውን በስድስት ክንፎች ይጋርዳሉና፡፡

የራቀ እስጢፋኖስ ግን በማመን/መስታዎቱ ጥራት

ከኹለቱ /ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ አብን ዐየ፣

ዐይኑ ሃይማኖት ነውና ፡፡

**ትንተና**

ከዚህ ላይ ቅኔው ሠሙ የሚያመለክተው አንዳንድ ሰዎች ጎላ ጎላ ያለ ዐይን እያላቸው ከቅርብ የማየት ችግር ይገጥማቸዋል፡፡ሌላው ግን መነጽር አድረጎ ከሩቅ ማየት መቻሉን ነው፡፡ባለቅኔው  የኪሩቤልን ለእግዚአብሔር ዙፋን መቅረብ እና የእስጢፋኖስን መራቅ አነጻጽሮ፣ ኪሩቤል ቅርብ ኾነው እግዚአብሔርን ማየት አለመቻላቸውን ጠቅሶ፤ የእስጢፋኖስን ማየት በተቃራኒው በመጥቀስ ቅኔውን አድርጓል፡፡ በዚህም ቅኔ ውስጥ ሃይማኖት ከዐይን ጋራ ተመስሏል እና የእይታው ኹሉ ምንጭ ነው፡፡ ለዐይን ትኩረት የሚሰጠውን ያህል ለሃይማኖታዊ ጉዳይም ትኩረት ይሰጠዋል፡፡ በዐይን ቀልድ የሌለውን ያህል በሃይማኖትም ቀልድ የለም፡፡ ዐይነቱ ግን ብዙ ፅንሰ ሐሳቦች የሚጠራ፣ ዐያሌ ሰብኣዊ ጉዳዮችን አምቆ በውስጡ የያዘ የኹለንተናዊ አካል  ብርሃን መኾኑን የሚጠቁም ነው፡፡

የቅኔው ታሪክ  ኪሩቤል መንበሩን ተሸክመው አብን ማየት አልቻሉም፤ እስጢፋኖስ ግን ሰማይ ተከፍቶ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን ማየት ችሏል፡፡ በሃይማኖቱ አስተምህሮ ኪሩቤል ዙፋኑን ተሸክመው ይታያሉ፤ ማየት ግን አልተፈቀደላቸውም፡፡ ፊታቸውን በክንፋቸው ይሸፍናሉ የሚል አስተምህሮ አለ፡፡ እስጢፋኖስ ደግሞ፣ አይሁድ ለኾኑ የክርስቶስን የሥጋዌ ትምህርት ሲነገራቸው አሻፈረን ብለው፣ በቃላት መደራደር ሲችሉ ድንጋይ ማንሣት ጀመሩ፡፡ የአቅም ውሱንነት ሲገጥማቸው የማፈር ይመስላል፣ ድንጋይ

---

[115] የሥ.ጥ.ቅ.1984፥287 (የቅኔው ባለቤት አለቃ ይርጉ)፡፡

እንሥተው በድንጋይ ሲወግሩት፣ ምስክር የመስማት ያህል ሰማይ ተከፍቶ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን ማየት ችሏል፣ በዚህ ጊዜ ከኪሩቤል መብለጡን ኪሩቤል ያላዩትን እሱ ማየቱን ለመግለጽ ነው፡፡ "እስመ ዐይኑ ሃይማኖት ውእቱ" ከዚህ ላይ የእስጢፋኖስ ዐይን እንደማንኛውም ዐይን አይደለም የተለየ ነው፡፡ ሃይማኖት የዐይንነቱን ስፍራ ሲወርስ እንመለከታለን፡፡ የእስጢፋኖስን ዐይን ከሌላው ልዩ የሚያደርገው ከዐይንነት በዘለለ ወደሃይማኖትነት መለወጡ ነው፡፡ በዐይን ብቻ ቢኾንማ ኖሮ፣ የዐጥቢያ ኮኮብ የመሰለ ስንት ዐይን አለ፡፡ ነገር ግን ሥላሴን ለማየት የተለየ የሃይማኖት ዐይን አስፈላጊ እንደኾነ የሚጠቁም ነው፡፡"እስጢፋኖስሰ ርኁቅ በጽርየተ አሚን መጽሔቱ" በሃይማኖት /በአጉሊ/ መነጽር ከሩቅ ኾኖ አብን ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ ተመለከተ፡፡ ሃይማኖቱ ዐይንም መነጽርም በመኾን ሲያገለግለው እንመለከታለን፡፡

### 3.3.2 ቅብዐት

**ቅኔ ፩ ሥላሴ**

ኢያድኀነ ንዴተ ሥጋ

ተዋሕዶተ ቃል ምስለ ሥጋነ፤

እመ ሐተትነ በልብ እንበለ ማሕየዊ ቅብዐት፡፡

ወኢይኩን በዐውደ ሮምያ በይነዝ ሁከት፡፡

ይክልኑ በእግር ተሐውሶ ኀበ ፍኖተ ላዕል ወታሕት፤

ነፍስ ዘአልቦ ሥጋ ምውት፤

ወጽልመተኑ ያሴስል እምዐይን ማኅቶት፤

ዘላዕሌሁ ኢሀለወ ዘይት [116]፡፡

**ትርጕም፦**ከሥጋችን ጋራ የቃል መዋሐድ

የሥጋን ችግር ባላዳነም ነበር፤

በልብ ብንመረምር ያለ አዳኝ ቅብዐት፤

በሮም ዐደባባይ በዚህ ነገር ብጥብጥ እንዳይኾን

---

[116] ኅሩይ፣ 1918፡183 (የቅኔው ባለቤት አራት ዐይና ጎሹ)፡፡

ነፍስ የተለየው ሥጋ በእግር በመንገድ ወደላይ ወደታች ማለት ይችላልን?

በላዩ ላይ ዘይት የሌለው መብራትስ ከዐይኑ ጨለማን ያስወግዳልን?፡፡

**ትንተና**

ሠሙ በጨለማ ያለ መብራት መንቀሳቀስ እንደሚከብድ፣ ነፍስ የተለየው ሥጋም በድን እንደኾነ፣ ዘይት የሌለው መብራትም ጨለማ ማስወገድ እንደማይችል ይጠቁማል፡፡ ወርቁ የቅብዐትን ሃይማኖታዊ አስተምህሮ የሚደግፍ ነው፡፡ ቅኔው የቅብዐትን ሃይማኖት በማሞገስ የቀረበ ነው፡፡ እንደ ሃይማኖቱ ትርክት ያለ መንፈስ ቅዱስ ቅብዐትነት ቃል ሥጋችንን መዋሐድ አያድነንም፡፡ ድኅነት ያገኘነው ክርስቶስ በቅብዐተ መንፈስ ቅዱስ ከከበረ በኋላ ነው ይላሉ፡፡ ነፍስ የተለየው ሥጋ ወደላይ ወደቻች መንቀሳቀስ እንደማይችል ከላይ ዘይት የሌለው ማብሪያ ጨለማን ማራቅ እንደማይችል፤ በማነጻጸር ቅብዐት የሕይወትን ጨለማ ለማስወገድ ወሳኝ ነው ይላል፡፡ የክርስቶስ ሰው መኾን ያለ መንፈስ ቅዱስ ቅብዐትነት ዋጋ የለውም ለማለት ነው፡፡ ከዚህ ላይ እንደ ቅብዐቶቹ ሃይማኖት ዕሳቤ ክርስቶስ ሰው የኾነው በቅብዐተ መንፈስ ቅዱስ ነው እንጂ በተዋሕዶ ብቻ አይደለም ይላሉ፡፡ ይህ እንግዲህ ባለቅኔዎች ቅኔውን በየጊዜው ለሃይማኖታዊ ስብከት ሲገለገሉበት እናያለን፤ ለእምነቱም ያላቸውን ተቆርቋሪነት ሲገልጹበት እንመለከታለን፡፡ ይህ በነገረ መለኮት አርቅቆት ላይ የሚመሠረት ቅኔ በሀገራችን ውስጥ ያለውን የቅብዐት እምነት ቀኖና የሚገልጽ ነው፡፡ እነዚህ ሊቃውንት ከአቻ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ሊቃውንት ጋራ በዕውቀት በሊቅነት ተመሳሳይ ናቸው፡፡ እጅግ አንቱ የሚባሉ ታዋቂ ሊቃውንት እንደ አራት ዐይና ጎሹ ጭምር የዚህ ቀኖና አራማጆች እንደኾኑ ይታወቃል፡፡ ሊቃውንቱ የየራሳቸው የነገረ መለኮት አስተምህሮ ዋና መኾኑን ለመግለጽ ቅኔያት ያደርጋሉ፡፡ ቅኔያትን እርስ በርስ ይላላካሉ፡፡ በዚህም ቅኔ ውስጥ ከነገረ መለኮት ዕውቀት ጋራ ተጣልፎ የቅባት እምነት አስተምህሮ ተገልጿል፡፡ እንደ ማሳያነትም "ማሕየዊ ቅባት፣ ሕያው ነፍስ እና ማኀቶት ዘይት" ተጠቅሰዋል፡፡ እነዚህ ማሳያዎች የቅባትን ሕይወት ሰጪነት፣ የሕያው ነፍስ ግብር፣ ዘይት ለቀንዲል ብርሃን ያለውን ጠቀሜታ የሚጠቅሱ ናቸው፡፡ በጥቅሉ የመለኮት ከሥጋ መዋሐድ ብቻ ድኅነት አያስገኝም፤ ማዳን የመንፈስ ቅዱስ ግብር ነው የሚሉ ናቸው፡፡

ከሃይማኖታዊ አስተምህሮ የተቃርኖ ዕሳቤ አንጻር የቅባትን እምነት ሕያውነት፣ በነፍስ ሕያውነት፣ በዘይት የብርሃን ምንጭነት አጉልተው የሚያነሡ ናቸው፤ ነፍስ ያለሥጋ፣ ዐይን

ያለመብራት፣ የመለኮት እና ሥጋ መዋሐድ ያለ መንፈስ ቅዱስ ዋጋ ቢስ መኾናቸውን የሚያጎሉ ናቸው፡፡ ስለዚህ በሮም አደባባይ ሁከት አይኹን አለ፡፡ ሮም የእውነተኛ ሃይማኖት ስፍራ ናት፡፡ አስተምህሮው እውነተኛ ነው እንጂ ሐሰተኛ አይደለም ለማለት ሮም ተጠቅሳለች፡፡

**ቅኔ ፪ ዋዜማ**

መንበረ ኪሩባዌ

ለእመ በቅብዐት ወረሰ ፍሬ ከርሥኪ ዕፁብ፤

ዘቤተ ድንጋሌ ማርያም ርግብ፤

እስመ ከማሁ ኵልነ ሱቱፋነ ቅብዐት ሕዝብ

እስፍንተ ያገምር መንበሩ ለአብ

ወእስፍንተ ይጸውር ኪሩብ [117]፡፡

**ትርጕም፡-** የኪሩብን ዙፋን

የሚያስደንቅ ሆድሽ ፍሬ በመቀባት ቢወርስ፣

የድንጋሌ ቤት ልጅ ማርያም ርግብ

ኹላችን እንደርሱው የቅባቱ ተሳታፊዎች ሕዝብ ነንና

የአብ ዙፋን ስንቱን ሰው ይችላል?

ኪሩብስ ስንቱን ይሸከማል? ፡፡

**ትንተና**

ቅኔው በቅብዐተ መንፈስ ቅዱስ ከበረ ለሚሉት ወገኖች ከተዋሕዶዎች የቀረበ መልስ ነው፡፡ በሃይማኖታዊ ቀኖና መለያየት በአብያተ ክርስቲያናት ታሪክ ረጅም ዕድሜ ያስቆጠረ ነው፡፡ ከዚህ ላይ ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ በቅበዐት ከበረ የምትሉ ከኾነ፣ ኹላችንም የዚህ ቅብዐት ተካፋዮች ነን ወልድን ከእኛ በምን ልትለዩት ነው? የአብ ዙፋን ስንቱን ይችላል፣ ኪሩቤልስ ስንቱን ይሸከማሉ? ከዚህ ላይ ባለቅኔው የአብ ዙፋን መጥበብ  የኪሩቤል መሸከም አሳዝኖት ሳይኾን፣ ኢየሱስ ክርስቶስን ተቀባ የምትሉ ከኾነ ኹሉም ክርስቲያን

---

117 ኅሩይ 1918፡148 (ቅኔው የዘታወስ ኃይሉ ጎንደር)፡፡

በዐርባ እና በሰማንያ ቀን ተጠምቆ፤ ሀብተ መንፈስ ቅዱስን አግኝቷል፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ወልድ በቅብዐት የከበረ ከኾነ ኹላችንም ከብረናል የክርስቶስንና የምዕመናን ቅብዐት መለየት ካልቻልክ፣ ልዩነቱን ማወቅ አለብህ እያለ በቅኔው ያስተምረዋል፤ ሃይማኖቱን ያፀናበታል፣ በፍጡርና በፈጣሪ መካከል ያለውን ልዩነት ማወቅ ይገባል፡፡ በወቅቱ በቅብዐትና በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት መካከል የጠበቀ ግጭትና ከፍተኛ አለመግባባት ነበር፡፡ ያኔ ብቻ ሳይኾን እስከ አኹን ድረስ፣ ሕዝብ ከሕዝብ ጋራ በማያውቀው ጉዳይ ያባቴና የእናቴ ሃይማኖት በማለት ብቻ፣ ደም ሲቃባ ይኖራል፡፡ “ሃይማኖቴ ግብዝ ነው አባቴ ታናሽ ነው” የሚል ስለማይኖር ይህን ጉዳይ ለማስጠበቅ ሲባል ጦርነቱ ይከፈታል፣ እርስ በርስ ይተላለቃል፡፡

ባለቅኔውም የራሱን ሃይማኖት /ኦርዶክስን/ ለማጽናት፣ በተጨባጭ ምሳሌ በራሱ በሕዝቡ፣ ምሳሌነት፣ ያስረዳል፡፡ ይህ ጉዳይ በሊቃውንቱ ዘንድ መተማመን እንዳይኖር አድርጓል፣ አንዱ አንዱን መጠርጠር ጀመረ፡፡ ሃይማኖት በመከፋፈሉ ምክንያት መንግሥት ከመንግሥት ሕዝብ ከሕዝብ ጋራ መጋጨት ጀመረ[118]፡፡ በዚያን ጊዜ የነበሩ ሊቃውንት ሃይማኖታቸውን የሚመሰክሩት በቅኔያቸው ነበር መናፍቃንንም በቅኔ ይገሥጿቸው ነበር[119]፡፡ ምክንያቱም ሊቃውንቱ ሐዘናቸውን እና ደስታቸውን የሚገልጹበት ዋና መግሪያቸው ቅኔ ስለነበር፣ የወቅቱ ክሥተት ሠናይም ኾነ እኩይ በቅኔው ሥግው ኾኖ ይስተዋላል፡፡

### ቅኔ ፫ መወድስ

ሃይማኖተ ቄርሎስ ኮነት ግማዳተ አብድ

ወኍልቄ ተመትሮ አብዝኀት ኀበ ኢህሎ ንጉሥ

ካህነ ደብረ ኤፍሬም ቅድመ እምዘመተራ ነአስ

ወአመ ኢዮርብዓም ለምሳሌ

በእደ ነቢይ ዘተሠጠት ልብስ፡፡

እምዝኒ ዘይብእስ

ወዘልቡና ያነድድ ኢትበሊ ኤዶምያስ

---

118 የኢ.ቤ.ክ.ታሪክ 1974፡67

119 የኢ.ቤ.ክ.ታሪክ 1974፡66

ተቀብዐ ቅብዐ ውላጤ ኅሩመ ተውላጥ ክርስቶስ፡፡

አምጣነ አኮ በተቀብዖቱ በኰረ ውሉዳ ለዮርዳኖስ፡፡

ወእንዘ ትትናገሪ ዘንተ በአትሕቶ ክሣድ ወርእስ፡

ከመ አነ ሰማዕኩኪ ኢይስማዕኪ ጳውሎስ [120]፡፡

**ትርጉም**፦የቁርሎስ ሃይማኖት የሰነፍ ዕራፌዎችን /ቁራጮችን/ኾነች፡፡

ንጉሥ ከሌለ ዘንድም የመቆረጥ ቁጥርን አበዛች፡፡

የኤፍሬም ተራራ ካህን አስቀድሞ ከቆረጣት ትንሽ አካልና

በኢዮርብዓም ጊዜ ለምሳሌ በነቢይ እጅ ከተቀደደች ልብስ

ይልቅ/የመቆረጥ ቁጥርን አበዛች፡፡/

ከሚብስም ልቡናንም ከሚያቃጥል ከዚህ ነገር ይልቅ/የተነሣ/

መለወጥን የተወ /ዕርም ያለ/ ክርስቶስ መለወጥ ቅባትን ተቀባ /አትበዪ፡፡/

በመቀባቱ የዮርዳኖስ ልጆች በኩር አልሆነምና /ለዮርዳኖስ ልጆች በኩር መሆኑ በመቀባቱ አይደለምና፡፡/

አንገትሽንና ራስሽን ዝቅ በማድረግ ይህን ስትናገሪም

እኔ እንደሰማሁሽ ጳውሎስ እንዳይሰማሽ፡፡

**ትንተና**

ባለቅኔው የቁርሎስ ሃይማኖት /ወልድ ዋሕድ፣ ሥግው ቃል/ በሚለው አሚነ መሠረት የቆመ ነው፡፡ ባለቅኔ በዘመኑ በነበረው ሃይማኖታዊ ልዩነት እና በዚያም ሳቢያ በተፈጠረው ምስቅልቅል ላይ ተመስርቶ ቅኔውን አድርጓል፡፡ የሰነፍ (የእብድ) እራፌዎችን ሰነፍ ልብሱን አይሰፋም፤ ቆራጣ ልብስ ሲጎትት ይኖራል፤ ይህም የስንፍና ምልክት ነው፡፡ ስንፍና የተቀዳደደ ልብስ ያስለብሳል፡፡ ከዚህ ላይ ያለውን ስንፍና ከሌላው የተለየ ያደርገዋል፤ ምክንያቱም የሃይማኖት ስንፍና ነውና፡፡ ከትክክለኛው ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ያፈነገጡት ማፈንገጣቸው አንዱ ስንፍና ሲኾን፤ ሌላው ደግሞ መቆራረጥ ሲባል ከግንዱ እየተለዩ ከቁርሎስ አስተምህሮ ተለይቶ የራስን ፍልስፍናዊ ሃይማኖት ማምጣት፤ በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ የሚያስወግር፤ ብሎም የሚያስወግዝ ነው፡፡ “ሰነፍ በልቡ

[120] ጎሩይ 1918፡91 (የቅኔው ባለቤት ሊቁ ክፍለ ዮሐንስ)፡፡

እግዚአብሔር የለም ይላል"[121]፡፡ መኖሩን ሃይማኖቱ ትክክል መኾኑን ተመራመሮ መጻሕፍትን አገላብጦ ከመረዳት ይልቅ በስንፍናው የተቆራረጠ ሃይማኖትን መያዝ ይፈልጋል፡፡ ይህ እንግዲህ በቅብዐተ መንፈስ ቅዱስ ከበረ ተለወጠ የሚሉትን ሰዎቸ ይገስጻል፤ ይመክራል፡፡ የክርስቶስ አምላክነት በተዋሕዶ ነው፡፡ አንገትንና ራስን ዝቅ በማድረግ ባዕድ ትምህርት የሚያስተምር ተነቅፏል፡፡ "ከመ አነ ሰማዕኩኪ ኢይስምአኪ ጳውሎስ" ማለት ጳውሎስ ማስተማር የማይገባው እንዳያስተምር ያወግዛል፡፡ ስለዚህ ጳውሎስ እንዳይሰማሽ አለ፡፡ ትክክለኛውን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት መመርምሮ ማወቅ ከስንፍ ይፈውሳል፤ ከዕራፌ ወደ ሙሉነት ያዘልቃል፡፡ አንገትን ደፍቶ በምንታዌ ከመናገር ወደአንቃዕድዎ ክሳድና ዋሕድነት /አንድነት/ ያመጣል፡፡ የቅብዐት ሃይማኖት ቁርጥራጪን አበዛች፤ በተለያዩ ታሪካዊ አጋጣሚዎች ሰውንም ኾነ ቁስን ከቆረጡ ሰዎች ይልቅ መቆረጥን አበዛች አለ የእነዚህ መቆረጥ የሥጋ ጉዳይ ነው፤ የሃይማኖት መቆረጥ ግን የመንፈስ /የነፍስ/ ነገር ነውና እንዲህ አለ፡፡አንድም የእምነቱን /የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን/ ተከታዮች ልቡና ለማነሣሣት ነው፡፡የማን እምነት እንዲህ ይከፋፈላል እኛ እያለን እንዲሉ፡፡

### 3.3.3 ኩትልክና

**ቅኔ ፩ ዘአምላኪየ**

ኮተሊክ ልብስ እንተ ጸጋሁ ለሰብእ፤

እንዘ ተላዊሁ እንድርያስ ቅብዕ፤

እስመ ፈጣሪሁ ለሮም ፈነዎ ለሰቢከ አፍርንጅ ወጽርዕ [122]፡፡

**ትርጕም፦** የሰዎች የጸጋ ልብስ ካቶሊክ፤

እንድርያስ ቅባት ተከታዩ ሲኾን፤

የሮም ፈጣሪ አውሮፓንና ግሪክን ለመስበክ ልኮታልና፡፡

---

[121] መዝ.53፡1

[122] አያሌው፣1953፡192

## ትንተና

ለሠሙ ሰው ጥሩ ልብስ ከለበሰ ያምርበታል፤ከልብሱ ጋራ ቅባት መቀባባት የበለጠ ውበትን ይጨምራል፡፡ "እስመ ልብሱ ለሥጋ ሞገሱ=ለሰው ክብሩ ልብሱ ነውና" የሚሉት አበው ለዚህ ነው፡፡

ካቶሊኮች ኹለት ባሕርይ የሚለውን ትምህርት ለመስበክ በኢትዮጵያ ይዘዋወሩ ነበር፡፡ ሰባኪዎቹም በቅኔው እንደገለጹት ኩትልክና ለሰዎች ጸጋ መኾኑን አስቀድመው ተናግረዋል፡፡ ከመነሻው ላይ ይህን ያሉት ሰማዕያኑን ለማለበም ይመስላል፡፡ የ"ክብር ልብስ" ነው ብለው ጀመሩ፡፡ ልብስ ለሰው ልጅ ሞገስ እንደኾነ የካቶሊክ ሃይማኖትም ለሰዎች መንፈሳዊ ክብር የሚሰጥ መኾኑ ተገልጿል፡፡ "የሮም ፈጣሪ" ማለት ሮም የካቶሊክ እምነት ተከታይ መኾኗን የሚያመለክት እና የካቶሊክ ሃይማኖት በሮም መጀመሩን የሚጠቁም ነው፡፡ ሰባኪዎቹ ሃይማኖቱን ለማስፋፋት በአውሮፓ እና በግሪክ ይላካሉ፡፡ ይህ እንግዲህ ካቶሊኮቹ ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋት ያደረጉትን ትግል ያሳያል፡፡ ካቶሊክ በልብስ ተመስሎ ቀርቧል፡፡ ቅኔው እንደሚያመለክተው የእኛ ሃይማኖት ለሰዎች ክብር የሚያስገኝ ነው፡፡ በእኛ ሃይማኖት የሚያምን የጸጋ ልብስ ይለብሳል ይላሉ፡፡ ባለቅኔው የካቶሊክን እምነት እና ቀኖና ታላቅነት ለመግለጽ በቅኔ አርቅቆት ውስጥ ኹለት ማሳያዎች ተጠቅሟል፡፡ እነዚህም ኮት (ኮት መላክ) እና ቅባት ናቸው፡፡

ከማዕረገ ሰብእ መገለጫዎች ውስጥ አንዱ አለባበስ ነው፡፡ አለባበስ ማኅበራዊ ደረጃ፣ ብዕል እና ጸጋ አመላካች ነው፡፡ በማኅበረሰቡ ዘንድ እምነትን መለወጥ እንዲያው እንደዋዛ የሚታይ ነገር አይደለም፡፡ እምነቱን የለወጠው ሰው ወይም የዚያ ሰው ልጅ እምነቱን እንደለወጠ የወሬ ጭምጭምታ ከተሰማ የሰውዬውን አለባበስ መሠረት በማድረግ በነገር ወጋ ማድረጉ የተለመደ ነው፡፡ "ልጅህ ኮት ልኳል" ልብስ የላከለት በማስመሰል እምነቱን መለወጡን እግረ መንገዳቸውን በመግለጽ ሰውዬውን በነገር ይነኩታል፡፡ ባለቅኔው ይህ በማኅበረሰብ ውስጥ በቃላት ስንጠቃ የተካኑትን የካህናትን አባባል ከስድብነት ወደ ሙገሳ በመውሰድ የሰው መከበሪያው እኮ ልብስ ነው፡፡ ሰው ያለ ልብስ ዕርቃኑን ቢቆም አያምርበትም፡፡ የአያ እገሌ ዘር መባል ሳይኾን ያማረ መልበስ፣ ወዘናን መጠበቅ፣ መቀባባት፣ ውበት፣ ደም-ግባት፣ ክብርና ሞገስ ያሰጣሉ በማለት አስቀድሞ ያነሣል፡፡ በቀጣይነት በእነዚህ ማሳያዎች ካቶሊክነት ልብሰ ጸጋ፣ ልብሰ ክብር እንጂ የሚታፈርበት ሃይማኖት አለመኾኑን ይገልጻል፡፡ ከኮቱ በተቃራኒ ያሉ መናኛ ልብሶች የኮቱን ክብር እና

ግርማ የሚያስተረጉሙ ናቸው፡፡ አለባበስ ወዘናን ከሚጠብቀው መቀባባት ጋራ እንደ ሚሠምር የካቶሊክ የእምነት አስተምህሮዎች ከቅባት እምነት አስተምሮ ጋራ ኩታገጠም መኾናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ቅባት እና ኮት የሚገኘው በጌትነት ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህም የሮም ፈጣሪ የላካቸው እንደኾኑ ተገልጠዋል፡፡

በሌላም ገጽታው እንድርያስ የሚባለው የካቶሊክ እምነት ሰባኪ የነበረው በዘይት በመመሰል የነበረውን ዕውቀት ገላጭ ነው፡፡ ሮም እና ጽርዕ፣ አውሮፓ መጠቀሳቸው እነዚህ ሦስቱ ሀገሮች የሀገር አውራዎች ናቸው፡፡ የጥበብ፣ የዕውቀት፣ የመንግሥት ሥርዓት የሥልጣኔ ምንጭ ናቸው፡፡ ይህ እምነት በእነዚህ ሀገሮች የተስፋፋ እምነት እንጂ እንዲሁ ተራ እምነት አይደለም ለማለት ተጠቅሰዋል፡፡ በተቃራኒ የካቶሊክ እምነት ዐዲስ መጤ ሃይማኖት አድርገው የሚናገሩትን፣ የሚያፍሩበትን ወገኖች የእምነቱን ታላቅነት ከተነሡት ሀገሮች ጋራ በማገናዘብ የሚያሳይ ዐጸፋ ምላሽን የሚከተል ቅኔ ነው፡፡ የራስን ሐሳብ ለማሥረጽ ቅኔ እስከ መጠቀም መድረሱን እንገነዘባለን፡፡

**ቅኔ ፪ ሥላሴ**

ንርአይ ተዋሕዶ በመጽሔተ ማርቆስ ወንጌላዊ

ወኢንበል ንሕነ ከመ ይቤሉ አሕባል።

መለኮት አኮ ዲበ ዕፅ ስቁል

በእደዊሁ ለዮሴፍ በሥጋ እንዘ በሰንዱናት ጥብሉል።

ወእንዘ በነፍስ ውስተ ሲዖል።

በብሂለ ቅዱስ ግንዙ ሥጋየ ዘይብል።

እስመ ኮነ ዘተሰብአ ቃል[123]።

**ትርጒም፡-**በወንጌላዊ ማርቆስ መስታወት ተዋሕዶን እንይ።

እኛም አሕዛብ እንደሚሉት አንልም

መለኮት በዕንጨት ላይ የተሰቀለ አይደለም

በዮሴፍ እጅ በሥጋ በሰንዱናት ሲጠቀለል

[123] አድማሱ 1963፡144 (ባለቅኔው አቶ የተሻ ወርቅ)፡፡

በነፍስም በሲዖል ውስጥ ሲኾን

ቅዱስ በማለት ሥጋዬን ገንዙ

ሰው የኾነ አምላክ ኾኗልና፡፡

**ትንተና**

በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት አስተምህሮ ወንጌላዊው ማርቆስ ትክክለኛውን የሃይማኖቱን አስተምህሮ የሰበከ ነው፡፡ ለዚህም ነው እስከንድርያ እናታችን፣ ማርቆስ አባታችን እየተባለ ሲነገር የኖረው፡፡ በሱ መስታወትነት ተዋሕዶን እንያት ማለት የማርቆስን ትምህርት እናስታውስ፡፡ በሃይማኖቱ አስተምህሮ መሠረት ክርስቶስ በሚሰቀልበት ጊዜ መለኮት አልተለየውም የሚል ነው፡፡ የዚህ ተቃራኒ ግን ክርስቶስ ሲሰቀል መለኮት ተለይቶት ነበር፤ ለዚህም ነው "አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ?" ያለው የሚል ሌላ ባዕድ ትምህርት አለ፡፡ በእነዚህም በኹለቱ መካከል ልዩነት ሲፈጠር ለማስታረቅ ወይም የኦርቶዶክስን አስተምህሮ ለማጽናት የተደረገ ቅኔ ነው፡፡ እንደሰነፎች አናስብ፤ መለኮት በመስቀል አልተሰቀለም፤ እንደሚሉት እንዳንስት፤ ዮሴፍ በሰንዱናት ሲገንዘው ነፍሱ በሲዖል ነበረች፤ በሚገንዙት ጊዜም ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያላችሁ ገንዙኝ አለ፤ ሰው የኾነ አምላክ ነውና። ለሃይማኖቱ ተከታዮች የማስረዳትና የማጽናት ጉዳይ ነው፡፡ የእምነቱ አራማጆች በተሳሳተ አመለካከት እንዳይወሰዱ፤ በጽሙና አስተውሉ፡፡ በመስቀልም በመቃብርም ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሐደው መኾኑን አስረጂዎችን መርምሩ፡፡ በመስቀል ላይ እያለ የተደረጉትን ተአምራት፣ በመግነዝ ወቅት ለምን ዝም ብላችሁ እንደሩቅ ብእሲ ትገንዙኛላችኹ? ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያላችሁ ገንዙኝ ብሎ መናገሩን ዐስቡ፡፡ በማርቆስ አስተምህሮ ተዋሕዶን እንያት፡፡ ተዋሕዶን ተመልከቷት፤ እያለ ተከታይዎቹን ያፅናናል፡፡

**ቅኔ ፫ ሣህልከ**

ሃይማኖተ ትምህር ኢናበውሓ፣

ለሮሜ ብእሲት እንተ ተሠውጠ ዲቤሃ ፣

ምንታዌ ዕፍረት ዘንስጥሮስ፣

ኢትመብል ላዕለ ዘቀደመ ጉባኤ ብእሲሃ [124]፡፡

ትርጕም፦ሃይማኖትን እንዲታስተምር አናሠለጥናትም

የንስጥሮስ ሽቱ ኹለትነትን የተርከፈከፈ ሮሜ ሴትን

በቀደመ ጉባኤ ባልዋ ላይም አትፈርድም፡፡

## ትንተና

ባለቅኔው የሮማን ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በሴት አምሳል በማቅረብ ኹለት ባሕርይ ማለቷን በተቀባችው ቅባት መስሎ፤ ጳውሎስ ሴት በጉባኤ አትሠልጥን ያለውን በመጥቀስ በቅኔ ይቀኛል፡፡ በሴት መስላ የተፈጥሮ አካል መሰብሰብ እና መቁረጥ የወንድነትን የበላይነት ሚና በመጥቀስ፣ ለሴትነት ግብር ማዳመጥን ብቻ በመስጠት የራሱን አሚነ መሠረት የበላይነት በቅኔ ውስጥ አንጸባርቋል፡፡ ለሠሙ አንዲት ሴት ኾን ብላ ሰውን ለመሳብ፣ ለማጥመድ "ለማሳት" ሽቱ ተቀባለች።ይህ ሽቱ ሌላ መዘዝ ስለሚያስከትል ትክክለኛ አልነበረም፡፡ ሴት እንድታስተምር የሃይማኖቱ ሥርዓት አይፈቅድም፡፡ በወንድም ላይ እንድትፈርድ አያሰናብትም፡፡ ይህ ሠማዊ ግላጼ ይምሰል እንጂ የሃይማኖት ጣጣ ነው፡፡ስለኾነም ወደወርቁ ለማለፍ ሠሙን መንካት ግድ ይላል፡፡በጳውሎስ መልእክት እንደተገለጸው ሴት የመማር እንጂ የማስተማር መብት አልተሰጣትም፤ ይለናል፡፡ ምክንያቱንም ሲገልጽ "አዳም ቀድሞ ተፈጠረ ሔዋን በኋላ ተፈጠረች አዳም አልበደለም፤ ሔዋን ሳተች እንጂ "ከዚህ የተነሣ እንዳታስተምር የሚለው ሕግ እንደጸደቀ ይገልጻል፡፡ይህ በሃይማኖቱ ዘንድ እስከ አኹን ድረስ ሥግው ኾኖ ይኖራል፡፡ሽቱ የተርከፈከፈች ሴት የሃይማኖት ትምህርት ላስተምር ብትል አይፈቀድላትም፡፡ ሮሜ የካቶሊክ ትምህርተ ሃይማኖት ተከታይ ናት፡፡ የንስጥሮስን የምንታዌ ትምህርት ሽቱ የተቀባች ሲል ነው፡፡ በንስጥሮስ ክልዔ ባሕርይ ትምህርት ያመነች በመኾኗ ለማስተማር አይፈቀድላትም፡፡ መጀመሪያ በጉባኤ ኬልቄዶን በ451 ተወግዛ ተለይታለችና[125]፡፡ በኋላ በጉባኤው ላይ መፍረድ አትችልም፡፡ ሮሜ የካቶሊክ ሃይማኖትን ምንታዌን እንድታስተምር አናሠለጥናትም፡፡ ባለቅኔው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን ለማስረጽ የምንታዌ ትምህርት የሚያስተምሩትን የመካላከል፤ ዘብ የመቆም ሥራ እየሠራ ነው፡፡ በኹለቱ ሃይማኖቶች መካከል የቀደመ ልዩነት መኖሩንና ልዩነቱ በጉባኤ መወሰኑን ያመለክታል።

---

124 አድማሱ 1963፡69 (የቅኔው ባለቤት መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ)፡፡

125 የቤ.ክ.ታ.በዓ. መ. 1978፡145

ያ ሽቱ የምንታዌ ትምህርት ኹኖ ይገኛል፡፡ሽቱው ትክክለኛ አለመኾኑ ሰውን ለማጥመድ መኾኑን ከዚህ ላይ ይገልጻል፡፡ "ኢናበውሓ" አኹን የተመቸ፡፡ ባዕድ ትምህርት የሚያስተምሩትን መከላከል፤ የሃይማኖቱ አስተማሪዎች ምርቱን ከእንክርዳዱ እየለዩ ማስተማር አለባቸው፡፡ የሌላም ሃይማኖት ሰርጎ እንዳይገባ መጠበቅ ግዴታቸው ነው፡፡ በጉባኤው ተወግዛ መለየቷ የተረሳልኝ መስሏት እንዳታስተምር ማድረግ፡፡ ምንታዌ ምንድነው? በክርስቶስ ተዋሕዶ ላይ መለኮት የመለኮትን ሥራ ይሠራል፤ ሥጋ የሥጋን ሥራ ይሠራል፤ ብሎ የሥራ ክፍፍል ማድረግ ነው፡፡ይህም የካቶሊካዊት እምነት አስተምህሮ ነው፡፡

**ቅኔ ፬ መወድስ**

ሮማዊ ንስጥሮስ ሐረገ ምንታዌ

በዐውደ ሮምያ ኢትሥጥጥ ወኢትክፍል በበክፍል

እንተአልቦቱ ርፍአት ባሕርየ አካል፡፡

በሰብእ ወመላእክት እወ ወአልቦ ኢይትበሀል ቃል

አምጣነ ይሰገድ በዋሕድና ዘበላዕለ ኪሩብ ሀለወ ወእንተ ነበረ በመስቀል፡፡

ለይኩንሂ ቅድመ ፈጣሪ በእንተ ማርያም ዘንብል

ከመ ኢይበሉነ ሰብአ ሮሜ አይቴኑመ ስመ ድንግል፣

ኀልፈተ ሰማይ ወምድር እስመ ይቀልል፣

እምትደቅ በኀቤነ ስብሐተ ማርያም ቃለ ወንጌል[126]፡፡

**ትርጉም፦**ሮማዊ ንስጥሮስ ሁለትነት ሐረግን በሮሜ አደባበይ አትቅደድ፤

በየክፍልም አትክፈል፡፡

በሰውና በመላእክት አዎ አይደለም ቃል አይባልም፡፡

በኪሩቤል ላይ ለተቀመጠውና በመስቀል ላይ ላለው በአንድነት ይሰገዳልና፡፡

ስለማርያም እያልን በፈጣሪ ፊትም ይሁን፤

የሮሜ ሰዎች የድንግል ስም የት ነው? እንዳይሉን፡፡

[126] አድማሱ 1963፡156 (ባለቅኔው መምህር ወልደ ጊዮርጊስ)፡፡

ሰማይ እና ምድር ቢያልፍ ይቀላልና

የወንጌል ቃል የማርያም ምስጋና በእኛ ዘንድ ከምትወድቅ፡፡

**ትንተና**

ይህ ቅኔ ከቀደሙ ቅኔያት ጋራ ተመሳሳይ በኾነ መልኩ በካቶሊክ አስተምህሮ ላይ የተሰነዘረ ነው፡፡ በዐዲስ ልብስ ባሕርይ አካል በማቅረብ መቅደድን በዚህም መደረት እንደማያስፈልግ በመግለጽ የሚቃወም ነው፡፡ "መክፈል እና መደረት" የሚለው ካቶሊካዊ የነገረ መለኮት አስተምህሮ ነው፡፡ በመስቀልና በኪሩቤል ላይ ለአንድ ማንነት በእኩል ይሰገዳል በማለት በአንድ አካል ኹለት ማንነት የለም የሚለውን የራሱ የቤተ ሃይማኖት ቀኖና አስቀድሞ ካነሣው ዐዲስ ልብስ ጋራ በማገናዘብ ሃይማኖታዊ አቋሙን በቅኔ ውስጥ አቅርቧል፡፡ ምንታዌ የሚለው ቃል በኦ.ዶ.ተ.ሃማኖት አስተምህሮ ውጉዝ ነው፣ይህን አስተሳሰብ የሚጠቀምም የውግዘቱ ተሳታፊ ነው፡፡ምንታዌ መከፋፈልን፣ መለያየትን ስለሚያስከትል "የምትለያይ መንግሥት አትጸናም" እንደተባለው በሃይማኖትም እንደዚያው ነው፡፡በመለያየት ምክንያት እኔ እነግሥ፣ እኔ እነግሥ ሃይማኖቶች ሲፋለሙ መንጋው ተጨፈለቀ፤ ደሙን ገበረ፤ በሃይማኖቱ ዘንድ በሞት የተሻለ ክብር ይገኛል ተብሎ ስለሚታሰብ፣ ወይም እንደሚገኝ አስቀድሞ ስለተሰበከ ኹሉም ሠራዊት እንደተሰለፈለት ሃይማኖት ደሙን ይገብራል፡፡ አዋጊዎቹ ግን ከዳር ቁመው ሲመለከቱ ይስተዋላል፡፡ እንግዲህ ይህ ኹሉ የምንታዌ ጣጣ ነው፡፡ ምንታዌ በፊደል አራት ሆሄያት ቢኾንም ከቁጥሩ ጋራ የማይመጣጠን በሚሊየን የሚቆጠሩ ሰዎችን የደም ምድር እንዲሆኑ አድርጓል፡፡

ከሊቅ እስከ ደቂቅ የማዋጋት ኃይል አለው፤ ገዳዩ ሲገድላቸው ፍርድ ቤት እንኳ አይጠይውም፡፡ ይህን ያህል ደም አፍስሶ አንድ ቀን ፍርድ ቤት ቁሞ አያውቅም፡፡ንስጥሮስ ምንታዌ ሐረግን በሮም አደባባይ አትከፋፍል፡፡ወጥ የኾነውን ባሕርየ መለኮት አትቅደድ፤አትከፈል፡፡የተከፍሎ ሐረግ ምንድነው? የተያያዘ የማይነጣጠል ነው፡፡ አንዱ ከአንዱ ከተለየ ይደርቃል፤ልምላሜ አይኖረውም፡፡ምንታዌ ኹለትነት በሐረጉ ላይ መድረቅን እንደሚያስከትል በእምነትም ሥጋንና መለኮትን ለያይቶ መመልከት ሐረጉን መከፋፈልና ማድረቅ ነው፡፡ አኹን በሥጋና በመለኮት መድረቅ ኑሮበት አይደለም፤ ንስጥሮስ ይቡሰ አእምሮ መኾኑን ለመግለጽ ነው፡፡ ወጥ የኾነ ነው አለ፤ በአካለ ሥጋና በባሕርየ መለኮት መለያየት እንደሌለ ሃይማኖቱ የሚሰብክ መኾኑን ለመግለጽ ነው፡፡

በኪሩቤል ላይ የተቀመጠው በመስቀል ላይ ያለው ነውና፡፡“ኢተስጥጥ ወኢትክፍል” ላለው ፤ በካቶሊካውያን ዘንድ ድንግል ማርያም ከፍተኛ የኾነ ክብር አላት፡፡ አንተ /ንስጥሮስ/ ከዚህ የማርያምን ስም ስታጠፋ የሮሜ ሰዎች /ካቶሊካውያን/ የድንግል ስም ክብር የት አለ? ይሉናል ማለትም በካቶሊካውያን ዘንድ ድንግል የምትከበር ከኾነ ያንተ የሐሰት ትምህርት ከምን የመጣ ነው? ድንግል ሰውን ወለደች እንጂ አምላክን አልወለደችም፤ትላለህ፡፡ የማርያምን ክብር ከምናሳጣስ ሰማይና ምድር ቢያልፍ ይቀላል፤ሰማይ ዙፋኑ ምድር የእግሩ መረገጫ ነው፡፡ እነዚህ ኹለቱ ቢያልፉ ይሻላል፤ ከተባለ ድንግል ማርያምን መንቀፍ እግዚብሔር ዙፋንና የእግር መረገጫ አይኑረው ማለት ነውና፡፡ ያ ዘመን በኢትዮጵያ የካቶሊክ እምነት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ላይ የተገዳደረበት ዘመን እንደነበር ጠቋሚ ነው፡፡ በተለይ ቅብዐት እና ፀጋ እስከ አኹን ድረስ ከኦርቶዶክስ ጋራ በመጨቃጨቅና ባለመግባባት ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶዎቹ በቅኔያቸው ሃይማኖታቸውን ይሰብካሉ፤ለትውልድ ያስተላልፋሉ፡፡

### 3.3.4 ሚመት ጽጽስና

ቅኔ ፩. መወድስ

ኃይለ ሥላሴ አዘዘ ከመ የሀብዋ

መጽሐፈ ኀጻጋ ለግብጽ፣ እለ ኪያሃ ጸዐሉ፡

ወዘእንበለ ወርቅ ይስተዩ ማየ ክህነቶሙ እሉ

በከመ ይቤ ባስልዮስ ኢሳይያስ፣

እስመ ኮነ ማየ ጽጽና ርኩበ ለኵሉ፣

ወአፍላገ ወንጌል ጳጳሳት፣ በኢትዮጵያ ወግብጽ፣

ቃላቲሆሙ አልዐሉ፡፡

ተመይጡሂ አበዊነ ዘአድያመ ግብጽ ዔሉ፣

ወርቅነ ጽጽስና ገብአተነ እንዘ ይብሉ፡፡

በኃይለ ሥላሴ አኮኑ እምቀደምቶሙ ኀየሉ፡፡

ወቦ ዘከፈሎሙ ነግደ መላእክት ይትቀበሉ [127]፡፡

**ትርጕም፡-** ኃይለ ሥላሴ አዘዘ ለግብጽ የፍቺ ደብዳቤዋን ይሰጧት ዘንድ (እንዲሰጧት) አዘዘ፡፡ እሷን የሰደቡበትን፣ የእነሱን ክህነት ውሃቸውን ያለወርቅ ይጠጣ ዘንድ ባስልዮስ ኢሳይያስ እንዳለ ጵጵስ ውሃ ለኹሉ የሚገኝ ኾኗልና፤ ይገኛልና የወንጌል ወንዞች ጳጳሳትም በኢትዮጵያና በግብፅ ቃላቸውን ከፍ አደረጉ (አሰሙ)፡፡ የግብጽን ክልል /አውራጃ/ የዞሩ አባቶቻችንም ተመለሱ፡፡ በኃይለ ሥላሴ ጵጵስና ወርቃችንን አገኘን እያሉ ተመለሱ ከእነሱ በፊት ከነበሩት ይልቅ በርትተዋልና መላእክትም በእንግድነት ይቀበሉ ዘንድ የከፈላቸው /ያደላቸው/ አሉ፣ ነበሩ ፡፡

**ትንተና**

ለሡሙ እንደሚታወቀው በዓለም አንዲት ሴት ከባሏ ጋራ በስምምነት በመግባባት የማትቀጥል ከኾነ የፍቺ ደብዳቤ ተሰጥቷት ትሰናበታለች፡፡ በባልና ሚስት መካከል ፍቺ ሲፈፀም የፍቺ ደብዳቤ የሚሰጠው ለሴቷ ነው፡፡ ለወርቁ ለግብጽ የፍቺ ደብዳቤዋ ተሰጣት፡፡ በኢትዮጵያና በግብጽ መካከል የጋብቻ ፍቺ ተደረገ፡፡ ግብጻውያን "ወሰብአ ኢትዮጵያሰ ኢይሚሙ ሊቀ እማእምራኒሆሙ፣ ኢትዮጵውያን ከሊቃውንቶቻቸው ጳጳሳት አይሹሙ" [128]፡፡ የሚለውን በመጥቀስ ኢትዮጵያ ከራሷ ልጆች ጳጳስ ብትሾም ከፈጣሪ መቅሰፍት እንደሚገጥማት አንድርገው ያስቡ ነበር፡፡ በዚህም የተነሣ ኢትዮጵያ ከ4ኛው እስከ 19ኛው ክ/ዘመን ድረስ በሃይማኖት ከምትመስላት ከግብጽ ጳጳስ ስታስመጣ ኖራለች፡፡ በኃይለ ሥላሴ ትእዛዝ ማለት በዘመነ ኃይለ ሥላሴ ኢትዮጵያ ከራሷ ልጆች ጳጳስ ሾመች፡፡ ኢሳይያስ ውሀ ለኹሉ ይገኛል ብሏል፡፡ ቅ/ጳውሎስም መላእክትን በእንግድነት ይቀበሉ ዘንድ ያደላቸው አሉ ይላል፡፡ ይህ እንግዲህ ማምጠቂያው ነው፡፡ የጵጵስና ማዕረግ የውሃን በኹሉ ቦታ መገኘት በአድናቆት ያነሣል፡፡ የወንዞች ሞላት እና የጳጳሳት መሾም በአንድ አንፃር በማቅረብ አነጻጽሯል፡፡

እንዲሁም ግብጽ በኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ጵጵስናን ለኢትዮጵያ አስረከበች፡፡ ምክንያቱም ጵጵስና ለግብጽ ብቻ ሳይኾን ለኹሉም ተገቢ ነውና "በከመ ይቤ ባስልዮስ" ማለት አቡነ ባስልዮስ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ኾነው ተሾሙ ማለት ነው፡፡ ጳጳሳት በኢትዮጵያና በግብጽ ድምፃቸውን አሰሙ ሲል ጵጵስና በግብጽ ብቻ ነበር፡፡ በኢትዮጵያም ታየ፤ ኢትዮጵያና ግብጽ ተመሳሳይ ኾኑ፡፡ በዘመኑ ጳጳስ እንዲላክ አማላጅ

[127] ይኄይስ 1960፡13 (የቅኔው ባለቤት መምህር ይኄይስ ወርቄ)፡፡
[128] ፍትሐ ነገሥት 1962፤30

ኾነው ወደ ግብጽ የሚላኩት አባቶች ብዙ መንከራተት ይደርስባቸው ነበር፡፡ አኹን ግን በደስታ ተመለሱ በኃይለ ሥላሴ ወርቃችን አገኘን ማለት ወርቅ ጵጵስና መኾኑ ነው፡፡ አንድም ለብዙ ዓመታት ኢትዮጵያውያን ከግብጽ ጳጳስ ለማምጣት የእጅ መንሻ ብዙ ወርቅ ይልኩ ስለ ነበር ያ መቅረቱን ለማጠየቅ ነው [129]፡፡

### ቅኔ ፪. መወድስ

ኃይለ ሥላሴ በፍትሕ (ዳግመ) እምድኅረ አግብኦ፣

ለሢመተ ክህነት አዳም ኀበ ዘትካት መንበሩ

ውእቱ ገብአ ኀበ ስብሐቲሁ ወክብሩ፤

ወአኀበረ ቀስመ ጵጵስና ምስለ ንግሥ ማዕረሩ፣

ወዐሳበ ግብጽ ኢ.ኀሠሠ፣ በይነ ማእረሩ ስብከት፣

አምጣነ ብዙኅ ገባሩ፤

ካህናትሂ ወመኳንንት በፍና ማዕርግ ኀብሩ፣

ኃይለ ሥላሴ አምጣነ ሖሩ፤

ወኢየሩሳሌም ሐዳስ ኢትዮጵያ ሀገሩ፣

ወርኀ ወፀሐየ እስመ ኢትፈቅድ ይትናጸሩ [130]፡፡

**ትርጒም፡-** ኃይለ ሥላሴ በፍርድ (ዳግመኛ) አዳም የክህነት ሹመትን ወደ ቀድመ ቦታው ከመለሰው በኋላ እሱ ወደ ምስጋናውና ክብሩ ገባ፡፡ ከንግሥ አዝመራው ጋራ ጵጵስና መልቀምንም አንድ አደረገ፡፡ ስለ አዝመራው ስብከት የግብጽን ምንደኞችም አልፈለገም፡፡ ሠራተኛው ብዙ ነውና ካህናትና መኳንንትም በሥልጣን መንገድ አንድ ኾኑ ከኃይለ ሥላሴ ጋር ሄደዋልና፡፡ዐዲሲቱ ኢየሩሳሌም ኢትዮጵያ አገሩም ፀሐይና ጨረቃ ይተያዩ ዘንድ አትወድምና፡፡

### ትንተና

የመጀመሪያው ሰው አዳም በፈጸመው ስህተት ከገነት ተባሮ ነበር፡፡ በኋላ ግን በጥፋቱ በመጸጸቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ቀደመ ቦታው ወደቀደመ ክብሩ መልሶታል፡፡ ኃይለ ሥላሴና ኢየሱስ ክርስቶስ፣ አዳምና ሹመት ምሳሌዎች ናቸው፡፡ ኃይለ ሥላሴ የጵጵስና

---

[129] የኢ.ቤ.ክ.ታሪክ 1974፡35

[130] ይኄይስ 1960፡12 (ባቅኔው መምህር ይኄይስ ወርቁ)፡፡

ሹመት ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጣ አደረገ፡፡ ኢትዮጵያ የሃይማኖት ነጻነት አገኘች፡፡ በሌላ ትሰበክ የነበረው በራሷ ልጆች መማር ጀመረች፡፡ "ገብአ ኅበ ስብሐቲሁ ወክብሩ" ማለት ኃይለ ሥላሴ ጵጵስና በማምጣቱ ልዩ ክብር አግኝቷል፡፡ ስሙ ከፍ ከፍ ብሏል፡፡ በዚህ ኹኔታ ኢትዮጵያን ከሰማያት ኢየሩሳሌም ጋራ በመመሰል ፀሐይ እና ጨረቃ ሳያስፈልጓት የምታበራ ከተማ አድርጎ በዐዲሱ ሥልጣን ጵጵስና የመጣው የተለየ ክብር በቅኔው ውስጥ በመግለጽ የራሱን አቋም አመልክቷል፡፡

ኢትዮጵያ ከግብጽ ተሹመው የሚመጡትን ኹሉም ባይኾኑ የተወሰኑት ምንደኞች ለመንጋው የማይጨነቁ በመኾናቸው አትፈልግም፡፡ ምክንያቱም የራሷ በቂ ምሁራን አሏትና፡፡ በዚህ ጊዜ ቤተ መንግሥትና ቤተ ክህነት በሥልጣን አንድ ኾኑ፡፡ ከዚያ በፊት ዓለማዊው እንጂ መንፈሳዊው ሥልጣን አልነበረምና ኢየሩሳሌም ማለት ሀገረ ሰላም ወፍቅር ማለት ነው፡፡ የኃይለ ሥላሴ ሀገር ኢትዮጵያም የፍቅር የሰላም ሀገር ስለኾነች ግብጽን ደጅ መጽናት አትፈልግም፡፡ በቅኔው ጸሐይና ጨረቃ ተጠቅሰዋል ጸሐይና ጨረቃ ተቃራኒ ናቸው፤ አንዱ ሲበራ አንዱ ይጠፋል፡፡ በአንድ ላይ እኩል ብርሃን አይሰጡም፡፡ ኢትዮጵያም የግብጽን ሡልጣኖችና ጳጳሳት አትሻም፡፡ ምክንያቱም ከዚህ መጥተው የሚያስተምሩ ባዕድ ትምህርት እንጂ የራሷን እምነት፣ ሥርዓትና ባህል አይደለምና፡፡

በጥቅሉ በነገረ ሃይማኖት ማመን፣ ምንፍቅናን፣ በሃይማኖት መከፋፈልን፣ የራስን ባህል እና ክብርን መጠበቅ ያለውን ጠቀሜታ ፣በዚህም ዙሪያ የነበሩ ስጣ ገባ እና ውጣ ውረዶችን፣ ምስቅልቅሎች በአግባቡ ለመረዳት ቅኔያት የራሳቸው አበርክቶት እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4.ማጠቃለያ

ይህ ጥናት እና ምርምር ከቤተ-መጻሕፍት ከየመጻሕፍቱ የተሰባሰቡትን ቅኔያት፣ ከማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሃይማኖታዊ ይዘት አንጻር ቀርቧል፡፡ በዋና ዐላማነት በቅኔያቱ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሃይማኖታዊ ፍካሬን ማቅረብ ይዞ ተነሥቷል፡፡ ይህን ጥናታዊ ምርምር በተሟላ መንገድ ለማካኼድ በዐይነታዊ የምርምር ዘዴ ውስጥ የሚነሡ ዐበይት የሥነ-ጽሑፍ ሥርዓቶች ተግባራዊ ኾነዋል፡፡ በጥናታዊ ሥራው ውስጥ የቀደምት ጥናቶች ውጤት እና ክፍተት በአግባቡ ተፈትሾ ቀርቧል፡፡ እንደ አንድ ዐቢይ ነጥብ የቅኔ ምንነት፣ ፅንሰ ሐሳብ፣ አጀማመር፣ የቅኔ ታሪክ፣ የቅኔ ዐይነቶች እና የቅኔ ኀዳናዎች ተነሥተው በጥልቀት ትንተና ተሰጥቶባቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በቀደምት ጥናቶች እንደ ክፍተት የሚታየውን የንድፈ ሐሳብ ማሕቀፍ ለማካተት ተሞክሯል፡፡ በዚህም ጥናት እና ምርምር ከትርጓሜ እና ከቅኔ ባህል ጋራ በተጣጣመ መልኩ የሚሠራው የሥነ ፍካሬ ንድፈ ሐሳብ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በዚህም የሥነ ፍካሬ ሥልት ውስጥ በቅኔ ባህል ውስጥ መታየት ያለባቸው ዐበይት እና ንኡሳን ፅሳቤዎች ቀርበው ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

በምዕራፍ ሦስት የጥናቱ ርእሰ ጉዳይ በአግባቡ ተነሥቶ በተሰበሰቡት መረጃዎች መሠረት ሰፊ ትንተና እና ፍካሬ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ ለትንተና የተመረጡ የቅኔያት ናሙና ከጉባኤ ቃና እስከ አሠረ ንጉሥ ያሉት ሲኾኑ ከተፈለጉበት ዐላማ አንጻር ተመርጠው ትርጓሜ እና ትንተና ቀርቦባቸዋል፡፡ በዚሁ ምዕራፍ በቅድሚያ ማኅበራዊ ጉዳዮች ተነሥተው በሰባት ንኡሳን ክፍሎች ተከፋፍለው ቀርበዋል፡፡ በዚህም ውስጥ የማኅበረሰብ ውጣ ውረድ፣ የሕይወት ገጠመኞች በቅኔያቱ ውስጥ የተወሡበት ኺደት በሰፊው ተዳሧል፡፡

በማኅበራዊ ጉዳዮች ሥር የማይነጠሉ ጥንድነት ያላቸው ምክር፣ ፍቅር፣ ጥላቻ፣ ሐዘን፣ ፍላጎት እና ምኞት እንደ አንኳር ነጥቦች ተነሥተው በእነርሱ ሥግው ኾኖ የተገለጠው የማኅበረሰቡ የኑሮ ዘይቤ እንደ አስፈላጊነቱ ተፈክሯል፡፡ ከማኅበራዊ ጉዳዮች መሀል በቅኔ ውስጥ የምናገኘው የማተኮሪያ ሐሳብ መሀል አንዱ ምክር ነው፡፡ ምክር ሰውን ለማረጋጋት፣ በባህሉ መሠረት ዝምታ እንዲመረጥ፣ ከጎረቤት ጋራ ተስማምቶ ለመኖር፣ በትዳር መሀል መግባባትን ለመፍጠር፣ የባህል ልማድ በማክበር መከናወኑ ተስተውሏል፡፡ ምክሩን

ለማጽኛነትም የእግዚአብሔር ስም እንደ አስፈላጊነቱ ተጠቅሷል፡፡ በዚህም ሥልታቸው ቅኔያቱ ማኅበራዊ ጉዳዩን በዋናነት የሚያነሡ፣ የባህሉን ልማድም የሚያጸኑ ናቸው፡፡

ሌላ በማኅበራዊ ጉዳይ ውስጥ የተነሣው ነጥብ ፍቅር ነው፡፡ በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ ከሚከሠቱ የማኅበራዊ ሕይወት ማጣፈጫዎች መሀል አንደኛው ነው፡፡ ጎረምሳው በጥምቀት በዓል ላይ የቀደመቺውን ነባር ጓደኛውን ሲተዋት፣ ሌላውን ሲያፈቅር፣ አንዱ በቀደመቺው ጓደኛው ፍቅር ተቃጥሎ ፀሓይ አይንካሽ ሲል ይታያል፡፡ ባለቅኔያቱ እነዚህን የስሜት፣ የውስጠት፣ የባህል ሰብአዊ ጣጣዎች ለሃይማኖቱ አስተምህሮ በሚመች መልኩ ለመግለጽ ማኅበራዊውን ጉዳይ ለሐሳብ ማጕያነት ተጠቅመውበታል፡፡

በማኅበራዊ ጉዳይ ውስጥ የሚነሣ ሌላኛው ጉዳይ ሐዘን ነው፡፡ ሐዘን በአንዳች አጋጣሚ የልብ ስብራት፣ የመንፈስ ድቀት መድረስን በሚመለከት ከሰው ልጅ አኗኗር የማይነጠል መኾኑ በቅኔያቱ ውስጥ ተገልጿል፡፡ በቀዳሚነት የተነሣው የሃይማኖት፣ የዕውቀት እና የባህል ማእከል የኾኑ ስፍራዎች ባልታሰበ አደጋ እና በውጪ ጠላት ሲወድሙ የሚፈጠር ነው፡፡ በቅኔ ውስጥ የባህል፣ የዕውቀት እና የሃይማኖት ማእከል የኾነችው ጎንደር በደርቡሾች በመወረሯ የደረሰውን የሐዘን ስሜት ባለቅኔው በቅኔ ውስጥ ድንቅ በኾነ የሠም እና ወርቅ አርቅቆት አቅርቦታል፡፡ ሌላኛው በማኅበራዊ ጉዳይ አርቅቆት ላይ የተነሣው አንኳር ነጥብ ፍላጎት ነው፡፡ ሰው ኾኖ በመፈጠር እና በመኖር ኺደት ውስጥ የሰው ልጅ ጉልቈ-መሳፍርት የሌሉት መሻቶች አሉት፡፡

የሰው ልጅ ከእነዚህ መሀል  እጅግ በጣም ጥቂት መሻቶቹ ብቻ ይፈጸሙለታል፡፡ የፍላጎት አለመሳካት ደግሞ የሐዘን ድባብ ይፈጥራል፡፡ አንዱ ልጅ ወልዶ ሚስት በማጣቱ ሲተክዝ፣ ሌላው ሚስት ኖሮት ልጅ ባለመውለዱ ያዝናል፡፡ በዚህም አጋጣሚ አንዳንድ ሰው "መሻቶቹ ኹሉ" እንደ ተሟሉለት ተሰምቶት የሚደሰት ይኖራል፡፡ በመሻት ደረጃ እንኳን በማኅበረሰቡ ውስጥ ሞት እና መቃብር ፈልገው እንኳን የሚያጡ መኖራቸው ተጠቅሷል፡፡ በመጨረሻም ይህ ሐሳብ በቅኔያቱ ውስጥ እንደ ማኅበራዊ ጉዳይ የተነሣው ትዝብት ነው፡፡ ትዝብት እራስን በነገሩ  በማስገባት አልያም ሦስተኛ አካል በመኾን የሚደረግ አእምሯዊ ግምገማ ነው፡፡ ባለቅኔው በዘመኑ ሊቃውንት በመማራቸው ክብር ሳይሰጣቸው ሲገፉ እና ሲንከራተቱ ይታወሱታል፡፡ ያልተማሩት ሰዎች ስፍራ በመያዛቸው ሲያሳድዷቸው ይመለከታል፡፡ ባለቅኔው ሊቅ እየተባሉ መንከራተትን ሲመለከት በተስማሚ ዐውድ

በማስገባት፣ ይህን እውነታ በቅኔው አሳይቶበታል፡፡ ከዚህም የተነሣ ባለቅኔው የብቸኝነት፣ እራስን የመጥላት፣ ሰውን የመጸየፍ ስሜት ውስጥ መድረሱን በቅኔያዊ ትዝብት ገልጿል፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ ማኅበራዊ ጉዳዮች በቅኔያቱ ዋልታ እና ማገር በመኾን ገብተዋል፡፡ ቅኔያቱ ከነገረ ሰብእ ጋራ ተጣጥመው በመግባታቸው ኹል ጊዜም ሕያውነት አላቸው፡፡ ሰው የሚባለው ፍጡር እስካለ ድረስ የዐዲስነት ባሕርይ ይይዛሉ፡፡ ቅኔያቱ ማኅበራዊ ተመክሮ በዋናነት በማንሣታቸው ኹሌም በትኩስነት እና በልምላሜ ይዘልቃሉ፡፡ ሰብኣዊ ጉዳይ ምን ጊዜም ተመሳሳይነት ስለማያጣው ያለፈ ጉዳይ ነው እንዳንል ገድቦናል፡፡

በመቀጠል ፖለቲካዊ ጉዳይ ያዘሉ ቅኔያት በትንተና ውስጥ ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ቅኔያት ስለ ፖለቲካ ምንነት፣ የቤተ-ክህነት እና የቤተ መንግሥት የጋራ ሚና የሚያነሡ ናቸው፡፡ አንዱ የሌላው አጋዥ ደጋፊ ስለኾነ በቀደመው ሥርዓት ውስጥ ቤተ-መንግሥት ያለ ቤተ-ክህነት ክንፍ የሌለው አሞራ ነው፡፡ ሊቃውንቱ ነገረ መለኮትን በሚሰብኩበት መድረክ ፖለቲካዊ ድጋፍ ሰጭ ዲስኩሮችን አድርገዋል፡፡ በዚህም መሠረት ከዐፄ ምኒልክ እስከ ዘመነ አብዮት ድረስ የነበሩትን ፖለቲካዊ ኹኔታዎች የሚያመለክቱ የሙገሳ እና የነቀፋ ቅኔዎች ተተንትነዋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በቅኔያቱ ውስጥ የተገለጠው የዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ የፖለቲካዊ አመራር ዘመን ነው፡፡

ቅኔያቱ በዘመኑ የነበረውን የንጉሡን ፖለቲካዊ አሠራር የሚያሞግሱ ናቸው፡፡ ንጉሡ የገጠማቸውን ፖለቲካዊ ቀውስ ለመፍታት የተጠቀሙት ዘዴ፣ የመንግሥታቸው ኃይል፣ የሊቃውንቱ በዐድዋ ጦርነት ላይ የነበራቸው ድርሻ በቅኔያቱ ውስጥ በዋናነት ተነሥቷል፡፡ ንጉሡ ኢትዮጵያን ከጠላት ሠራዊት ኃይል ያዳኑበት ሥልት አዳም ከተፈጠረበት መለኮታዊ ግብር ጋራ ተነጻጽሮ ቀርቧል፡፡ የዐፄ ምኒልክ ትዕግሥት ሰው ሕያው ነፍስ ከኾነበት መለኮታዊ እስትንፋስ ጋራ ተመስሏል፡፡ የመንግሥቱን ኃይል ከማእዘን ድንጋይ ጋራ በማነጻጸር፣ በሀገሪቱ ፖለቲካ ዙሪያ አወንታዊ ፍካሬ ያዘሉ ቅኔያት በአብዛኛው ቀርበዋል፡፡

በቀጣይነት ፖለቲካዊ አንድምታ ያላቸው ቅኔያት የሚመለከቱት የዐፄ ኃይለሥላሴን የመንግሥት ዘመን ነው፡፡ ይህ ዘመን አወንታዊ እና አሉታዊ ገጽታ ያላቸው ቅኔያት የተደረጉበት፣ የወቅቱን የፖለቲካ ኹኔታ የሚገልጹ ቅኔያት የታዩበት ወቅት ነው፡፡ በእነዚህም ቅኔያት ውስጥ የራስ ተፈሪ መኰንን እና የንግሥት ዘውዲቱ ፖለቲካዊ ሽኩቻ፣

በአንድም በሌላም መልኩ የዐፄ ኃይለሥላሴን ለንጉሠ ነገሥትነት መመረጥ፣ የንጉሡን ተራማጅነት፣ በዘመናቸው የነበረው የፍትሕ መታጣት፣ ዙፋኑን ለማርጋት ሲባል የተወሰዱትን ርምጃዎች በአወንታ እና በአሉታ መልኩ የሚያነሡ ቅኔያት ተደረገዋል፡፡ በራስ ተፈሪ እና በንግሥት ዘውዲቱ መሀል ያለው ፖለቲካዊ ኺደት "ሔዋንን ያሳተ እባብ የአርማጌዶን ዘንዶ  አያስትሽ!" በማለት ሊመጣ ያለውን የእርስ በርስ ጦርነት እና ጉዳት በማመላከት፣ በማስፈራራት፣ ድጋፍ በመስጠት ላይ የተመሠረቱ ቅኔያት ተዘርፈዋል፡፡

ዐፄ ኃይለሥላሴ ለንጉሥነት መመረጣቸው ከናትናኤል መጠራት እና ሐዋርያ ከመኾን ጋራ ተጣምሯል፡፡ ሊቃውንቱ የንጉሡን ሹመት "መለኮታዊ ጥሪ" አድርገው በማቅረብ ፖለቲካዊ ሚና በሚሰጥ መልኩ ይኹንታ ሰጥተውበታል፡፡ ይኹን እንጂ የመጣውን ለውጥ "በዐዲስቱ ኢየሩሳሌም" ሲያቀርቡ "ፍትሕ በገንዘብ" የተነሣ መሞቷን ሳያወሡ አላለፉም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዙፋኑን ለማርጋት በወሰዱት የፍትሕ ርምጃ /በእነ በላይ መገደል/ "አብ ሲነካ ወልድ ይነካ ነውና" የቤተ-ክህነት ሊቃውንት አወንታዊ ድጋፍ መስጠታቸውን እንረዳለን፡፡ እንደዚህ ዐይነቱ ከባድ አደጋ ሲመጣ "ጠላቶቻችሁን ይቅር በሉ" ሳይኾን "የቀባኳቸውን አትንኩ" ነው ነጋ ጠባ የሚሰበከው፡፡ በጥቅሉ በዚህ ዘመን ያለው የፖለቲካ ቀውሶች አወንታዊ እና አሉታዊ ገጽታን ለመረዳት ቅኔያቱ የራሳቸውን አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡

በሦስተኛ ደረጃ የተነሣው እምብዛም የቅኔ ውዳሴ ያልጎረፈለት፣ ነገር ግን የሥርዓቱን ለውጥ የሚያሞግሱ ቅኔያት የተደረጉበት ዘመን አብዮታዊው ዘመን ነው፡፡ በዚህም አብዮታዊ ዘመን የሠራተኛውን መደብ የሚያወድሱ፣ ማርክሲዝምን የሚቀድሱ፣ የዐፄ ኃይለሥላሴን ፊውዳላዊ አገዛዝ የሚያሔሱ ቅኔያት ቀርበዋል፡፡ በዚህም ኺደት ሊቃውንቱ ከዐዲሱ ሥርዐት ጋራ ያላቸውን ቀረቤታ አመልክተዋል፡፡ ውዳሴው "የድካምህን ፍሬ ተመገብ" የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ-መር ያደረጉ እና "ያለዘር" ክርስቶስ ሰው የኾነበትን ምስጢር ከመንግሥት ምሥረታ ጋራ አጣጥመው የሚያቀርቡ ናቸው፡፡ ይኹን እንጂ የአብዮቱ ችግር፣ ግፍ፣ የሰዎችን መገደል የሚያወሡ ቅኔያት እምብዛም አይሰሙም፡፡ ያለመሰማታቸው ምክንያት ከወቅቱ ፖለቲካዊ ኺደት ጋራ የሚገናኝ ይመስላል፡፡

በመጨረሻም ቅኔያት ሃይማኖታዊ ጉዳይን ለመንፈሳዊ እና ለሥጋዊ ባህል የእኩል ግዛት አድርገው የተጠቀሙባቸው የቅኔያት ትንተና ቀርቧል፡፡ በዚህም በሃይማኖታዊ ቅኔያት አቅርቦት ውስጥ የሃይማኖት ዕውቀት ወሳኝ መኾኑ ተጠቅሷል፡፡

በዚህም አንኳር ሐሳብ ሥር ሃይማኖት የዐይንን ስፍራ በመተካት ያለው ኹለንተናዊ ጠቀሜታ ተገልጿል፡፡ በኹለተኛ ደረጃ ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት እና አስተምህሮ በተቃራኒ የሚገኙ የቅብዐት እና የጸጋ ቤተ ሃይማኖት አስተምህሮዎችን የሚያወግዙ ናቸው፡፡ በዚህም ጠባዩ ቅኔ የሃይማኖት ቀኖና መግለጫ ሚናነት እንዳለው እንረዳለን፡፡ የቅኔዎቹ ድምፀት ውግዘትን፣ ስደትን፣ መከራን፣ የመንፈስን ድቀት፣ የመንፈስን ብልየት የሚገልጹ ናቸው፡፡ በዚህም መከፋፈል የተነሣ የእምነቱ አባላት እርስ በርስ ተዋግተዋል፤ ብዙ ደምም ፈሷል፡፡ ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት አስተምህሮ ውጪ እንዳሉ የሚታሰቡ አካላት እንደ “እብድ፣ ሰነፍ” ተደርገው በቅኔ አስተማስሎ ውስጥ ቀርበዋል፡፡ በሦስተኛ ደረጃ በካቶሊክ እና በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖታዊ አስተምህሮ መሀል ያለውን የነገረ መለኮት ልዩነት የሚያነሡ ናቸው፡፡ በዚህ ሒስ ውስጥ “የንስጥሮስ እና የልዮን” አስተምህሮ ካቶሊካዊ መኾኑን በማቅረብ በእነርሱ ላይ ነገረ መለኮታዊ ሒሶች በቅኔያቱ አማካይነት ቀርበዋል፡፡

በዚህም ውስጥ “ሴት ወንጌል አታስተምር” የሚለውን መልእክት ከሮም ካቶሊካዊት ቤተ-ክርስቲያን ጋራ በማጣቀስ “እንስታዊ” ስፍራን በመስጠት የራስን አስተምህሮ በማላቅ ቅኔያቱ ተደርገዋል፡፡ ከዚህ ሃይማኖታዊ እሰጥ-አገባ የነገረ መለኮት ተጠየቅ ውጭ በቅኔያቱ ውስጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን ጳጳሳት መሾም መቻሏን ከመንፈስ አርነት ጋራ ተጣቅሶ ቀርቧል፡፡ በጥቅሉ ቅኔያቱ በወቅቱ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፣ በቅብዐት እና በካቶሊክ መካከል ለነበረው የሃይማኖት ክርክር፣ ለሃይማኖት መስበኪያነትእና መቃወሚያነት ታላቅ ሚናን ተጫውተዋል፡፡

በአጠቃላይ ቅኔያቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የተከሠቱትን ማኅበራዊ ጉዳዮች፣ ፖለቲካዊ ሥርዓት፣ ሃይማኖታዊ ታሪኮች እና ክርክሮችን በማሳየት፣ በመደገፍ፣ በመተቸት ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ እንዲህ በመኾናቸው በማኅበራዊ፣ በፖለቲካዊ እና በሃይማኖታዊ ምርምሮች፣ በሥነ-ጽሑፍ ዘርፍ ለምሁራን ጥልቅ መረጃ የሚሰጡ ናቸው፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች

## ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች


ሀብተማርያም ወርቅነህ፤1963፤ *ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት*፤ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡

ኅሩይ ወልደሥላሴ፤ 1918፤ *መጽሐፈ ቅኔ*፤ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

አድማሱ ጀንበሬ (መልአከ-ብርሃን)፤ 1963፤ *መጽሐፈ ቅኔ፣ ዝክረ ሊቃውንት*፤ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡

ኤልያስ ነቢየ ልዑል (አለቃ) እና ከፍያለው መራሒ (ቀሲስ)፤ 1992፤ *ትርጓሜ ቅኔ ፈለገ ሕይወት*፤ አዲ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ዓለማየሁ ሞገስ ፤1967፤ *የግዕዝ ቅኔ ዜማ* ፤ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ፤ 1980፤ *የግዕዝ ቅኔያት የሥነ- ጥበብ ቅርስ*፤ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ይኄይስ ወርቄ፤ 1960፤ *ንባብ ወትርጓሜ ዘቅኔያት፣ አዕማደ ምሥጢራት*፤ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡


## ካልዓይ የመረጃ ምንጮች


*መንግሥቱ ለማ* ፤1959፤ *መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ*፤ አዲስ አባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ፡፡

ማርዬ ይግዛው ፤2006፤ *ቅኔያዊ የዕውቀት ፈጠራ*፤ አዲስ አበባ፣ ዜድኤ ማተሚያ ቤት፡፡

ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ (ሊቀመዘምራን)፤1957፤ *መጽሐፈሥነ-ፍጥረት*፤ *አሥመራ*፣ በኮከበ ጽባሕ ዘማኅበረ ሐዋርያት ፍሬ ሃይማኖት ማተሚያ ቤት ታተመ፡፡

በላይነህ ደሴ ፤1999፤ "የቅኔ ቈጠራ፣ ነገረና ዘረፋ በተመረጡ የጎጃም ጉባኤዎች ውስጥ" አ.አ.ዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ -ጽሑፍ ክፍል ዲግጽ ፡፡

ባሕሩ ዘውዴ፤ 2003፤ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847-1983*፤ በአዲስ አበባ፣ አ.አ.ዩ የማተሚያ ቤት፡፡

ብርሃኑ ድንቄ፤ 1987፤ *አልቦ ዘመድ*፤ አዲስ አበባ፣

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፤ 1964፤ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ* ፤ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ፡፡

ታደለ ገድሌ፤ 1997፤ *ቅኔና ቅኔያዊ ጨዋታ ለትዝታ*፤ አዲስ አበባ፣ ጉተንበርግ ማተሚያ ቤት፡፡

ትርጓሜ ወንጌል አንድምታ  አዲስ አበባ፣በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ፡፡

ትንሣኤ አሳታሚ ድርጅት፤ 1962 ፤ *ፍትሐ ነገሥት* ፤ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡

አበበ ከበደ፣1993፤ "የመልአከ መልአክ ተስፋ የዋሸራ ውስጠ ዘ የግዕዝ ቅኔና ቅኔው ከሌሎች ቅኔዎች የሚለይባቸው ባሕርያት" አ.አ.ዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍል፣ ዲግጽ ፡፡

አያሌው ታምሩ (ሊቀ-ጠበብት)፤ 1953፤ *መች ተለመደና ከተኩላ ዝምድና፤* አዲስ አበባ፣ በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ፡፡

አድማሱ ጀንበሬ (መልአከ-ብርሃን)፤1949፤ *ኩሉሕ ሃይማኖት*፤ አዲስ አበባ፣በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ፡፡

አጥናፍ ሰገድ፤ 2006፤ *አቤቶ ኢያሱ*፤ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፤ 1978፤ *ማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት*፤ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፡፡

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ፤1948፤ *መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ* ፤ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ዓለማየሁ ሞገስ፤1950፤ *ሰዋስወ ግዕዝ ምስለ ተሰነአወ* ፤አዲስ አበባ፣ ተስፋ ማተሚያ ቤት፡፡

ዕንባቆም ቃለ-ወልድ (አለቃ)፤1966፤ "ስለቅኔ ትምህርትና ስለ ጥቅሙ፡፡"Third International Conference:: አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ቅጽ ፣ቁጥር ፣ ገጽ 117- ፡፡

ዘላለም መሠረት (ዶ/ር)፡1998፡ "የግዕዝ ሚና ለአማርኛ ማደግና መማር ማስተማር፡፡" አ.አ.ዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ -ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ዲግጽ ፡፡

____________፤2008፤ "ቅኔ፡ ምንነቱ፣ ትምህርቱ፣ ደረጃው ከምሳሌዎቹ ጋራ፡፡" *ለኢትዮጵያ የሳይንስ አካዳሚ የቀረበ ጥናት* ፤ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡፡

ዜና ማርቆስ እንዳለው ፤1994፤ *ቅኔ ለወጣቶች ቁጥር አንድ* ፤ አዲስ አበባ ሆራይዘን ማተሚያ ቤት፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፤ 2000፤ *መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት*፤ አዲስ አበባ፣

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ ፤1984፤ *የግዕዝ ቅኔያት የሥነ- ጥበብ ቅርስ*፤ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፤ 1995፤ *የግዕዝ ቅኔያት የሥነ- ጥበብ ቅርስ*፤ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ያለው እንዳወቀ ሙሉ (ዶ/ር)፤2001፤ *የምርምር መሠረታዊ መርሆችና አተገባበር*፤ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ይኄይስ ኃይለ ሚካኤል፤1975፤ ፣ "የግዕዝ መወድስ ቅኔ" አ.አ.ዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍል ዲማጽ ፡፡

ይኩኖአምላክ መዝገቡ፤1997፤ "የሴት ገጸባሕርያት በግዕዝ ቅኔ ውስጥ" አ.አ.ዩ. የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነ -ጽሑፍ ክፍል፣ ዲማጽ፡፡

ይኩኖ አምላክ ገብረ ሥላሴ፤1966፤ "የጥንት ቅኔዎች፡፡"የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ መጽሔት ፤አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ቅጽ4 ፣ቁጥር1፣ገጽ79 ፡፡

ዮሐንስ አድማሱ፤1959፤"ሠምና ወርቅ" አ.አ.ዩ. የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍል፣ ዲማጽ ፡፡

ዮናስ አድማሱና ሌሎች፤ 1966፤ "አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ፡፡" አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ያልታተመ)፡፡

ዮናስ አድማሱ፤1992፤"አስረኛንኩዋ? ሀዲስ ዓለማየሁና ማኅበራዊ ሂስ ሥልታቸው፡፡" *የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ መጽሔት* ፤ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

ደስታ ተክለወልድ ፤1962፤ *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት*፤ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ታተመ፡፡

ጎርጎርዮስ (አባ) ፤1974፤ *የኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያን ታሪክ*፤ አዲስ አበባ፣ በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ፡፡

____________፤(1978፤ *የቤተ-ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ*፤ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ፡፡

ጽጌ አባተ፤1972፤ "ቅኔያዊ ውርስ" ኢ.አ.ዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነ -ጽሑፍ ክፍል፣ ዲማጽ ፡፡

ፍቅረ ድንግል በየነ ፤1963፤ "ቅኔ መቀኘትና መቍጠር (በግዕዝ)" ኢ.አ.ዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ- ጽሑፍ ክፍል፣ ዲማጽ ፡፡

Gayle L. and Alan D.(ed).1981.*The Hermeneutic Tradition*.State University of New York Press.

Durant, Will. 1926. *The Story of Philosophy*. New York.

Northcoth, Michaels.1999. *Approaches to the Study of Religion*. Ed Peter Connolly. London: Continuly.

SIRGIW GELAWE (PHD).2009**.**"Historical Development of Geez Qene in Different periods"A.A.U.Forein Laneguags and Literature Institute of Language Studies.

# ዐባሪ

## የግዕዝ ቅኔ መንገዶች ምሳሌዎች

**1.ተራ ምሳሌ (ሠምና ወርቅ)**

**ምሳሌ፡-** ኢትሕዝኒ እም ጉባኤ ቃና በብሂለ ታሕት ወላዕል፣
አምጣነ የአምር ለኪ ዘፈጠረኪ አስካል፡፡

**ትርጉም፡-** እናት/ጉባኤ ቃና ታች ላይ በማለት አትዘኚ፣
የፈጠረሽ/አስካል ያውቅልሻልና

<u>እም</u> ሠም ሲሆን <u>ጉባኤ ቃና</u> ደግሞ ወርቅ ነው፡፡

**2.ኅብር መንገድ**

**ምሳሌ፡-** ሰሎሜ ስመኪ ኢታሐሥሚ ወኢትግሥሢ መሶበ፤
እንበለ አሐዱ ኅብስት አምጣነ አልቦ ዘቀርበ፡፡

**ትርጉም፡-** ሰሎሜ! ስምሽን አታጥፊ፤ መሶብንም አትንኪ፣
ከአንድ እንጀራ በቀር የቀረበ የለምና፡፡

**3.ውስጠ ወይራ፡-**

**ምሳሌ፡-** ጌራ ወርቅ ዘተቀጸል
ንጉሠ አማልክት ዳጎን <u>አሣዕነ ያዕቆብ</u> ገብረ
ኢይኪድ በአእጋሪሁ ዳግሚተ ምድረ
<u>ሕልቀተ እዴሁ ለቶማስ</u> እስመ በእዴሁ ተአስረ፣
ወበጥቅመ ሰናየር ዳጎን ምስጢሮ ሰወረ፣
እስመ ፈርሀ ኃይለ ጽዮን ፀረ፡፡

**ትርጉም፡-** የራስ ወርቅ የተቀዳጀ የአማልክት ንጉሥ
ዳጎን የያዕቆብን ጫማ አደረገ፤
ዳግማዊት ምድርን በእግሩ እንዳይረግጥ፣
የቶማስ የእጅ ቀለበት በእጁ ታስሯልና፡፡
ዳጎን በሰናየር ግንብም ምስጢሩን ደበቀ፡፡
የጽዮን ኃይል ጠላትን ፈርቷልና፡፡

4.ዝምድ መንገድ

ምሳሌ፡- ጾም ባሕረ ኢየሱስ ረሐብ ይእቲ፣
እንስሳ ዐበይት እስመ ይትሐውሱ ባቲ፡፡
ትርጕም፡- የኢየሱስ ባሕር ጾም ሰፊ ናት፣
ታላላቅ እንስሳት ይመላለሱባታልና፡፡

5.ዐይነ ውሃ (ልብሰ ወርቅ)

ምሳሌ፡- ማርያም ከርካዕ እንተ አሕመልመለት ቈጽለ፣
ጸገየት ድንጋሌ ወፈረየት ቃለ፡፡
ትርጕም፡- ቅጠልን ያለመለመች ማርያም ሎሚ፣
ድንጋሌን አበበች፤ ቃልንም አፈራች፡፡

6.ሠም ለበስ

ምሳሌ፡- እወልድሂ በድምፅ እንዘ ኢይዘርዕ ዘርዐ፣
እልፈ አራዊተ ወእልፈ አባግዐ፡፡
ትርጕም፡- ዘር ሳልዘራ በድምጽ እወልዳለሁ፡፡
ዐሥር ሺ አራዊትን ዐሥር ሺ በጎችም፡፡

7.ጽድቅ መንገድ

ምሳሌ፡- እኩያን አይሁድ ፈጣሪሆሙ ሰቀሉ፣
ንባበ ኦሪት ቅድስተ እስመ አጥፍአ በቃሉ፡፡
ትርጕም፡- ክፉዎች አይሁድ ጌታቸውን ሰቀሉ፤
የተለየች የኦሪትን ንባብ በቃሉ አጥፍቷልና፡፡

8.ጉራማይሌ (ፍርንዱስ)

ምሳሌ፡- ንኢ ንኢ ጉባኤ ቃና ድመት፣
አምጣነ ተክዕወ ለኪ ልበ ተማሪ ወተት፡፡
ትርጕም፡- ጉባኤ ቃና ድመት ነዪ፤ ነዪ፤
የተማሪ ልብ ወተት ተደፍቶልሻልና፡፡

9.ሠም ገፊ፡

ምሳሌ፡- ኢይተርፍ ግፍዕ ለዘዕድሜሁ ጕንደየ፣
እሥራኤል ለፈርዖን እስመ አጸርዎ ማየ፡፡

**ትርጒም፡-** ዕድሜው ለዘገየ ሰው ግፍ አይቀርም፤

እሥራኤላውያን ፈርዖንን ውሀ አሸክመውታልና፡፡

10.ወርቅ ገፊ

**ምሳሌ፡-** <u>ምንት ውእቱ ፍድፉዱ ዚአሃ</u>

<u>ለምክሃ ጠቢባን ጥበብ</u> እስመ በጥበብ ወምክር፣

ኢይጸዕዱ ጸሊም ወኢይነውኅ ኀጺር፣

ወለአብድ ዘይጸንሕዎ ክልዔቱ አፅራር፣

ሞት ወመቃብር፣

ይጸንሕዎ አኮኑ ለጠቢብ ወማእምር፣

ከመሰ ኢያስጥመነ ብሂለ ዕመቅ ባሕር፣

ታኀስር የዋሀት ወጥበብ ታከብር፣

እንዘ የዋሂት ርግብ በዐለ አክናፍ ወእግር፣

የሐውር በእንግድዓ ጠቢብ አርዌ ምድር፡፡

**ትርጒም፡-** የጠቢብን ትምክህት ጥበብ ለእሷ ጥቅሟ

ምንድ ነው? በጥበብ እና በምክር ጥቁር አይነጣምና፤ ዐጭርም አይረዝምምና፤

ሰነፍን የሚጠብቁት ሁለቱ ጠላቶች ሞትና መቃብር ጠቢብን ዐዋቂንም

ይጠብቁታልና፡፡ ጥልቅ ባሕር ሐሳብ እንዳያሰጥመን ግን የዋህነት ስታዋርድ

ጥበብ ታከብራለች፡፡ የዋህነት ርግብ ክንፍና እግር ሲኖራት የምድር እባብ

ጠቢብ በደረቱ ይሳባል፡፡

11.ፍላጻ (የቀስት ጦር)

**ምሳሌ፡-** ይትወላወል ሰብእ ልበ ፈሪሳዊ ቀሊል፣

<u>እምጊዜ ልደቱ ኦሪት</u> እስከ <u>ጊዜ ሞቱ ወንጌል፡፡</u>

**ትርጒም፡-** ከልደቱ ከኦሪት ጀምሮ እስከ ሞቱ ወንጌል ድረስ፣

ቀላል የኾነ የፈሪሳዊ ልብ ሰው ይጠራጠራል፡፡

12.ሠረዝ መንገድ

**ምሳሌ፡-** <u>እምከዊነ ካህን</u> ይኄይስ <u>ከዊነ ኖላዊ</u>

ወኀለ እንስሳ ትትበደር እምቤተ መቅደስ ዐባይ፣

እስመ ቤተ መቅደስ ኮነት ቤተ ፈያታይ፣

ወበላዕለ ኖሎት ኢህለወ

ላዕለ ካህናት ዘሀሎ እከይ፣
ትእምርተ ዝኒ ከመ ንርአይ፣
በኀለ እንስሳ ሠረቀ ዘኢየዐርብ ፀሐይ፣
ወኖሎት ተዛውዑ ምስለ ሐራ ልዑል ሰማይ፣
ዓዲ እምቅድመ ዝንቱ እመካነ ኖሎት ወመራዕይ፣
ከመተጸውዑ ደምፀ እግረ ቃለ ዜና ሠናይ፣
ወልደ እንበረም ለምስፍና ወለቅብዐ መንግሥት ወልደ ዕሴይ፡፡
**ትርጒም፡-** ካህን ከመሆን እረኛ መሆን ይሻላል፤
የእንስሶች በረትም ከታላቅ ቤተ መቅደስ ትመረጣላች፡፡
ቤተ መቅደስ የሽፍታ ቤት ሆናለችና፤
በካህናትም ላይ ያለ ክፋትም በእረኞች ላይ የለምና፤
የዚህን ምልክት እናይ ዘንድ
የማይጠፋ ፀሐይ በእንስሳት በረት ወጣ፡፡
እረኞችም በከፍተኛ ሰማይ ጌታ መላእክት ጋራ አብረው ተወዳጁ፤
ዳግመኛም ከዚህ በፊት በእረኞችና በመንጎች ቦታ
የእንበረም ልጅ (ሙሴ) ለመስፍንነት የዕሴይም ልጅ(ዳዊት)
ለመንግሥት ቅባትእንደተጠሩ የመልካም ምሥራች ኮቴ ተሰማ፡፡

13.ውስጠ ዘ መንገድ

**ምሳሌ፡-** በወይነ ገለአድ ቶማስ ነዋሚ አመ ዘዘካርያስ ዖቀ፣
ተውኔተ አስይፍት ለጊጋር ሐራሁ ምልዐ ሰብእናሁ ተጠምቀ፡፡
**ትርጒም፡-** ዘካርያስ ተጫዋች በሚያውቀው በጊጋር ጭፍራዎች ሰይፎች ጨዋታ ጊዜ
ቶማስ እንቅልፋም በገለአድ አለቃ ጠላ (ወይን) ሰውነቱን ኹሉ ተጠመቀ፡፡

**14.አንጻር መንገድ**

**ምሳሌ፦** ኀሊና ዮፍታሔ

ለአብርሃም ኮነ ጊዜ መሥዋዕት

ወኀበ ዮፍታሔ ተመይጠ ኀሊና አብርሃም ዝንቱ፤

እስመ ሦዐ በግዐ ምሳሌ አብርሃም በቤቱ፣

ወሕፃነ ሦዐ ዮፍታሔ፣ ሰማዕተ ልዳ ባሕቱ፣

በግብር ኢ.ይኩን ከመ ክልዔቱ፣

ሦዐ ርእሶ በሥምረቱ፣

እስመ ወልድ ወበግዕ አልቦቱ፡፡

**ትርጕም፡-** የዮፍታሔ ሐሳብ በመሥዋዕት ጊዜ እንደ አብርሃም ሆነ፤

የዚህ የአብርሃም ሐሳብ ወደ ዮፍታሔ ተመለሰ፤

አብርሃም በቤቱ ምሳሌ በግን ሠውቷልና፤ ዮፍታሔም

ሕፃንን ሠዋ፤ የልዳ ሰማዕት ግን በሥራ እንደ ሁለቱ እንዳይሆን በፈቃዱ ራሱን

ሠዋ፤ ልጅና በግ በቤቱ የለውምና፡፡

# ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው

I know not what to say to it; but experience make it manifest, that so many interpretations dissipate the truth, and break it. Who will not say that glosses augment doubts and ignorance, since there is no book to be found either human or divine, which the world business itself about, whereof the difficulties are cleared by interpretation. The hundredth commentator passes it on to the next, still more knotty and perplexed than he found it.( p.1)

When were we ever agreed among ourselves: “this book has enough; there is now no more to be said about it?”… do we find any end to the need of interpreting? Is there, for all that, any progress or advancement toward peace, or do we stand in need of any fewe advocates an judges? There is more ado to interpret interpretations than to interpret thingsl and more books upon books than upon any other subject; we do nothing but comment upon one another.(p.1)

Every place swarms with commentaries…..Is it not the common and final end of all studies? Our opinions are grafted upon one another, the first serves as a stock to the second, the second to the third and so forth. (p.1)

The authority and the significance the “truth” of these claims is dispersed, placed in circulation through a proliferation of interpretations. We change one word for another, and often for one less understood.(p.3)

Is this not a central consequence of the hermeneutical circle or, at the very least, of the chain of discourses and interpretations which identify and determine the “hermeneutical circle”. The search after truth, as it were, is deferred, diverted, caught in a network of contextually bound and generated commentaries.(p.3)

The question of the unity of knowledge and understanding into questions concerning the unity of sign and signified of word and object, the harmony of language and reality of thought and reality of thought and action.(p.5)

Like everything metaphysical” writes Ludwig Wittgenstein in Zettel, “the harmony between thought and reality is to be found in the grammar of the language. (Wittgensteinian … language-games) demonstrates, ironically, how the proposition “there are only interpretations….” Cannot be granted the status of law, cannot be taken as a first principle nor as the last word. (p.5)

As Michel Foucault remarks, an interpretation "always has to interpret itself.. [it] cannot fail to return to itself. This is the "experience" of interpretation to which Montaigne refers: interpretation finds itself always positioned, as it comments on other "texts", to comment on itself endlessly, "always correcting itself.(p.7)

This is the "life of interpretation, and this "experience", this practice, this "life," constituting the complex domain of hermeneutics, is the subject for the essays included in this volume. (p.7)

In general, Schleiermacher is credited with taking the first steps toward establishing a general hermeneutic methodology in contrast to a variety of regional hermeneutic approaches.(p.11)

The threefold conception of understanding leads Ast to distinguish between three corresponding forms of explication (Erklarung) (1) the hermeneutics of the letter (section 83); (2) the hermeneutics of meaning (section 84); and (3) the hermeneutics of the spirit (section 85ff). (p.12)

"the meaning of every word in a given passage must be determined in relation to its coexistence with the words surrounding it) and technical interpretation. Because discourse is thinker the art of understanding must grasp their interaction.(p.13)

Betti explicates four cannons that will guide the interpreter in the task of objectively reproducing the original meaning. First and fore most is the "cannon of the hermeneutical autonomy of the object." According to Betti, for the object to be regarded as autonomous means that it "should be judged in relation to the standards immanent in the original intention: the intention, that is, which the created forms should correspond to from the point of view of the author and his formative impulse in the course of the creative process.(p.19)

The second canon Betti calls "the canon of the coherence of meaning" or the "principle of totality." According to this cannon, there is an internal relationship between the individual parts of a speech or text and between these parts and the whole. In this cannon, Betti formulates his version of the circularity of understanding: "the meaning of the whole has to be derived from its individual elements, and an individual element has to be understood by reference to the comprehensive, penetrating whole of which it is a part" (p.165). Third is the "cannon of the actuality of understanding" by which Betti acknowledges that the interpreter, in the process of reconstructing the author's creative process and intended meaning, will necessarily appropriate

these processes and intended meaning, will necessarily appropriate these processes and this meaning in terms of his or her own subjectively. Fourth is the “cannon of the hermeneutical correspondence of meaning” or “meaning-adequacy in understanding,” which encourages the interpreter to bring his or her own subjectivity into the “closest harmony with the stimulation.” (p.19)

Habermas argues. “language is also a medium of domination and social power; it serves to legitimate relations or organized force” (p.21)

The ideological dimension of language as the transmitter of tradition leas Habermas’s analysis of psychoanalytic depth hermeneutics leads him to the conclusion that certain forms of communication are “systematically distorted”. (p.21)

Gadamar focuses on the human sciences’ attempt to overcome distantiation (verfremdung) from the tradition, Habermas is concerned with the critical social sciences and the emancipatory possibilities of critical reflection on institutional reifications. Further, Gadamer takes “misunderstanding” as the inner obstacle to understanding, whereas Habermas focuses on ideology, understood as the “systematic distortion of communication by the hidden exercise of force” (p.313). (4) Finally, where Gardamer sees the task of hermeneutics as arriving at a prior understanding “the dialogue which we are” which misunderstanding presupposes, Habermas looks forward to a notion of “an unrestricted and unconstrained communication” which will serve as a regulative ideal. (p.23)